የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የልዩ ልዩ የመንግሥት መ/ቤቶች
የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት
ዓመታዊ ሪፖርት

ጥራዝ 1

ሚያዝያ 2005

አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

1. መግቢያ……………………………………………………………………. 1

2. ኦዲት በተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተገኙ

ዋና ዋና ግኝቶች የተጠቃለለ ሪፖርት /Summery Report/……………………… 4

3. የፌዴራል ልዩ ልዩ መንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር ኦዲት ሪፖርት

3.1 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን…………………………..54

3.2 የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች………………………………..99

3.3 የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች………………………………………..118

3.4 የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት መ/ቤቶች…………………….....154

3.5 የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች…………………………………..197

3.5.1 የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር 2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት…….211

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የልዩ ልዩ የመንግሥት መ/ቤቶች

የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

ዓመታዊ ሪፖርት

I. መግቢያ

የዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 101 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራሉን መንግሥት ዕቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጡት ሕጎች፣ በአስፈጻሚው አካል በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የፋይናንስ፤ የክዋኔ የአካባቢ ጥበቃ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩ ለክልልና ለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ /ስታንዳርድ/ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው::

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፣
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥትና የክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል አስፈላጊውንም ቁጥጥር ያደርጋል፣
- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣
- ለግል ኦዲተሮችና የሂሳብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ የሂሳብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለማሰማራት የሚያስችላቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣

ይህንኑ ስልጣን መሰረት በማድረግ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችን ኦዲት ለማከናወን ለፋይናንስና የህጋዊነት ኦዲት በእንጌጅሜንት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በ4 ዘርፍ በተደረጁ መ/ቤቶች፡- የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች፤ የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች፤ የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች እና የልማትና ማህበራዊ

መ/ቤቶች እና በ2 የክዋኔ ኦዲት ዳይሬክቶሬቶች፣ እንዲሁም በገ/ኢ/ል/ሚኒስቴርና ክልል መንግስታት የሚከናወነውን የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ /PBS/ ተከታታይ ኦዲት ለማከናወን በ1 የድጋፍና ድጎማ ኦዲት ዳይሬክቶሬት የኦዲቱ ስራ ተከናውኗል፡፡ ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል እንዲሁም አንዳንዴም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት በዓለም አቀፍ ሂሳብ ኦዲት ደረጃዎች እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው::

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች፤ ኦዲት የተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን፣ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍን በተመለከተ በተለያዩ ክልሎች ሥር ባሉ የሴክተር ቢሮዎች፣ የወረዳና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤቶችን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም በተከታታይ ኦዲት በማድረግ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ነው::

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተከናወነው የኦዲት ሥራ እንዳለቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉ ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የፌዴራል መ/ቤትና ተቆጣጣሪ መ/ቤት እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ለሥራ አመራር ሪፖርት መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን አስተያየት ያገናዘበ ነው::

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ ተከታታይ ኦዲት ደግሞ ኦዲቱ እንዳለቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የሴክተር ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች ጋር የመውጫ ውይይት የተደረገበትና የኦዲት ሪፖርቱም በየሩብ ዓመቱ ተጠቃሎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር እየተላከ ውይይት የተደረገበትና አጠቃላይ ሂሳቡም ላይ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡

II. መ/ቤታችን በሚከተለው የኦዲት ጊዜ አቆጣጠር ከጥር 1/2004 እስከ ታህሣሥ 30/2005 ዓ.ም የ117 በፌዴራል መ/ቤቶች የ2004 በጀት ዓመት ሂሳብ መደበኛ ኦዲት፣ 7 የልዩ ኦዲት ስራዎች እና በ283 የወረዳና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤቶች የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲትና የተጠቃለለው የPBS ሂሣብ ኦዲት አከናውኗል፡፡ በመደበኛና በልዩ ኦዲት የተከናወኑትን ኦዲቶች ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች ሪፖርት የላከ ሲሆን፤

የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተ ደግሞ በየሩብ ዓመቱ እና የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተልኳል።

III. ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በርካታ ሲሆኑ፣ እነዚህ ጉዳለቶች በዚሁ ጥራዝ ከገጽ 53 ጀምሮ በየኦዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን፣ የታዩት ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርበዋል።

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ3 መ/ቤቶች ብር 247,210.19 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንደሚገኝ ተውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 7 ተመልክቷል/ በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ2 መ/ቤቶች ቆጠራው በብር 133,466.99 በማነስ እና በ9 መ/ቤቶች በብር 3,433,156.03 በመብለጥ ልዩነት ታይቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ-8 ተመልክቷል/፡፡

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በማነስና በመበለጥ የታየው ልዩነት ተጣርቶ እንዲስተካከልና ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፤ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን

ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ24 መ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ- 9 እና አባሪ-10 ተመልክቷል፡፡/

ከሚታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያየዝ ጉድለቶች፤

- የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከመዝገብ (ሌጀር) ጋር የማይመሳከር መሆኑ፤
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርጉ /የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አድርገናል ቢሉም ማስረጃ ያላቀረቡ/ መሆኑ፤
- የዋና ገንዘብ ያዥ የጥሬ ገንዘብ መቆጣጠሪያ መዝገብ አለማዘጋጀት፤
- በባንክ ሂሣብ ገቢ ለሆኑ ሂሣቦች የገቢ ደረሰኝ አለማዘጋጀትና አለመመዝገብ፤
- የተሰበሰበውን ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ አለማድረግ፤
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ መሆኑ፤
- ለልዩ ልዩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ያለማስፈቀድ እና ከተፈቀደውም በላይ በሳጥን ማስቀመጥ ወይም በግዥ ሠራተኞች እጅ እንዲያዝ መደረጉ፤
- በ3 መ/ቤቶች ብቻ ብር 1,308,104.69 በካዝና እንዲቀመጥ ከተፈቀደው የጥሬ ገንዘብ በላይ በሳጥን የተገኘባቸው መሆኑ፤
- ተንጠልጣይ ሰነዶች ሳይወራረዱና ለሒሳብ ክፍል ሳይተላለፉ ከአንድ ዓመት በላይ በገንዘብ ያዥ እጅ የሚያቆዩ መሆኑ፤
- የመደበኛና የእርዳታ ሂሳብ በአንድ የባንክ የሂሳብ ቁጥር የሚንቀሳቀስ መሆኑ፤
- ከክፍያ መመሪያ ውጪ በመመሪያው ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወጪ የሚደረግ መሆኑ፤
- በውጭ ምንዛሪ ባንክ ያለ ገንዘብ /4102/ ተብሎ ሪፖርት የተደረገውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የባንክ ሂሣብ መግለጫና የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያልቀረበለት መገኘቱ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፤ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ እንዲዘጋጅ፤እንዲሁም በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ

ገንዘብ ሂሣብ ጋር ከቆጠራው ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሣብ

2.1 በደንቡ መሰረት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኘባቸው መ/ቤቶች

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ57 መ/ቤቶች ብር 1,369,377,900.98 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-11 ተመልክቷል/ ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	182,301,059.43
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		644,459,753.54
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		235,322,553.47
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		307,294,534.54
ጠ/ድምር		1,369,377,900.98

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የትምህርት ሚኒስቴር ብር 401.75 ሚሊዮን፣ የግብርና ግብርና ሚ/ርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ብር 220.29 ሚሊዮን፣ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር 173.75 ሚሊዮን፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 159.45 ሚሊዮን፣ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 86.36 ሚሊዮን፣ በሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና የፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 83.08 ሚሊዮን፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 69.02 ሚሊዮን፣ የፌዴራል ፖሊስ 29.77 ሚሊዮን እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 21.39 ይገኙበታል፡፡

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይና የአንዳንድ መ/ቤቶች እየጨመረ የሄደ መሆኑ፣ በአብዛኛው ቀደም ባሉት ኦዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

ስለተሰብሳቢው ሂሳብ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ከሰጡት ምላሽ፤ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ለሥራ አመራር ሪፖርት በሰጠው መልስ ብር 18,500,490.05 በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ማለት በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ብር 11,593,098.46 እና በሌሎች 8 ክፍሎች በድምሩ ብር 6,907,391.59 የወደመ፣ የጠፋና የተሰረቀ መሆኑን እና በፋይናንስ ሕግ መሠረት ከመዝገብ ለማሰረዝ ኮሚቴ መቋቋሙን፣ ለዝቋላ ስቲል ማምረቻ ፋብሪካ በበጀት ዓመቱ በብድር የተሰጠው ብር 45,000,000.00 እና ከ3 ዓመት በፊት ለብራና ማተሚያ ቤት በብድር የተሰጠው ብር 3,000,000.00 በ2005 በጀት ዓመት በሙሉ እንደሚሰበሰብ፣ በአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ በተሰብሳቢ የሚገኘው ውስጥ ብር 4,213,093.82 በተመለከተ የአስተደደር መምሪያው ምን ያህል እንደሰበሰበ ቀሪው ምን ያህል እንደሆነ ከወጪ ቀሪው እንዲሁም እስካሁን እርምጃ ያልተወሰደባቸው ካሉ በማጣራት እንዲሰበሰብ እርምጃ እንደሚወሰድ ሌሎቹ በተለያየ ምክንያት ሊሰበሰቡ ያልቻሉትን በማጣራት ለውሣኔ እንደሚያቀርብ፣ ከተቋራጮች ስለሚፈለገው ብር 10,627,372.19 ከመከላከያ መሠረተ ልማትና ግንባታ ዘርፍ በተሰጠው ምላሽ መሠረት የመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬቱ ክትትል እንደሚያደርግ፤ ትምህርት ሚኒስቴር ለየዩኒቨርስቲዎች ግንባታ የተሰጠውን በርካታ ገንዘብ እንዲወራረድ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑንና የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ከውጭ ሀገር ለመንግስት መ/ቤቶች ተሽከርካሪዎች ግዥ ሂሳብ ሆኖ ተሽከርካሪዎቹ እየገቡ ስለሆነ በቅርቡ እንደሚያወራርድ ሲገልጽ፤ ሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶችን በመጥቀስ ሂሳቡን ለማወራረድ ጥረት እንደሚያደርጉ በመግለጽ ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

- በአብዛኞዎቹ መ/ቤቶች ለእቃ ግዥ ሰራተኞችና ሌሎች ሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ በተደጋጋሚ የሚሰጥ በመሆኑና በእያንዳንዱ የእቃ ግዥ

ሰራተኛ ተቀጽላ ሌጀር ባለመኖሩ ማስረጃ ቀርቦለት ያልተወራረደና ከሰራተኛው የሚፈለግ ቀሪ እዳ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥና ለይቶ ኦዲት ለማድረግ አለመቻሉ፤

- በሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 619,842.28 ገንዘቡ ወጪ ተደርጎ ለመሰጠቱ ማስረጃው ባለመቅረቡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰብሳቢ ሂሳብ ለመሆኑ ማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 435,339.00 የተሰብሳቢ ሂሳብ ክሬዲት አቅጣጫ የሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,273.20 በተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር ላይ፣ ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 1,517,936.10 እና ወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 4,063,581.50 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ABNORMAL CREDIT BALANCE) በክሬዲት ላይ የተመለከተ መሆኑ፡
- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛ አካውንት ውስጥ ገቢ ተደርጎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ መሆን የነበረበት የግንባታ ተቋራጮች የሲሚንቶ ብድር ተመላሽ ሂሳብ ብር 8,790,970.02 ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈሰስ ሳይደረግ አለአግባብ በውስጥ ገቢ አካውንት ውስጥ ገቢ ሆኖ የተገኘናበተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ መሆኑ፡
- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ከኮንስትራክሽን ድርጅቶቹ የሚፈለግ የሲሚንቶ ብድር ብር 2,245,974.10 ተቀንሶ ክፍያ እንዲፈፀም የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት የገለፀ ቢሆንም የፋይናንስ ክፍሉ ግን ሳይቀንስ/ሳይሰበስብ/ ክፍያውን የፈጸመ መሆኑ ፣
- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,310,087.73 በተሰብሳቢ ሂሳብ 4211 ለግዥ ሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ እና ብር 3,489,841.88 በሂሳብ መደብ 4251 ለሥራ ተቋራጮች ቅድመ ክፍያ በድምሩ ብር 5,799,929.61 ተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ ቢያዝም የሂሳብ ሠነዱ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑና ከመቼ ጀምሮ የሚፈልግ ሂሳብ እንደሆነ የሚገልጽ ማስረጃ እና ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የተገኘው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሂሳቡን በወሰደው በእያንዳንዱ ግለሰብ ወይም ድርጅት ስም የተከፈተ ሌጀር /subsidiary ledger/ የሌለ መሆኑ፣

- በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4201 የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ በእያንዳንዱ ገንዘቡን በወሰደው ሰው/ድርጅት ስም የተከፈተ ተቀጥያ ሌጀር (subsidiary ledger) ባለመኖሩ ያልተወራረደው ሂሳብ ከማን እንደሚፈለግ የማይታወቅ መሆኑ ፡
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,380,069.18 ለሌሎች ቅድሚያ ክፍያ እና ብር 789,111.40 ለግዥ ሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ በድምሩ ብር 3,169,180.58 ማስረጃዎቻቸው ለኦዲት አለመቅረቡ ታውቋል፡፡

- <u>በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር</u>

  - ለሥራ ማስኬጃና ለሠራተኞች ውሎ አበል በቅድሚያ የተከፈለው ሂሳብ ብር 863,969.80 በሂሳብ መደብ 4211 መመዝገብ ሲገባው በ4203 የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፣
  - ከሠራተኞች የሚፈለግ የረጅም ጊዜ ብድር ብር 87,678.62 በሂሳብ መደብ 4203 መመዝገብ ሲገባው የግዥ ቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በሚመዘገብበት የሂሳብ ኮድ በ4211 የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፣

- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሂሣብ መደብ 4201 በተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት የተደረገው ሂሣብ በተቀጽላ ሌጀሮች ድምር ከታየው በብር 1,798,758.33 በልጦ መገኘቱንና ይህ ባለፉት ኦዲቶችም ልዩነት መታየቱና እስካሁንም አለመጣራቱ፡

- <u>የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ</u>

  ኤጀንሲው በ2004 በጀት አመት መጨረሻ ከ52 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ ያልተሰበሰበ ቀሪ ሂሳብ ብር 1,490,646,401.65 ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር በቀረበው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት አለማቅረቡን በመግለጽ ኤጀንሲው የፋይናንስ መመሪያው በሚያዘው መሰረት በየወሩ ለሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ከሚያቀርበው ሂሳብ ሪፖርት ጋር ያልተሰበሰቡ ቀሪ ሂሣቦችን ማቅረብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡ ኤጀንሲው የበጀት ሂሳብ የሚመዘግብበት IBEX ፕሮግራም የተሸጡ ድርጅቶችን ወለድ በየቀኑ ለማስላት የማያስችል በመሆኑ በሪፖርቱ ውስጥ ያልተካተተ መሆኑንና ለወደፊቱ ግን ከሪፖርቱ ጋር አያይዘው

እንደሚያቀርብ በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅትና በሰጠው ምላሽ ገልጸዋል፡፡

➢ **በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

በሰኔ 30/2004 የተመለከተው ተሰብሳቢ ሂሳብ በዝርዝሩ መሠረት፣

- የሂሳብ መደባቸው ያልተገለፀ/የማይታወቅ ብር 2,326,798.36
- ማስረጃ የሌለው /የክፍያ ቅጽና ማዘዣዎች/ “ 64,879,336.68
- ከማን እንደሚሰበሰብ ያልተገለፀ/የማይታወቅ “ 60,098,423.70
- በኔጌቲቭ /ክሬዲት/ የተመዘገበ ሂሳብ “ 7,379,716.96

መገኘቱን ጠቅሰን የተሰብሳቢ ሂሣቦች ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ተመሳሳይ ችግር የተስተዋለባቸው መሆኑን፤ እንዲስተካከሉ በተደጋጋሚ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት መሆኑን ይሁን እንጂ ችግሮቹ ሊቀረፉ አለመቻላቸውን በመግለጽ መ/ቤቱ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ችግሩ እንዲወገድ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ እና ባልተሟላ ማስረጃ ሪፖርት እንዳይዘጋጅ ቁጥጥር በማድረግ፣ ለበርካታ ዓመታት ሳይወራረዱ የቆዩና ያለበቂ ማስረጃ በተሰበሳብ ሂሳቦች ስለሚያዙ ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ በመኖሩ፤በቆይታ ብዛትም ሂሳቦቹን የመሰብሰቡ ሂደት ውስብስብና አዳጋች እየሆነ የሚሄድ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ፤ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብለቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግለቸው፤ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

3.1 <u>በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት

የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶችና በ6 የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 29,205,484.95 በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ- 13 ተመልክቷል/ ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	27,147,903.66
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		604,056.11
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		1,453,525.18
ድምር		29,205,484.95

በአዋጁ በመሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ ምስራቅ አዲስ አበባ ብር 25.09 ሚሊዮንና ውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 1.06 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፤ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S .Code) እና Custom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሳበሳበ የንግድ ትርፍ ግብር እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች ወሳኝ ስለሆነ፤ ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል::

3.2 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በስሩ ባሉ ስድስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር **853,920,158.83** እና በሌሎች 6 መ/ቤቶች ብር 12,250,953.19 በድምሩ ብር 866,171,112.02 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-12 ተመልክቷል/

ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አ.አ ወጪ እና ሌሎች ዕቃዎች ቅ/ጽ/ቤት ብር 475.95 ሚሊዮን፤ በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ብር 315.06 ሚሊዮን፤ በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 23.ሚሊዮን፤ ምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 16.19 ሚሊዮን ፤ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 12.03 ሚሊዮን ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት 14.10 ሚሊዮንና በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ብር 6.18. ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

መ/ቤቶቹ ለስራ አመራር ሪፖርታችን በሰጡት ምላሽ

- የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት የንብረት መውረስ ደብዳቤ ለድርጅቶቹ ተጽፎ ክትትል እየተደረገ መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ያለውን ቀሪ ሂሳብ በመመሪያ ቁጥር 69/2004 መሰረት ወደ ንብረት መያዝ ለማስተላለፍ የማጥራት ስራ መጀመሩን፣
- በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግዴታቸውን ባልተወጡ ደንበኞች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ወደ ህግ ማስከበርና ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማሣወቃቸውን፣
- የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ለ4 ግብር ከፋዮች የብር 7,035,679.02 የውሳኔ ማስታወቂያ የተላከ መሆኑንና ለቀሪዎችም አስፈላጊውን እርምጃም የሚወስዱ መሆኑን፣

- የሀዋሳ ለ6 ግብር ከፋዮች የብር 563,899.43 የግብር /ታክስ ማስታወቂያ የተላከ መሆኑና የሌሎችን የማጥራት ስራ እየተከናወነ መሆኑን፣
- የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ለአራት ድርጅት የግብር ማስታወቂያ ወጥቶ ሁለት ድርጅቶች ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታ አቅርበው በዝርዝር እየታየ ያለ መሆኑንና፣

ሌሎች ድርጅቶችም በቀረበው የኦዲት ግኝት መሰረት የግብር ማስታወቂያ ወጥቶላቸው በውሳኔው ላይ ቅሬታ ቀርቦ በመታየት ላይ ያለ መሆኑንና የተሠጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀበለውት ውዝፍ ገቢውን ለመሰበሰብ የተለያየ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ለስራ አመራር ሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢ እርምጃ በመውሰድ የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ለየመ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል::

3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 75,049.27 እና በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,888,598.34 በድምሩ ብር 4,963,647.61 የገቢ ደረሰኝ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፤የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል::

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፤ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።

3.4 የውስጥ ገቢን ሂሳብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ5 መ/ቤቶች የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ብር 24,606,079.30 ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ

ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ- 15 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር 13,136,062.00
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	663,646.38
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	10,806,370.92
በድምር	24,606,079.30

ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱት መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ በገንዘብ ያልተገለፀ የውስጥ ገቢ ሂሳብ በሪፖርት የማያካትቱ በ15 መ/ቤቶች /ዝርዝራቸው በአባሪ-15 ተመልክቷል/ ከልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ገንዘብ የሚሰበስቡና ሪፖርትም የማያደርጉ እንዲሁም ያለ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ፍቃድ የገቢ ደረሰኝ አሳትመው ገቢ የሚሰበስቡ 5 መ/ቤቶች ያሉ/አባሪ-18/ መሆኑ ታውቋል፡፡

ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪም ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቡትን ገቢ ሕገዊ በሆነ መንገድ በታተሙ ደረሰኞች ብቻ በመጠቀም እንዲሰበስቡና የገቢን ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት ሂሳብ የማይሰበሰቡ መ/ቤቶች

የወጪ መጋራት አሰባሰብ መመሪያ ቁጥር 26/2001 ክፍል 5.2/ሀ መሰረት የተቀጣሪዎች የእፎይታ ጊዜ እንደተጠናቀቀ ከጥቅል የወር ደመወዝ ላይ 10% በአሰሪው እየተቀነሰ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ፈሰስ የሚደረግ

መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶች - የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የጅማ ዩኒቨርስቲ እና የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት ሂሳብ የማይሰበስቡ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ወጪ መጋራት ሂሳብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች እንዲሰበስቡ አሳስበናል፡፡

3.6 ከየመኖሪያ ቤት አበል ግብር የማይቀንሱ መ/ቤቶች

በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 12/1 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማንኛውም ክፍያ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት ደንቡ በሚያዘው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ፣ የጅማ ዩኒቨርስቲ እና ህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት የመኖሪያ ቤት አበል በጥሬ ገንዘብ ከሚከፈላቸውና መኖሪያ ቤት በአይነት ከተሰጣቸው መምህራንና ሠራተኞች ላይ የገቢ ግብር የማይቀነስ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

መሰብሰብ ያለበት የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ ሳይሰበሰብ ሊዘገይ ከመቻሉም በላይ ሳይሰበሰብ ሊቀር የሚችልበትም አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡

በመሆኑም ያልተሰበሰበው ሂሳብ ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ተሰብስቦ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.7 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ ተመዝግቦ ስለተገኘው ሂሳብ

የተመዘገበው ሂሳብ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የሂሳብ መደቡን ጠብቆ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:-

በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን 3 ቅ/ጽ/ቤቶች ከተለያዩ የታክስ አይነቶች የሚሰበሰበው ገቢ በመንግስት የታክስ አስተዳደር (SIGTAS) ላይ በትክክለኛው ሂሳብ መደብ የማይመዘገብ መሆኑንና 2 መ/ቤቶች በተገቢው ሂሳብ መደብ ባለመመዝገቡ በተለያዩ በሂሳብ መደብ በድምሩ ብር

201,109,973.12 በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የገቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-17 ተመልክቷል/

የገቢ ሂሳብ በተገቢው የሂሳብ መደብ ካልተመዘገበ የሂሣብ ሪፖርት እና የአፈጻጸም ሪፖርት ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አወቃቀር መሰረት ትክክለኛውን የሂሳብ መደብ ተከትሎ ሊመዘገብ እና የሂሳብ መግለጫውም ትክክለኛውን የገቢ አፈጻጸም በገቢው አይነቱ እንዲያሳይ ተደርጎ ሊስተካከል ይገባል፡፡

3.8 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል።

3.8.1 በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 66 መሠረት በእቃዎች አያያዝ፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሣብ አሠራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ በስድስት ወራት ውስጥ ለከፋዩ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱም ሆነ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በበጀት አመቱ በተለያየ ምክንያት በስህተት ተሰብስቦና በገቢም ተመዝግቦ ነገር ግን ለባለመብቱ ተመላሽ የሚደረግ ሂሳብ ተገቢው ማስተካከያ የማይደረግለት መሆኑ፤
- በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 5/2000 አንቀጽ 5 መሰረት:-

  የጫት ላኪ ማህበራት ማህበራት በቀን ኮታቸው መሰረት ጫቱን ለሶጂክ የሚያቀርቡ መሆኑንና አገሪቷ ከውጪ ንግዱ ማግኘት ያለባትን የውጪ ምንዛሬ እያገኘች መሆኑን እንዲሁም በቀን ኮታቸው ልክ በመመሪያው መሰረት በማያቀርቡት ላይ ተገቢው እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል

ማህበራት በልዩ ልዩ ምክንያት በኮታው መሰረት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በቀን ኮታቸው ልክ የማያቀርቡ መሆኑንና በዚህም ምክንያት አገሪቷ በ2004 በጀት አመት ብቻ 3,099,618 የአሜሪካ ዶላር የውጪ ምንዛሬ ያጣች መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ለወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 543/1999 አንቀጽ 11 (9) የጉምሩክ ባለሥልጣን ስሌቱን የሚሠራው ቫወቸሩ በታደሰ ከ11ኛው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ሲሆን ስሌቱ በ30 ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለበትና በአንቀፅ 11(10) ደግሞ አምራቹ የምርት ሥራው እንዳይስተጓጎል ለሦስት ጊዜ ብቻ በኢንሹራንስ ዋስትና እቃዎች ወደ አገር ሊያስገባ ይችላል ብሎ ይደነግጋል፡፡ መመሪያው በትክክል ለመዋሉ ኦዲት ሲደረግ አብዛኛው የቫውቸር ተጠቃሚዎች መጀመሪያ ካስገቡት በተጨማሪ በኢንሹራንስ ዋስትና ዕቃዎች ወደ አገር አስገብተው ሳያወራርዱ ለዓመታት የቆዩ መኖራቸውን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- በታክስ ኦዲተሮች የግብር ውሳኔ መሰረት የሚሰበሰበው ሂሳብ በትክክለኛው የታክስ አይነትና የሂሳብ መደብ እየተመዘገበ የሂሳብ ሪፖርት የሚዘጋጅ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል አንድ ድርጅት ከተለያየ የታክስ አይነት ተጨማሪ የግብር ውሳኔ ሲደርሰው ለየታክስ አይነቱ የክፍያ ስምምነት መግባት ሲኖርበት በጥቅል ስምምነት እንዲገባ የሚደረግ ሲሆን ክፍያ ሲፈጽምም ለተለያዩ የታክስ አይነቶች የከፈለ ቢሆንም የሚመዘገበው ግን በአንዱ የታክስ አይነት ላይ በማጠቃለል በመሆኑ፤ የሚዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን ሁኔታ የማያሳይ መሆኑ፤
- በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 ክፍል 7 አንቀጽ 26 ታክስ ስለማስታወቅና ስለመክፈል ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እያንዳንዱ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ለታክስ ባለስልጣን ማስታወቅ እንዳለበት ያዛል፡፡ ስራው በዚሁ መሰረት የሚሰራ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት/
    - ቻይና ጂሊን ፕሮቪንስ ትራንስሚሽን ኤንድ ሰብስቴሽን ፕሮጀክት ካምፓኒ (0000043793) ከ2001 በጀት

አመት በኃላ የተጨማሪ እሴት ታክስም ሆነ የንግድ ትርፍ ያላሳወቀ መሆኑ፣

- ፍላወር ፖርት ካርጎ ድርጅት /0005021831/ ከጥር 2004 ጀምሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቀ በመሆኑ፣ ምክንያት ለመንግስት ገቢ መሆን የሚገባው ገንዘብ በወቅቱ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

➢ ከግብር ከፋዩ የሚሰበሰብ ግብር/ገቢ ሙሉ በሲግታክስ (በሲስተም ላይ) የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአዳማና በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤቶች ከተወሰኑ ግብር ከፋዮች በማኑዋል ደረሰኝ የተሰበሰበ ገቢ በሲግታክስ (ሲስተም ላይ) የማይመዘገብ መሆኑን ፣
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በታክስ ኦዲትም ሆነ በዴስክ ኦዲት የሚገኙ (የሚጠየቁ) ተጨማሪ የግብር ዉሳኔዎች በሲግታክስ (ሲስተም ላይ) የማይመዘገቡ መሆኑ፣
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት የሚሰበሰበው ገቢ በመንግስት ታክስ አስተዳደር ስርዓት/SIGTAS/ ላይ የማይመዘገብ መሆኑ፣ የግብር ከፋዩን መረጃ በተሟላ ሁኔታ ስለማይገኝ የታክስ ኦዲት በሚሰራበት ጊዜ ዕዳ ያለበትና የሌለበትን በሚለይበት ጊዜ፣ በጊዜው ታክስ ያሳወቁና ያላሳወቁትን ለመለየት የማይቻል መሆኑ፤

➢ በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ሳጋ ሎጊታ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሀምሌ ወር 2003 ዓ.ም የተጨማሪ እሴት ታክስ ሽያጭ ብር 57,272.70 በነሐሴ ወር 2003 ውስጥ መክፈል ሲገባው ጥር ወር 2004 በመክፈሉ ቅጣትና ወለድ አለመክፈሉ፤

➢ ስለፌደራል መንግስት አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀፅ 70 መሰረት ማናቸዉም የመንግስት መስሪያ ቤት ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለዉጪ ኦዲተሮች ለማናቸዉም ጉዳይ በመረጃነት የሚያስፈልጉትን የፋይናንስ መረጃዎችና መዛግብት ቢያንስ ለአስር አመት ማቆየት እንዳለበት ያዛል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ፡-

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል 67 ዲክላራሲዎኖች ለኦዲት ተጠይቀው ባለመቅረባቸው፣.

- በምስራቅና ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤቶች በኩል በተወሰኑ ግብር ከፋይ ፋይሎች ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች በፋይላቸው ውስጥ ባለመገኘቱ፣
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዲክላራሲዮን ቁጥር C-827/2011 ለተመዘገበው እቃ ከዲክላራሲዮኑ ጋር በአባሪነት የዋጋ ሰነዱ የሌለ በመሆኑ
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል የማስጫኛ ዋጋ (airway bill) አንድ ሶስተኛው ብቻ ለቀረጥ ማስከፈያነት የሚወሰድ ቢሆንም ይህን ስሌት ለመጠቀም የሚያስችል መመሪያ ወይንም ሰርኩላር ለኦዲት ባለመቅረባቸው የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ብር ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

➢ በገንዘብ ትልልፍ መመሪያ ቁጥር 22/2001 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት እያንዳንዱ የባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት የሰበሰበውን የተጨማሪ ዕሴት ታክስና የቅድመ ታክስ ክፍያን ወሩ ባለቀ ከ10/አስር/ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወደ ባለሥልጣኑ ዋናው መ/ቤት የአደራ ሂሳብ/አካውንት መተላለፍ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ሆኖም
  - በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 41,589,986.08 እንዲሁም
  - በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 37,163,801.33

በ2004 በጀት አመት የሰበሰቡትን የክልል መንግሥታትና የከተማ አስተዳደሮች የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ቅድመ ግብር ድርሻ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ወደ ዋናው መ/ቤት የአደራ ሂሣብ /አካውንት መመሪያው በሚያዘው መሠረት በወቅቱ ያልተላለፈ መሆኑ ተውቋል፡፡

በመሆኑም የመንግስት ገቢ የወጡትን የገቢ ደንብና መመሪያዎችን መሰረት በማድረግ እንዲከናወንና ለታዩትም ድክመቶች አስፈላጊውን ማስተካከያዎች በማድረግ በገቢው እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

3.8.2 የሌሎች መ/ቤቶች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ ፣

- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የግል ጤና አገልግሎቱ ከሚያገኘዉ ገቢ ዉስጥ በመመሪያው መሰረት የሆስፒታሉን ድርሻ 15% ገቢ ያላደረገ መሆኑ
- የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች ሽያጭ ገቢ የሚሰበስብ ሲሆን፣ ለሚሰበሰበው ገቢ ግን በሚመለከተው አካል የጸደቀ ተመን የሌለው መሆኑ ፣
- የማሪታይም ጉዳዮች ባለስልጣን ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያስከፍለውን ልዩ ልዩ ታሪፍ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሕግ (በደንብ) ሳያጸድቅ ለባህረኛ መታወቂያ ደብተር መስጠትና ማደስ፤ የመርከብ መኮንኖች የብቃት ማረጋገጫ ዕውቅና የምስክር ወረቀት፤ የወችኪፒንግ የምስክር ወረቀት፤ የጤንነት ምርመራ ማረጋገጫ ውጤት ዕውቅና የምስክር ወረቀት፤ እና የመልቲ ሞዳልትራንስፖርት አከናዋኞች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፤ የንግድ ስራ ፈቃድና የሰነድ መመርመሪያ ክፍያ የምስክር ወረቀት ለሰጠበት ገቢ የሰበሰበ መሆኑ፣

➢ <u>**የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ**</u>

- ♦ ኮሌጁ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ለሰበስበው ገቢ በመረጃ የተደገፈ የገቢ ተመን የሌለው መሆኑ ፤
- ♦ ኮሌጁ ከውስጥ ገቢ ከሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ ለኮሌጁ ካፌ ብር **100,000.00** በብድር የሰጠ መሆኑ፤
- ♦ ለኦዲት ከቀረበው የገንዘብ መቀበያ ሰነድ ቁጥር **05101-05150** ውስጥ የገንዘብ መቀበያ ሰነድ ቁጥር **05104** ለኦዲት ሥራው ያልቀረበ መሆኑ፤
- ♦ ከቁጥር **06501-06550** እና **05701-05750** የሆኑ ሁለት የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ፓዶች ከዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ የተደረጉ ቢሆንም በኦዲት ወቅት ያልቀረቡ መሆኑ፤

➢ <u>**የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ**</u>

- ♦ ኮሌጁ በ2003 በጀት ዓመት ብር 20,005.16 ከተለያዩ የገቢ ርዕሶች የሰበሰበውን ገቢ ያልመዘገበ ፣ ወደ ባንክ ገቢ

ያላደረገ እና ለግብርና ቴክኒክ ሙ.ያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ሪፖርት ያላደረገ መሆኑ፤

- <u>የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ</u>

  - ከግል ጤና አገልግሎቱ ከሚያገኘዉ ገቢ ዉስጥ በመመሪያው መሰረት የሆስፒታሉን ድርሻ 15% ገቢ ያላደረገ መሆኑ ፤
  - የመያዣና የተመላሽ ሂሳብ በመዝገብ (በሌጀር) የማይመዘገብ፤ ከወጪ ቀሪው የማይታወቅ እንዲሁም በፋይናንስ መመሪያው መሰረት በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ እንዲታይ ያልተደረገ መሆኑ ፤

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሥራ ተቋራጮች በፀደቀ የውል ማራዘሚያ መሠረት ስራቸውን አጠናቀው ማስረከብ ሲኖርባቸው ባለማስረከባቸው እስከ 2004 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በድምር ብር 81,110,000.00 ዩኒቨርሲቲው ከሥራ ተቋራጮች በቅጣት መልክ Liquidation Damage ካሳ ማስከፈል ሲገባው ያላስከፈለ መሆኑ፣በተጨማሪም አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት በወቅቱ ንብረቱን ገቢ ባለማድረጋቸው በድምሩ ብር 2,625,402.93 የቅጣት ክፍያ እንዲከፍሉ መደረግ ሲገባው እንዲከፍሉ ያልተደረገ መሆኑ በአጠቃላይ ድምር ብር 83,735,402.93 የቅጣት ክፍያ አልተሰበሰበም፡፡
- ተቋራጮች በገቡት ውል መሠረት የግንባታ ሥራቸውን ባለማጠናቀቃቸው በጠቅላላው ድምር ብር 17,320,938.60 ቅጣት /Liquidation Damage/ መክፈል ሲገባቸው በአማካሪ ድርጅቱም በኩል ሆነ በዩኒቨርሲቲው እንዲከፍሉ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ከመደበኛ በጀት እንቅስቃሴ የሚገኙ የመልካም አፈጻጸም ዋስትናና ቅጣት ገቢዎች ወደ ውስጥ ገቢ ሂሳብ የሚገቡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ገቢ በሚሰበሰበው ልክ ወደ ሂሳብ ቋት ብሎም ወደ ሪፖርት በትክክል መወሰዱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርትና በሂሳብ

መመዝገቢያ ቋት መካከል ልዩነት ብር 2,016,742.21 የታየ መሆኑ ታውቋል፡፡

- የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ-ዋናው ግቢ እና የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ-የህክምናና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የውስጥ ገቢ ደረሰኞች ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የገቢው ዓይነት፣ የተከፈለበት ምክንያት፣ የሂሳብ መደብ ባለመያዛቸው፣ የሃዋሳ ዩኒቨርስቲ-የግብርና ኮሌጅ የውስጥ ገቢ ሂሳብ የገቢ ማመንጫዎች የሆኑት የገቢ ዓይነቶች ዝርዝርና የገቢ ማስከፈያ ተመን በዝርዝር የሚገልጽና በሚመለከተው አካል የጸደቀ ዶክመንት የሌለው በመሆኑ እና ለሎች 10 መ/ቤቶች /ዝርዝራቸው በአባሪ-16 ተመልክቷል/ በተሟላ መልኩ ምዝገባ ባለመከናወኑ የውስጥ ገቢ ሂሳብ በዝርዝር ኦዲት ማድረግ አልተቻለም፡፡

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፣ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፣ እንድሁም በገቢ ደረሰኝ አያያዝ ረገድ የሚደረገው ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

4. የወጪ ሂሣብ

4.1 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ22 መ/ቤቶች ብር 13,803,414.08 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝረዝሩ በአባሪ - 21 ተመልክቷል/
ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፡

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	6,912,883.08
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		71,023.36
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		6,819,507.64
ድምር		13,803,414.08

ተገቢውን ማስረጃ አለማቅረብ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

4.2 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ13 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 132,364,911.31 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ- 20 ተመልክቷል::/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	103,720.00
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		132,261,191.31
ድምር		132,364,911.31

ሆኖ ተገኝቷል::

ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚየሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፤ በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጎላ ያሉት ናቸው::

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል::

4.3 ከደንብና መመሪያ ወጪ አለአግባብ የተፈጸመሙ ክፍያዎች

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ21 መ/ቤቶች ብር

137,363,575.83 ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል። /ዝርዝሩም በአባሪ- 23 ተመልክቷል/ ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	345,361.96
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		135,940,434.62
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		869,414.24
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		208,365.01
ድምር		137,363,575.83

ሆኖ ተገኝቷል።

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ ክፍያዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤

በጅማ ዩኒቨርሲቲ 77.61 ሚሊዮን፣አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ 34.77 ሚሊዮንና ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ 10.82 ሚሊዮን ሲሆን፤ ከምክንያቶቹም በድምሩ 97.95 ሚሊዮን በግንባታ ቦታ ላይ ያሉ ዕቃዎች (materials on site) ተብሎ የተከፈለና ሌሎችም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመፈጸም፣ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈልና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የሃላፊነት አበል ለዩኒቨርሲቲ የስራ አመራሮች ክፍያ መፈጸሙና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በተጨማሪም በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን በቁጥር መ30/ጠ/ጠ13137/820 በቀን 5/13/2001 ዓ.ም ባስተላለፈው ሠርኩላር መሠረት የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተግባራዊ እንዳይሆን መመሪያ የተላለፈ ቢሆንም፤ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በ2004 በጀት ዓመት ለትርፍ ሰዓት ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት መመሪያ የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተፈከለውም ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል።

4.4 ግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዠዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ30 መ/ቤቶች ብር 353,568,759.15 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -22 ተመልክቷል፡፡/ ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	5,089,629.84
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		306,772,006.14
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		3,930,292.66
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		37,776,830.51
ድምር		353,568,759.15

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 240.22 ሚሊዮን፤ የኢንፎረሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ 36.19 ሚሊዮን፤ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ 20.34 ሚሊዮን፤ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ 14.08 ሚሊዮን ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 8.75 ሚሊዮንና ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 6.74 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን የግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈጸም እና የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴን ተግባራዊ የሚሆነው ግልጽ ጨረታ ሁለት ጊዜ ወጥቶ እቃው በሚፈለገው ጥራትና መጠን ካልተገኘ ቢያንስ አምስት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ መጋበዝ የሚለውን ሳያሟሉ ግልጽ ጨረታ ያላወጣና በውስን ጨረታው የግዥ ዘዴ በቂ አቅራቢዎች ሳይጋብዙ ግዥን ማከናወን የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፤ የመንግስትን አዋጅ

በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

4.5 የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ

በበጀት ዓመቱ መ/ቤቶች የፈጸሙት ክፍያ ትክክለኛነት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች በተለያየ ምክንያት የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 3,507,062,927.60 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 30 ተመልክቷል/ ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	ብር 3,410,102,390.27
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	96,960,573.33
በድምሩ	3,507,062,927.60

የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሣብ ውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 3.16 ቢሊዮን የሠራዊት ደመወዝና ብር 51.98 ሚሊዮን ለመረጃ ግዥ ወጪ ያደረገው፤ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት 187.85 ሚሊዮን፤ እንዲሁም ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 41.28 ሚሊዮን፤ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 29.70 ሚሊዮንና ሰመራ ዩኒቨርሲቲ ብር 14.00 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የደመወዝ ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ በበጀት ዓመቱ የተቀጠሩ በዝውውር የመጡ በጡረታ የተገለሉ እና በተለያየ ምክንያት የተሰናበቱ የሠራዊት አባላት ስም ዝርዝር እና የተወሰኑ ዓመታተ በማገልገላቸው ማበረታቸ የተሰጣቸው አባላት ስም ዝርዝር ለኦዲት ተጠይቆ መ/ቤቱ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሠራዊት ደመወዝ ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ፤ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልገሎትና በሥሩ የሚገኙ ዋና መመሪያዎች ለደመወዝ ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ፔሮሉ በኮድ በመቅረቡ ኮዱን የሚገልጽ ማስረጃ ለመሰጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፤ ሌሎቹ የወጪ ሂሣቦች ለምሳሌ የመኪና ጥገና የነዳጅ ለማጣራት የመኪኖች ታርጋ የስልክ ቁጥሮችና የመሳሰሉት ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ከሚስጥራዊነት አንጻር ማቅረብ እንደማይቻል በኦዲት ወቅት መገለፁና የሌሎችም ክፍያ የተፈጸመባቸው ደጋፊ የክፍያ ሰነዶች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር በላከው መልስ ከመረጃው ሚስጥራዊነት አንጻር የተሰዉ የሰራዊት አባላትና አዲስ የተቀጠሩት ሠራዊት አባላትን ከደህንነት አንጻር ችግር ያለበት በመሆኑ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ሚስጥራዊ ሰነዶችን አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

4.6 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆረጠለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ6 መ/ቤቶች በብር 20,240,407.36 የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 25 ተመልክቷል/::

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	20,196,215.78
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		5,284.49
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		<u>38,907.49</u>
ድምር		<u>20,240,407.36</u>

ከዚህም ውስጥ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 18.87 ሚሊዮን እና መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 1.32 ሚሊዮን ለተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆን፣ በተጨማሪም በ4 መ/ቤቶች ብር 634,568,430.11 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸው (የዝርዝራቸው አባሪ 25/1) ከዚህም ውስጥ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብር 409.80 ሚሊዮን ትምህርት ሚኒስቴር ብር 171.00 ሚሊዮንና ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ብር 49.83 ሚሊዮን ይገኝበታል፡፡

4.6.1 <u>በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ከውጪ ተገዝተው ገቢ ያልተደረጉ ዕቃዎች</u>

- በዩኤስ ዶላር 1,620.76 የተገዛው ቢት ብሬከር 17 1/2 እንዲሁም 10,000.00 ዶላር ከሚያወጣው ስታንዳርድ አክሰሰሪስ ፎር ድሪሊንግ ውስጥ ሁለት አዳብተር ቢት ብሬከር ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤

- በዩኤስ ዶላር 812,800.04 የተገዛው የውሃ መቆፈሪያ ሪግ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤
- በዩኤስዶላር 3,235.00 የተገዛው የድሪሊንግና ሌሎች ተጓዳኝ መሣሪያዎች መለዋወጫ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ከተገዙት የመለዋወጫ ዕቃዎች ውስጥ በዩኤስ ዶላር 4,600.00 የተገዙት የመለዋወጫ ዕቃዎች ያልመጡ መሆኑ፤

  በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

የዚህ ዓይነት አሠራር ለንብረት ብክነት ስለሚያጋልጥ አሠራሩ ተገቢ ሆኖ ባለመገኘቱ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ሊደረግና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ንብረቶች ለየመ/ቤተቶቹ አገልግሎት ለመዋላቸው በማስረጃ እንዲረጋገጥ ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.7 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ12 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 546,599,171.27 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 24 ተመልክቷል/ ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	182,735,541.78
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		363,864,181.49
ድምር		546,599,273.27

ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች መካከል ውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 302.9 ሚሊዮን፤ጂማ ዩንቨርሲቲ 123.9 ሚሊዮን፣ ትምህርት ሚ/ር 47.98 ሚሊዮን እና ማዕድን ሚኒስቴር 28.68 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርተችን አሳስበናል፡፡

4.8 በብልጫ የተከፈለ ወጪ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፣ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡ በ 7 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግዢዎች ብር 542,220.60 እና ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በ4 መ/ቤቶች ብር 851,589.66 በጠቅላላው ብር 1,393,810.26 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 29 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ዕደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፣በድገሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገበው ውል ውጭ በመክፈልና ከውሎ አበል ተመንና የትርፍ ሰዓት ክፍያ በላይ በመክፈል የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የግዢ ስርዓቱን ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው በብልጫ የተከፈለውም ወጪ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.9 የወጪ የሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ17 መ/ቤቶች ብር 18,255,126.27 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -28 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	2,657,943.52
የአቅም ግንባታ		2,176,732.67
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		13,420,450.80
ድምር		18,255,126.47

የወጪ ሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የኢትዮ. ጂኦሎጂካል ሰርቬይ 11.73 ሚሊዮን እና የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 2.37 ሚሊዮን እና በሀገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ 1.61 ሚሊዮን ከፍተኛዎቹ ናቸው።

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.10 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ

በወጭ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 34,801,740.53 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2004 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -27 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	199,691.14
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		7,584,789.91
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		27,017,259.48
ድምር		34,801,740.53

የተገኘ ሲሆን ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ6 የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች ብር 159,482,075.35 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ/ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-26 ተመልክቷል/ ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የውስጥ ገቢ ሂሳባቸውን በሪፖርት የማያካትቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት /አባሪ-15 ይመልከቱ/ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት እንደማያደርጉ ተውቋል፡፡

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. የተከፋይ ሂሣብ

5.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ29 መ/ቤቶች ብር 317,303,705.48 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-31 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	496,549.30
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		113,897,476.65
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		333,599,268.11
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		43,135,173.52
ድምር		491,128,467.58

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች ሀገር መከላከያ ሚ/ር ብር 173.82 ሚሊዮን፤ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 159.33 ሚሊዮን፤ ትምህርት ሚኒስቴር ብር 64.329 ሚሊዮን፤ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 25.01 ሚሊዮን እና የግብርናና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማስተባበሪያ ብር 23.12 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ በሌሎች መ/ቤቶችም የተከፋይ ሂሳቡ የሠራተኞች የጡረታ መዋጮንና በሌሎች የገቢ መሰብሰብ ግዴታዎች ምክንያት ተሰብስበው ለሚመለከተው አካል ያልተከፈሉትን ይጨምራል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰኔ 30/2004 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ብር 163.50 ሚሊዮን የሠራዊቱ አባላት ደመወዝ ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ሂሣብ የተያዘና ሂሣቡም በወጪ የተመዘገበ መሆኑን /እና ሌላ ብር 10.32 ሚሊዮን ለበርካታ ዓመታት በተከፋይ የተያዘ/ በመጥቀስ አሠራሩ ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በመሆኑ እንደማንኛውም የፌደራል መንግሥት መ/ቤት ያልተከፈለ ደመወዝ በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት ደመወዝ ካልተከፈላቸው አባላት ጥያቄ ሲቀርብ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር እየተጠየቀ እንዲከፈልና ሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በትምህርት ሚኒስቴር በዴቢት ብር 378,511.65 ተመለከተ መሆኑ፤

- በሀገር አቀፍ የተምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 2,670,005.52 በዴቢት የተመለከተ መሆኑ፤
- ጅማ ዩኒቨርሲቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በአጠቃላይ ብር 25,010,347.22 ተከፋይ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን ምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደቆየ እና ለማን እንደሚከፈል ለማረጋገጥ ሰነዶቹ ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን ብር 110,531.08 በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5035 ባልተለመደ ዴቢት ሚዛን /Abnormal Balance/ ሪፖርት ተደርጎ የተገኘ ሲሆን ሰነዱም ሆነ ስለሁኔታው የቀረበ አጥጋቢ ምክንያት የሌለ መሆኑ፤
- በዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 846,728.84፣ ወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 59,741.11፣ ሠመራ ዩኒቨርስቲ ብር 118,124.17፣ ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ ብር 1,121,585.97 እና ሃዋሳ ዩኒቨረስቲ ወንዶ ገነት ኮሌጅ ብር 296,703.55 በዴቢት የተመለከተ መሆኑ፤
- ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በአጠቃላይ ብር 2,842,529.98 ተከፋይ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን ተቀጽላ ሌጀር ባለመቋቋሙ ለነማን እንደሚከፈልና ለምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደቆየ ለማረጋገጥ አለመቻሉ ፤
- በአምቦ ዩኒቨርስቲ የተከፋይ ሂሳቦች በተገቢው የሂሳብ መደብ እየተመዘገቡ ሪፖርት የሚደረጉ ለመሆናቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ ብር 154,448.67 የኮንትራት መያዣ ሂሳብ በበጀት አመቱ መጨረሻ በሪፖርት እንዳይታይ በሚል የሂሳብ ማስተካከያ (ሪቨርሲንግ) የተሰራ መሆኑ፤
- የተከፋይ ሒሳቦች ምዝገባ ሁኔታ ሲጣራ በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 2,365,746.50 አለአግባብ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱና የተከፋይ ሂሣብ አጠቃላይ ሌጀር በተቀጽላ ሌጀሮች ላይ ከተመዘገቡት ጋር ተመሳሳይ ለመሆናቸው ሲጣራ በተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ ብር 344,856.43 በዴቢት አቅጣጫ የሚታይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2004 የሂሳብ ሪፖርት የተመለከተውን የተከፋይ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለኦዲት በቀረበው የተከፋይ ሂሣቦች ዝርዝር መሠረት፣

- የሂሳብ መደባቸው ያልተገለፀ/ ብር 8,240,700.09
- ሂሳቡ የተመዘገበበት ቀን ያልተገለፀ " 10,562,176.07
- ሂሳቡ የተመዘገበበት ሰነድ ያልተገለፀ " 69,628,309.76
- ለማን እንደሚከፈል ያልተገለፀ " 91,367,682.10
- በነገቲቭ /ዴቢት/ የተመዘገበ ሂሳብ " 8,568,445.89

በመገኘቱ የተከፋይ ሂሣቦች ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ተመሳሳይ ችግሮች የተስተዋለባቸው መሆኑና፣ እንዲስተካከሉ በተደጋጋሚ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ መሆኑን፤ ይሁን እንጂ ችግሮቹ አለመቀረፋቸውን በመጥቀስ መ/ቤቱ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ችግሮቹ እንዲወገዱ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ ባልተሟላ ማስረጃ ሪፖርት እንዳይዘጋጅ ቁጥጥር እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

ለረጅም ጊዜ ሲንከባለል የቆየውን የተከፋይ ሂሣብ ክምችት መልክ ለማስያዝና መፍትሄ እንዲያገኝ የመ/ቤቱ የበላይ አመራር ትኩረት በመስጠት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ፣ የኮንትራት ሠራተኞች ቀጥሮ ሂሣቡን የማጣራትና ዝርዝር በማዘጋጀት የተጓደሉትን መረጃዎች ማለትም ቀን፣ የሂሣብ መደብ የማጣቀሻ ቁጥር እና ሌሎች ማስረጃዎችን የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሶ በኦዲት ግኝቱ ቀን የሌላቸው ተብሎ ከተገለጸው ውስጥ ብር 18,219,620.05 ቀኑ እንዲሟላ መደረጉን፣ የማጣቀሻ ቁጥር የሌላቸው ተብሎ ከተጠቀሰው ሂሣብ ብር 42,522,328.04 እና ከማን እንደሚሰበሰብ ካልተገለጸው ብር 5,210,531.90 ማስረጃዎቹ እንዲሟሉ መደረጉን መ/ቤቱ ገልጿል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱት የአሠራር ችግሮች ምክንያት የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

6. የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ27 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ብር 212,476,799.01 ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ-32 ተመልክቷል::/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	17,952,494.26
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		192,593,650.27
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		1,395,369.47
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		535,285.01
ድምር		212,476,799.01

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 40.97ሚሊዮን፣ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 30.49 ሚሊዮን፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 28.21 ሚሊዮን\ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ 22.22 ሚሊዮን እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር የቆላ ንብ ማጥፍያ ፕሮጀክት 21.63 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱም መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙም የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል::

6.2 ያልተሠራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% ላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ84 መ/ቤቶች ብር 2,761,425,768.89 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-32 ተመልክቷል፡፡/ ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	167,316,281.89
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች		141,724,380.49
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		310,705,414.10
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች		2,141,679,692.56
ድምር		2,761,425,768.89

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ትምህርት ሚኒስቴር ብር 657.51 ሚሊዮን ፤ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 234.15 ሚሊዮን ፤ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ብር 221.67 ሚሊዮን ፤ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 198.42 ሚሊዮን ፤ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 161.57 ሚሊዮን እና የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ብር 112.74 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም ሌሎች መ/ቤቶች በመንግስት ተፈቅዶላቸው ሊጠቀሙበት የሚችሉትን በጀት እንዳይጠቀሙ ከማድረጉም በላይ የብቃት ማነስን (inefficiency) የሚያመለክት በመሆኑ፤ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች ተገኝቷል፡፡

ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	21 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	18 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	12 መ/ቤቶች
ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ	20 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	33 መ/ቤቶች
ተያያዥነት ያለቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	3 መ/ቤቶች

እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-33 ተመልክቷል፡፡/ መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንም በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

7.2 በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች

- የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 208/2000 በተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት መሰረት መስራት ሲገባው፡-
- ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸውን ንብረቶች መዝግቦ የሚይዝበት መቆጣጠሪያ መዝገብ ያለማዘጋጀቱ፣

- ከፕራይቬታይዜሽን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ የሚላከው የንብረት ርክክብ መረጃ በዝርዝር ሳይሆን በጥቅል መሆኑ

በመሆኑም ንብረቶቹን መዝግቦ የሚይዝበት መቆጣጠሪያ መዝገብ ካለዘጋጀ የተረከባቸውን ንብረቶች ለሌላ ጥቅም ሊውል ስለሚችልና በአካል የተገኙትን ንብረቶች ብቻ ርክክብ ማድረጉ ወደ ገቢ ያልተላለፉትን የንብረቶቹን ዝርዝር ስለማያሳይ በሙሉ ቦርዱ ላይረከብ ይችላል፡፡ በመሆኑም ባላአደራ ቦርዱ የመቆጣጠሪያ መዛግብት በማዘጋጀት የተረከባቸውን ንብረቶች በሃላፊነት ሊይዝና ሊጠብቅ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ባላአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታዜሽን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ንብረቶችን ሲረከብ በመጠን በዓይነት እና በዋጋ ተለይተውና ተዘርዝረው ሊረከብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

- <u>ከመነሻ ዋጋ በታች የተከናወነ የንብረት ሽያጭ</u>

የፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 በክፍል አራት አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1/2/3 ላይ በተደጋጋሚ ጨረታ ስለማወጣት እንደተቀመጠው በሁለተኛ ዙር ለመሸጥ ተሞክሮ በቂ ተወዳዳሪ /ገዥ/ ካልተገኘ የግምት ዋጋውን በማሻሻል ለሦስተኛ ጊዜ የጨረታ ማስታወቂያ በማወጣት በተገኘው ዋጋ ሽያጩ ይፈጸማል ብሎ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ በዚሁ መሠርት መስራቱን ኦዲት ሲደረግ የንብረቶቹ ሽያጭ የግምት ዋጋው ሳይሻሻል ከመነሻ ዋጋው በታች በመሸጡ በልዩነት ምክንያት ብር 3,995,192.88 በማነስ በሥራ አመራር ቦርድ በተወሰነው መሠረት ሽያጩ ተከናውኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ከመነሻ ዋጋ በታች ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት የግምት ዋጋውን በማሻሻል በድጋሚ ጨረታ ቢወጣ በተሻለ ዋጋ ሊሸጥ ስለሚችል በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ መሆን እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

- <u>የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ለተረከባቸው ንብረቶች ሽያጭ ጨረታ ሰነድ አለመቅረቡ</u>

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ የተረከባቸውን የተለያዩ ንብረቶች የፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003

መሰረት በማድረግ ሽያጩ መከናወኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከንብረት ሽያጭ የተሰበሰበው ብር 2,000,000.00 ሽያጩ የተከናወነበት የጨረታ ሰነድ ለኦዲት ስራ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡ በመሆኑም ሽያጩ በመመሪያው መሠረት ላይከናወን ስለሚችል በተጨማሪም በአ/ማህበር ገቢ የተደረገው ሂሳብ ትክክል ላይሆን ስለሚችል በአ/ማህበሩ የተከናወኑ ሽያጮች ሂሳብ ገቢ ሲደረግ ሽያጩ የተካሄደበት ሰነድ ከገቢ ማስረጃው ጋር በማያያዝ ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

- በትምህርት ሚኒስቴር በኮሪዶር ላይ የተቀመጡ በርካታ የሸንት ቤት ዕቃዎችና የእጅ መታጠቢያ ሲንኮች ፣ ጠረጴዛና ወንበሮች ፣ በአንድ ዕቃ ግ/ቤት የተለያዩ በካርቶን ታሽገውና ተበታትነው የተቀመጡ የትምህርት መጻሐፍት ፣የማባዣ ወረቀትና በርካታ ቶነሮች ለመኖራቸው በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በICT መጋዘን ውስጥ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች አያያዝ ሲታይ፡-
  - ዕቃ ግ/ቤት ሰራተኛ የነበሩት ግለሰብ ወደሌላ መ/ቤት ተመድበው ከሄዱበት ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ እስከአሁን ድረስ አምስቱ እስቶሮች የታሸጉ እና ሙሉ በሙሉ ርክክብ ያልተከናወነ መሆኑን፣
  - በታሸገው እስቶር ውስጥ የሚወገዱና የሚያገለግሉ ዕቃዎች ሳይለዩ በአንድ ላይ በመቀመጣቸው ንብረቶች ለብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡
- በሃገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ የተለያዩ መወገድ የሚገባቸው አሮጌ ወንበሮች፤ ጠረጴዛዎች፤ ኮምፒውተሮች፤ፕሪንተሮች፤ ሸልፎች፤ ቁምሳጥኖች፤ ሸንትሌተሮች፤ የመኪና ጎማዎችና መለዋወጫ እቃዎች፤ ስካነሮችና የተለያዩ የጽህፈት መሳርያዎች ሳይወገዱ ተከማችተው ተገኝተዋል::
- <u>ጅማ ዩኒቨርሲቲ</u>
  - ግዥ ከመፈፀሙ በፊት በቋሚም ሆነ በአላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት ውስጥ ንብረት ለመኖሩና ላለመኖሩ የግምጃ ቤት ሰራተኛው የሚያረጋግጥበት አሰራር የሌለ መሆኑ፣
  - ጥቅም ላይ ውለው የተመለሱ ዕቃዎች ግምጃ ቤት ውስጥ በርካታ በሽያጭ፣በስጦታ ወይም መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡- የመኪና ጎማ 7.5*16 ብዛት 801፣ጎማ

11*20 ብዛት 32፣ ዴል ኮምፒውተር ብዛት 139፣የቁም ፍሪጆች ብዛት 35 እና ሌሎች በርካታ ንብረቶች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

- በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ቤት መሰል ትልቅ ፍሪጅ ለበርካታ ዘመን ያለስራ የተቀመጠ መሆኑና የፍሪጅ ዕቃዎቹ በአቀማመጥ ምክንያት ለብልሽት በሚዳርግ ሁኔታ ላይ የሚገኙ መሆኑና አገልግሎት ሳይሰጡ በንብረት ክፍሉ ውስጥ የሚገኙ የመስክ ድንኳኖች ብዛት 18፣ አልጋ ብዛት 21፣ water pamp ከተገዛ ጊዜ ጀምሮ የማይሰራ የሚገኙ መሆኑ፣
- በ Building and Spare part ግምጃ ቤት ውስጥ ያለውን ንብረት በተመለከተ በንብረት ክፍል ውስጥ ባለው ቢን ካርድ ላይ የሚታየው እና በስቶክ ላይ የሚታየውን የንብረት ከወጪ ቀሪ እኩል ለመሆኑ ኦዲት ሲከናወን የተለያየ ከወጪ ቀሪ እንደሚያሳይ ለማየት ተችሏል፡፡ (ለምሳሌ፡- ፕላግ አዳብተር በንብረት ክፍል የሚገኝ ብዛት 1,728.00 በቢን ካርድ ላይ 1,426 እና ስቶክ ላይ 1,360.00)

➢ <u>ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ</u>

- በንብረት መጠበቂያ መጋዘን የሚገኙት እቃዎች በዓይነት፣በባህሪይና በሚሰጡት አገልግሎት ተለይተው በሥርዓት ያልተቀመጡ በመሆኑ ከፍተኛ ዋጋና ብዛት ያላቸው እቃዎች ለብልሽትና ለጉዳት የተዳረጉ መሆኑ፣
- ብዛት ያላቸው ያገለገሉ ዕቃዎች በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች ተበታትነው የሚገኙ መሆኑ፣
- በቀን 19/12/04 ዓ.ም በጣለው ከፍተኛ ዝናብ ምክንያት በሾንጋ ወንዝ አቅራቢያ የሚገኘው የዩኒቨርሲቲው ምግብ ቤት በጎርፍ በመጥለቅለቁ ብር 422,251.08 የሚሆን የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ ከጥቅም ውጭ መሆኑ <u>ለምሳሌ</u>፡- አተር ክክ ብዛት 1800 ኪ.ግ፣ሩዝ ብዛት 3250 ኪ.ግ፣የጤፍ ዱቄት ብዛት ኪ.ግ 1200 እና የመሳሰሉት፣(ይህም ዩኒቨርሲቲውን መሃል ለመሃል ወንዝ አቋርጦ ከማለፉ አንጻር የምግብ ቤቱና የምግብ ዕቃዎች ስቶር አሰራር ግንዛቤ ያልተወሰደበትና የዩኒቨርሲቲው ግንባታ ከማከናወኑ በፊት የስጋት ጥናት / Risk Assesment / ያለማከናወኑን ያሳያል)
- በርካታ ወንበሮች ቁጥራቸውን ለማወቅ የማይቻል አገልግሎት መስጠት የሚችሉና የማይችሉ ተደባልቀው በተማሪዎች ምግብ ቤት አካባቢ በሚገኝ ንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣

- 2 የእህል ሚዛን፣19 ባለ 100 ሊትር የውሀ ፕላስቲክ በርሜል፣13 ባለ 20 ሊትር የውሀ ፕላስቲክ በርሜል፣8 ሎከሮች እና በርካታ እንጀራ መጋገሪያ ምጣዶች አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- በተማሪዎች መመገቢያ አካባቢ በሚገኘው የምግብ ግምጃ ቤት ውስጥ 10 ፓኬት ብዛት 10*20 = 200.00 ቼራሊያ ፓስታ፣1 ኩንታል አተር ክክ፣ ሶስት ባለ 100 ኩንታል ምስር ክክ፣ አንድ ኩንታል ጎመን ዘር፣ አንድ ኩንታል መኮረኒ እና 4 ኩንታል ሩዝ ለምግብ አገልግሎት መዋል የማይችሉ የምግብ እህሎች የሚገኙ መሆኑ፤
- በተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ ውስጥ በርካታ ትልልቅ ማሽኖች የሚገኙ ቢሆንም አይነታቸውን፣ንብረቶቹ የዩኒቨርሲቲው ለመሆኑ ማረጋገጫ፣በማን ቁጥጥር ስር እንደሆኑ የሚገልፅ ማስረጃ ሊቀርብ ያልተቻለ መሆኑና አንድ የዳቦ ማቡኪያ ትልቅ mixer 100 OMG ያለጥንቃቄ በመቀመጡ ለብልሽት የተጋለጠ መሆኑ፣
- በሚዛን እና በቴፒ ካምፓስ በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በርካታ ንብረቶች ለቁጥጥር አመቺ ባልሆነ ሁኔታ ተደባልቀውና ተበታትነው የተገኙ መሆኑ፣
- በርካታ የሠራተኛ ነጭ ጋወን በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም መሬት ላይ በመቀመጡ ለብልሽት የተጋለጠ መሆኑ፣
- በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ Bentonite powder, Nitric Acid, Acetone ch3coch3, DL-CAMPHOR ብዛት ያላቸው የተለያዩ ኬሚካሎች ከአመት በላይ ከአላቂ ዕቃ ጋር ተደባልቀው የሚገኙ መሆኑና ኬሚካሎቹ በባለሙያ ታይተው በፍሪጅ መቀመጥ የሚገባቸው ኬሚካሎች ተለይተው መቀመጥ ሲገባቸው ያልተቀመጡ መሆናቸው፣ኬሚካሎቹ ለጤና አስጊ በመሆናቸው ሽታ ያመጡ መሆኑና የሚመለከተው ዲፓርትመንት ወጪ አድርጎ የማይጠቀማቸው መሆኑ፣
- በሚዛን ካምፓስ የቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አሰር ከምፒውተር ብዛት 98፣ኤች ፒ ሌዘር ጄት ፕርንተር ብዛት 6 ኦኪ ፕሪንተር ብዛት 19፣ዴል ኮምፒውተር ብዛት 7 እና የመሳሰሉት የተበላሹ ንብረቶች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት ሲችሉ በግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣

- በቴፒ-ካምፓስ ቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በጣም በርካታ የሆኑ የተለያዩ በዝናብ ምክንያት የተበላሹ የባዮሎጂ እና የኬሚስትሪ ዕቃዎች መኖራቸውን ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣
- በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የመጡ 7 የማተሚያ ማሽኖች ከ2 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት በሚዛን ካምፓስ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተቀምጠው የተገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

➢ <u>አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ</u>

- የመድሃኒት ገቢና ወጪ የሚመዘገብበት ካርድ ምዝገባው ባለመጠናቀቁ ወቅታዊ ከወጪ ቀሪ የማያሳይ መሆኑ፣
- በንብረት ክፍል ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ እና ውጭ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች የሚገኙ ሲሆን የሚሸጡ፣የሚተላለፍ ወይም የሚወገዱ ተለይተው እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፣
- በተመለሡ ዕቃዎች ስቶር ውስጥ ያሉ የተለያዩ ዕቃዋች አቀማመጣቸዉ ሲታይ የተበላሹትንና ያልተበላሹትን ለይቶ ለማወቅ በሚያስቸግር ሁኔታ እንደተቀመጡና አያያዛቸውም ጥንቃቄ በጎደለው መሆኑ ታውቋል፡፡

➢ <u>መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ</u>

- በቋሚና አላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ሲሰሩ የነበሩት ንብረት በኃላፊነት የሚጠብቁ ሰራተኞች በአዲስ ሰራተኛ ሲተኩ በቆጠራ ርክክብ የተፈጸመ ሲሆን በርክክቡ ወቅት የነበሩት ንብረቶች ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲት አልተረጋገጠም፡፡
- ተመላሽ የተደረጉ ዕቃዎች ወደ ንብረት መጋዘን በሚገቡበት ጊዜ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው አንዳንድ ዕቃዎች መኖራቸውና ስላሉበት ሁኔታ የሚገልጽ ዝርዝር መግለጫ የሌላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡
- በመለዋወጫ ንብረት መጋዘን አካባቢ የተለያዩ ብረታ ብረቶች እና የወላለቁ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች… ወዘተ ተከማችተው መገኘታቸውና ለንብረቶቹ ተገቢው የቁጥጥር ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በብልሽት ምክንያት ተመላሽ የተደረጉ ኮምፒዩተሮች መከማቸታቸውን፣ ለጽዳት አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች ከአላቂ ዕቃዎች ጋር መከማቸታቸው፣ ከ2 ዓመት በላይ የሆናቸው የተለያዩ የፕሪንተር ቀለሞች ያለአገልግሎት መገኘታቸው፣ አሮጌ የመኪና ዕቃ መለዋወጫዎች፣ ብረታ ብረቶች መከማቸታቸው እና የግንባታ ቋሚ ዕቃዎች የተለየ መዝገብ አለመቋቋሙ ታውቋል፡፡

- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ መጽሐፍ ኮፒ አድርጎ የሚጠርዝ ማሽን አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣ ከ2 ዓመት በላይ የሆናቸው ከትምህርት ሚኒስቴር የመጡ በእንጨት የታሸጉ የወጥ ቤት ዕቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ዩኒቨርሲቲው ያለተረከባቸውና አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆኑ፣ የጤፍ ወፍጮ ተገዝቶ አገልግሎት ላይ ያልዋለ መሆኑ እና ለምግብ ዝግጅት የምግብ ጥሬ ዕቃ የሚወጣው በግምት መሆኑ ታውቋል፡፡
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የመድሃኒቶች ምዝገባ ባለመደረጉ ቆጠራውን ከመዝገብ ጋር ለማስታረቅ አለመቻሉ፣ ጊዜአቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች በመድሃኒት ንብረት ክፍል መገኘታቸውና በሌሎች የንብረት ክፍሎች ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ዕቃዎች መኖራቸው ታውቋል፡፡

➢ <u>ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ</u>

- ከኮድ ኢትዮጵያና ከሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች በዕርዳታ የተገኙ መጻህፍቶች ዓይነትና ብዛት በዝርዝር የሚገልጽ ማስረጃ ካለመኖሩ በተጨማሪ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው መሆኑ፤
- በምግብ ዕቃ ግምጃ ቤት ገቢና ወጪ የሚደረጉ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ

➢ <u>ዲላ ዩኒቨርቲ</u>

- በአገልግሎት ላይ ያልዋሉ ብዛት ያላቸው ቋሚ ንብረቶች / አልጋዎች፤የውኃ ማጠራቀሚያ ታንከሮች /Roto/ በዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ በጸሐይና በዝናብ ለብልሽት የተዳረጉ መሆኑ፤
- ዓይነታቸውና ብዛታቸው ተለይቶ የማይታወቅ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው በርካታ መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ መሆኑን፤

➢ <u>ሠመራ ዩኒቨርስቲ</u>

- ተቋሙ የንብረት ማከማቻ መጋዘን ሌለው በመሆኑ ንብረቶች በመማሪያና በላብራቶሪ ክፍሎች የሚገኙ መሆኑ፤
- በግዥ የሚገኙት የምግብ ግባቶችና ሌሎች አላቂና ቋሚ ዕቃዎች መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ /Stock Card/ የሌለ መሆኑ፤

➢ <u>በግብርና ሚኒስቴር</u>

- በእቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ እቃዎች አገልግሎት ከማይሰጡ እቃዎች ጋር ተቀላቅለው የተከማቹ ከመሆኑም

በላይ የማያገለግሉ ንብረቶች ቦታ በመያዛቸው አዲስ የገቡ ንብረቶችን ለብልሽት በሚያጋልጥ መልኩ መሬት ላይ የተከማቹ መሆኑ፤

- የንብረት መጋዘኖች እጅግ ቆሽሸውና እና እቃዎችም በአቧራ ተሸፍነው የሚታዩ መሆኑ፤
- የንብረት መጋዘኖች የእሳት አደጋ መከላከያ የሌላቸው መሆኑ፤
- የአገልግሎት ግዜ ያለፈባቸው የላብራቶሪ ኬሚካሎች፤ በርካታ ሲሚንቶዎች ፤ሰብሎች፤ እጅግ ብዛት ባላቸው ኮንቴነሮች የታሸገ የመሬት ማዳበሪያ እና ሌሎች ቋሚና አላቂ እቃዎች እርምጃ ሳይወሰድባቸው ለረጅም ጊዜ በመጋዘን ውስጥ እና ከመጋዘን ውጭ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- በግምጃ ቤት ገቢ የተደረጉ እና በተለይም በ1996 ዓ.ም የተለያየዩ መሥሪያ ቤቶች ሲዋሃዱ ተመላሽ የተደረጉ ንብረቶች በአይነትና አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡት ሳይለዩ ለቁጥጥር በሚያስቸግር ሁኔታ ለረጅም ዓመታት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ ፤

አገልግሎት በማይሰጡ ንብረቶች ላይ በ2003 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት አሰፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ ታውቋል።

- **<u>በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>**
  - ኮሌጁ ስታክ ካርድ ጥቅም ላይ ባለማዋሉ ምክንያት እያንዳንዱ ስታክ የእህል መጠን እና እንቅስቃሴ የማይታወቅ መሆኑ፤
  - በማከማቻ መጋዘኑ የሚገኙ እቃዎች በአይነታቸው ተለይተው የመለያ ኮድ ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
  - ጥቅም ላይ ቢውሉ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የተለያዩ እቃዎች (ዳቦ መጋገሪያ ፣ የዘር መዝሪያ ማሽን ፣ የጸረ አረም መርጫ ማሽን፣ ኮምፐርሰር፣ የማስተማሪያ የእርሻ መሳሪያዎች እና የመሳሰሉት) ያለአገልግሎት ለረጅም ጊዜ የተቀመጡ በመሆኑ ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፤
  - በበጀት አመቱ መጨረሻ በተከናወነው የንብረት ቆጠራ በማነስ የታዩ የተለያዩ እቃዎች ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያልተደረጉና አስፈላጊው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

- በመጋዘኖች ውስጥ የተበላሹና የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው እቃዎች ከደህናው ዕቃ ተለይተው ያልተቀመጡና በወቅቱም ያልተወገዱ መሆኑ፤
- በቋሚና አላቂ እቃ መጋዘኖች ውስጥ እቃዎች እጅግ በተዘበራረቀና በተዝረከረከ መልኩ የተከማቹ መሆኑ፤
- የእቃ ማከማቻ መጋዘኖቹ የእሳት አደጋ መከላከያ የሌላቸው መሆኑ፤
- በቋሚና አላቂ እቃ ማከማቻ መጋዘኖች እቃዎች በአግባቡና በሥርዓቱ ካለመደርደራቸው ወይም ከመዝረክረካቸው የተነሳ በቂ መተላለፊያ መንገድ የሌላቸው በመሆኑ ምክንያት መጋዘኖቹ ንጽህናቸውን የጠበቁ አለመሆናቸው፤
- በአሳሳ የሚገኘው የእቃ ማከማቻ መጋዘን እቃ ከመጋዘን የሚወጣው በሚመለከተው አካል በጸደቀ የእቃ መጠየቂያ አለመሆኑ፤
- አሳሳ በሚገኘው የእህል ማከማቻ መጋዘን እህሉን የያዙ ማዳበሪያዎች በመቀደዳቸው እህሉ በመጋዘኑ ሜዳ ላይ በብዛት ፈሶ የሚታይና ሰው የሚረማመድባቸው መሆኑ፤
- የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው (771 ሊትር ቱ4ዲ የጸረ ቅጠል ሰፋፊ ኬሚካልና 2 ሊትር ሰልፈሪክ አሲድ) በአንድ ክፍል ውስጥ ለረጅም ጊዜ ታሽገውና በመጋዘኖች ውስጥ ከደህናው እቃ ጋር ተቀላቅለው የሚገኙ መሆኑ፤
- በንብረት አስተዳደሩ ላይ በታዩት በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች ላይ ቀደም ሲል በ2003 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድባቸው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑ፤

➢ <u>**በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ**</u>

- የንብረት መጋዘን ኃላፊዋ እቃዎችን የምትረከበው እቃውን ለመረከብ የሚያስችል ከሚመለከተው ሥራ ክፍል በተሰጠ ትእዛዝና ስፔስፊኬሽን መሰረት ያለመሆኑ ፣
- በመጋዘኖች ውስጥ የተበላሹና የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው እቃዎችና ኬሚካሎች (ጸረ አረም፤ ጸረ ተባይና የአፈር ኬሚካል) ከደህናው እቃ ተለይተው ያልተከማቹና እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑ፣

- በቋሚና አላቂ እቃ እንዲሁም በተመላሽ እቃ ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ አቃዎች እጅግ በተዘበራረቀና በተዝረከረከ ሁኔታ በመከማቸታቸውና በአግባቡና በሥርዓቱ ባለመደርደራቸው ምክንያት፡
    - በቂ መተላለፊያ መንገድ የሌላቸው መሆኑ ፣
    - አንዳንድ እቃዎች ያለአግባብ ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣
    - መጋዘኖቹ ንጽህናቸውንያልተጠበቀና ከጸዱም ረጅም ጊዜ የሆናቸው መሆኑ፣
- የእቃ ማከማቻ መጋዘኖቹ የእሳት አደጋ መከላከያ የሌላቸው መሆኑ፣
- ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ እቃዎች እርምጃ እንዲወስድባቸው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፣
- የኮሌጁ የዳቦ መጋገሪያ በሰው ኃይል እጥረት በሚል ምክንያት ለረጅም ጊዜ አገልግሎት መስጠት በማቆሙ የተነሳ ለብልሽት እየተዳረገ መሆኑ፣

> **<u>በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጁ</u>**

- በማከማቻ መጋዘኑ የሚገኙ እቃዎች በአይነታቸው ተለይተው የመለያ ኮድ ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- በ2004 በጀት አመት የንብረት ቆጠራ የተከናወነ ቢሆንም እስቶክ ካርድ ባለመቋቋሙ ምክንያት የቆጠራውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ
- እቃ የመረከብና መጨ የማድረግ እንዲሁም የመመዝገብ ሥራ በአንድ ሰው የሚከናወን መሆኑ፤
- በመጋዘኖች ውስጥ የተበላሹና የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው እቃዎችና ኬሚካሎች (ማላታይን፤ቦሪክ ሲድ ፓውደር፤ፋርማሊን እና ካርብሪል መድሃኒት) ከደህናው እቃ ተለይተው ያልተከማቹና እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑ፤
- ከአንድ አመት በፊት ወደ ኮሌጁ የገቡት የጠብታ መስኖ እቃዎች ያለምንም አገልግሎት በኮሌጁ ቅጥር ግቢ ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- በአላቂና በቋሚ እቃ ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ አቃዎች እጅግ በተዘበራረቀና በተዝረከረከ መልኩ ከመከማቸታቸውም በላይ አንዳንድ እቃዎች ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፤

- የእቃ ማከማቻ መጋዘኑ የእሳት አደጋ መከላከያ የሌለው መሆኑ፤
- በኮሌጁ የሚገኙ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ እቃዎች እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፤

➢ <u>በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ</u>

- የኮሌጅ የመድኃኒት ክፍል ተረኞች በሚቀያየሩበት ወቅት የመድኃኒት ርክክብ ሳይደረግ ተረኛው ባለሙያ ወደ ሥራ የሚሰማራ መሆኑ፣
- የግል ህክምና አገልግሎት ክፍሉ ከመደበኛ በጀት የሚጠቀመው የአላቂ ህክምና መገልገያ ዕቃዎች በወቅቱ ተመላሽ ባለመደረጋቸው ምክንያት በመደበኛው ሥራው ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽህኖ እያሳደረ መሆኑ፣
- የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸዉ መድሃኒቶች እና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የህክምና እቃዎች ላይ የማስወገድ እርምጃ ሳይወሰድ በንብረት ክፍል ተከማችተዉ የሚገኙ መሆኑ፤•
- ከጥር ወር 2004 ዓ.ም በፊት ያሉት በተለያዩ ምክንያት ተበላሽተዉ በኮሌጁ ጥገና ክፍል ጥገና ተደርጎላቸው የተቀየሩ አሮጌ ንብረቶች ወደ መጋዘን ያልተመለሱ መሆኑ፤
- በተለያዩ አሮጌ ንብረቶች ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወሰድባቸው በንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን፤ በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ደግሞ መወገድ የሚገባቸው የተለያዩ የተንቃቀሉ የቢሮ ዕቃዎች፣ ጣውላዎችና የመሳሰሉት ንብረቶች ያልተወገዱ ከመሆኑም በተጨማሪ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶች አገልግሎት መስጠት ከሚችሉ አላቂ ንብረቶች ጋር ተደባልቀው የሚገኙ መሆኑ

➢ <u>በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ</u>

- በዋና የመስክ ዕቃ ግምጃ ቤት የሚያገለግሉ እና የማያገለግሉ ዕቃዎች ባንድ ላይ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

➢ <u>መካኒሳ በሚገኘው የዕቃ መጋዘን</u>

- ግምጃ ቤቱ በአለቁ የኬሚካል ጠርሙሶች እና በመሳሰሉት እስከ ውጭ ድረስ ተሞልቶ የሚገኝ ሲሆን ባስቸኳይ ካልተወገደ በአካባቢውና በጤና ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ የሚገኙ ፈሳሽ ኬሚካሎች ብዙ ጊዜ ከመቆየታቸው የተነሳ

እየተነኑ እንደሚገኙ እና አንዳንድ የኬሚካል ጠርሙሶችም ደግሞ በመሰበራቸው ምክንያት ኬሚካሉ እየፈሰሰ አካባቢው ለብክለት እየተጋለጠ መሆኑ፤

- አገልግሎት የማይሰጡና ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የድሪሊንግ ቁጥር አንድ ግምጃ ቤት በቆርቆሮ የተሰራና አጥሩም አስተማማኝ ባለመሆኑ ለደኅንነት እና ለጥበቃ ምቹ አይደለም። ነገር ግን በግምጃ ቤቱ ውስጥ በጣም ውድ የሆኑ የድሪሊንግና የመሳሰሉት መለዋወጫ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

➢ **<u>የፌዴ.ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር</u>**

- በከፍተኛ ፍርድ ቤት አካባቢ በሚገኘው በአስተዳደሩ የድሮ ዳቦ ቤት መጋዘን ውስጥ ብዛት ያላቸው ኮምፒዩተሮች፤ ፕሪንተሮች፤ የሂሳብ መደመሪያ ማሽኖች፤ የስልክ ቀፎዎች፤ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፤ የበርና የመስኮት መዝጊያዎች እና የመሳሰሉት ለረጅም ዓመታት ከጥቅም ውጪ ሆነው ተከማችተው ተገኝተዋል።

በመሆኑም በየመ/ቤቶቹ አንፃር የተዘረዘሩት ከፍተኛ የንብረት አያያዝ ችግሮች ንብረቶቹ ከዚህ የባሰ ሳይበላሹና አንዳንዶቹም በሰው፣ በእንስሳትና በአካባቢው ላይ የከፋ ጉዳት ሳያስከትሉ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በአጠቃላይ የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው መመሪያ መሠረት እንዲከናወነ አሳስበናል፡፡

7.3 <u>ተሽከርካሪ</u>

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል::

ዝርዝር	መ/ቤቶች	ተሽከርካሪዎች
ሊብሬ ያልቀረበላቸው	14	375
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	17	287
በተለያዩ ድርጅቶች ሥም ሊቢሬ ያላቸው ወደ መ/ቤቱ ስም ያልተቀየረላቸው	4	15

መኖራቸው ታውቋል:: /ዝርዝሩም በአባሪ -34 ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ/እንዲወገዱ፤ሊብሬ ያሌላቸው እንዲወጣለቸውና ሊብሬያቸው በሌላ መ/ቤት ስም የተገኙት ወደ ባለይዞታው መ/ቤት እንዲዞሩ እንዲደረግ ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

7.3.1 <u>የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም በተመለከተ</u>

- የበጀት ዓመቱን የነዳጅ አጠባበቅና አያያዝ ኦዲት ለማድረግ ተሞክሮ የብሄራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት ሰነዶች ሊቀርብ ባለመቻሉ ኦዲት ለማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡
- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-12464 በቀን 30/10/04 ብቻ 326 ሊትር ነዳጅ የቀዳ መሆኑ፣
- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጃቸው የሚሠሩ የዩኒቨርሲቲው መኪናዎች ወጥነት ባለው አሰራር የተጓዙበት ርቀት /ኪሎ ሜትር/ እየተሰላ እና እየተቀናነሰ በአግባቡ ነዳጅ መስጠት እንዲያስችል አንድ መኪና በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር መሄድ እንሚችል የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

➢ <u>በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

- እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ከተገዛበት ጊዜ ጀምሮ የነዳጅ እና ቅባት ፍጆታ እንዲሁም የመለዋወጫ እና የጥገና ወጪን በግልጽ የሚያሳይ የግል ማህደር የሌላቸው መሆኑ ፣
- ተሽከርካሪዎች በሚጓዙበት ርቀት (ኪሜ) ተሰልቶ ነዳጅ የማይሞላ መሆኑ፣

➢ <u>በግዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

- ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ መኪና የነዳጅ እና ቅባት ፍጆታ እንዲሁም የመለዋወጫ እና የጥገና ወጪ በግልጽ የሚያሳይ የግል ማህደር ያልተቋቋመ መሆኑ፤

- ተሽከርካሪ መኪናዎቹ በሰአት ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚሄዱ በተቀመጠው የምርመራ ስታንዳርድ መሰረት በሚጓዙበት ርቀት (ኪ.ሜ) ልክ ተሰልቶ ነዳጅ የማይሞላ መሆኑ፤

➢ **<u>በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>**

ለተሽከርካሪዎችበብዛት ነዳጅ ተገዝቶ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦ ገቢ ከተደረገ በኋላ የተጠቃሚዎች የነዳጅ ጥያቄ ሳይኖር ወዲያው ወጪ የሚደረግ ከመሆኑም በላይ ወጪ ከተደረገ በኋላ በየጊዜው ለተጠቃሚዎች ያለምንም ህጋዊ ማስረጃ የሚታደል መሆኑ፤

➢ **<u>የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም</u>**

- የተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም በተመለከተ የሰሌዳ ቁጥር 4-12187 ሱዙኪ ቪታራ ተሽከርካሪ የኪሎሜትር ንባብ የማይሰራ በመሆኑ የተሽከርካሪውን የነዳጅ ፍጆታ መጠን ለመቆጣጠር የሚቻልበት አሰራር አለመኖሩ ፤
- በሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያሉት ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ለተቋሙ አገልግሎት መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ተሽከርካሪዎቹ ለሥራ በሚሰማሩበት ወቅት የተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያ እና መዘዋወሪያ ቅፅ የማይዘጋጅ መሆኑ፤

  ታውቋል፡፡

የተሽከርካሪው የኪሎ ሜትር የንባብ መሣሪያ የማይሰራ በመሆኑ የፈጀው /የተጠቀሙትን/ የነዳጅ መጠን እና ኪሎ ሜትር ማረጋገጥ የሚቻልበት አሰራር አለመኖሩ፤ የተቋም የነዳጅ አጠቃቀምን ትክለኛነት ማረጋገጥ እንዲቻል የመንግሥት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያ ቅጅ መጠቀምና የነዳጅ ፍጆታ መቆጣጠር የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

8. ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:–በ24 መ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ ሲሆን /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ-35 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦች በየመ/ቤቶቹና በየዘርፉ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ክፍል ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል፡፡

9. ልዩ ልዩ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 208/2000 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ሥልጣንና ሃላፊነት መሰረት የሚተላለፉለትን የልማት ድርጅቶች ተሰብሳቢ ሂሳቦችና ዕዳዎችን የሚመለከቱ ሰነዶችን በመረከብ ወደግል ይዞታ በሚዛወሩበት ወይም ወደ አክስዮን ማህበር ወይም ለቀድሞ ባለቤቱ በሚተላለፉበት ወቅት ወደ አዲሱ ባለቤት የማይተላለፉ የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን በመያዝ እንደሚያስተዳድርና ትክክለኛ የሂሳብ ሰነዶችንና መዛግብትን በመያዝ ኦዲት ማስደረግ እንዳለበት ያዛል ፡፡ ሆኖም ቦርዱ በዚሁ መሰረት ተፈፃሚ የሚያደርግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ባለአደራ ቦርዱ የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት /consolidations financial statement/ የማያዘጋጅ በመሆኑ የድርጅቶችን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በመሆኑም የቦርዱን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳብ ትክክለኛ ገጽታ ለማሳወቅ አያስችልም፡፡ እንዲሁም ከ1997 ጀምሮ ስራው በትክክል እንዲሰራ የኦዲት አሰተያየት የተሰጠ ቢሆንም በቦርዱ የሚሰጠው ምላሽ ተመሳሳይነት ያለውና እልባት ያላገኘ ጉዳይ መሆኑ አሳሳቢነቱን የጎላ ያደርገዋል፡፡ ስለ መ/ቤቱ የሚመለከታቸው ሃላፊዎች በተደጋጋሚ የሚነሱትን የሰው ሃይልና ሌሎች ችግሮች ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ሥራው የሚከናወንበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል፡፡

ወለጋ ዩኒቨርሲቲ

- ልዩ ልዩ ሕንጻዎች ግንባታ ወጪ ሆኖ የተመዘገበው ሂሳብ ትክክል መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ለአንድ ኮንስትራክሽን ድርጅት ከተፈጸመው ክፍያ ሂሳብ ላይ የተቀነሰው መያዣ (Retention) ብር 173,993.71 መያዣ (Retention) በተከፋይ ሂሳብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

- በ2003 እና በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ ያልተሰራባቸው የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በሴሪና በቁጥር (ከ-እስከ-ከ) ተለይቶ ቆጠራ ባለመደረጉ በ2004 በጀት ዓመት የውስጥ ገቢ ሂሳብ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ምን ያህል እንደሆኑ ለማወቅ ባለመቻሉ የውስጥ ገቢ ተሰብስቦበት ደረሰኝ ሳይመለስ ሊቀር እና ገንዘቡ ለግል ጥቅም ሊውል ስለሚችል የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በሴሪና በቁጥራቸው እየተቆጠሩ ሁሉም ደረሰኞች መኖራቸው እና በደረሰኞቹ ተሰብስበው ሁሉም ገንዘብ ገቢ መሆኑ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

- ዩኒቨርሲቲው ከመቋቋሙ በፊት ሀጂ ናስር ደረቅ ቡና መቀሽሪያ የሚሰራበትን ቦታ ለዩኒቨርሲቲው አስረክቦ ሲለቅ ድርጅቱ ሲጠቀምበት በነበረው ቦታ ላይ የቡና ገለባ በመኖሩ ገለባው በዝናብ ምክንያት እየታጠበ ወደ ሾንጋ ወንዝ የሚገባ በመሆኑ ወንዙን የሚበክልበት ሁኔታ እና መጥፎ ጠረን የፈጠረ መሆኑ፣

- በሚዛን ካምፓስ ከተማሪዎች ካፍቴሪያ የሚወጣ ተረፈ ምግብ፣የሽንኩርት ልጣጭ፣የድንች ልጣጭ፣አመድ፣ አጥንት እና የመሳሰሉት በመመገቢያ አዳራሽ አቅራቢያ እና በሾንጋ ወንዝ አካባቢ በአግባቡ ባልተሰራ የቆሻሻ ማስወገጃ እየተደፋ በመሆኑ በአካባቢው ላይ መጥፎ ጠረን እና ወደ ወንዙ የሚገባበት ሁነታ በመኖሩ ወንዙ የሚበክልበት ሁኔታና ለጤና አስጊ ደረጃ ላይ ቢደርስም የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ልብሳቸውንና ገላቸውን እንደሚታጠቡበት ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

- በቴፒ ካምፓስ ጊዜአዊ ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውል በቆርቆሮ የተሰራ መጸዳጃ ቤት እና ገላ መታጠቢያ አብሮ የተሰራ ሲሆን መጸዳጃው ተማሪዎች ማደሪያ ክፍል/ዶርም/ አካባቢ የሚገኝ በመሆኑ እና መጸዳጃውና ገላ መታጠቢያ አብሮ በመሰራቱ መጸዳጃ ቤቱ ቶሎቶሎ በመሙላቱ አካባቢው

ላይ መጥፎ ጠረን መፍጠሩና ገላን ለመታጠብ እንደማይቻል በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማየት የተቻለ መሆኑ፣

- ዩኒቨርሲቲው ባጠናው BPR ጥናት መሠረት ሠራተኛ እንደ አዲስ ሲደለደል የሰው ኃብት ልማት አስተዳደር እና የበጀት፣ ፋይናንስ፣ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ኃላፊ ያልተመደበላቸው ሲሆን በቦታው የነበሩ የቀድሞ ኃላፊዎች ያለውክልና እየሰሩ ሲሆን በተለይ የበጀት፣ ፋይናንስ፣ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ባልተመደቡበትና የዩኒቨርሲቲው ውክልና በሌለበት ሁኔታ በቦታው እየሰሩ እና እስከ ብር 50,000.00 ወጪ የሚያጸድቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ሠመራ ዩኒቨርስቲ፡-</u>

- ለኦዲት ሥራ ተፈላጊ የሆኑ ዶክመንቶች ሰነዶችና ልዩ ልዩ መረጃዎች ለኦዲት ሊቀረቡ ባለመቻሉ በ2004 በጀት ዓመት ለኮንስትራክሽንና ለመሠረተ ልማት ግንባታ ማስፈጸሚያ የተመደበው ብር 14,000,000.00 ካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን እንዲሁም የግንባታው ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ተጠናቅቆ የሚፈለገውን አገልግሎት መስጠቱን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- የአስተዳደርና የመምህራን ቢሮዎች፣ ወርክሾፕና ላይብረሪ ግንባታ፣ ከፕሮጀክቱ ጠቅላላ ዋጋ ብር 28,332,773.92 ላይ ብር 20,143,721.71 ለተቋራጩ የተከፈለ ሲሆን በውል የተመለከተው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና የማስረከቢያ ቀን ማርች 29/2010 ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ 1657 ቀናት ወይም ከ 4 ዓመት በላይ የዘገየ ከመሆኑ በተጨማሪ የፕሮጀክቱ ሥራ ሙሉ በሙሉ መቋረጡንና አብይ ኃይሉ የተባሉት የፕሮጀክቱ ሥራ ተቋራጭ የግንባታውን ሥራ በማቋረጥ ጥለው መሄዳቸው እንዲሁም ውል ተቀባይ አብይ ኃይሉ የህንጻ ተቋራጭ በብድር የወሰዱት የሲሚንቶ ዋጋ ብር 642,044.88 ተመላሽ አለመደረጉ የተረጋገጠ ቢሆንም የህንጻ ተቋራጩ በገቡት ውል መሠረት ባለመፈጸማቸው በተቋሙ ላይ ለደረሰው ጉዳትና ኪሳራ G.I.Z.በተባለው ድርጅት እና M.H.ተብሎ በሚጠራው የፕሮጀክቱ ተቆጣጣሪና አማካሪ መሃንዲስ ወይም በተቋሙ ማኔጅመንት ምንም ዓይነት እርምጃ አለመወሰዱ ተረጋግጧል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
የ2004 በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫ ኦዲት
የስራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 መሰረት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብ በተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዋና መ/ቤት ፣ የስምንት ቅ/ጽ/ቤቶችንና የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

የሪፖርቱ አላማ

የዚህ ሪፖርት አላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት የባለስልጣን መ/ቤቱ ባዘጋጃቸው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

በዚህም መሰረት የባለስልጣን መስሪያ ቤቱን፣ 8 ቅ/ጽ/ቤቶችን (ማለትም የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች፣ የምስራቅ አዲስ አበባ፣ የአዲስ አበባ ኤርፖርት፣ የድሬዳዋ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ፣ እና የአዲስ አበባ ወጪና ሌሎች እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤትን) እንዲሁም የተጠቃለለ የ2004 በጀት አመት የሂሳብ እንቅስቃሴ ኦዲት ተደርጓል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፡-

- በዋናው መ/ቤት በተጠቃለሉ የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን መመርመርን፣

- የሥራ አመራሩ ሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋና መ/ቤት የሂሣብ ሪፖርት ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ ሪፖርቶቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

በዋናው መ/ቤት የተጠቃለሉ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ በሚሰጥና መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋና መ/ቤት ሥራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት ማድረግና በባለስልጣን መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫዎች ላይ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

በኦዲቱም መሰረት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ቀጥለው ቀርበዋል::

የኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋና መ/ቤት የ2004 በጀት ዓመት የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የጉምሩክ ገቢ ሂሳብ

1.1 በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.code) እና የጉምሩክ ስነስርአት ኮድ (cpc-code) እቃዎች ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 751,987.18 መገኘቱ

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2009 አንቀጽ 45(1) መሰረት ዕቃዎች፡-

I. በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.Code) ባለመመደባቸው ምክንያት

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 153,208.29
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 102,334.11
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 26,676.11
- በአ. አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ብር 323,234.91

II. በትክክለኛው CPC Code ባለመመደባቸው ምክንያት እቃዎች ያለአግባብ ሁለተኛ መደብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመደረጉ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በዲክላራሲዎን ቁጥር C-3131/12 ከገባው እቃ ብር 146,533.76 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ተገኝቷል፡፡

ከአራቱም ቅ/ጽ/ቤ/ቶች በድምሩ ብር 751,987.18 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

እቃዎች በሀርሞናይዝድ ሲስተም ታሪፍ አተረጓጎም አጠቃላይ ደንቦች መሰረት የተመደቡ ለመሆኑና የፍተሻ ውጤቱ በታሪፍ ላይ የሚያመጣው ለውጥ በአግባቡ በሚመለከታቸው ሰራተኞች ተገቢው ትኩረት እየተሰጠው ካልተመረመረ መንግስት ከገቢ እቃዎች ማግኘት ያለበትን ገቢ እንዲያጣ ያደርገዋል::

ማሻሻያ እርምጃ

ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር ባለመመደባቸው ምክንያት ያልተሰበሰበው ሂሣብ ብር ብር 751, 987.18 ከሚመለከታቸው ድርጅቶች እንዲሰበሰብ እንዲሁም እያንዳንዱ እቃ በሀርሞናይዝድ ሲስተም ታሪፍ አተረጓጎም አጠቃላይ ደንቦች መሰረት የተመደቡ ለመሆኑና የፍተሻ ውጤቱም በእቃዎች ታሪፍ አመዳደብ ላይ ልዩነት የሚያመጣ ለመሆኑ የሚመለከታቸው ሰራተኞች ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው ስራቸውን እንዲሰሩ ለየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የስራ አመራሮች አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

በ12/06/05 በተደረገው የኦዲት መውጫ ውይይትና በ18/06/2005 በቁጥር 10/465/16 ከባለስልጣኑ መ/ቤት በተጻፈው ደብዳቤ መሰረት

- የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ቀሪ ሂሳቡ እንዲሰበሰብ ለአስመጪዎቹ መጠይቅ የተላከ መሆኑን፣
- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ከተገኘው ቀሪ ሂሳብ ውስጥ ለብር 25869.54 ማስታወቂያ የተላከ መሆኑና ክፍያ ባለመፈጸሙ አገልግሎት እንዳያገኝ መደረጉን ገልጸ የብር 806.57 ደግሞ እየተጣራ ነው በማለት ምላሽ

  ሰጥተዋል ፡፡

- የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ወደ አገር የገባው እቃ used Toyota Hiace ሚኒባስ (Mini bus) መኪና መሆኑን በመግለጽ ሚኒባስ ደግሞ የመጫን አቅሙ 15 ሰው በመሆኑ እና ከመንገድ ትራንስፖርት ሁሉም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ መኪኖችን አንድ ወጥ በሆነ ሁኔታ ለማስተናድ በተሰጠው ልኬት ርዝመት 2.8 ሜትርና ከዚያ በላይ የሆነውን በታሪፍ ቁጥር አንቀጽ 8702 እንዲስተናገዱ ተወስኗል፡፡ በዚህ መሰረት የቅ/ጽ/ቤቱ ማኔጅመንት ውይይት አድርጎ በቁጥር አንዐ10/ወ10/38 በቀን 30/12/2003 በተፃፈው ደብዳቤ በወሰነው መሰረት መስተናገዱ ትክክል መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ተጨማሪ ማጣራት እየተደረገ መሆኑን በተላከው ደብዳቤ ገልጸዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

ከአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የተሰጠውን ምክንያት በተመለከተ ከዋጋና ታሪፍ ምደባ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት በቁጥር 3.1.0/81/3 ቀን 19/12/2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ወንበር ሳይገጠምላቸው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ሚኒባስ (Mini bus) ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ በከፊል ወንበር ተገጥሞላቸውም ሆነ ምንም ወንበር ሳይገጠምላቸው የሚመጡ ተሽከርካሪዎች ወንበራቸው የፋብሪካ ቢሆንም ባይሆንም ከመንገድ ትራንስፖርት በተሰጠው ልኬት መሰረት ጋቢናውን ሳይጨምር ውስጥ ለውስጥ ርዝመት 2.8 ሜትርና ከዚያ በላይ የሆኑትን በታሪፍ ቁጥር አንቀጽ 8702 እንዲስተናገዱ ተወስኗል፡፡ ነገር ግን ጽህፈት

ቤቱ በቁጥር አንዕ10/ወ10/38 በቀን 30/12/2003 የተፃፈው ደብዳቤ በተራ ቁጥር 1 ላይ "የፋብሪካ ወንበር ተገጥሞላቸው የሚመጡ ተሽከርካሪዎች እንደሚጭኑት የሰው ብዛት በታሪፍ መጽሐፍ መሰረት በአንቀጽ 87.02 ወይም 87.03 ከመንገድ ትራንስፖርት የተላከውን ርዝመት ልኬት ሳይወስድ እንዲስተናገዱ" የሚል ሲሆን በፈታሹ የወንበር ብዛት ተረጋግጦ እያለና የፍተሻ ውጤቱም በከፊል የማይል በመሆኑ በፍተሻ ውጤት አለመስተናገዱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ዋናው መ/ቤት በጉዳዩ ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

1.2 የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው እቃዎችና ሌሎች የማነጻጸሪያ እቃዎች አገልግሎት ላይ ባለው የሲዲ ዋጋ መሰረት ባለመስተናገዳቸውና ትክክለኛው የማስጫኛና ኢንሹራንስ ዋጋ ባለመወሰዱ ምክንያት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 322,543.53 መገኘቱ

ግኝት

የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት አዘገጃጀትና ስርጭት አጠቃቀምን አስመልክቶ በወጣው መመሪያ ቁጥር 10/1996 መሰረት የገቢ ዕቃዎች ዋጋ ከጉምሩክ ሪከርድ መነሻ እና ማነጻጸሪያ ዋጋ አንፃር መመሳከር እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ ትክክለኛው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ (CIF value) ባለመወሰዱ ምክንያት ፡-

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 170,675.66
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 151,867.87

በድምሩ ከሁለቱም ቅ/ቤ/ቶች ብር 322,543.53 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

ወደ ሀገር በሚገቡ እቃዎች ላይ ትክክለኛው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ እየተወሰደ ካልተሰራ መንግስት ከገቢ እቃዎች ማግኘት ያለበትን ገቢ ያሳጣዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ትክክለኛው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ባለመወሰዱ ምክንያት ያልተሰበሰበ የቀረጥ መጠን ብር 322,543.53 ከሚመለከታቸው ድርጅቶች እንዲሰበሰብ እንዲሁም ለወደፊቱ የሚመለከታቸው ሰራተኞች የፍተሻ ውጤት በዋጋና ታሪፍ ላይ ለውጥ የሚያመጣ ለመሆኑ በአግባቡ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን፣ ለዚህም

የሚመለከተው ክፍል አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ እንዳለበት ለየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የስራ አመራሮች አስተያየታችንን ሰጥተናል::

የስራ አመራሩ አስተያየት

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ከተገኘው ቀሪ ሂሳብ ውስጥ ብር 101,395.63 የሚፈለግበት ድርጅት ዲፖዚት አስይዞ ቅሬታ በማቅረቡ እየታየ መሆኑንና ብር 69,254.22 የክፍያ ማስታወቂያ ለድርጅቶች መላኩንና ክፍያውን ባለመፈጸማቸው አገልግሎት እንዳያገኙ መደረጉን በደ.ቁ.10/465/16 በ18 የካቲት 2005 ከዋናው መ/ቤት በሰጡት ምላሽ ገልጿል፡፡

1.3 ለቀረጥ ማስከፈያነት የተወሰደውን ዋጋ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ

ግኝት

የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት፣አዘገጃጀት፣ስርጭትና አጠቃቀም አስመልክቶ የወጣውን መመሪያ ለማስፈጸም በወጣው የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 2/1996 አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የመለዋወጫ ዋጋን በተመለከተ በአስመጪው የቀረበው የዋጋ ዝርዝር ሙሉ ለሙሉ በመነሻ ዋጋ ዝርዝር ውስጥ በማይገኝበት ጊዜ በመነሻ ዋጋ ዝርዝር ውስጥ በተገኙት እና በአስመጪው በማሳነስ በቀረበው ዝርዝር መካከል በተገኘው አማካኝ ልዩነት መሰረት በመነሻ ዋጋ ዝርዝር ውስጥ ያልተገኙትን የመለዋወጫ እቃዎች ዋጋ ማስተካከል እንደሚገባ ያዛል፡፡ በዚሁ መሰረት ስራው የሚሰራ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት አስመጪው ብቸኛ አስመጪ ነው በሚል በመመሪያው መሰረት ዋጋው ተስተካክሎ ለቀረጥ ማስከፈያነት ያልተወሰደ ሲሆን ድርጅቱ ግን ብቸኛ አስመጪ ለመሆኑ መረጃ ሊቀርብልን ባለመቻሉና በተወሰኑ ሌሎች ሰነዶች ላይ ይኸው አስመጪ ያቀረበው ሰነድ በመመሪያው መሰረት የተስተናገደ በመሆኑ ከታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት ለቀረጥ ማስከፈያነት የተወሰደው ዋጋ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካለመቻሉም በላይ ስራው ወጥነት የሌለው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ዲክላራሲዎን ቁጥር	የአስመጪው ድርጅት ስም	የእቃው አይነት	አገልግሎት ላይ የነበረው የዋጋ CD	የተሰበሰበው የቀረጥ መጠን	መግለጫ
C-200/12	JUGEL PLC	የባለ ሶስት እግር የሚኒዶር መለዋወጫ	15ኛ	1,712,216.40	JUGEL PLC በዲ/ዮን ቁጥር C-905/11 ያስገባው ተመሳሳይ እቃ ያቀረበው ዋጋ በመመሪያው መሰረት ከፍ (up lift) የተደረገ መሆኑ
C-292/12	JUGEL PLC	የባለ ሶስት እግር የሚኒዶር መለዋወጫ	15ኛ	1,765,834.33	
C-110/12	JUGEL PLC	የባለ ሶስት እግር የሚኒዶር መለዋወጫ	15ኛ	1,410,547.61	
ጠ/ድምር				4,888,598.34	

ስጋት

መመሪያው በሁሉም ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ካልሆነ መንግስት ከገቢ እቃዎች መሰብሰብ ያለበትን ገቢ እንዳይሰበስብ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ድርጅቱ ባቀረበው ሰነድ መሰረት ለምሳሌ በዲ/ዮን ቁጥር C-200/2012 እና C-292/2012 ከመጡት እቃዎች ውስጥ oil pump assembly ስራ ላይ ካለው የCD-ዋጋ አንጻር ከፍተኛ ልዩነት (ከ10% በላይ) ያለው በመሆኑ አስመጪው ብቸኛ አስመጪ ነኝ ስለአለ ብቻ በዋጋ ሰነዱ መሰረት ማስተናገዱ አግባብ ስለአልሆነና የዋጋ መመሪያ ቁጥር 10/1996ን ለማስፈጸም በወጣው መመሪያ ቁጥር 2/1996 አንቀጽ 11(3) መሰረትም ድርጅቱ ብቸኛ አስመጪ ቢሆንም እንኳን ያቀረበው ዋጋ ከአለም አቀፍ ዋጋ አንጻር ከፍተኛ ልዩነት ካለው ከአለም አቀፍ የመረጃ ምንጭ በሚገኝ ዋጋ (CD-price) መሰረት መስተካከል እንዳለበት ስለሚገልጽ ቅ/ጽ/ቤቱ ድርጅቱን በአቀረበው የዋጋ ሰነድ መሰረት ማስተናገዱ አግባብ ስላልሆነ ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

አሁን ባለው ሁኔታ በሬሽዮ (ratio) እየተሰራ ቢሆንም ግለሰቡ ባቀረቡት ቅሬታ ለታሪፍና ዋጋ ትመና በተጻፈው መሰረት ያልተሰበሰበ ሂሳብ ካለ ተጣርቶ እንደሚሰበሰብ ከኦዲት መውጫ ውይይት በኋላ በተጻፈው ደብዳቤ ገልጸዋል፡፡

1.4 የማስጫኛን ዋጋን በሚመለከት

ግኝት

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል የማስጫኛ ዋጋ (airway bill) አንድ ሶስተኛው ብቻ ለቀረጥ ማስከፈያነት የሚወሰድ ቢሆንም ይህን ስሌት ለመጠቀም የሚያስችል መመሪያ ወይንም ሰርኩላር ሊቀርብ አልቻለም፡፡

ስጋት

የአሰራር ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሣብ

ለወደፊቱ ቅ/ጽቤቱ የሚጠቀምበት አሰራር በሙሉ በመመሪያ፤ ቃለ ጉባኤ ወይንም በሌሎች ማስረጃ የተደገፉ ሊሆኑ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

አሰራሩን ለዘለቄታው በመመሪያ ለማስደገፍ በመ/ቤቱ እየተዘጋጀ ባለው የገቢ እቃዎችና የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ረቂቅ መመሪያ ውስጥ እንዲካተት መደረጉን በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅትና ከዚያ በኋላ በተጻፈው ደብዳቤ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

1.5 የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ቀሪ የገቢ ግብር ሂሳብን በተመለከተ

ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 77፣በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 31፣በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/95 አንቀጽ 10 እና በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅቁጥር 308 አንቀጽ 13 መሰረት እንዲሁም በጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 አንቀጽ 7 (1 እና 2) መሰረት የቀሪ ቀረጥና ታክስ የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ባለእዳ በ30 ቀናት ውስጥ እዳውን መክፈል ወይም ለመክፈል ከስምምነት መድረስ እንዳለበት ነገር ግን በውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ቅሬታ ያለው ባለእዳ ውሳኔው በደረሰው 15 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ እንደሚችል ይህንን በማይፈጽም ላይ ግን የንብረት መያዝ ስርአት ተፈጻሚ እንደሚሆንበት ይደነግጋል፤ ከዚህ አንጻር ያልተሰበሰበ የመንግስት ቀሪ ሂሳብ እና ግብር በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ተመላሽ ለማድረግ ቅ/ጽ/ቤቶቹ እየሰሩ መሆኑን ማጣራት ሲደረግ:-

- በድሬዳዋ ቅ/ቤት በኩል የጉምሩክ እና የአገር ውስጥ ቀሪ ሂሳብ ላይ ቅሬታ ያልቀረበበት እና ቀሪ ሂሳቡን ተመላሽ ለማድረግ የንብረት መያዝ ስርአት ተፈጻሚ ያልሆነበት በድምሩ ብር 12,306,587.08 ያልተሰበሰበ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ከ1999 እስከ 2004 ድረስ የጉምሩክ ቀሪ ሂሳብ ብር 315,062,445.8 ያልተሰበሰበ መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መሰብሰብ ሲገባው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 457,836,992.12 የሚገኝ መሆኑን

ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

በወቅቱ መሰብሰብ ሲኖርበት ባልተሰበሰበ ሂሳብ ላይ በመመሪያዉ መሰረት እርምጃ ካልተወሰደበት በቆይታ ብዛት በተለያየ ምክንያት መሰብሰብ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል። በዚህም ምክንያት መንግስት ሊያገኝ ይችል የነበረውን ገቢ ያጣል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ቀሪ ሂሳብ በማይከፍሉት ላይ በመመሪያው እና በአዋጁ መሰረት ተገቢው እርምጃ በወቅቱ ሊወሰድ ይገባል::

የስራ አመራሩ አስተያየት

- የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት የንብረት መውረስ ደብዳቤ ለድርጅቶቹ ተጽፎ ክትትል እየተደረገ መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ያለውን ቀሪ ሂሳብ በመመሪያ ቁጥር 69/2004 መሰረት ወደ ንብረት መያዝ ለማስተላለፍ የማጥራት ስራ መጀመሩን፣
- በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግዴታቸውን ባልተወጡ ደንበኞች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ወደ ህግ ማስከበርና ለሚመለከታቸው ክፍሎች ማሣወቃቸውን

በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅትና በ18/06/2005 በቁጥር 10/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈው ደብዳቤ ገልጸዋል፡፡

2. ኤክስፖርት /የወጪ እቃን በተመለከተ

2.1 የጫት ላኪ ማህበራት ጫት ወደ ጅቡቲ ለሚልከው ድርጅት በተፈቀደላቸው ኮታ መጠን የማያቀርቡ መሆኑ ግኝት

በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 5/2000 አንቀጽ 5 መሰረት:-

ሀ. የጫት ላኪ ማህበራት በየቀኑ ያልተጣራ ክብደት 5474 ኪሎ ግራም/ የተጣራ ክብደት 5200 ኪሎ ግራም የሆነ ጫት ከኢትዮጵያ ወደ ጅቡቲ ጫት ከሚልኩ ማህበራት ላይ ጫት ለሚቀበለው በጅቡቲ ለሚገኝ ድርጅት(ሶጂክ) ማቅረብ እንዳለባቸው የተገለጸ ሲሆን ይህንኑ ኮታ የውጪ ንግድ ጽ/ቤት በቁጥር 01-1-4-9/83 በቀን 04/07/04 በተጻፈ ደብዳቤ የጅቡቲ መንግስት ወደ ሀገሩ የሚያስገባውን የቀን ጫት ኮታ ማሳደጉን በመግለጽ የማህበራት የቀን ኮታ በፊት ከሚልኩት በ650 ኪሎግራም እንዲጨምር የወሰነ መሆኑን፤

ለ. ማህበራት በልዩ ልዩ ምክንያት በኮታው መሰረት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ጫት ማቅረብ የማይችሉ ሲሆን ሁኔታውን ከ 48 ሰአት በፊት ለድሬዳዋ ውጪ ንግድ ጽ/ቤት፣ ለምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት እና ለተቀባዩ ለሶጂክ ተወካይ ማሳወቅ እንዳለባቸው፤

ሐ. ከላይ በ "ለ" ላይ የተጠቀሰው ሁኔታ ሲከሰት የድሬዳዋ ውጪ ንግድ ጽ/ቤት ለተቀሩት ማህበራት ጥያቄ በማቅረብ በሚሰጠው መልስ ቅደም ተከተል መሰረት ሳይቀርብ የቀረውን የጫት መጠን ሊያቀርብ ከሚችል ሌላ ማህበር ለሶጂክ እንዲቀርብ በማድረግ ለምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጽ/ቤት እንደሚያሳውቅ፣

መ. የምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ ጫት ላኪ ማህበራት ከላይ (ሀ) ላይ በተገለጸው መሰረት የተመደበላቸውን ኮታ መላካቸውንና "ለ" ላይ በተገለጸው መሰረት ከ 48 ሰአት በፊት ያላሳወቁትንና ወይም በኮታቸው መሰረት ሳይልኩ የቀሩትን እየተከታተለ በየጊዜው ለውጪ ንግድ ጽ/ቤት መላክ እንዳለበት ተገልጿል፡፡

ከዚህ አንጻር በመመሪያው መሰረት ማህበራት በቀን ኮታቸው መሰረት ጫቱን ለሶጂክ የሚያቀርቡ መሆኑንና አገሪቷ ከውጪ ንግዱ ማግኘት ያለባትን

የውጪ ምንዛሬ እያገኙ መሆኑን እንዲሁም በቀን ኮታቸው ልክ በመመሪያው መሰረት በማያቀርቡት ላይ ተገቢው እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ማህበራት በቀን ኮታቸው ልክ የማያቀርቡ መሆኑንና በዚህም ምክንያት አገሪቷ በ2004 በጀት አመት ብቻ 3,099,618 የአሜሪካ ዶላር የውጪ ምንዛሬ ያጣች መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

በተፈቀደላቸው ኮታ ልክ ጫት ለውጪ ገበያ በማያቀርቡ ማህበራት ላይ በመመሪያው መሰረት ተገቢው እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ አገሪቷ ከጫት ንግድ ማግኘት ያለባትን የውጪ ምንዛሬ እንድታጣ ያደርጋታል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በመመሪያው መሰረት በተፈቀደላቸው የኮታ መጠን ለሶጂክ ድርጅት በማያቀርቡትና ማቅረብም እንደማይችሉ ከ 48 ሰአት በፊት በማያሳውቁት ላይ መረጃውን ለውጪ ንግድ ጽ/ቤት እንዲቀርብ በማድረግ የሚመለከተው መስሪያ ቤት ሌሎች አማራጮችን ተጠቅሞ የጂቡቲ መንግስት ለመቀበል በሚፈልገው ኮታ መጠን ጫቱ እንዲቀርብ በማድረግ አገሪቷ ከጫት ኤክስፖርት ማግኘት ያለባትን የውጪ ምንዛሬ የምታገኝበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡ዋናው መስሪያ ቤትም ተገቢውን ክትትል በማድረግ ችግሩ ቶሎ የሚስተካከልበትን ሁኔታ መፍጠር አለበት፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

- እስከአሁን ባለው አሰራር በየቀኑ የተላከውን የጫት መጠን ለውጪ ንግድ ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከመቅረጫ ጣቢያው በስልክ መገናኛ በየቀኑ በየማህበራቱ ስም ተለይቶ ሪፖርት የሚደረግ በመሆኑ ውጪ ንግድ ጽ/ቤት ከኮታ በታች እንደሚላክ የሚያውቅ መሆኑን በመግለጽ አሁንም በተሰጠው አስተያየት መሰረት መረጃውን ለውጪ ንግድ ጽ/ቤት ሪፖርት የማድረጉ ስራ መጀመሩን በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅትና ከውይይቱ ቡኃላ ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ደብዳቤ ገልጸዋል፡፡

2.2 ከቀረጥ ነፃ ባስገቡት ጥሬ ዕቃ ያመረቱትን ምርት ወደ ውጪ ስለመላካቸው ማስረጃ ያልቀረበና የቫውቸር ተጠቃሚዎች ወለድ መሰላት የነበረበት ካቋረጡበት ቀን ጀምሮ መሆን ሲገባው ጥያቄ ካቀረቡበት ጀምሮ በመሰላቱ ምክንያት ያልተሰበሰበ በድምሩ ብር 15,305,560.71 መገኘቱ

ግኝት

የተሻሻለው የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ማጽደቂያ አዋጅ 543/1999 ክፍል ሁለት አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት ወደ አገር ውስጥ ከገባው ጥሬ ዕቃ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋለ ከተገኘ እንዲሁም የጊዜ ገደቡ በአንቀጽ 11(7) ካልተራዘመ በስተቀር አምራቹ ባስገባው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፍል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እስከነወለዱ እንዲከፍል መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በኩል 12 ድርጅቶች የማወራረጃ ጊዜያቸው አልፎ ባለማወራረዳቸው ሊከፍሉ የሚገባ ቀረጥና ታክስ ብር 15,114,059.02 መገኘቱ ታውቋል፡፡

ስጋት

ቀረጥ ሳይከፈልበት በማበረታቻ ስም ወደ አገር ውስጥ የገባ ጥሬ ዕቃ ለተባለው ዓላማ ሳይውል በሀገር ውስጥ ገበያ ሊሸጥ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት የውጭ ምንዛሬ ሊያሳጣ እና ሊሰበሰብ የሚገባው ቀረጥና ታክስም ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑት የተፈቀደላቸውን ጥሬ ዕቃ አስገብተው በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ ያላደረጉት ባስገቡት ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ እንዲከፍሉ መደረግ እንዳለበት አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ከተጠቀሱት ድርጅቶች መካከል አንድ ድርጅት መክፈል መጀመሩን፣ ሶስት ድርጅቶች ጥሬ እቃ አለማስገባታቸውና ስምንቱን ለማስከፈል ክትትል መጀመሩን በደ.ቁ.10/405/16 የካቲት 18 2005 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ደብዳቤ ገልጸዋል፡፡

2.3 <u>የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑት ድርጅቶች ወደ አገር ውስጥ በኢንሹራንስ ዋስትና ጥሬ ዕቃ አስገብተው /Import/ ያላወራረዱ ድርጅቶች መገኘታቸው</u>

<u>ግኝት</u>

ለወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 543/1999 አንቀጽ 11 (9) የጉምሩክ ባለሥልጣን ስሌቱን የሚሠራው ቫወቸሩ በታደሰ ከ11ኛው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ሲሆን ስሌቱ በ30 ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ እንዳለበትና በአንቀፅ 11(10) ደግሞ አምራቹ የምርት ሥራው እንዳይስተጓጎል ለሦስት ጊዜ ብቻ በኢንሹራንስ ዋስትና እቃዎች ወደ አገር ሊያስገባ ይችላል ብሎ ይደነግጋል፡፡ መመሪያው በትክክል ለመዋሉ ኦዲት ሲደረግ አብዛኛው የቫውቸር ተጠቃሚዎች መጀመሪያ ካስገቡት በተጨማሪ በኢንሹራንስ ዋስትና ዕቃዎች ወደ አገር አስገብተው ሳያወራርዱ ለዓመታት የቆዩ መኖራቸውን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

የቫውቸር ተጠቃሚዎች ክፍተቱን በመጠቀም ላያወራርዱ ይችላሉ፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑት ድርጅቶች /ሰዎች/ የተፈቀደላቸውን ጥሬ ዕቃ በመመሪያው መሠረት የሚወራረድበትን የውስጥ ቁጥጥ ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ያላወራረዱ ተጠቃሚዎች ባቀረቡት መረጃ መሰረት የማቀናነስ ስራ መጀመሩንና አፈጻጸሙን በመከታተል እልባት እንደሚያገኝ ከዋናው መስሪያ ቤት ከኦዲት መውጫ ውይይት ቡኃላ በተጻፈ ደብዳቤ ገልጸዋል፡፡

3. የአገር ውስጥ ገቢ ሂሳብን በተመለከተ

3.1 ያልተፈቀደ ወጪ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ በመቀናነሱ ምክንያት ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 19,054.95 ፣

ግኝት

የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/2002 አንቀጽ 11(4) መሰረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 21 ንኡስ አንቀጽ 3(ለ) አፈጻጸም የተመዘገበ ሰው ሀላፊዎች ፣ሰራተኞች ወይም ደንበኞች በሬስቶራንት የምግብ አገልግሎት እንዲያገኙ ወይም ሰራተኞች ለመዝናናት ከስራ ቦታቸው ውጪ በሚጓዙበት ጊዜ ለመኝታ እና ለምግብ በሚፈጸመው ግዥ ላይ የሚከፈለው ታክስ እንዲቀናነስ አይፈቀድም፡፡ ከዚህ አንጻር ያልተፈቀዱ ወጪዎች ያልተቀናነሱ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሰረት በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ከድርጅቱ ስራ ጋር የማይገናኙና ያልተፈቀዱ ወጪዎች በድምሩ ብር 19,054.95 እንዲቀናነሱ የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር	ግዥው የተፈጸመበት ድርጅት ስም	የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ የሰነድ ቁጥር(Document Number)	ግዥ የተፈጸመበት ቀን	የግዥው መጠን	የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ(input vat)
0000053805/0016295696-2	Addis fana General mds & hotel	45361180004	14/3/2012	123480	18,522
	Mesert seifu supermarket	45361180004	8/9/04	3553	532.95
ጠቅላላ ድምር				127468	19,054.95

ስጋት

ከአዋጁ አንጻር መቀናነስ የማይገባቸው ወጪዎች ያልተቀናነሱ ለመሆኑ ተገቢው ጥንቃቄ ካልተደረገ ከተጨማሪ እሴት ታክስ መሰብሰብ የሚገባው ገቢ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

መቀነስ የማይገባው ወጪ በመቀናነሱ ምክንያት ያልተሰበሰበ ገቢ ብር 19,054.95 ከሚመለከተው ግብር ከፋይ መሰብሰብ ይኖርበታል:: ለወደፊቱም

ከድርጅቱ ስራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው ወጪዎች አለመቀናነሳቸው በአግባቡ በሚመለከታቸው ሰራተኞች እየተረጋገጠ ገቢው እየተሰበሰበ ለመሆኑ አስፈላጊውን ክትትል መደረግ እንዳለበት አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

ወንጂ ስኳር ፋብሪካ ከአዲስ ፋና General mds እና Mesert seifu super market ጋር የፈጸመውን የግዢ አይነት በተያያዘው የማሳወቂያ ቅፅ ላይ በግልፅ ባለማስፈሩ እና በማጥራት ሂደቱ ወቅት ሳይታይ መታለፉ እንደከፍተት የሚታይ መሆኑን በመግለፅ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ወደ ድርጅቶቹ ስልክ በመደወል በስልክ የተሰጠውን ምላሽ መሰረት በማድረግ ከአዲስ ፋናና ከመሰረተ ሰይፉ ያልተፈቀደ ወጪ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተቀናነሰ መሆኑን ለመረዳት የቻሉ መሆኑን በመግለፅ ድርጅቱ ሰነዶቹን በአፋጣኝ ማቅረብ ባለመቻሉ ሪፖርቱ ከመተላለፉ በፊት በተቻለ መጠን ሰነዶችን መርምረው በስልክ የተሰጠው መረጃ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ የተወሰነ ቀን ቢሰጣቸው የተሻለ መሆኑን ገልፀው በማጥራት ሂደት ላይ የሚሳተፍ ሁሉም የስራ ሂደቱ ፈፃሚዎች ግን ሀላፊነት ወስደው ስራቸውን በአግባቡ እንዲተገብሩ የቡድን መሪዎችም ተገቢውን ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው የጋራ ስምምነት የተደረሰ መሆኑንና በተጨማሪም በግብዓት ላይ ተቀናሽ የተደረገ ያልተፈቀደ የተጨማሪ እሴት ታክስ ወጪ በዴስክ ኦዲት ከማህደር እየተጣራ እንዲወሰን ለሚመለከታቸው ኦፊሰሮች መተላለፉን በቅ/ጽ/ቤቱ በተደረገ የኦዲት መውጫ ውይይት የተገለጸ ሲሆን፣ በተጨማሪም የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ደብዳቤ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የተ.እ.ታ ሂሳብ የሚሰበሰብ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

3.2 <u>በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያና በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ መካከል የሽያጭ ልዩነት መገኘቱ</u>

<u>ግኝት</u>

ግብር ከፋዮች ባቀረቡት መረጃ መሰረት የ2003 በጀት ዓመት በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው ጠቅላላ ሽያጭ በትክክል ወደ ትርፍ እና ኪሳራ ማሳወቂያ ላይ ማስተላለፋቸውን እና በዚህም መሰረት ግብርና ታክስ በትክክል ማሳወቃቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በንግድ ትርፍ እና

ኪሳራ መግለጫ የተመለከተው የሽያጭ ሂሳብ በተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመለከተው ጋር ልዩነት ያለው በመሆኑ ምክንያት ፡-

- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል ሊሰበሰብ የሚገባው ተጨማሪ እሴት ታክስና የንግድ ትርፍ ግብር በድምሩ ብር 14,101,310.35 ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
- በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር 23,305,332.23 የንግድ ትርፍ ግብር ያልተሰበሰበ እንዲሁም በሂሳብ ስሌት ስህተት ምክንያት ብር 3,991.30 የተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑን፣
- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ብር 16,193,432.23 የንግድ ግብር ያልተሰበሰበ መሆኑ፣፡፡

ከሶስቱም ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 53,600,074.81 ግብርና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገንዘብ ሊያጣ ከመቻሉም በተጨማሪ መንግስት ሊሰበስብ ያቀደውን ዕቅድ ያፋልስበታል:: በመሆኑም የሥራ አፈፃፀሙ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል፡፡

የማሻሻያ እርምጃ

ከላይ የታየው ያልተሰበሰበው ግብርና ታክስ ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ግብር ከፋዮች ያመኑበትን ግብር ከፍለው ከሄዱ በኋላ በግብር ከፋዮች የቀረበውን ማስረጃ ወዲያውኑ እንዲገናዘብ ተደርጎ ትክክለኛነቱ መረጋገጥ እንዳለበት አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

- የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ለ4 ግብር ከፋዮች የብር 7,035,679.02 የውሳኔ ማስታወቂያ የተላከ መሆኑንና ለቀሪዎችም አስፈላጊውን እርምጃም የሚወስዱ መሆኑን፣
- የሀዋሳ ለ6 ግብር ከፋዮች የብር 563,899.43 የግብር /ታክስ ማስታወቂያ የተላከ መሆኑና የሌሎችን የማጥራት ስራ እየተከናወነ መሆኑን፣

- የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ለአራት ድርጅት የግብር ማስታወቂያ ወጥቶ ሁለት ድርጅቶች ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ቅሬታ አቅርበው በዝርዝር እየታየ ያለ መሆኑን፣

ከዋናው መስሪያ ቤት በተደረገው የኦዲት መውጫ ውይይትና የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁጥር 1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ደብዳቤ ገልጸዋል፡፡

3.3 የበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቆጠራ ውጤት በትክክል ባለመያዙና በእርጅና ቅናሽ አቀናነስ ስህተት ምክንያት ብር 26,017,420.60 ግብርና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ

ግኝት

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተመለከተ የንግድ እቃዎች ቆጠራ ከወጪ ቀሪ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ በትክክል ባለመያዙ ምክንያት በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ያልተሰበሰበ ብር 25,090,951.15 ግብርና ታክስ መገኘቱ፣ ዝርዝሩም

መለያ ቁጥር	የድርጅቱ ስም	መሰብሰብ የነበረበት ግብር (ብር)	ተሰብስቦ የተገኘ (ብር)	ያልተሰበሰበ ግብር (ብር)
0000007059	ፎርቹን ኢንተር ፕራይዝ	4,169,987.38	711,523.99	3,458,463.39
0000012403	ጂ ኤንድ ኤ ኢንዱስትሪ	1,189,743.61	1,133,670.51	56,073.09
0004372810	ቻይና ኮሚኒኬሽን ኮንስትራክሽን			21,576,414.67
ጠቅላላ ድምር				25,090,951.1

- በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ታቦር ሴራሚክ ባሰወቀው የንግድ ትርፍ እና ኪሳራ ማሳወቂያ መሰረት የ2002 በጀት ዓመት የመጨረሻ እቃዎች ቆጠራ ውጤት ወደ 2003 በጀት ዓመት የመጀመሪያ እቃዎች ቆጠራ ሲዞር በትክክል ያልተያዘ በመሆኑ እና በጥቅል የእርጅና ቅናሽ አቀናነስ ስርዓት መሰረት መሆን ሲገባው በቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ አቀናነስ ስርዓት መሰረት በመሰራቱ ምክንያት በድምሩ ብር 926,469.45 ግብር እና ታክስ ያልተከፈለ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

ስጋት

አሰራሩ ህገወጥነት እንዲበረታታ ይገፋፋል፡፡ መንግስትም ማግኘት ያለበትን ገቢ ያሳጣዋል፡፡

የማሻሻያ እርምጃ

ያልተሰበሰበው ግብርና ታክስ ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ግብር ከፋዮች የሂሳብ መግለጫ በሚያቀርቡበት ወቅት ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎች በአግባቡ መጣራት እንዳለበት አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት አንድ ድርጅትን አስመልክቶ የኮንስትራክሽን ድርጅት መሆኑና የሂሳብ አያያዙም ስርአት ፐርሴንቴጅ ኮምኘሊሽን መሆኑንና በሚከፈለው ግብር ላይ ለውጥ እንደማያመጣ የገለጸ ሲሆን፣ ሌሎች ድርጅቶቹ በቀረበው የኦዲት ግኝት መሰረት የግብር ማስታወቂያ ወጥቶላቸው በውሳኔው ላይ ቅሬታ ቀርቦ በመታየት ላይ ያለ መሆኑን
- የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት የተሠጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የተቀበሉት መሆኑን

ገልጸዋል፡፡

3.4 በታክስ ኦዲተሮች የግብር ውሳኔ ሪፖርት መሰረት የሚሰበሰበው ሂሳብ በትክክለኛው የታክስ አይነትና የሂሳብ መደብ እየተመዘገበ ሪፖርት የማይዘጋጅ መሆኑ

ግኝት

በታክስ ኦዲተሮች የግብር ውሳኔ መሰረት የሚሰበሰበው ሂሳብ በትክክለኛው የታክስ አይነትና የሂሳብ መደብ እየተመዘገበ የሂሳብ ሪፖርት የሚዘጋጅ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል አንድ ድርጅት ከተለያየ የታክስ አይነት ተጨማሪ የግብር ውሳኔ ሲደርሰው ለየታክስ አይነቱ የክፍያ ስምምነት መግባት ሲኖርበት በጥቅል ስምምነት እንዲገባ የሚደረግ ሲሆን ክፍያ ሲፈጽምም ለተለያዩ የታክስ አይነቶች የከፈለ ቢሆንም የሚመዘገበው ግን በአንዱ የታክስ አይነት ላይ በማጠቃለል መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፤፤

ስጋት

የሚዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርገዋል

የማሻሻያ ሀሳብ

የችግሩ ዋንኛ መንስኤ በታክስ ኦዲተሮች የሚጠየቅ የግብር ውሳኔ በሲስተም (sigtas) ላይ እንዲመዘገብ አለመደረጉ እንዲሁም በደንበኞች አገልግሎት በኩል ግብር ከፋዩ የግብር እዳ ስምምነት ሲገባ በየታክስ አይነቱ ስምምነት እንዲገባ አለመደረጉ በመሆኑ ችግሩን ለማቃለል መረጃው ሲስተም ላይ እንዲመዘገብ ማድረግና ግብር ከፋዩ የግብር እዳ ስምምነት ሲገባም ለየታክስ አይነቱ መሆን እንዳለበት አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት አሰራሩ የተስተካከለ መሆኑን የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

3.5 በስሌት ስህተት ምክንያት ያልተሰበሰበ ብር 33,506.10 የኤክሳይዝ ታክስ መገኘቱ፡፡

ግኝት

በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በተጨማሪ በኤክሳይዝ ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 570/2000 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት ሀዋሳ ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ የመጋቢት ወር 2004 ዓ.ም የኤክሳይዝ ታክስ በሚያሳውቅበት ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ በትክክል ያልተሰላ በመሆኑ ያልተሰበሰበ ብር 33,506.10 መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

በትክክል አሰስመንት አለመሰራቱ ለመንግስት ገቢ መሆን ያለበት ገንዘብ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ያደርጋል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ይከፍታል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ያልተሰበሰበውን ግብር እና ታክስ ብር 33,506.10 ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች እንዲሰበሰብ አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት የውሳኔ ማስታወቂያ የተላከና ክትትልም እየተደረገ መሆኑን የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

3.6 ግብርን በወቅቱ ያለማሳወቅ

ግኝት

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 ክፍል 7 አንቀጽ 26 ታክስ ስለማስታወቅና ስለመክፈል ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እያንዳንዱ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ለታክስ ባለስልጣን ማስታወቅ እንዳለበት ያዛል፡፡ ስራው በዚሁ መሰረት የሚሰራ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት/

- ቻይና ጂሊን ፕሮቪንስ ትራንስሚሽን ኤንድ ሰብስቴሽን ፕሮጀክት ካምፓኒ (0000043793) ከ2001 በጀት አመት በኃላ የተጨማሪ እሴት ታክስም ሆነ የንግድ ትርፍ ያላሳወቀ መሆኑ፣
- ፍላወር ፖርት ካርጎ ድርጅት /0005021831/ ከጥር 2004 ጀምሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቀ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ስጋት

በወቅቱ ያላሣወቁ ግብር ከፋዮች ክትትል የሚደረግበት የቁጥጥር ሥርዓት ደካማ በመሆኑ ምክንያት ለመንግስት ገቢ መሆን የሚገባው ገንዘብ በወቅቱ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

የማሻሻያ እርምጃ

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ እና በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ሪፖርት ያላቀረቡ ግብር ከፋዮችን በወቅቱ በመለየት እና ክትትሉን በማጠናከር ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

ቻይና ጂሊን ፕሮቪንስ ትራንስሚሽን ኤንድ ሰብስቴሽን ፕሮጀክት ካምፓኒ በተመለከተ በህግ ማስከበር በኩል በተደረገ ክትትል ካምፓኒው ከሀገር

በመውጣቱ ሊገኝ አለመቻሉን ሆኖም ድርጅቱ ከመብራት ኃይል በነበረው የስራ ግንኙነት የስራ ውል በሪቴንሽን የተያዘው ብር እንዳይከፈል እንዲሁም ከስራ ውሉ ጋር የሚከፈሉ ሌሎች ክፍያዎች ካሉ እንዲታገዱ ደብዳቤ መጻፉን፣ፍላወር ፖርት ካርጎ ግን ገቢውን እንዲያሳውቅ መደረጉን የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

3.7 በሲግታክስ (ሲስተም ላይ) የማይመዘገብ ገቢ ስለመኖሩ

ግኝት

ከግብር ከፋዩ የሚሰበሰብ ግብር/ገቢ ሙሉ በሲግታክስ (በሲስተም ላይ) የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአዳማና በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤቶች ከተወሰኑ ግብር ከፋዮች በማኑዋል ደረሰኝ የተሰበሰበ ገቢ በሲግታክስ (ሲስተም ላይ) የማይመዘገብ መሆኑን ፣
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በታክስ ኦዲትም ሆነ በዴስክ ኦዲት የሚገኙ(የሚጠየቁ) ተጨማሪ የግብር ዉሳኔዎች በሲግታክስ (ሲስተም ላይ) የማይመዘገቡ መሆኑን ፣
- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል ከከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት የሚሰበሰበው ገቢ በመንግስት ታክስ አስተዳደር ስርዓት/SIGTAS/ ላይ የማይመዘገብ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ስጋት

የግብር ከፋዩን መረጃ በተሟላ ሁኔታ ስለማይገኝ የታክስ ኦዲት በሚሰራበት ጊዜ፣ዕዳ ያለበትና የሌለበትን በሚለይበት ጊዜ ፣ በጊዜው ታክስ ያሳወቁና ያላሳወቁትን ለመለየት፣ አይቻልም፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ቅ/ጽ/ቤቶቹ ወደ ሲስተም ያልገቡትን ገቢ በሙሉ በSIGTAS መመዝገብ እንዳለባቸው አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

- የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በቀጣይ ሙሉ በሙሉ በሲስተም እንዲደገፍ የተሰጠውን አስተያየት ተከትሎ ቅ/ጽ/ቤቱ ጉዳዩን በዋናው መ/ቤት ደረጃ እየተሰራ መሆኑን፣
- የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በማኑዋል ደረሰኝ የተሰበሰቡትን በተመለከተ በቀድሞ የታክስ ኦዲት ወቅት አብዛኞቹ ዉሳኔዎች የታክስ ፔሬዳቸዉ ሳይገለጥ ከ---እስከ ተብሎ የተወሰነ በመሆኑ መረጃዉ ሊገባ አለመቻሉን ገልፀዉ እያንዳንዱን ቻርጅ የተደረገዉን ዉሳኔ በየታክስ ፔሬዱ ኦዲተሮች እንዲያስገቡ ተደርጎ በመረጃ የማጥራቱ ሂደት በመስተካከል ላይ የሚገኝ መሆኑን፣
- የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት መረጃዎች ወደ ሲስተም እየገቡ መሆኑና እስከ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም ለማጠናቀቅ የጊዜ ሰሌዳ መዘጋጀቱን፣ ፣
- የሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት የተሰጠውን አስተያየት የተቀበሉት መሆኑን፣

የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

3.8 ዘግይቶ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ

ግኝት

በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ሳጋ ሎጊታ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሀምሌ ወር 2003 ዓ.ም የተጨማሪ እሴት ታክስ ሽያጭ ብር 57,272.70 በነሐሴ ወር 2003 ውስጥ መክፈል ሲገባው ጥር ወር 2004 በመክፈሉ ቅጣትና ወለድ አለመክፈሉ ታውቋል፡፡

ስጋት

በመመሪያው መሰረት በወቅቱ በማያሳውቁት ላይ ወለድና ቅጣት ካልታሰበ መንግስት ማግኘት ያለበትን ገቢ ያሳጣዋል፡፡

የማሻሻያ እርምጃ

ቅርንጫፉ በሲስተም የሚሰራ ከሆነ የመክፈያ ጊዜው ያለፈበትን ራሱ ሲስተሙ መቅጣት ሲገባው ወለድና ቅጣት ያልተከፈለ በመሆኑ ከሚመለከተው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳሬክቶሬት (MIS) ጋር በመነጋገር ችግሩ በአስቸኳይ መስተካከል እንዳለበት አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

ችግሩ የተፈጠረው በሲስተም አቀናነስ ስህተት ነው፡፡ ሆኖም ወለዱን ብር 4589.23 ድርጅቱ እንዲከፍል የውሳኔ ማስታወቂያ የተላከ መሆኑን የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

3.9 በሲስተም /SIGTAS / ላይ ተመዝግቦ የሚገኘውን የገቢ ሂሳብ በተመለከተ

በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ከተለያዩ የታክስ አይነቶች የሚሰበሰበው ገቢ በመንግስት የታክስ አስተዳደር (SIGTAS) ላይ በትክክለኛው ሂሳብ መደብ የማይመዘገብ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ለምሳሌ ያህል፡-

- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በኩል ከሀገር ውስጥ የተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ መንግስት በሚያዘው ለገቢ አርእስት ከ1000-1999 በተሰጠው የገቢ ሂሳብ መደብ መሰረት መመዝገብ ሲገባው ፍሬ ግብር፣ ቅጣትና ወለድ በድምር ብር 72,551,142.12 በ8881 ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን በተጨማሪ የኤክሳይዝ ታክስ የገቢ መለያ ቁጥር ከ1201-1279 ሲሆን በኘት የገቢ መለያ ቁጥር በ1124፣ 1126፣ 1133 እና በ1169 በድምሩ ብር 54,884,120.51 ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ፣
- በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩልም በተለያየ የገቢ አርእስቶች የተሰበሰበ በድምሩ ብር 48,280,680.10 በሲስተም /SIGTAS/ ላይ ያለ ሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

ስጋት

በገቢ ዓይነቱ የተሰበሰበው የገቢ ግብር በሂሳብ መደቡ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ የማይቻል ከመሆኑም ባሻገር ቅርንጫፍ መ/ቤቱን በዕቅዱ መሰረት ግብሩን መሰብሰቡን ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ቅርንጫፍ መ/ቤቱ የሚሰበስበውን የገቢ ግብር መንግስት በሚያዘው የሂሳብ አወቃቀር ስርዓት መሰረት በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ሊመዘግብ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

በየቅ/ጽቤቶቹ ደረጃ መስተካከል የሚቻሉት በሙሉ እንዲስተካከሉ የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህ ውጭ ያሉት በቀጣይ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱና የገ/ኢ/ል/ሚ/ር የሚሰጠው የገቢ አርእስት ኮድ አንድ የሚሆንበት ሁኔታ እንዲመቻች ጥረት የሚደርግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

3.10 ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተቀንሶ ገቢ የሚደረገውን ሂሳብ በተመለከተ ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 መሰረት ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ቀጣሪው ቀንሶ ያስቀረውን ግብር ከእያንዳንዱ ወር መጨረሻ አንስቶ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለበትና በዚህ ዓይነት ተቀንሶ የቀረው ግብር ገቢ በሚደረግበት ጊዜ በወሩ ውስጥ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያገኙትን ሠራተኞች ዝርዝር
የሚያሳይ መረጃ ተያይዞ መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ይሁን እንጂ በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በኩል:-

- ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲና ከሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ የተቀነሰውን ግብር ከእያንዳንዱ ወር መጨረሻ አንስቶ ካሉት 30 ቀናት ውስጥ ማስገባት ሲገባቸው እስከ ስድስት ወር አዘግይተው ወደ ባለስልጣኑ ገቢ ያደረጉት ብር 1,705,617.59 መኖሩ ፡፡
- በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲና በሐዋሣ ዩኒቨርሲቲ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያገኙትን ሠራተኞች ዝርዝር የሚያሳይ መረጃ ሣይያዝ ብር 75,049.27 ገቢ በመደረጉ ምክንያት ሰለ ግብሩ ትክክለኛ ስሌት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት

በትክክል አሰስመንት አለመሰራቱ ለመንግስት ገቢ መሆን ያለበት ገንዘብ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ያደርጋል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ይከፍታል፡፡

የማሻሻያ እርምጃ

የመንግስት ገቢ በወቅቱ ሊሰበሰብ በሚችልበት መልኩና ግብር ከፋዮች የሂሳብ መግለጫ በሚያቀርቡበት ወቅት ተያያዥነት ያላቸውን ማስረጃዎችን

ማጣራትና በትክክል ያልቀረበ የሂሳብ መግለጫ ሲገኝ ወዲያውኑ ግብር ከፋዩ እንዲያውቀው ቢደረግ ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ በወቅቱ ሊሰበሰብ ይችላል ፡፡

<u>የሥራ አመራሩ አስተያየት</u>

የዘገየውን የሥራ ግብር ወለድና ሌሎች ቅጣቶች ተሰልቶ እንዲስተካከል የሚደረግ መሆኑን በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅት ገልጸዋል፡፡

4. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

4.1 <u>የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ</u>

<u>ግኝት</u>

የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን በቁጥር መ30/ጠ/ጠ13137/820 በቀን 5/13/2001 ዓ.ም ባስተላለፈው ሠርኩላር መሠረት የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተግባራዊ እንዳይሆን መመሪያ ተላልፏል፡፡ ነገር ግን በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በ2004 በጀት ዓመት ለትርፍ ሰዓት ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

<u>የማሻሻያ እርምጃ</u>

ከላይ እንደተጠቀሰው ከፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን በተላለፈው መመሪያ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተግባራዊ እንዳይሆን ተወስኗል፡፡ ስለዚህ የተፈፀመው ክፍያ አግባብነት የለውም፡፡
ከመ/ቤቱ የሥራ ባህሪ አንፃር ትርፍ ሠዓት የሚያስፈልገው አስገዳጅ ሁኔታ ካለ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድ ከሆነ ጉዳዩን ለሚመለከታቸው አካላት አሳውቆ በመመሪያ እንዲደገፍ መደረግ ይኖርበታል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ አስተያየት</u>

ሁኔታውን አስመልክቶ የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ የትርፍ ክፍያን አስመልክቶ ጥር 1 ቀን 1990 ዓ.ም በቁጥር ጠ80-ሐ2/01/17 ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በተፈቀደው መሰረት ይህንኑ በመተግበር ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ይሁን እንጂ የተጠቀሰውን ሁኔታ አሰመልክቶ፣

- በወቅቱ የጉምሩክ ባለስልጣን በሰው ኃይልና በመገናኛና ትራንስፖርት እንዲሁም በሌሎች የስራ ማስኪያጃ ወጪዎች በነበረበት ችግር ምክንያት

ለጉምሩክ የኦፕሬሽን፣ ፍተሻና የመጋዘን ሰራተኞች ብቻ የትርፍ ስዓት ክፍያ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽቤት የተፈቀደበት ሁኔታ የነበረ መሆኑንና በአሁኑ ወቅት ባለስልጣኑ ያለበት ሁኔታ የተሻለ በመሆኑ፣

- ባለስልጣኑ መስሪያቤት በአሁኑ ሰዓት የትርፍ ስዓት ክፍያ እየፈጸመ ያለው ግን ከተጠቀሱት የስራ መደቦች ውጪ መሆኑ፣
- የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የትርፍ ስዓት የከለከለበት ዋናው ምክንያት መስሪያ ቤቶች የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ያደረጉ በመሆኑና የትርፍ ስዓት ክፍያ ከተጠቀሰው ለውጥ ጋር የማይጣጣም ነው በማለት ሲሆን ባለስልጣኑ ደግሞ ይህን ለውጥ ካደረጉ መስሪያ ቤቶች ዋነኛው በመሆኑ፣
- ለጉምሩክ ባለስልጣን የተፈቀደው የትርፍ ሰዓት ክፍያ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ማቋቋሚያ አዋጅና በዚሁ አዋጅ መሰረት በወጣው መመሪያ መሰረት የተሻረ በመሆኑ፣

ከባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የተሰጠውን ምክንያት በኛ በኩል አልተቀበልነውም፡፡

5. <u>ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ</u>

<u>ግኝት</u>

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱንና ሂሳቡም በወቅቱ መወራረዱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በባለስልጣን ዋና መስሪያ ቤቱ በኩል በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 4210 ብር 5,046,709.48 ከአንድ ዓመት በላይ እድሜ ያለው ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

<u>ስጋት</u>

የመንግስት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊዘገይ ወይም ሳይሰበሰብ ባክኖ ሊቀር የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ሂሳቡ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 (1) መሰረት በወቅቱ እንዲወራረድ ተገቢው ጥረት መደረግ ያለበት ከመሆኑም በላይ ሂሳብ

ሊወራረድ የማይችል ከሆነ ደግሞ በፋይናንስ ደንቡ መሰረት የሚሰረዝበት ሁኔታ ሊመቻች እንደሚገባ አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

- ብር 3,405,349.04 በበጀት ዓመቱ በፒስካፕ ፊንድ በቂ በጀት ባለመኖሩ ለጣት አሻራ አማካሪ ኩባንያ (የኮፒ ካት ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር) ለሰጠው አገልግሎት የተከፈለ (ከመደበኛ በጀት ወጪ ተደርጎ) እና በመደበኛ በጀት እንዲሸፈን የሚደረግ መሆኑን፣
- ለአዲስ አበባ መስተዳደር በ10 ክፍለ ከተሞች ላሉ ኃላፊዎች የተከፈለ ደመወዝ ብር 1,372,280.91 ሲሆን ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር የበጀት ጥያቄ ቀርቦ ያልተፈቀደ በመሆኑ በቀጣይ ለአ.አ መስተዳድር ፋይናንስ ቢሮ በማቅረብ የሚፈቀድበት ሁኔታ በማመቻቸት እንደሚወራረድ፣
- ቀሪዎቹ ሌሎች የቅድሚያ ክፍያዎች በቀጣይ ተጣርተው እርምጃ የሚወሰድባቸው መሆኑን፣

የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

ባለስልጣኑ በጀት ሳይኖረው ይህን ያህል ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ ማድረጉ በኛ በኩል ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

6. ንብረት አስተዳደርን በተመለከተ ተሸርከርካሪዎችን በተመለከተ ግኝት

በመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 9 መሰረት የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢው ጥገናና እንክብካቤ የሚደረግለት መሆኑንና ሊወገዱ የሚገባቸው ንብረቶችም መወገዳቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በዋና መ/ቤት ፤

- ለረጅም ጊዜ አገልግሎት መስጠት ያቆሙ 10 ሞተር ሳይክሎች ያሉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 6 የሚሆኑት ሞተር ሳይክሎች አዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የሚገኙ መሆኑ እና የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ/ የሌላቸው መሆኑ፤

- 2 ተሽከርካሪዎች ያለአግልግሎት ለረጅም ጊዜ የቆሙ መኖራቸው እና አንደኛው (ሰሌዳ ቁ. 4-14314 የሆነው) ተሽከርካሪ ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት ለብዙ ጊዜ የቆመ እና የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ ሊብሬ/ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

የመንግስት ንብረት ሳይጠገን ወይም ሳይወገድ በቆየ ቁጥር ለበለጠ እርጅናና ብልሽት ሊጋለጥ ይችላል፡፡ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሌብሬ/ አለመኖር በስም ማዛወርና በሌሎች ሂደቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል::

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት በወቅቱ ጥገና ተከናውኖላቸው ለአገልግሎት እንዲበቁ፣ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የማይችሉት ደግሞ በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሰረት እንዲወገዱ ሊደረግ የሚገባ ሲሆን የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ/ የሌላቸውን በተመለከተ ሊብሬ እንዲኖራቸው ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ አስተያየት</u>

በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚገኙትን ተሽከርካሪዎች በማሰባሰብ ለመንግስት ንብረት ማስወገድ ኤጀንሲ በማስተላለፍ እንዲወገዱ እንደሚያደርጉና የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ/ያልተገኘላቸውን ሞተር ሳይክሎች በተመለከተ ቅ/ጽቤቶች በአስቸኳይ እንዲልኩ የተገለፀላቸው መሆኑንና ተሽከርካሪውን በተመለከተ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደበተሩ /ሊብሬው/ ከመንገድ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ጋር በመነጋገር ተለዋጭ ሊብሬ የሚገኝበት ሁኔታ ይመቻቻል በማለት ገልጸዋል::

7. <u>የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫን በተመለከተ</u>

7.1 <u>የ2004 በጀት ዓመት በቅርንጫፍ መ/ቤቶች ሂሳብ መግለጫ የታየው ጠቅላላ ሂሳብ ከተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ጋር እኩል አለመሆን፣</u>

<u>ግኝት</u>

በ2004 በጀት ዓመት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያሳወቀው የተጠቃለለ ሂሳብ፤ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች

ባቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት የተዘጋጀ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተላከው የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ

- በተለያዩ የገቢ ሂሳብ መደቦች በመብለጥ ብር 29,511,446.64 በማነስ ብር 29,598,569.16 ፣
- በተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች በማነስ ብር 69.09 በመብለጥ ብር 3,934,945.66፣
- በተለያዩ የተሰብሳቢ ሂሳብ መደቦች በመብለጥ ብር 24,824,963.78፣
- በተለያየ የተከፋይ ሂሳብ መደቦች በማነስ ብር 469,444.33 በመብለጥ ብር 24,869,819.00 ፣
- በተለያየ የዝውውር የሂሳብ መደቦች በዴቢት ብር 11,395,312,138.59 በማነስ ብር 11,832,200,790.79 በመብለጥ እንዲሁም በክሬዲት ብር 23,697,835.45 በማነስ ብር 302,511,594.40 በመብለጥ ፣
- የጥሬ ገንዘብ በ4101 ብር 579,562.50 በመብለጥ እና በ4103 ሂሳብ መደቦች በመብለጥ ብር 219,107,867.96

ታይቷል፡፡

<u>ስጋት</u>

ዋናው መ/ቤት ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ያቀረበው የተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን የተቋሙን የሂሳብ እንቅስቃሴ ላያሳይ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

የባለስልጣን መ/ቤቱ ከየቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና በዋናው መ/ቤት በቀረበው የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት ትክክለኛ የሂሳብ መደብ በሚያሳይ መልኩ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

<u>የስራ አመራሩ አስተያየት</u>

- በወጪ የተመለከተው ልዩነት ባንኮች በየቀኑ ለገ/ሚ/ር ፈሰስ እንዲያደርጉ በተሰጣቸው ቋሚ ትእዛዝ መሰረት ከሚልኩት ገንዘብ ላይ የአገልግሎት ክፍያቸውን ቀንሰው በማስቀረታቸው ምክንያት የተከሰተ ልዩነት መሆኑን፣
- ከዝውውር ሂሳብ ውስጥ ብር 242,060,065.52 በተመለከተ ከገ/ሚ/ር ጋር በነበረው የሂሳብ አለመጣጣም ምክንያት ከባንክ ቤቶች ጋር በተደረገው የማጣራት ስራ ባንክ ቤቶቹ በጀመሩት ኮር ባንኪንግ መሰረት የቅ/ጽ

ቤቶቹን አካውንት ሳያስነኩ ወጪ አድርገው ለገ/ሚ/ር የላኩትና በዋናው መስሪያቤት በኩል ሂሳቡን ለመዝጋት ሲባል ገ/ሚ/ር ገቢ ሆኖ የተገኘውን የገንዘብ መጠን ከ4009 ላይ በመጨመርና ከ4103 ላይ በመቀነስ የተመዘገበና ቅ/ጽ/ቤቶቹ እንዲመዘግቧቸው ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑን፣

የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

ለማንኛውም የሂሳብ ማስተካከያ ወይም ምዝገባ ተገቢ የሆነ ማስረጃ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን ሂሳቡን ለመዝጋት ሲባል ተብሎ የተደረገው ምዝገባ በኛ በኩል ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በተጨማሪም ቅ/ጽ/ቤቶች ሂሳባቸውን እንዲያስተካክሉ ስምምነት ተደርሷል ስለተባለው ሁኔታም ቅ/ጽ/ቤቶች ሂሳባቸው አስተካክለው ስለመላካቸው ማስረጃው ለኦዲት ባለመቅረቡ ትክክል ነው ብሎ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

7.2 የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት የባንክ ሂሳብ (ሂሳብ መደብ 4103-2) የመጨረሻ ሚዛን በብር 38,768,393.79 ያልተለመደ ሚዛን (ክሬዲት) የሚያሳይ መሆኑ

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 (2ለ) መሰረት እያንዳንዱ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ ለመሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የባንክ ሂሳብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበት ዴቢት ሚዛን ቢሆንም ሰኔ 30/2004 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት በባንክ ሂሳብ ቁጥር 551 ላይ የባንክ ሂሳብ (ሂሳብ መደብ 4103-2) በብር 38,768,393.79 ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑንና ይህም ሂሳብ በተጠቃለለው ሂሳብ ላይ መካተቱ ታውቋል፡፡

ስጋት

ሒሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ከላይ የተገለጸው ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ያልጠበቀበት ሁኔታ ሊጣራና አስፈላጊው ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ሒሳቡ ከመዘጋቱ በፊት ሁሉም የሂሳብ እንቅስቃሴ የተመዘገበ

ለመሆኑና የባንክ አካውንቱ ውስጥ ገቢና ወጪ የሆነ ሂሳብ ለመኖሩ ከባንኮች ጋር ወቅታዊ ግንኙነት በማድረግ ሂሳቡን በአግባቡ መቆጣጠር እንደሚያስፈልግ ለስራ አመራሩ አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

ለ2004 በጀት አመት በሪኮንሲሌሽን ላይ የሚታዩትን ሌጀራቸው የማያውቃቸውን ሂሳቦች ለቅመው ለባንክ የገቢ አድቫይሶች የጠየቁ መሆኑንና በቀጣይም ከባንክ ምላሽ እንደመጣ አስፈላጊው ማስተካከያ የሚደረግ መሆኑን ቅ/ጽ/ቤቱ የገለጸ ሲሆን በተጨማሪም የማስታረቅ ስራው ተጀምሮ የካቲት 2004 መድረሱን የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ደብዳቤ ገልጸዋል፡፡

7.3 ለዋስትና ሂሳብ ሪፖርት የማይዘጋጅ መሆኑ

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 6 (2ለ እና ሐ) መሰረት በሂሳብ ሌጀሮች ላይ በፋይናንስ ምንጫቸው የተመዘገቡ ሂሳቦች ሚዛንን በመውሰድ ወርሀዊና አመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶች ለየፋይናንስ ምንጩ መዘጋጀት እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚህ መሰረት ወርሃዊና አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ለየፋይናንስ ምንጩ የሚዘጋጅ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል ለዋስትና ሂሳብ (Deposit Account) ሪፖርት የማይዘጋጅለትና ለዋናው መስሪያ ቤትም ሪፖርት የማይደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስጋት

ሒሳቡን በትክክል ለመቆጣጠር የማይቻል ከመሆኑም በላይ የዋስትና ሂሳብን በተመለከተ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን የበጀት አመቱን እንቅስቃሴ ማወቅ አይቻልም፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በመመሪያው መሰረት ለዋስትና ሂሳብ ወርሃዊና ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ሊዘጋጅለትና ለዋናው መ/ቤትም መላክ እንዳለበትና በተጠቃለለው ሂሳብ ላይ መካተት እንዳለበት ለስራ አመራሩ አስተያታችንን ሰጥተናል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

ወርሀዊ የባንክ ማስታረቂያ ስራ የተጀመረ ሲሆን በቀረበው አስተያየት መሰረት በየወሩ ሪፖርቱ ለዋናው መስሪያ ቤት የሚቀርብ ይሆናል በማለት የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

7.4 ብር 112,870.20 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የሚታይ መሆኑ

ግኝት

በባለስልጣን ዋና መስሪያ ቤቱ በኩል በ2004 በጀት ዓመት በሂሳብ መግለጫ ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4202 ብር 112,870.20 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት የሚታይ ሲሆን ከዚህም ጉድለት ውስጥ ብር 28,258.85 በ2004 በጀት ዓመት የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

ሁኔታው ገንዘብ ለማጉደል የሚያስችል ሁኔታ መኖሩን ከመጠቆሙም በላይ በወቅቱ እርምጃ አለመወሰዱ ደግሞ ሌሎች ጉድለቶች እንዲፈጸሙ ሊገፋፋ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በጉድለት የሚታየው የመንግስት ገንዘብ በአስቸኳይ ገንዘቡን ካጎደሉ ሠራተኞች እንዲተካ፣ገንዘቡን ያጎደሉ ሠራተኞች በህግ እንዲጠየቁ እና ወደፊት ተመሳሳይ ጉድለት እንዳይደርስ ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

ብር 21,996.06 አስመልክቶ በየወሩ ብር 751.45 እየተሰበሰበ መሆኑን ቀሪውን ሂሳብ በተመለከተ አጣርተው እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

7.5 የተጣራ ሀብት (Equity account) የመጨረሻ ሚዛንን በተመለከተ

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6(2ለ) መሰረት በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበት ሚዛን ክሬዲት መሆኑ ይታወቃል፡፡

ነገር ግን ሰኔ 30/2004 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ፡-

- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል የመደበኛ ሂሳብ የተጣራ ሀብት

  በብር 254,406.97

  እንዲሁም በአገር ዉስጥ ገቢ ሂሳብ በኩል

  (ባንክ ሂሳብ ቁጥር 4005/4164) ብር 23,712,153.76
- ሞያሌቅ/ጽ/ቤት 18,072.15
- ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት 816,547.49
- ሁመራ ቅ/ጽ/ቤት 2,632.60
- ሞጆ ቅ/ጽ/ቤት 428,768.87
- ጅማ ቅ/ጽ/ቤት 229,708.97

በድምሩ ብር 25,462,290.80 በሂሳብ መደብ 5601 ባልተለመደ ሚዛን (ዴቢት) ማሳየቱና ይህም ሂሳብ በተጠቃለለ ሂሳብ ላይ መካተቱ ታውቋል፡፡

ስጋት

የቅርንጫፍ መ/ቤቶች የአመዘጋገብ ስህተት ሊሆን ከመቻሉም በላይ የመ/ቤቱን ትክክለኛ የሂሳብ ሪፖርት ላያሳይ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የቅርንጫፍ መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛ የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ሊያሳይ ይገባል፡፡ በመሆኑም ሁኔታው ተጣርቶ ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

ችግር ያለባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በማጥራት ላይ ሲሆኑ አንዳንዶቹ በ2005 በጀት ዓመት ወደ ተለመደ ሂሳብ ሚዛን መምጣታቸውን የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

7.6 የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያን በተመለከተ

ግኝት

በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 8/መ እና 9 መሰረት በሂሳብ ማመዛዘኛ

ሪፖሪት ላይ የሚታየው የባንክ ሂሳብ እና የባንክ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነት በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በማዘጋጀት መረጋገጥ እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚህ መሰረት በትክክል የሚሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል የዋስትና ሂሳብ (Deposit Account) ላይ:-

- በመንገድ ላይ ያለ ገቢ /በባንክ በገቢነት ያልታወቀ ገቢ/ ከ/March 2009-Jun2011/ ብር 18,736,997.60 መገኘቱ
- በባንክ ያልተመዘገበ ወጪ /Jun2008-Feb28/2012/ ብር 535,948.56 መገኘቱ
- ባንክ በገቢነት የመዘገበው መዝገብ ግን በገቢነት ያልመዘገበው ገቢ ከ July 28/2008- May 2/2012 ብር 38,728.38 እንዲሁም ከ/Jan 20/2009 - Jun 2011 ብር 21,006,727.83 መገኘቱ
- ባንክ የቀነሰው ነገር ግን በሌጀር ያልተቀነሰ /Aug 02/2010-Decem 7/2010 ድረስ ብር 3,578,281.20 የተገኘ ሲሆን እነዚህ የተንጠለጠሉት ሂሳቦች የቆይታ ግዜአቸው ከ3-4 አመት የሆናቸው በመሆኑ በባንኩ ያለው ባላንስም ሆነ የባንክ ሌጀር/4103/ ባላንስ ትክክለኛውን መረጃ ያሳያል ማለት አያስችልም::

<u>ስጋት</u>

ትክክለኛውን የቅ/ጽ/ቤቱን እንቅስቃሴ ማወቅ አይቻልም፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የተንጠለጠሉት ሂሳቦች ማጣራት ተደርጎበት ማስተካከያ ሊደረግበት እንደሚገባ አስተያየታችንን ሰጥተናል ፡፡

<u>የሥራ አመራሩ አስተያየት</u>

ችግሩ ከአንድ እስከ አራት ዓመት ሲንከባለል የመጡ ሂሳቦች በመሆናቸው በቀጣይ አጣርተን ትክክለኛውን ሚዛን እንዲያሳይ የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡የማጥራት ስራ መጀመሩንም የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

8. <u>ልዩ ልዩ</u>

8.1 <u>በበጀት አመቱ በተለያየ ምክንያት በስህተት ተሰብስቦ ነገር ግን ለባለመብቱ ተመላሽ ሲደረግ ከገቢ ሂሳቡ ላይ ተቀናሽ የማይደረግ መሆኑ</u>

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 66 መሠረት በእቃዎች አያያዝ፣ በታሪፍ አመዳደብ፣ በዋጋ አተማመን ወይም በሌላ የሂሣብ አሠራር ስህተት ምክንያት በብልጫ የተከፈለ የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሲቀርብ በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ በስድስት ወራት ውስጥ ለከፋዩ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱም ሆነ በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በበጀት አመቱ በተለያየ ምክንያት በስህተት ተሰብስቦና በገቢም ተመዝግቦ ነገር ግን ለባለመብቱ ተመላሽ ቢደረግም ማስተካከያ ሳይደረግበት በዘመኑ የተሰበሰበው ትክክለኛ ገቢ ጋር ተዳምሮ እየተመዘገበ ሪፖርት እንደሚደረግ ታውቋል፡፡

ስጋት

የሚዘጋጀዉ ሂሳብ መግለጫ ትክክለኛዉን ሁኔታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የበጀት አመቱ ተመላሽ ሂሣብ ትክክለኛውን ሁኔታ እንዲያሳይ በገቢ የተመዘገበው ሂሣብ ማስተካከያ እንዲደረግበት ማድረግ ችግሩን የሚያስወግድ በመሆኑ አሠራሩ በዚህ መልኩ ሊስተካከል ይገባል፡፡

8.2 ለኦዲት ያልቀረቡና በፋይላቸው ውስጥ የተሟላ መረጃ የሌለ መሆኑን በተመለከተ

ስለፌደራል መንግስት አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀፅ 70 መሰረት ማናቸዉም የመንግስት መስሪያ ቤት ለመስሪያ ቤቱ ወይም ለዉጪ ኦዲተሮች ለማናቸዉም ጉዳይ በመረጃነት የሚያስፈልጉትን የፋይናንስ መረጃዎችና መዛግብት ቢያንስ ለአስር አመት ማቆየት እንዳለበት ያዛል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ:-

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል 67 ዲክላራሲዮኖች ለኦዲት ተጠይቀው ባለመቅረባቸው፣.
- በምስራቅና ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤቶች በኩል በተወሰኑ ግብር ከፋይ ፋይሎች ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች በፋይላቸው ውስጥ ባለመገኘቱ ፣

- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዲክላራሲዮን ቁጥር C-827/2011 ለተመዘገበው እቃ ከዲክላራሲዮኑ ጋር በአባሪነት የዋጋ ሰነዱ የሌለ በመሆኑ

የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ብር ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት

በሰነዶቹ የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አይቻልም።

የማሻሻያ ሃሳብ

የግብር ከፋዩ ፋይሎች በቀላሉ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ በአግባቡ ተደራጅተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል። ለኦዲት ያልቀረቡ ዲክላራሲዮኖችንም ሆነ የተሟላ መረጃ ባልቀረበባቸው ፋይሎችን በተመለከተ ተፈልገው የሂሳቡ ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲት ተረጋግጦ ውጤቱ ሊገለጽልን እንደሚገባ አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ 15 ዲክላራሲዮኖች ተገኝተው በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲተሮች እየተመረመሩ መሆኑ፣ በሁለቱ ዲክላራሲዮኖች ብር 204,987.98 ልዩነት በመገኘቱ የማስከፈል ሂደት መጀመሩን፣ 32ቱ የግል መገልገያ የተስተናገደባቸው መሆኑን 4ቱ የጉምሩክ ስነስርአት ያልተፈጸመባቸው መሆኑን፣ አንድ ግን እስካሁን አለመገኘቱን፣
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት መረጃውን ከንብ ባንክ ለማግኘት ደብዳቤ ተጽፎ ክትትል እየተደረገ የሚገኝ መሆኑን፣

የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በቁ.1.0/465/16 ከዋናው መስሪያ ቤት በተጻፈ ድብዳቤ ገልጸዋል፡፡

8.3 የገንዘብ ትልልፍ ሂደትን በተመለከተ

ግኝት

በገንዘብ ትልልፍ መመሪያ ቁጥር 22/2001 አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት እያንዳንዱ የባለሥልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት የሰበሰበውን የተጨማሪ ዕሴት ታክስና የቅድመ ታክስ ክፍያን ወሩ ባለቀ ከ10/አስር/ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወደ ባለሥልጣኑ ዋናው መ/ቤት የአደራ ሂሳብ/አካውንት መተላለፍ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር

- በምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 41,589,986.08 እንዲሁም

- በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ብር 37,163,801.33 በ2004 በጀት አመት የሰበሰቡትን የክልል መንግሥታትና የከተማ አስተዳደሮች የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ቅድመ ግብር ድርሻ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ወደ ዋናው መ/ቤት የአደራ ሂሣብ /አካውንት መመሪያው በሚያዘው መሠረት በወቅቱ ያልተላለፈ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

የክልል መንግስታትና መስተዳድሮች ገንዘቡ በወቅቱ ካልተላከላቸው በእቅድ የያዙዋቸው ስራዎች ሊስተጓጎሉ ይችላሉ፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

መንግስት ወጪን ለመሸፈን በዋናነት የሚጠቀመው ከአገር ውስጥ በሚሰበስበው ገቢ በመሆኑ፣ በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳ ወደ ባለሥልጣኑ ሒሳብ በማስተላለፍ የግብር አሰባሰብ እና ክትትል የሥራ ሂደትም አሰራሩ ሊቀላጠፍ የሚችልበትን ስልት በመቀየስ የክልሎችን ገቢ በወቅቱ መለየት እና በመመሪያ መሰረት ገንዘቡን ለዋናው መ/ቤት የአደራ ሂሳብ አካውንት መተላለፍ እንዳለበት አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

የሥራ አመራሩ አስተያየት

- ምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ በወቅቱ በተፈጠረ የስራ ጫና ስለነበረ በአሁኑ ወቅት ችግሩ የተቀረፈ መሆኑን በመግለጽ ዊዝሆልዲንግ ታክስን በተመለከተ ግን ችግሩ አሁንም ያለ ስለሆነ የሚቀበሉት መሆኑን ገልጸዋል፡፡.
- በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት ግብር ከፋዮች በአብዛኛው Bank Transfer የሚጠቀሙ በመሆኑና በባንክ የገባው ገንዘብ የግብር አይነቱን ለማወቅ መረጃው በወቅቱ ስለማይመጣ ሪፖርቶቹ የዘገዩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

8.4 በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ጫት በመኪና (land transport) ወደ ጅቡቲ የሚላክ ስለመሆኑ፣

በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል ጫት በመኪና (land transport) ወደ ጅቡቲ የሚላክ ቢሆንም ሲስተም ላይ ግን በፕሌን/አውሮፕላን እንደሚላክ ተደርጎ የሚመዘገብ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

አሰራሩ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ያለዉን ትክክለኛ ሁኔታ የማያሳይ ከመሆኑም በላይ የሲስተም መረጃን የሚጠቀሙ ሌሎች የተለያዩ አካላትን የተሳሳተ መረጃ እንዲወስዱ የሚያደርግ ይሆናል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ወደ ጅቡቲ የሚላክ ጫት ትክክለኛ በተጓጓዘበት የትራንስፖርት አይነት(በመኪና ወይም በአውሮፕላን/ፕሌን) ሲስተም ላይ ተመዝግቦ የሲስተም መረጃ ትክክለኛዉን ሁኔታ መግለጽ ስላለበት አሰራሩ በዚሁ ሁኔታ መስተካከል ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት

ወደ ጅቡቲ በአዉሮፕላን ይጓጓዝ የነበረዉ ጫት ወደ መኪና ማጓጓዣ ሊቀየር የቻለዉ አዉሮፕላን በድንገት በመቋረጡ በወቅቱ የበላይ አካላት አዉቀዉት ኤክስፖርቱ እንዳይቋረጥ ጊዜያዊ መፍትሄ ለመስጠት ሲባል በሲስተም ተመዝግቦ በመንገድ ወረቀት (T1) ላይ ደግሞ በመኪና እንደሚጓጓዝ ተመዝግቦ ሲሰራ የቆየ መሆኑን በመግለጽ ለወደፊቱ በተሰጠዉ አስተያየት መሰረት ጫቱ በትክክል በተጓጓዘበት የትራንስፖርት አይነት ሲስተም ላይ እየተመዘገበ እንዲሰራ ቢደረግ በመቅረጫ ጣቢያዉ የሚደገፍ ቢሆንም የአዉሮፕላን ማጓጓዣ እስካልቀረበ ድረስ አመዘጋገቡን ለመቀየር ከመቅረጫ ጣቢያዉ አቅም በላይ በመሆኑ ለማስተካከል ስለማይቻል የበላይ ሀላፊዎች ዉሳኔን የሚጠይቅ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት

የአዉሮፕላን ማጓጓዣ እስካልቀረበ ድረስ አመዘጋገቡን ለመቀየር ከመቅረጫ ጣቢያዉ አቅም በላይ እንደሆነ በመቅረጫ ጣቢያዉ የተሰጠዉ ምላሽ በእኛ አስተያየት አሳማኝ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እቃዉ በመኪና እየተጓጓዘ ሲስተም ላም በመኪና እንደተጓጓዘ መመዝገብ ከአዉሮፕላን መቅረብ አለመቅረብ ጋር የሚያገናኘዉ ነገር ስለሌለ የተሰጠዉ ምላሽ አሳማኝ ሆኖ አላገኘነዉም፡፡

1. <u>እቃዎች በትክክለኛው የታሪፍቁጥር (H.S.code) ባለመመደባቸው ተጨማሪ ቀሪ ሂሳብ የተገኘባቸው ዲክላራሲዮኖች ዝርዝር</u> (<u>አባሪ</u>-1)

ዲ/ዮን ቁጥር	በተፈጠረው ስህተት ምክንያት ያልተሰበሰበ የቀረጥ መጠን(ብር)	ቀሪ ሂሳቡ የተገኘበት ቅ/ጽ/ቤት
c-2870/12	753.33	አዳማ
c-3905/12	70,272.99	አዳማ
c-9387/11	8,652.02	አዳማ
c-9955/11	907.95	አዳማ
c-7984/11	131.52	አዳማ
c-2731/12	2,805.53	አዳማ
c-3517/12	4,008.16	አዳማ
c-2155/12	438.66	አዳማ
c-44/12	10,717.31	አዳማ
c-3116/12	14,560.09	አዳማ
c-10120/11	21,886.66	አዳማ
c-10807/11	527.94	አዳማ
c-1249/12	1682.81	አዳማ
c-1238/12	10662.81	አዳማ
c-1419/12	3,087.66	አዳማ
c-9529/11	3,007.71	አዳማ
C-482/2012	8,819.19	ድሬዳዋ
c-514/12	3,933.38	ድሬዳዋ
C-425/12	7,739.10	ድሬዳዋ
c-110/12	51,001.03	ድሬዳዋ
C-293/12	7,347	ድሬዳዋ
C-200/12	4,401.45	ድሬዳዋ
C-174/2012	3,069.63	ድሬዳዋ
C-239/12	11,718.5	ድሬዳዋ
C-653/2012	4,304.83	ድሬዳዋ
c-38795/11	2,471.25	ኤርፖርት
c-51747/11	806.57	ኤርፖርት
C-2730/11	323,234.91	አዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ
ጠ/ድምር	582,949.99	

2. <u>ለቀረጥ ማስከፈያነት ትክክለኛው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ (CIF value) ያልተወሰደባቸው ዲክላራሲዎኖች ዝርዝር</u>-------- (<u>አባሪ-2</u>)

ዲ/ዮን ቁጥር	በተፈጠረው ስህተት ምክንያት ያልተሰበሰበ የቀረጥ መጠን (ብር)	ቀሪ ሂሳቡ የተገኘበት ቅ/ጽ/ቤት
c-145/12	22,537.79	ድሬዳዋ
c-393/12	70,967	ድሬዳዋ
c-224/12	54,325.85	ድሬዳዋ
c-86/12	4,037.23	ድሬዳዋ
c-42731/11	57,599.87	አዲስ አበባ ኤርፖርት
c-24090/12	68,738.10	አዲስ አበባ ኤርፖርት
c-7123/12	7,085,422.51	አዲስ አበባ ኤርፖርት
c-75977/11	887.32	አዲስ አበባ ኤርፖርት
c-47937/11	574.29	አዲስ አበባ ኤርፖርት
c-40792/11	7,232.21	አዲስ አበባ ኤርፖርት
c-48147/11	1,679	አዲስ አበባ ኤርፖርት
c-54855/11	101,395.63	አዲስ አበባ ኤርፖርት
c-641/12	910.87	አዲስ አበባ ኤርፖርት
c-59007/11	370.76	አዲስ አበባ ኤርፖርት
ጠ/ድምር	<u>7,476,678.43</u>	

3.በጊዜያዊነት ተስተናግደው የጊዜ ገደቡ የተጠናቀቀባቸው ዲክላራሲዎኖች ዝርዝር (አባሪ-3)

ዲ/ዮን ቁጥር	ቦንድ ቁጥር	ዋስትና የሰጠው መ/ቤት ስም	የዋስትና ቀን	የዋስትናው ጊዜ ገደብ የሚያልቅበት ቀን	የዋስትናው መጠን (ብር)	መግለጫ
c-512/08	p/01/1706/2008/170/10	Africa insurance	1-Feb-08	27-nov-10	391,540.88	
c-4418/07	p/01/1706/2007/170/135	Africa insurance	21-oct-07	21-apr-10	2,368,887.22	
c-292/04	NLBB/CUB/0045/1004	Nile Insurance	13-oct-04	13-dec-04	61,048.51	
c-672/05	NLBB/CUB/0050/0105	Nile Insurance	11-jan-05	11-apr-05	51,454.68	
c-673/05	NLBB/CUB/0047/0105	Nile Insurance	11-jan-05	11-apr-05	1,879.65	
c-676/05	NLBB/CUB/0048/0105	Nile Insurance	11-jan-05	11-apr-05	44,315.95	
c-731/05	NLBB/CUB/0052/0105	Nile Insurance	24-jan-05	24-apr-05	49,051.57	
c-96/04	NLBB/CUB/0035/0804	Nile Insurance	5-aug-04	5-aug-06	113,989.43	
c-3338/06	P/09/070/08/8011/06/158	Nile Insurance	1-dec-06	1-mar-07	150,000.00	
c-19/07	P/01/070/08/8011/06/184	Nile Insurance	28-dec-07	28-dec-08	87,500.00	
c-7/07	P/01/070/08/8011/07/2	Nile Insurance	2-jan-07	2-jan-09	330,292.19	
c-9/07	P/01/070/08/8011/07/3	Nile Insurance	2-jan-07	2-jan-09	331,085.26	
c-874/07	P/09/070/08/8011/07/68	Nile Insurance	8-mar-07	8-aug-09	435,200.00	
c-2973/08	AIC/B1/CGBD/0336/2008	Awash	12-jun-08	11-dec-08	77,132.18	
c-556/04	UCO/IN/CN/120/1/0576/2004	Nyala Insurance	7-dec-04	7-apr-08	73,044.93	
c-4455/07	P/01/1706/2007/170/137	Africa insurance	22-oct-07	22-oct-11	139,706.23	
c-32/08	EN/4/BOCG/7637/08	Ethiopian insurance corpo.	2-jan-08	9-sep-11	1,467,011.35	
c-3989/09	04/BOCG/00040/09	Lion Insurance	22-aug-09	21-nov-11	1,149,517.29	
c-3967/08	P/03/070/08/8011/08/213	Lion Insurance	17-sep-08	20-dec-11	197,271.92	
c-3820/10	01/BOCG/00436/10	Ilon insurance	18-jun-10	17-apr-12	165,855.55	
c-2656/11	01/bocg/00695/11	Ilon insurance	22-03-2011	21-mar-12	163,614.48	
c-7295/10	01/bocg/00509/10	Ilon insurance	22-10-10	21-jan-11	595,945.93	
c-2182/07	B-96-02262	United insurance	19-jun-07	10-jan-10	9,387,596.16	
c-2164/06	B-96-01344	United insurance	17-aug-06	10-jan-10	265,796.48	
c-3213/06	B-96-01430	United insurance	24-nov-06	10-jan-10	6,571,722.76	
c-3517/08	P/03/070/08/8011/08/194	Nile Insurance	14-aug-08	3-feb-10	703,055.00	
c-4069/08	P/03/070/08/8011/08/218	Nile Insurance	22-sep-08	3-feb-10	107,067.27	
ጠ/ድምር					25,480,582.87	

3. በ2004 በጀት አመት በተፈቀደላቸው ኮታ መጠን የጫት ላኪ ማህበራት ጫት ወደ ጅቡቲ ለሚልከው ድርጅት ያልቀረበው የኮታ መጠን ዝርዝር -----------(አባሪ አራት)

የጫት ላኪ ማህበራት ስም	በአመት መላክ ያለባቸው የተጣራ ክብደት የኮታ መጠን (በኪሎ ግራም) (A)	በአመት የተላከው የተጣራ ክብደት መጠን (በኪሎ ግራም) (B)	በተፈቀደው ኮታ መጠን ያልተላከው የተጣራ ክብደት (በኪሎግራም) C=(A-B)	በኮታው መጠን ባለመላኩ አገሪቷ ያጣችው የውጪ ምንዛሬ መጠን D=($6/kg)*(C)	መግለጫ
የኢትዮጵያ የጫትና የእርሻ ውጤቶች ላኪ አ.ማ.	(850የቀን ኮታ* 30 ቀን* 8 ወር) +(4ቀን*850) +(26ቀን*980)+(980 የቀን ኮታ *30 ቀን*3ወር) +(6ቀን የጳጉሜ*850) =326180 ኪሎግራም	277726	48454	290,724 dollar	ከመጋቢት 4/2004 በኋላ የቀን ኮታው በ130ኪሎግራም ጨምሯል
ቢፍቱ ዲንሾ ኀ/የተ/የግ/ማ	(2070 የቀን ኮታ* 30ቀን*8ወር) + (4ቀን*2070)+(26ቀን*2347)+ (30ቀን*2347*3ወር)+(6ቀን የጳጉሜ*2070) =789752 ኪሎግራም	551527	238225	1,429,350 dollar	ከመጋቢት 4/2004 በኋላ የቀን ኮታው በ277 ኪሎግራም ጨምሯል
በርዋቆ የጫት ላኪዎች አ.ማ.	(1080 የቀን ኮታ*30ቀን*8ወር) +(4ቀን*1080) +(26ቀን*1220) +(3ወር*30ቀን*1220)+(6ቀን የጳጉሜ *1080) =411520 ኪሎግራም	378329	3391	199,146 dollar	ከመጋቢት 4/2004 በኋላ የቀን ኮታው በ140 ኪሎግራም ጨምሯል
ኩልምዬ ትሬዲንግ አ.ማ.	(680 የቀን ኮታ*30ቀን*8 ወር)+(4ቀን*680)+(26 ቀን*783)+ (3ወር*30ቀን*783)+(6 ቀን የጳጉሜ*680) =260,828 ኪሎግራም	254,415	6,413	38,478 dollar	ከመጋቢት 4/2004 በኋላ የቀን ኮታው በ103 ኪሎግራም ጨምሯል
ሁምበና ጨርጨር አ.ማ.	(520 የቀን ኮታ *30 ቀን*12 ወር) +(6ቀን የጳጉሜ *520) =190320 ኪሎግራም	0	190320	1,141,920 dollar	ከመጋቢት 4/2004 በኋላ የቀን ኮታው አልተጨመረለትም
ጠ/ድምር				3,099,618 dollar	

4. <u>በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያና በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ መካከል በታየ ጠቅላላ የሽያጭ ልዩነት ምክንያት ያልተሰበሰበ ግብርና ታክስ ዝርዝር</u>---- (አባሪ አምስት)

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር	የድርጅቱ ስም	ያልተሰበሰበው የታክስ አይነት	ያልተሰበሰበው ግብርና ታክስ መጠን	ልዩነቱ የታየበት ቅ/ጽ/ቤት	መግለጫ
0000011859	ባርጉባ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የ.ማህበር	ተ.እ.ታ	4,936.74	ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	
0004739544	ኤ.ቲ.ኤል ትሬዲንግኃ.የተ.የ. ማህበር	ተ.እ.ታ	361,142.40	ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	
0001600360	አለታ ላንደኮፌኃ.የተ.የ. ማህበር	የንግድ ትርፍ	6,520,498.86	ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	
0000010518	አልፎዝ ኃ.የተ.የ.ማህበር	ተ.እ.ታ	628,700.30 3,679,411.51	ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	
0000007365	ይርጋ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የ.ማህበር	ተ.እ.ታ	7,160,929.48	ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	
0000022829	አርባ ምንጭ ጨርቃጨርቅ አ.ማ	ንግድ ትርፍ	384,907.15	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0000669693	ህብር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ.የተ.የግ.ማ	ንግድ ትርፍ	1,213,154.00	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0003436817	ጋትስ አግሮ ኢንዱሰትሪ	ንግድ ትርፍ	1,852,120.75	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0000041706	ዳፍ ኃ/የተ/ የግ/ማ	ንግድ ትርፍ	224,662.77	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0000044575	ታምሬ እና ቤተሰቦቹ ኃ.የተ.የግ. ማህበር	ንግድ ትርፍ	16,415.19	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0016224217	ሙሉ ሶርሳ ተራራ ኃ.የተ.የግ. ማህበር	ንግድ ትርፍ	681,754.84	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር	የድርጅቱ ስም	ያልተሰበሰበው የታክስ አይነት	ያልተሰበሰበው ግብርና ታክስ መጠን	ልዩነቱ የታየበት ቅ/ጽ/ቤት	መግለጫ
0000041696	አተም ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ	ንግድ ትርፍ	780,391.84	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0000047201	ይረጋለም ኮንስትራክሽን	ንግድ ትርፍ	129,153.04	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0000027450	ወንዶ ንግድ ኩባንያ	ተ.እ.ታ	13,885,774.00	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0000793933	ቆንጋ ኮፊኃ.የተ.የግ. ማህበር	ተ.እ.ታ	3,404.51	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0000027435	አዋሳ ጨርቃ ጨርቅ አ.ማህበር	ተ.እ.ታ	3,680,393.93	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0000041642	ገላና ኃ.የተ.የግ. ማህበር	ንግድ ትርፍ	80,192.05	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0000041601	ኢዲዶ ተራመድ ኃ.የተ.የግ. ማህበር	ንግድ ትርፍ	85,285.45	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	
0003129619	ትሬድ ፖዝ ኢንተርናሽናል	ተ.እ.ታ	5,674,068.89	የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት	
0004837029	ኤም ደብሊው ኢንተርናሽናል	ተ.እ.ታ	8,372,178.32	የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት	
0000041974	ገላን ብረታብረት ኢንዱስትሪ	ተ.እ.ታ	2,147,185.02	የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት	
0000027422	ፒና ሆቴል	ንግድ ትርፍ	287,722.71	ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	በተጨማሪ የእርጅና ቅናሽ ወጪ በብር 549,151 ከፍ
ጠ/ድምር			<u>54,174,972.24</u>		

5. በታክስ ኦዲተሮች ተጠይቆ የሚሰበሰበው የግብር ውሳኔ በትክክለኛው የታክስ አይነትና የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበው ዝርዝር-------- (አባሪ ስድስት)

ቀን	የግብር ከፋይ ስም	የደረሰኝ ቁጥር (በማንዋል የተሰበሰበበት)	የግብር ውሳኔ ክፍያ የተፈጸመበት የግብር(ታክስ አይነት)				በጠቅላላ የተሰበሰበው የግብር መጠን	የተሰበሰበው ግብር (ታክስ) በሂሳብ መግለጫ ላይ በጥቅል የተመዘገበበት ታክስ አይነት
30/12/03	ናስ ፉድስ ድ/ጨ/ፋብሪካ	733363	vat	Excise	wht	Income tax	382,799.27	ሁሉም የቫት እንደሆነ በመቁጠር በቫት የተመዘገበ
29/01/04	ናስ ፉድስ ድ/ጨ/ፋብሪካ	733450	vat	Excise	wht	Income tax	379,254.04	ሁሉም የዊዝሆልዲንግ ታክስ እንደሆነ በመቁጠር በዊዝሆልዲንግ የተመዘገበ
30/6/04	ናስ ፉድስ ድ/ጨ/ፋብሪካ	734138	vat	Excise	wht	Income tax	361,527.89	ሁሉም የቫት እንደሆነ በመቁጠር በቫት የተመዘገበ
12/8/04	ናስ ፉድስ ድ/ጨ/ፋብሪካ	734309	vat	Income Tax	wht		1,500,000	ሁሉም የኤክሳይዝ ታክስ እንደሆነ በመቁጠር በኤክሳይዝ የተመዘገበ
30/3/04	ናስ ፉድስ ድ/ጨ/ፋብሪካ	733827	vat	Income Tax	wht	Excise	372,163.58	ሁሉም የቫት እንደሆነ በመቁጠር በቫት የተመዘገበ
ጠ/ድምር							2,995,744.78	

የፋይናንስና ኮሙዩኒኬሽን መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2004 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት ማጠቃለያ

የ2004 በጀት ዓመት በፋይናንስና ኮሚኒኬሽን ኦዲት መ/ቤቶች ስር የሚገኙ መ/ቤቶች ዓመታዊ ሪፖርትማጠቃለያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የፋይናንሻልና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም

በፋይናንስና ኮሚኒኬሽን ኦዲት መ/ቤቶች ዳይሬክቶሬት በ2004 በጀት ዓመት 30 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችን ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ አቅዶ የ30 መ/ቤቶችን ኦዲት አከናውኗል፡፡ ይህም 100% እንደተከናወነ ያሳያል፡፡ የኦዲቱ ሥራ የተከናወነው በ1 ዳይሬክቶሬትና በ3 የኦዲት ማናጀሮች ነው፡፡

ዳይሬክቶሬቱ በ2004 በጀት ዓመት በፌዴራል መ/ቤቶች ላይ በመደበኛ ኦዲት ያከናወነው የፋይናንስ ኦዲት የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብን ጨምሮ 30 የኦዲት ሪፖርቶችን ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች የላከ ሲሆን፣ ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባህርይ አንፃር ሲተነተኑ፣

- አልፎ አልፎ ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion) 15 መ/ቤቶች፣
- የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት (Adverse opinion) የተሰጠው 2 መ/ቤት እና
- አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Clean opinion) የተሰጠባቸው 13 መ/ቤቶች ሲሆኑ ዝርዝራቸው ከአባሪ-2 እስከ አባሪ-6 ቀርቧል ፡፡

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛነት አያያዝና አጠባበቅ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የውስጥ ኦዲተሮች ባደረጉት ምርመራ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,680.11 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና ክትትል መደረግ እንዳለበት ለመ/ቤቱ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታየባቸው መ/ቤቶች

የገንዘብ ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፣ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣በሰኔ 30 በተደረገው ቆጠራ እና በሂሳብ ሪፖርቱ መካከል በ2 መ/ቤቶች (መንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እና በቤተመንግስት አስተዳደር) በድምሩ ብር 9,854.27 በመብለጥ እንዲሁም በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ብር 121,463.64 የተቆጠረው በማነስ የታየ ሲሆን በ6 መ/ቤቶች ደግሞ የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ - 8 እና አባሪ 10 ተመልክቷል/

ከሚታዩት ዋናዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያየዝ ጉድለቶች፣

- የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከመዝገብ (ሌጀር) ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣
- የተሰበሰበውን ገንዘብ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ አለማድረግ፣
- በባንክ ሂሣብ ገቢ ለሆኑ ሂሣቦች የገቢ ደረሰኝ አለማዘጋጀትና አለመመዝገብ፣
- ከተፈቀደውም በላይ በሳጥን ማስቀመጥ፣

  የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከር፣ የሚሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ እንዲደረግ እንዲሁም በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከቆጠራው ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2. ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ

2.1 በየመ/ቤቶቹ የተገኘ ተሰብሳቢ ሂሣብ

ስለመንግስት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የስራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዥ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡ ይሁን

እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ12 መ/ቤቶች ብር 182,301,059.43 የሰነድ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -11 ተመልክቷል/

በመሆኑም ውዝፍ ሰነዱን በወቅቱ አለማወራረድ ለመንግስት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2 በተሰብሳብ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች

በሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 619,842.28 ገንዘቡ ወጪ ተደርጎ ለመሰጠቱ ማስረጃው ባለመቅረቡ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰብሳቢ ሂሳብ ለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ተጣርቶ አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግላቸው፤ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለመ/ቤቱ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3. የገቢ ሂሣብ በተመለከተ

3.1 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሰረት የመንግስት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 9,775,464.70 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሳብ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ ገቢን በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች የኢትዮጵያሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ከደንበኞቹ ለ17 ዓመታት ያልሰበሰበው ውዝፍ ገቢ ብር 6,168,994.78፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለ7 ዓመታት ያልተሰበሰበ ብር 3,564,840.80 እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሮድካስት ድርጅት ለ3 ዓመታት ሳይሰበሰብ የቆየ ብር 41,629.12 ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢው እርምጃ በመውሰድ የመንግስት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ለየመ/ቤቶቹ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.2 መሰብሰብ ከሚገባው በታች የተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳብ፤

ከማስታወቂያ የተሰበሰበው ገቢ መሰብሰብ በነበረበት ልክ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት መሰብሰብ የነበረበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 9,702.00 መሆን ሲገባው ብር 7,761.00 ብቻ በመሰብሰቡ ብር 1,941.00 በማሳነስ ተሰብስቦ ተገኝቷል፡፡ ሊሰበሰብ ከሚገባው በታች በመሰብሰቡ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያሣጣው ስለሚችል ያላግባብ ሣይሰበሰብ የቀረው ገንዘብ ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ ሊደረግ እንደሚገባና ለወደፊቱም ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.3 በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ውስጥ ብር 13,136,062.00 ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ያልተደረገ እና በፋይናንስ አዋጅ መሰረት ባልተፈቀደ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ገቢ የሚሰበሰብ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው የሚያዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይ ይሆናል፡፡ ይህም የመንግስት ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ትክክለኛውን የመንግስት ገቢ ላያሳይ ስለሚችል በአዋጁ መሰረት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ማድረግ እንዳለበት፤ የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኙ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባሳተመው ወይም እንዲታተም በፈቀደው ደረሰኝ መሰብሰብ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡

3.4 ከእቅድ በታች ስለተሰበሰበ የገቢ ሂሳብ

በበጀት ዓመቱ ይሰበሰባል ተብሎ በታቀደው ልክ ለመሰብሰቡ ሲጣራ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት ይሰበሰባል ተብሎ የታቀደው ብር 320,000,000.00 ሲሆን የተሰበሰበው ግን ብር 169,552,869.44 በመሆኑ የብር 150,447,130.56 (47%) ልዩነት ያለው መሆኑ ታውቋል፡፡ እቅዱን ለማስተካከል ተገቢው ጥረት አለመደረጉን ወይም እቅዱ የተጋነነ ሊሆን ስለሚችል ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት መስተካከል እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበቂ ማስረጃ የተደገፉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ6 መ/ቤቶች ብር 6,912,883.08 ማስረጃው ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሲሆን ከዚህ ሂሳብ ውስጥ ብር 2,943,103.08 በባንክ በኩል የተላከ ሲሆን ብር 3,969,780.00 ደግሞ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ለክልሎች ቅርስ እንክብካቤ የተላከና የማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ለመኪና ኪራይ ተከፍሎ የወጪ ማስረጃው ሳይቀርብ በቀጥታ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ- 21 ተመልከቱ) ተገቢውን ማስረጃ አለማቅረብ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

4.2 ያለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በተመለከተ፡-

የትርፍ ሰዓት ክፍያን አስመልክቶ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀፅ 93 ንኡስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ኤጀንሲው ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ/30/ጠ13/36/83 በተፃፈ ደብዳቤ የአፈፃፀም መመሪያያወጣና መመሪያውም ከ ሐምሌ 1 ቀን 2001ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል ማድረጉ እና ኤጀንሲው በቁጥር መ/30/ጠ/13/87/820 ጳጉሜ 5 ቀን 2001 በፃፈው ደብዳቤ መመሪያው ለጊዜው ተግባራዊ ሳይደረግ እንዲቆይ አግዶታል፡፡ ይሁን እንጂ ያለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያን አስመልክቶ ኦዲት ሲደረግ በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 345,361.96 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል:: (ዝርዝሩ በአባሪ- 23 ተመልክቷል)

በመሆኑም አፈፃፀሙ ስራዎች በመደበኛ የስራ ሰዓት እንዳይሰሩ የሚገፋፋና ያልተፈቀዱ ክፍያዎችን በመፈፀም መንግሥትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል በመመሪያው መሰረት መስራት ወይም የሚመለከተውን ክፍል ማስፈቀድ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.3 በትክክለኛው የወጪ ሂሳብ መደብ ሳይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች

ሂሳቦች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የሂሳብ አወቃቀር ሥረዓት /chart of account/ መሰረት በትክክለኛው የሂሳብ መደባቸውን ጠብቀው መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ5 መ/ቤቶች ብር 2,657,943.00 የወጪ ሂሳብ መደብ ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡

ዝርዝሩ በአባሪ- 28 የተመለከተ ሲሆን የሂሳብ መደብን ጠብቆ ያለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅእኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም ከበጀት በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱንም ያዛባል፡፡ በመሆኑም የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ትክክለኛ የሂሣብ መደቡን ጠብቆ መመዝገብ ያለበት ሲሆን ሂሣቡም በትክክል ስለመመዝገቡ የሚረጋገጥበት ሥርዓትም መዘርጋት አለበት፡፡

4.4 የግዢ አዋጅ ፣ ደንብና መመሪያን ያልተከተለ ግዥ

በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት የተገዛ የተፈፀመ ግዥ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ በ4 መስሪያ ቤቶች በብር 3,603,831.50 የመንግስት ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ- 22 ተመልክቷል/

በመሆኑም ከመመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል ለወደፊቱ መመሪያው ተፈፃሚ መሆን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.5 በብልጫ የተከፈለ ወጪ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡ በድሬድዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,200.00 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡ በመሆኑም በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም ተገቢውን ማስተካከያ ሊደረግለት እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.6 ውል ሳይፈፀም የተፈፀሙ ግዢዎች

የዕቃ ወይም የአገልግሎት ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት ተገቢው ውል የተገባላቸው ወይም ውላቸው የታደሰ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በድምሩ ብር 1,452,045.84 ከአቅራቢዎች ጋር የውል ስምምነት ሳይፈጸም ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት አገልግሎቱን ከሚሰጠው

አካል ጋር የተዋዋለበት ውል ሳይኖረው የብር 1,032,298.43 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ ሲሆን ብር 411,247.41 ደግሞ የመጀመሪውን ውል ባለመቅረቡ ውሉ ጊዜውን ጠብቆ መታደሱን እና ሌላ ጨረታ መውጣት ያለበት መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ ብር 8,500.00 ለመኪና ክራይ ክፍያ ውል የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ለወደፊቱ ከአቅራቢዎች ጋር የውል ስምምነት እንዲፈጸም እና በውል ስምምነት ላይ ላልተገለጹ ወጪዎች ደግሞ ክፍያ እንዳይፈጸም ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንደሚያስፈልግ አሳስበናል።

4.7 ግብር ያልተቀነሰበት የቤት አበል ክፍያ

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 13 እንዲሁም በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀፅ 3 ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም የተቀጣሪ ክፍያ (ጥቅማ ጥቅም) በወር ደመወዝ ላይ እየተደመረ ግብር እንዲከፈል ይደነግጋል፡፡ይሁን እንጂ በ2004 በጀት ዓመት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት ለምክር ቤት አባላት ከሚከፍለው የቤት አበል ላይ ተገቢውን ግብር እንደማይቀንስ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም አዋጅና መመሪያን ተግባራዊ አለማድረግ በህግ ሊያስጠይቅ ከመቻሉም በላይ ሁኔታው በመንግስት ገቢ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ለወደፊቱ ጽ/ቤቱ በገቢ ግብር አዋጁ እና ደንቡ መሰረት ሊሰበሰብ የሚገባውን የመንግስት የገቢ ግብር ከባለጥቅሞች ላይ መሰብሰብ እንደሚኖርበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.8 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ አላግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በቀን 17/03/1997 በቁጥር ጠ80-አጠ3/01/02 በተጻፈ የምክር ቤቱ መመሪያ በሚኒስትሮች ም/ቤት ስለፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በተመለከተ ጥቅምት 19 ቀን 1997 ባካሄደው 118 መደበኛ ስብሰባ ማሻሻያ በማድረግ ከህዳር 1 ቀን 1997 ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውል የተወሰነው የከፍተኛ መንግሥት ኃላፊዎች የአገር ውስጥ የውሎ አበል ለምግብ ብር 70 ፤ ለአልጋ በደረሰኝ የሚወራረድ ሆኖ ከብር 70 የማይበልጥ መሆን እንዳለበት ያዛል፡፡ ሆኖም በብሔራዊ የስነ ልክ ኢንስቲትዩት አላግባብ በብልጫ የተከፈለ የውሎ አበል ክፍያ ብር 903.49 መገኘቱ ታውቋል፡፡ መንግሥት አሻሽሎ የሚያወጣቸው መመሪያና ደንቦችን አውቆ ተግባራዊ አለማድረግ አላአግባብ ክፍያ

እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ተሻሽሎ የሚወጡት መመሪያና ደንቦች ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.9 የሂሳብ ማስተካከያ ተሰርቶለት ማስረጃ ያልቀረበት የወጪ ሂሳብ

በመ/ቤቶች በዓመቱ መጨረሻ ማስተካከያ የተሠራላቸው ሂሳቦች ሁሉ በትክክል የተዘጋጁ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በወለጋ ዩኒቨርስቲ ቀደም ሲል በስህተት በወጪ መመዝገቡን የሚያሳይ ማስረጃ ያልተገኘ መሆኑ ለማየት ተችሏል፡፡በማስረጃ ያልተደገፈ የሂሳብ ማስተካከያ ተዓማኒነት የለውም፡፡ ለተከሰተው የአሰራር ስህተት ማስተካከያ እንዲሠራለት አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለወደፊቱ ማንኛውም ማስተካከያ የሚዘጋጅለት ሂሳብ ሁሉ በማስረጃ የተደገፈ መሆን እንደሚገባው በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ያለመዘጋጀቱ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የመንግስት መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ የሚፈጽሙትን ግዥ የሚያሳይ ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀት እንዳለባቸውና የተዘጋጀው የግዥ ዕቅድ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ፀድቆ ለግዥ ኤጀንሲ በየዓመቱ እስከ ሐምሌ 30 ቀን መላክ እንዳለበት አዋጁ የሚያዝ ቢሆንም የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የግዥ ዕቅድ ያላዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም ግዥው ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዳይፈፀም የሚያደርግና የመንግሥትም ገንዘብ ለብክነትና ለምዝበራ ሊዳረግ ስለሚችል ማንኛውም የአገልግሎትም ሆነ የዕቃ ግዥ በመንግስት ግዥ ዕቅድ መመሪያ መሠረት መከናወን እንደሚኖርበት በላክነው ስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. የተከፋይ ሂሳብ

5.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ4 መ/ቤቶች ብር 496,549.49 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 31 ተመልክቷል/ ተከፋይ ሂሳቦችን በወቅቱ አለመክፈል መ/ቤቶችን ላልተፈለገ ዕዳ (ክፍያ) ሊዳርግ ይችላል፡፡ በመሆኑም ተከፋይ ሂሳብ

በደንብና መመሪያው መሰረት ለሚመለከታቸው መከፈል እንደሚኖርበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6. ንብረት

6.1 የቋሚ እና አላቂ ንብረት አስተዳደር በተመለከተ

መ/ቤቶች የመንግስትና ንብረት በደንቡ መሰረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት፤ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያላደረጉ መሆኑ፤

6.2 የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከወጪ ቀሪ ያልተመሳከረ ስለመሆኑ

በመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 በአንቀፅ 65 በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀፅ 6 መሰረት በ9 መ/ቤቶች ንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም በመዝገብ ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ - 33 ተመልክቷል/

ንብረቶች ከምዝገባ ባለመመሳከራቸው የጠፋ ወይም የጎደለ ንብረት ካለ ማወቅ አያስችልም፡፡ ይህም ለንብረት ብክነት በር ከፋች ሊሆን የሚችል ከመሆኑም በላይ በወቅቱ እርምጃ ለመውሰድም አያስችልም፡፡

በመሆኑም የመንግሥትን ንብረት ከብክነትና ከጥፋት ለመጠበቅና ለመከላከል እንዲሁም ለክትትልና ቁጥጥር የተመቻቸ እንዲሆን ለማድረግ ይቻል ዘንድ መዝገብ ከሚያሳየው ከወጪ ቀሪ ጋር መመሳከር እንደሚኖርበት በላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.3 ለረጅም ዓመታት ሳይወገዱ የተገኙ ንብረቶች በተመለከተ

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል አራት ከአንቀጽ 19-27 በተጠቀሰው መሰረት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች መወገድ እንዳለባቸው ይገልፃል፡፡ በመሆኑም በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ መወሰዱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ11 መ/ቤቶች ልዩ ልዩ ዕቃዎች ለረጅም ዓመታት በንብረት ክፍል ተከማችተው ሳይወገዱ ተገኝተዋል፡፡ዝርዝሩም **በአባሪ-33** ተመልክቷል/

ንብረቶች ተከማችተው ያለጥቅም ከተቀመጡ በመቀመጣቸው ብዛት ለአላስፈላጊ ተጨማሪ ብልሽት፣ ብክነት እና ጉድለት ሊጋለጡ ስለሚችሉ ያረጁና ሊወገዱ የሚገባቸው ንብረቶች በመንግስት የንብረት አወጋገድ ስርዓት መሰረት እንዲወገዱ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.4 በንብረት ላይ የሚታዩ ልዩ ልዩ ችግሮች

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 208/2000 በተሰጠው ስልጣንና ሃላፊነት መሰረት መስራት ሲገባው፡-

- ባለአደራ ቦርዱ የተረከባቸውን ንብረቶች መዝግቦ የሚይዝበት መቆጣጠሪያ መዝገብ ያለማዘጋጀቱ፣
- ከፕራይቬታይዜሽን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ የሚላከው የንብረት ርክክብ መረጃ በዝርዝር ሳይሆን በጥቅል መሆኑ፣

በመሆኑም ንብረቶቹን መዝግቦ የሚይዝበት መቆጣጠሪያ መዝገብ ካለዘጋጀ የተረከባቸውን ንብረቶች ለሌላ ጥቅም ሊውል ስለሚችልና በአካል የተገኙትን ንብረቶች ብቻ ርክክብ ማድረጉ ወደ ገዥው ያልተላለፉትን የንብረቶቹን ዝርዝር ስለማያሳይ በሙሉ ቦርዱ ላይረከብ ይችላል፡፡ በመሆኑም ባላአደራ ቦርዱ የመቆጣጠሪያ መዛግብት በማዘጋጀት የተረከባቸውን ንብረቶች በሃላፊነት ሊይዝና ሊጠብቅ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ባላአደራ ቦርዱ ከፕራይቬታዜሽን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ንብረቶችን ሲረከብ በመጠን በዓይነት እና በዋጋ ተለይተውና ተዘርዝርው ሊረከብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.5 ከመነሻ ዋጋ በታች የተከናወነ የንብረት ሽያጭ

የፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 በክፍል አራት አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1/2/3 ላይ በተደጋጋሚ ጨረታ ስለማወጣት እንደተቀመጠው በሁለተኛ ዙር ለመሸጥ ተሞክሮ በቂ ተወዳዳሪ /ገዥ/ ካልተገኘ የግምት ዋጋውን በማሻሻል ለሦስተኛ ጊዜ የጨረታ ማስታወቂያ በማወጣት በተገኘው ዋጋ ሽያጩ ይፈጸማል ብሎ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ በዚሁ መሠርት መስራቱን ኦዲት ሲደረግ የንብረቶቹ ሽያጭ የግምት ዋጋው ሳይሻሻል ከመነሻ ዋጋው በታች በመሸጡ

በልዩነት ምክንያት ብር 3,995,192.88 በማነስ በሥራ አመራር ቦርድ በተወሰነው መሠረት ሽያጩ ተከናውኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ከመነሻ ዋጋ በታች ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት የግምት ዋጋውን በማሻሻል በድጋሚ ጨረታ ቢወጣ በተሻለ ዋጋ ሊሸጥ ስለሚችል በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ መሆን እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.6 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ለተረከባቸው ንብረቶች ሽያጭ ጨረታ ሰነድ አለመቅረቡ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ የተረከባቸውን የተለያዩ ንብረቶች የፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት በማድረግ ሽያጩ መከናወኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከንብረት ሽያጭ የተሰበሰበው ብር 2,000,000.00 ሽያጩ የተከናወነበት የጨረታ ሰነድ ለኦዲት ስራ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡ በመሆኑም ሽያጩ በመመሪያው መሠረት ላይከናወን ስለሚችል በተጨማሪም በአ/ማህበር ገቢ የተደረገው ሂሳብ ትክክል ላይሆን ሰለሚችል በአ/ማህበሩ የተከናወኑ ሽያጮች ሂሳብ ገቢ ሲደረግ ሽያጩ የተካሄደበት ሰነድ ከገቢ ማስረጃው ጋር በማያያዝ ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.7 የተሽከርካሪን አያያዝና አጠባበቅ ሁኔታ በተመለከተ

በመ/ቤቶች የሚገኙ ተሽከርካሪዎች አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው በ5 መ/ቤቶች 84 ተሽከርካሪዎችና ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የቆሙ በ6 መ/ቤቶች 104 ተሽከርካሪዎች /ዝርዝሩ በአባሪ-34 ተመልክቷል/ መሆኖራቸው ታውቋል፡፡

በኢት/ ካርታ ስራ ኤጀንሲ አንድ እንዲሁም በማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ሁለት ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው (ሊብሬያቸው) በመ/ቤቶቹ ስም አለመሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም የተሽከርካዎቹ የባለቤትነት መታወቂያ ካለበት ቦታ ተጠይቆ ሊሟላና የመንግስት ንብረት ውጤታማ ሳይሆን ሲቀር በመመሪያው መሰረት ማስወገድ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.8 የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ

በጀት ዓመቱን የነዳጅ አጠባበቅና አያያዝ ኦዲት ለማድረግ ተሞክሮ የብሄራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት ሰነዶች ሊቀርብ ባለመቻሉ ኦዲት ለማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ የነዳጅ ፍጆታ /አጠቃቀም/ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ሪፖርት የማይቀርብለት ከሆነ ነዳጅ አለአግባብ ጥቅም ላይ ሊውል ስለሚችል ለወደፊቱ የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት ላይ አሳስበናል፡፡

7. የበጀት አፈጻጸም በተመለከተ

7.1 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ

በ2004 በጀት ዓመት በመ/ቤቶች እንዲሰራበት ከተፈቀደው በጀት የወለጋ ዩኒቨርሲቲ መደበኛ በጀት ውስጥ ብር 1,482,444.61 እንዲሁም ከሰበሰበው ገቢ እንዲጠቀም በተፈቀደለት በጀት ውስጥ ብር 16,420,368.44 በድምሩ ብር 17,902,813.05 እንዲሁም የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጽ/ቤት ደግሞ ብር 49,681.21 ከበጀት በላይ ወጪ ማድረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ መንግስት ለልዩ ልዩ ውጤታማ ሥራዎች የመደበው ገንዘብ ያለአግባብ ባክኖ ሊቀር ስለሚችል በጀት ከተመደበለት በላይ ወጪዎች ሲያጋጥሙ በጀት እንዲፈቀድ ወይም የበጀት ዝውውር ጥያቄ በማቅረብ እና በማስፈቀድ ስራ ላይ ማዋል የሚቻል በመሆኑ መ/ቤቶቹ የበጀት አፈጻጸም የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንቡን የተከተለ እንዲሆን ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግበት አሠራር መዘርጋት እንደሚኖርባቸው በሪፖርታችን አሳስበናል ፡፡

7.2 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት በተመለከተ

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ ማዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከ12 መ/ቤቶች ብር 167,316,281.74 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩን **በአባሪ- 32** ተመልከቱ)

በመሆኑም መንግስት ለሌሎች መሠረታዊ ለሆኑ ሥራዎች ሊያውል የሚችለውን ገንዘብ በበጀት ዓመቱ ስራ ላይ እንዳይውል ሊያደርግ ስለሚችል የበጀት ዝግጅት ጥያቄ መ/ቤቶች ሲያቀርቡ በተጨባጭ ሊሰራ ከታቀደው ተግባር ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ያለፉትን ዓመታት የዕቅድ አፈፃፀም በመገምገም ሊከናወን

የሚገባ ሲሆን ለወደፊቱም የበጀት ጥያቄ ሲቀርብ ከእቅድ ጋር እየተገናዘበ የሚቀርብበት ሁኔታ እንዲመቻች ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አሳስበናል::

8. ልዩ ልዩ

8.1 የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ የማይዘጋጅ ስለመሆኑ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 208/2000 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ሥልጣንና ሃላፊነት መሰረት የሚተላለፉለትን የልማት ድርጅቶች ተሰብሳቢ ሂሳቦችና ዕዳዎችን የሚመለከቱ ሰነዶችን በመረከብ ወደግል ይዞታ በሚዛወሩበት ወይም ወደ አክስዮን ማህበር ወይም ለቀድሞ ባለቤቱ በሚተላለፉበት ወቅት ወደ አዲሱ ባለቤት የማይተላለፉ የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን በመያዝ እንደሚያስተዳድርና ትክክለኛ የሂሳብ ሰነዶችንና መዛግብትን በመያዝ ኦዲት ማስደረግ እንዳለበት ያዛል ፡፡ በመሆኑም ቦርዱ በዚሁ መሰረት ተፈፃሚ የሚያደርግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ባለአደራ ቦርዱ የተጠቃለለ የሂሳብ ሪፖርት /consolidations financial statement/ የማያዘጋጅ በመሆኑ የድርጅቶችን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በመሆኑም የቦርዱን የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳብ ትክክለኛ ገጽታ ለማሳወቅ አያስችልም፡፡ እንዲሁም ከ1997 ጀምሮ ስራው በትክክል እንዲሰራ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በቦርዱ የሚሰጠው ምላሽ ተመሳሳይነት ያለውና እልባት ያላገኘ ጉዳይ መሆኑ አሳሳቢነቱን የጎላ ያደርገዋል፡፡ ስለ መ/ቤቱ የሚመለከታቸው ሃላፊዎች በተደጋጋሚ የሚነሱትን የሰው ሃይልና ሌሎች ችግሮች ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ሥራው የሚከናወንበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል፡፡

"የተጠቃለለ ሪፖርት ለማውጣት የሚደረገው ጥረት የሚቀጥል መሆኑን በመግለፅ ከየድርጅቶቹ የተላለፉት የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳቦች እስከ 40 እና ከዚያ በላይ ዓመታት እየተንከባለሉ የቆዩ በመሆኑ የሚሰበሰቡትና የሚከፈሉት ከሚተላለፉት ላይ በጣም አነስተኛ በመሆናቸው እንዲሁም መሰብሰብም ሆነ የመክፈል ሁኔታዎች የሚፈፀመው አድራሻቸው ለታወቁ፣ በመረጃ ለተደገፉና የመፈጸም ጊዜ ያለፈባቸውን በማጣራት ስለሆነ ተጠቃሎ ቢወጣም ለምንም ዓይነት ስራ ጠቀሜታ እንደማይውል" በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡ ሆኖም የሂሳብ

ሪፖርት ሣይዘጋጅና ሊሰበሰብም ሆነ ሊከፈል የማይችል ሂሳብ መሆኑን ለሚመለከተው ክፍል አሳውቆ እርምጃ ለመውሰድ የማያስችል በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ሊሰረዝ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም ትኩረት በመስጠት የተጀመረውን ስራ በማጠናቀቅ ሊሰበሰብም ሆነ ሊከፈል የማይችለው ሂሳብ ላይ እርምጃ ሊወሰድ የሚችልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል በማለት ለኦዲት ተደራጊ መ/ቤት አሳስበናል::

8.2 በወቅቱ ያልተሰበሰበ በውዝፍ የተገኘ ሂሳብ

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅትየድርጀቱ ደንበኞች ከሆኑ የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በተገባው ውል መሰረት በወቅቱ ያልተሰበሰበና ለ17 ዓመታት የቆየ ውዝፍ ሂሳብ ብር 6,168,994.78 መኖሩ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትድርጅቱ በዱቤ የተሰጠ የማስታወቂያ ውዝፍ የአገልግሎት ሂሳብ ከ1988-2002 ድረስ ብር 3,564,840.80 ሰኔ 30/2004 መኖሩ፡፡ በድምሩ የውዝፉ ሂሳብ ብር 9,733,835.58 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ጊዜው በረዘመ ቁጥር የመንግስት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊቀር ስለሚችል ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ውዝፍ ሂሳቡ የሚሰበሰብበት ወይም በውሉ መሰረት ተገቢው ህጋዊ እርምጃ የሚወሰድበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል በማለት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት ላይ አሳስበናል፡፡

8.3 ሊሰበሰብ ያልቻለን ሂሳብ ከመዝገብ ስለመሰረዝ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2001 አንቀጽ 38 መሰረት ሊሰበሰብ ያልቻለን ሂሳብ ከመዝገብ የመሰረዝ አፈጻጸምን የሚከታተል እና የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ከ3-5 አባላት ያሉት አጣሪ ከሚቴ በእያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤት መቋቋም እንዳለበት እንዲሁም የመ/ቤቱ ኃላፊም በአጣሪ ኮሚቴ በሚቀርብለት የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በተሰጠው የስልጣን ገደብ ውስጥ ውሳኔ የሚሰጥና ከብር 10,000 የማይበልጥ የእዳ ስረዛ ማድረግ እንደሚችል የተገለፀ ሲሆን በብሔራዊ ስነልክ ኢንስቲትዩት የብር 13,360.70 እዳ መሰረዙ እና የውሰኔ ሀሳብ የተሰጠውም በተቋቋመ አጣሪ ኮሚቴ ሳይሆን በማኔጅመንት ስብሰባ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም የመ/ቤቱ ኃላፊ በአጣሪ ኮሚቴ በሚቀርብለት የውሳኔ ሀሳብ ውሳኔ ካልሰጠ በማኔጅመንት ስብሰባ ውሰኔ መስጠቱ ውሳኔውን ትክክለኛ ላያደርገው ስለሚችል ተገቢውን የማጣራት ሥራ የሚሰራ ኮሚቴ

ተቋቁሞ መመሪያውን መሠረት በማድረግ ሊሠራ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት ላይ አሳስበናል፡፡

8.4 በመ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የአሰራር ግድፈቶች

- በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትና በማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ጅማ ቅርንጫፍ የንብረት መመዝገብና የመጠበቅ ስራ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ ታይቷል፡፡ በመ/ቤቶቹ ተጠያቂነት እንዳይሰፍን እንቅፋት ሊሆን እና የመንግስት ንብረትም ለብክነት እንዲጋለጥ ሊያደርግ ስለሚችል አሰራሩ እንዲስተካከል በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡
- በወለጋ ዩኒቨርሲቲ ልዩ ልዩ ሕንጻዎች ግንባታ ወጪ ሆኖ የተመዘገበው ሂሳብ ትክክል መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ለአንድ ኮንስትራክሽን ድርጅት ከተፈጸመው ክፍያ ሂሳብ ላይ የተቀነሰው መያዣ (Retention) ብር 173,993.71 መያዣ (Retention) በተከፋይ ሂሳብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡
- የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ በ2003 እና በ2004 በጀት ዓመት መጨረሻ ያልተሰራባቸው የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በሴሪና በቁጥር (ከ-እስከ-ከ) ተለይቶ ቆጠራ ባለመደረጉ በ2004 በጀት ዓመት የውስጥ ገቢ ሂሳብ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ምን ያህል እንደሆኑ ለማወቅ ባለመቻሉ የውስጥ ገቢ ተሰብስቦበት ደረሰኝ ሳይመለስ ሊቀር እና ገንዘቡ ለግል ጥቅም ሊውል ስለሚችል የውስጥ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በሴሪና በቁጥራቸው እየተቆጠሩ ሁሉም ደረሰኞች መኖራቸው እና በደረሰኞቹ ተሰብስበው ሁሉም ገንዘብ ገቢ መሆኑ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

8.5 የስጋት አስተዳደር ፖሊሲ ያልተዘጋጀ ስለመሆኑ

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 በክፍል 4 የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ለመዘርጋትና ለመገምገም እንዲያስችል በተራ ቁጥር 3 ላይ የስጋት ተጋላጭነት ዳሰሳን ለመተግበር የመንግስት መ/ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈፀም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችንና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የውስጥና የውጪ ኦዲተሮችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የስጋት ምንጮች ዳሰሳ በየጊዜው ማካሄድ እንዳለበት ይገልፃል፡፡

ሆኖም በ21 መ/ቤቶች የስጋት ምንጮች ዳሰሳ አለማድረጋቸው ታውቋል፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ 6 ቀጥሎ ይመልከቱ)

መ/ቤቶችም የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈፀም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት ለሚከሰቱ ችግሮች ተጋላጭነታቸው የሰፋ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ስለሆነም መ/ቤቶች የስጋት ምንጮች በሆኑበት አካባቢ የሚከሰቱ ችግሮችና የተጋለጭነት ደረጃ በመለየት ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት እና የመከታታያ ስልት ለመዘርጋት ስጋቶችን ለመቀነስ እንዲቻል ለይቶ ማወቅና ስጋቶችንም ለመቀነስ ተገቢው የስጋት አስተዳደርና ፖሊሲ ሊዘጋጅ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት ላይ አሳስበናል፡፡

የስጋት አስተዳደር ፖሊሲ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም
1	የማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ
2	የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት
3	የኢ.ት/ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት
4	የወሊጋ ዩኒቨርስቲ
5	የኢ.ት/ ፕሬስ ድርጅት
6	የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት
7	የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
8	የቤተመንግስት አስተዳደር ጽ/ቤት
9	የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት
10	የደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ
11	የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ
12	የመንግስት ግዥና ን/አስተዳደር ኤጀንሲ
13	የፕሬዘዳንት ጽ/ቤት
14	የኢ.ት/ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን
15	ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጽሐፍት ኤጀንሲ
16	የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት
17	የፌዴሬሽን ምክር ቤት
18	የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን
19	የብሄራዊ የስነ ልክ ኢንስቲትዩት
20	የመንግስት የፋይናንስ ድርጅት ኤጀንሲ
21	የኢ.ት/ ብሮድካስት ባለስልጣን

ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ዝርዝር እና በጀት

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	21/05/2005			490,206,700.00
2	የመንግሥት አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ	10/08/2004			
3	የማዕከላዊ እስታስቲክስ ኤጀንሲ	21/02/2005	48,652,122.20	154,201,482.00	202,853,604.20
4	የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በጀት	30/01/2005	444,239,856.85	170,000,000.00	614,239,856.85
5	የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ	21/01/2005	5,410,980.00	-	5,410,980.00
6	የሴቶችና የወጣቶችና የህፃናት ጉዳዮች ሚኒስቴር	21/02/2005	22,247,779.45	-	22,247,779.45
7	የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት	09/02/2005	39,831,495.00	1,232,122.00	41,063,617.00
8	የኢት/ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት	30/01/2005	97,044,220.50	569,036,170.00	666,080,390.50
9	የወለጋ ዩኒቨርስቲ	22/02/2005	110,170,781.00	101,278,050.00	211,448,831.00
10	የኢት/ ፕሬስ ድርጅት	26/02/2005	62,626,700.00	1,822,300.00	64,449,000.00
11	የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት	23/12/2005	105,706,100.00	15,000,000.00	120,706,100.40
12	የቤተመንግስት አስተዳደር ጽ/ቤት	21/02/2005	82,315,279.48	108,399,943.00	190,715,222.48
13	የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት	2/13/2004	93,759,498.00	3,000,000.00	96,759,498.00
14	የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	04/03/2005	44,917,153.40	-	44,917,153.40
15	የኢት/ ካርታ ስራ ባለስልጣን	30/01/2005	19,313,120.00	4,996,400.00	24,309,520.00
16	የደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ	30/12/2004	91,399,277.00	105,738,743.27	197,138,020.27
17	የድሬደዋ ዩኒቨርስቲ	21/02/2005	84,089,430.00	125,216,270.00	209,305,700.00
18	የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ	14/03/2005	87,375,869.00	104,285,810.00	191,661,679.00
19	የመንግስት ግዥና ን/አስተዳደር ኤጀንሲ	01/02/2005	3,959,441.00	-	3,959,441.00
20	የፕሬዘዳንት ጽ/ቤት	05/04/2005	13,602,563.00	-	13,602,653.00
21	የኢት/ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን	01/02/2005	5,408,769.00	-	5,408,769.00
22	ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጽሐፍት ኤጀንሲ	22/02/2005	10,840,713.10	1,600,000.00	12,440,713.10
23	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ስብሰባ ማዕከል	09/02/2005	2,958,600.00	-	2,958,600.00
24	የመድን ፈንድ ጽ/ቤት	18/01/2005	7,779,540.00	-	7,779,540.00
25	የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት	13/02/2005	237,705,596.00	-	237,705,596.00

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
26	የፌዴሬሽን ምክር ቤት	01/02/2005	20,535,360.31	-	20,535,360.31
27	የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	22/02/2005	29,408,253.00	-	29,408,253.00
28	የብሄራዊ የስነ ልክ ኢንስቲትዩት	23/01/2005	18,685,286.25	-	18,685,286.25
29	የመንግስት የፋይናንስ ድርጅት ኤጀንሲ	26/03/2005	4,609,200.00	-	4,609,200.00
30	የኢ.ት/ ብሮድካስት ባለስልጣን	06/02/2005	7,925,711.00	-	7,925,711.00
ድምር			**1,802,518,784.54**	**1,465,807,290.27**	**3,268,326,074.81**

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የ2004 በጀት ዓመት ዕቅድና ክንውን ሪፖርት

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንጻርና በእቅዱ መሰረት (በእቅዱ መሰረት ያልተከናወነ የኦዲት ሥራ የለም) በማከናወን ይህ ሪፖርት ከጥር 2004 ዓ.ም.እስከ ከታህሳስ 2005 ዓ.ም.ድረስ ያለውን የአንድ ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ለማመላከት የተዘጋጀ ሪፖርት ነው፡፡

ሪፖርቱም ከተዘጋጀው ዕቅድ አንፃር የተከናወኑትን የኦዲት ሥራዎች ከማመላከቱም ባሻገር፣ የተገኙትን ዋና ዋና ግኝቶች አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

በዚህም መሰረት የ2004 በጀት ዓመት ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ

1.1. የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የለም፡፡

1.2. በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ውጤትና በሂሣብ መግለጫ መካከል ስለታየው ልዩነት

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	በማነስ	ብልጫ
1	ዲላ ዩኒቨርስቲ	12,003.35	1,209.69
2	የሃዋሳ ዩኒቨርስቲ-ዋናው ግቢ		3,122,599.49
3	የሃዋሳ ዩኒቨርስቲ የህክምናና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ		151,567.41
4	የሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ወንዶ ገነት የደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ		110,162.68
5	የሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ግብርና ኮሌጅ		12,659.12

በበጀት ዓመቱ የሂሣብ መግለጫዎች ላይ ሪፖርት የተደረገውና በየመ/ቤቱ በተደረገው ቆጠራ ከተገኘው ጥሬ ገንዘብ ጋር ሲመዛዘን በ1 መ/ቤት ብር 12,003.35 የጥሬ ገንዘብ ቆጠራው በማነስ በ5 መ/ቤቶች ብር 12,659.12 በመብለጥ መገኘቱ ታውቋል፡፡

በመሆኑም በማነስ የታየው ሂሳብ እንዲተካና በመብለጥ የታየውም ሂሳብ እንዲጣራ ለየመ/ቤቶቹ አሳስበናል፡፡

1.3. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች

1.3.1. የጥሬ ገንዘብ ማማዛዘኛ የማይሰራ ስለመሆኑ

በአምቦ ዩኒቨርስቲ ጥሬ ገንዘብና እንደጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩ ሰነዶች በተወሰነ ወቅት ቆጠራ እየተካሄደ በጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሌጀር ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር እየተመዛዘነ ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡በሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ በፋይናንስ ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር የሥራ ሂደት በየቀኑ፤ በየሳምንቱ ወይም በየወሩ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማይደረግና የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ጂማ ዩኒቨርስቲ፣የጎንደር፣ዲላ ዩኒቨርስቲ፤ ወሎ ዩኒቨርስቲ፤ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ፣ የመቀሌና የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲዎች የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ቆጠራ ተደርጎ መዝገብ (ቋት) ከሚያሳየው ከወጪ ቀሪ ጋር የማይገናዘብ መሆኑ ተረጋግጧል ፡፡

በፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 መሰረት በተወሰነ ጊዜ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ ከጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሌጀር ከወጪ ቀሪ ጋር ሊመዛዘን እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

1.3.2. በካዝና ውስጥ ስለሚገኝ ጥሬ ገንዘብ

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ በመደበኛ ገንዘብ ያዥ ካዝና ብር 42,151.24 በውስጥ ኦዲተር ተቆጥሮ ተገኝቷል፡፡ በትምህርት ሚኒስቴር ብር141,243.57 በሳጥን በገንዘብ ያዦች እጅ መኖሩን የ2004 ሂሳብ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያመለክታል:: የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ ፣ ለልዩ ልዩ ጥቃቅን ወጪዎች በሳጥን ሊያዝ ከሚገባው ጥሬ ገንዘብ (ፔቲ ካሽ) መጠን በላይ በሂሳብ መግለጫ ብር 1,124,709.88 ታይቷል፡፡

መንግሥት መስሪያ ቤቶች በካዝና እንዲይዙ የሚፈቀድላቸው የጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ የገንዘብ መጠን ከብር 30,000 /ሰላሣ ሺህ ብር/ እንዳይበልጥ የፌደራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ

ቁጥር 3/03 ክፍል 4 ተራ ቁጥር 11.4 ያዛል፡፡ በመሆኑም የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ከላይ በተጠቀሰው መመሪያ መሰረት የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት ገልጸናል፡፡

1.3.3. ከክፍያ መመሪያ ውጪ በቼክ ስለተከፈለ ገንዘብ

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ን.አንቀጽ 4 እና 5 መሰረት በጥሬ ገንዘብ የሚከፈለው መጠናቸው እስከ ብር 2,000.00 ድረስ እና ከብር 2,000.00 እስከ 50,000.00 ድረስ በቼክ ከብር 50,000.00 በላይ የሆኑ ወጪዎች መከፈል ያለባቸው ወደ ባለመብቱ ባንክ ሒሳብ በማስተላለፍ ይሆናል ይላል፡፡ሆኖም

- በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ብር 12,986.65 በቼክ መፈጸም ሲገባው በጥሬ ገንዘብ ክፍያ፣
- በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መ/ቤት ብር 5,124,894.11
- በአምቦ ዩኒቨርስቲ ብር 57,317,692.71 በባንክ ሒሳብ ማስተላለፍ ሲገባ በቼክ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡
- በትምህርት ሚኒስቴር ከሐምሌ 1/2003 እስከ ሰኔ 29/2004 ዓ.ም ብር 471,849,128.77 ለተለያዩ ድርጅቶች በቼክ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል::
- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ መጠናቸው ከብር 120,981.60 እስከ ብር 10,000,000.00 በድምሩ ብር 21,866,401.57 የሆኑ የተለያዩ ክፍያዎች በባንክ ዝውውር ለባለጥቅሙ መከፈል ሲገባ ገንዘቡ ከባንክ ወደ ሳጥን እንዲመጣ ተደርጎ ከሳጥን በጥሬ ገንዘብ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣
- ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 7,965,886.29 እና ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 80,937,928.78 በድምሩ ብር 88,903,815.07 በቼክ ክፍያ ፈፅመዋል፡፡

ለወደፊቱ በክፍያ መመሪያው መሰረት እንዲፈጽሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

1.3.4. ሌሎች የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ አያያዝ ድክመቶች

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 61,465,839.30 ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በማያውቃቸውና ባልተፈቀዱ ዘጠኝ የተለያዩ የባንክ የሂሳብ ቁጥሮች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በድምሩ ብር 13,391,005.85 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የመንግሥት መ/ቤቶችን የባንክ ሂሳብ እንዲያንቀሳቅሱ ውክልና ባልሰጣቸው የግል ባንኮች (ዳሽንና አቢሲንያ ባንክ) የሚገኝ መሆኑ፣
- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ከተለያዩ እርዳታ ድርጅቶች የሚያገኘው ድጋፍ የሂሳብ ሪፖርት የማይዘጋጅለት መሆኑ፣
- መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ገንዘብ ያዥዎች ስራ ሲለቁ ወይም ወደ ሌላ ክፍል በሚዛወሩበት ወቅት በእጃቸው የሚገኘውን ጥሬ ገንዘብና እንደ ጥሬ ገንዘብ የሚቆጠሩትን ከሳጥን ከወጪ ቀሪ ጋር ሳይመዛዘን ርክክብ የሚፈጸም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- በሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ የ2004 በጀት ዓመት የጥሬ ገንዘብ የመነሻ ሂሳብ ሚዛን በብር 1,012,767.32 በመብለጥ የሚያሳይ መሆኑ በተጨማሪም የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢዎች በየዕለቱ የሰበሰቡት ጥሬ ገንዘብ በየዕለቱ ባንክ ስለማያስገቡ በአማካኝ 30,825.00 መጠን ያለው ጥሬ ገንዘብ ከ2 እስከ 10 ቀናት በእጃቸው ላይ የሚቆይ መሆኑ ታይቷል፡፡
- በሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ወንዶ ገነት የደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ በገንዘብ ያዥነት የተመደቡ 2 የኮሌጁ ሠራተኞች ዋስትና ወይም ተያዥ የሌላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

በተቀመጠለት የአሠራር መርህ መሠረት አስፈላጊው ማስተካከያ፣ በበጀት አመቱ መጨረሻና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብና ሰነድ ድምር በሰኔ 30/2004 ተቀጽላ ሌጀር ከሚታየው ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘንና በገንዘብ ያዥነት የተመደቡ ሠራተኞችም ዋስትና ወይም ተያዥ እንዲያቀርቡ የሥራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

- ❖ ወሎ ዩኒቨርስቲ፣ ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ፣የሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ወንዶ ገነት ኮሌጅ፣የሃዋሳ ዩኒቨርስቲ የሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ተገቢውን የሂሳብ አያያዝ

ሥርዓት ተከትሎ የማይዘጋጅ የማይዘጋጅ መሆኑታውቋ፡፡ ስለሆነም የባንክ ሂሳብ በአግባቡ አለማስታረቅ በባንክ ያለው ሂሳብ መገኘት በሚገባው ልክ መገኘቱን ማረጋገጥ ካለማስቻሉም በላይ በጊዜ ብዛት ሂሳቡ እየተወሳሰበ በቀላሉ ወደ ማይታረቅበት ደረጃ ሊደርስ ስለሚችል የተቋማቱ ሃብት በአግባቡ ተመዝግቦ እንዲያዝ ከወጪ ቀሪውን በትክክል ለማወቅና ምዝበራንም ለማስቀረት የባንክ ሂሳብ በአግባቡ እንዲታረቅ አሳስበናል፡፡

2. የገቢ ሂሳብ

2.1 የገቢ ግብር የማይቀነስ ስለመሆኑ፣

በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የመኖሪያ ቤት አበል በጥሬ ገንዘብ ከሚከፈላቸውና መኖሪያ ቤት በአይነት ከተሰጣቸው መምህራንና ሠራተኞች ላይ የገቢ ግብር የማይቀነስ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 12/1 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማንኛውም ክፍያ ከወር ደመወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት ደንቡ የሚያዝ በመሆኑ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.2 ሪፖርት ያልተደረገ የገቢ ሂሳብ

በፋይናንስ መመሪያው መሰረት የሚሰበሰቡት ገቢዎች በተገቢው የሂሳብ ኮድ ተመዝግበው በሒሳብ ሪፖርት ውስጥ የሚካተቱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሁለት መ/ቤቶች ብቻ ብር 10,806,370.92 በገቢ ሪፖርት ያልተካተተና በሌሎች 15 መ/ቤቶች ደግሞ በገንዘብ ያልተገለጸ ገቢ ተሰብስቦ ነገር ግን በሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-15 ተመልክቷል/

የተሰበሰበው ገቢ፣ ምን ያህል ወጪ ተደርጎ ጥቅም ላይ እንደዋለ የሚያሳይ ትክክለኛ ሪፖርት በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

2.3 በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የታዩ የአሰራር ድክመቶች ጅማ ዩኒቨርሲቲ

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ የመኖሪያ ቤት አበል በጥሬ ገንዘብ ከሚከፈላቸው መምህራን ላይ አበሉ ከደመወዛቸው ጋር ተደምሮ የሥራ ግብር እንዲከፍሉ አያደርግም፡

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ የሥራ ተቋራጮች በፀደቀ የውል ማራዘሚያ መሠረት ስራቸውን አጠናቀው ማስረከብ ሲኖርባቸው ባለማስረከባቸው እስከ 2004 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በድምር ብር 81,110,000.00 ዩኒቨርሲቲው ከሥራ ተቋራጮች በቀጣት መልክ Liquidation Damage ካሳ ማስከፈል ሲገባው ያላስከፈለ መሆኑ፣በተጨማሪም አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት በወቅቱ ንብረቱን ገቢ ባለማድረጋቸው በድምሩ ብር 2,625,402.93 የቅጣት ክፍያ እንዲከፍሉ መደረግ ሲገባው እንዲከፍሉ ያልተደረገ መሆኑ በአጠቃላይ ድምር ብር 83,735,402.93 የቅጣት ክፍያ አልተሰበሰበም፡፡

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ከመንግሥት ተቋማት በመደበኛው መርህ ግብር ተመርቀው ከ21/2/2001 ዓመተ ምህረት ጀምሮ ለቀጠራቸው የአስተዳደር ሠራተኞች ከሚያገኙት የወር ገቢ 10% ከገቢ ተከፋይ በሆነ መልክ እየተቀነሰ ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባው ገቢ የማያደርግ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

- ተቋራጮች በገቡት ውል መሠረት የግንባታ ሥራቸውን ባለማጠናቀቃቸው በጠቅላላው ድምር ብር 17,320,938.60 ቅጣት /Liquidation Damage/ መክፈል ሲገባቸው በአማካሪ ድርጅቱም በኩል ሆነ በዩኒቨርሲቲው እንዲከፍሉ ያልተደረገ መሆኑ፣

- ዩኒቨርሲቲው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርን ሳያስፈቅድ ባሳተመው የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ እና ኩፖን ገቢ የሚሰበስብ መሆኑ ታውቋል፡፡

ሌሎች ዩኒቨርስቲዎች

- የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ከመደበኛ በጀት እንቅስቃሴ የሚገኙ የመልካም አፈጻጸም ዋስትናና ቅጣት ገቢዎች ወደ ውስጥ ገቢ ሂሳብ የሚገቡ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ገቢ በሚሰበሰበው ልክ ወደ ሂሳብ ቋት ብሎም ወደ ሪፖርት በትክክል መወሰዱን ለማረጋጋጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርትና በሂሳብ መመዝገቢያ ቋት መካከል ልዩነት ብር 2,016,742.21 የታየ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህም፡-

በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት መሠረት	ብር	8,289,079.21
በሂሳብ መዝገብ (ቋት)		6,272,337.00
ልዩነት (የሂሣብሪፖርቱ በመብለጥ)		2,016,742.21

- የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ-ዋናው ግቢ፣ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ-የህክምናና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ-ወንዶ ገነት የደንና የተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ፣ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የግብርና ኮሌጅና የአክሱም ዩኒቨርስቲ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፍቃድ ሳያገኙ በስማቸው ባሳተሙት የገቢ ደረሰኝ በ2004 በጀት ዓመት የውስጥ ገቢ የሰበሰቡ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም አስፈላጊነታቸው ታምኖበት የወጡ አዋጆች፣ደንቦችና መመሪያዎችን የመተግበር ብሎም ተፈጻሚነታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት የሥራ አመራሩ በመሆኑ በስማቸው የታተሙት የውስጥ ገቢ ደረሰኞችና የሂሳብ ቫውቸሮች ዓይነት፣ ብዛት፣ የታተሙበት ጊዜና እንዲሁም በሥራ ላይ የዋሉትና ያልዋሉትን በመዘርዘር ለሚመለከተው አካል ሪፖርት እንዲደረግ፣ ዝርዝር መረጃዎቹ በጥንቃቄ እንዲጠበቁ ለወደፊቱም የሚኒስቴሩን ስምምነት ሳይጠየቅና ፈቃድ ሳይገኝ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝና ቫውቸሮች እንዳይታተሙ አሳስበናል፡፡

2.4 የውስጥ ገቢ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች

የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 እና የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 62፣,65፣,66 እና 69 መሠረት የመንግስት ተቋም የገቢና የወጪ ሂሣብን ጨምሮ አግባብነት ያለው የሂሣብ አያያዝና ሪፖርት የማቅረቢያ ሥርዓት መዘርጋት እንዳለበት የታዘዘ በመሆኑ በአዋጁ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ12 መ/ቤቶችና 3 ሂሳባቸው ከዋና መ/ቤት ጋር የሚጠቃለል

- የውስጥ ሂሳብ ተገቢውን የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ተከትሎ ባለመያዙ ፣
- የውስጥ ገቢ ሂሳብ የፋናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ አግባብነት ያላቸው ሪፖርቶች በተሟላ መልኩ ያልተዘጋጁና ለሚመለከታቸው ክፍሎች በወቅቱ ያልቀረቡ፣
- ለእንዳንዱ የገቢ ማስገኛ ምንጭ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ማስከፈያ ተመን ባለማዘጋጀቱና

- የውስጥ ገቢ ደረሰኞች ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የገቢው ዓይነት፣የተከፈለበት ምክንያት፣ የሂሳብ መደብ እንዲይዙ ተደርገው ባለመዘጋጀታቸው

  የውስጥ ገቢ ሂሳቡን ኦዲት ማደረግ አልተቻለም/የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ-16 ተመልክቷል/

በመሆኑም የውስጥ ሂሳብ ተገቢውን የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ተከትሎ እንዲያዝ፣ የውስጥ ሂሳብ የፋናንስ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ አግባብነት ያላቸው ሪፖርቶች በተሟላ መልኩ እየተዘጋጁ ለሚመለከታቸው ክፍሎች በወቅቱ እንዲቀርቡ፣ለእንዳንዱ የገቢ ማስገኛ ምንጭ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ማስከፈያ ተመን በማዘጋጀት ዶክመንቱ በጥንቃቄ እንዲጠበቅ፣ የውስጥ ገቢ ደረሰኞች ተፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የገቢው ዓይነት፣የተከፈለበት ምክንያት፣ የሂሳብ መደብ እንዲይዙ አሳስበናል፡፡

3. የወጪ ሂሳብ

3.1 በብልጫ የተከፈለ

- በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 500.00 ለውሎ አበል
- በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 3,232.27 ለነዳጅና ናፍታ በብልጫ የተከፈለ ወጪ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡
- የጅማ ዩኒቨርሲቲ የምህንድስናና ጠቅላላ አገልግሎት የሥራ ሂደት ቡድን መሪ አቶ አሸናፊ ስመኝ እና የሥራ ሂደቱ ባልደረባ አቶ መሀመድ ሙስጠፋ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ በዩኒቨርሲቲው የመኖሪያ ቤት የተሰጣቸው ቢሆንም ከተቀጠሩበት ጀምሮ በየወሩ ብር 1,000.00 ለየመኖሪያ ቤት አበል የሚከፈላቸው መሆኑና እስከ ሰኔ 30/2004 ዓ.ም ድረስ በድምሩ **ብር 90,000.00** አለአግባብ ተከፍሏቸው ተገኝቷል፡፡በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው መምህራን ለክረምት ትምህርት ፕሮግራም ላስተማሩበት የስራ ጫና /over load/ ክፍያ ሲፈጸም ከትርፍ ሰዓት አከፋፈል ተመን በላይ በድምሩ **ብር 846,336.48** አለአግባብ በብልጫ የተከፈለ ሲሆን በአጠቃላይ ድምር **ብር 936,336.48** በብልጫ ተከፍሏል፡፡
- ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ ከተገባው ውል ስምምነት ውጭ ብር 261,033.15፣ ወልድያ ዩኒቨርስቲ ብር 17,888.48 እና ወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 150,880.50 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

በብልጫ ወጪ የተደረገው ብር ተመላሽ እንዲደረግ በሪፖርታችን ገልጸናል፡፡

3.2 በጀት ዓመታቸውን ያልጠበቁ

- በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አቅም ግንባታ ፕሮግራም ብር 88,459.91
- በአምቦ ዩኒቨርስቲ ትርፍ ሰዓት ላስተማሩ መምህራን የተከፈለው ብር 111,231.23 አገልግሎቱ የ2002 እና 2003 በጀት አመት ሆኖ ክፍያው በ2004 በጀት ዓመት ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ለወደፊቱ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይከሰት ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.3 ያለአግባብ የተከፈለ የኃላፊነት አበል

በአምቦ ዩኒቨርስቲ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የሃላፊነት አበል በጥቅሉ ብር 65,650.00 ለዩኒቨርሲቲው የስራ አመራሮች ክፍያ መፈጸሙ ተረጋግጧል፡፡ ያለአግባብ የተከፈለው ብር ተመላሽ እንዲደረግ ለወደፊቱም የሚመለከተውን አካል አስፈቅዶ ተገቢውን በጀት በመያዝ ክፍያውን መፈጸም እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 በውሉ መሰረት ያልተጠየቀ የጉዳት ካሳ

በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ/2002 በክፍል 4 አንቀጽ 16 ን.አንቀጽ 27 ን.ን.አንቀጽ 3(ሸ) እና 4 አንድ አቅራቢ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ አቅራቢው ሳይፈጽም በቀረው የውሉ መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ የጉዳት ካሳ መክፈል አለበት ይላል፤ሆኖም

- አምቦ ዩኒቨርስቲ ብር 686,892.28
- አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ በድምሩ ብር 57,269.09

አቅራቢዎቹ በውሉ ከተመለከተው ጊዜ ዘግይተው ገቢ ሲያደርጉ ለዩኒቨርስቲው የጉዳት ካሳ መክፈል ሲገባቸው አለመክፈላቸው ተረጋግጧል፡፡

በውሉመሰረት ድርጅቱ ላዘገየበት ጊዜ ተገቢውን ካሣ መክፈል እንዳለባቸው በተላከው ሪፖርት ገልጸናል።

3.5 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ

- በአምቦ ዩኒቨርስቲ ብር 461,879.92
- በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 55,660.00 የወጪ ሂሳብ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡
- የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ብር 44,256.60 በትክክለኛው የወጪ ሂሳብ መደብ አልመዘገበም፡፡

- በሀገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ለአፕልኬሽን ፎርሞች በኤልሲ ለተፈፀመው ግዥ ለባንክ አገልግሎት የተከፈለውን ብር 1,614,532.75 ከዕቃው ዋጋ ጋር በመጨመር በመሆኑ፣ የባንክ አገልግሎት ክፍያ ያለሂሣብ መደቡ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ከተቻለ የሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ ማከናወንና ለወደፊቱም ምዝገባ ሲከናወን ጥንቃቄ እንዲደረግ በላክነው ሪፖርት ገልጸናል፡፡

3.6 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ

የአምቦ ዩኒቨርስቲ

- ለተለያዩ ኮንራክተሮች ቅድሚያ ክፍያ በድምሩ ብር 1,683,618.34፣
- ከሬዲዮ ፋና እና ከትምህርት ሚኒስቴር ለመጡ እንግዶች ከመጡበት መ/ቤት የውሎ አበል ያልተከፈላቸው ለመሆኑ ሣይረጋገጥ ብር 3,500.00፣
- ብር 959,903.04 ከኮንትራክተሮቹ ቅድሚያ ክፍያ ላይ መቀነስ ያለበት ዊዝሆልዲንግ ታክስ ለመቀነሱ፣

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

- የግዥ መጠየቂያ ከሚመለከተው ክፍል ሳይቀርብ ብር 763,144.21፣
- ግገርው ሳይከናወን በተሰረዘ ቼክ ብር 48,949.92፣
- ብር 5,000.00 ለተማሪዎች ሕብረት ለመድረሱ፣

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ለሥራ ተቋራጮች የተከፈለ ቅድመ ክፍያ/Advance Payment/ **ብር 123,905,491.52** በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦና ሪፖርት ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ከውስጥ ገቢ በድምሩ **ብር 25,552,100.00** በጅማ ዩኒቨርሲቲ ቁሳቁስ ማምረቻ እና ጥገና ኢንተርፕራይዝ ስም አክሲዮን (ሼር) ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ የገዛ ቢሆንም ኢንተርፕራይዙ በስሙ የተገዛለትን ተጨማሪ አክሲዮን ያልተረከበ መሆኑና በሂሳብ ሪፖርቱም ላይ አይታይም፡፡

በአጠቃላይ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ድምር ብር 149,457,591.52 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

- ዩኒቨርሲቲው ከደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት በቤንች ማጂ ዞን የሚዛን አማን ከተማ ቤቶች ል/ፕሮ/ቅ/ጽ/ቤት 120 መኖሪያ ቤቶችና 20 የንግድ ቤቶች ለመግዛጽ ውል ገብቶ ለከፈለው ቅድሚያ ክፍያ **ብር 10,000,000.00** በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው ላልተረከበው ንብረት እንደ ወጪ መዝግቦ ሪፖርት ያደረገ ሲሆን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገንዘቡን ለመቀበሉ የሚያረጋግጥ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፣

- ብር 3,499,999.98 ለጀኔሬተር ግዥ በሚል ያለአግባብ በሰኔ 30/2004 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ መሆን የነበረበት ገንዘብ ከመደበኛው በጀት አካውንት ወደ ውስጥ ገቢ አካውንት እንዲዛወር ተደርጎ የተቀመጠ መሆኑ፣

- ለተክለጻዲቅ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ብር 775,518.28 ሲከፈላቸው ክፍያ ያቀረቡት ማስረጃ ለብር 321,587.40 ብቻ በመሆኑ ለቀሪው ብር **453,930.88** ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣

- አይሻ ሱፐር ማርኬት በድምሩ ብር 1,917,458.92 የምግብ እህሎች ላቀረቡበት ክፍያ ሲፈፀም እና ለለገሠ ፈይሳ ህንፃ ሥራ ተቋራጭ በድምር ብር 2,484,579.97 በጠቅላላ ድምር **ብር 4,402,038.89** ክፍያ ሲፈፅም ለክፍያ ማስረጃነት የቀረበው የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፣

  በአጠቃላይ በሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ድምር ብር 18,355,969.75 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

- **በብር 446,062.00** በሆነ ሂሳብ ከመዳን አስመጪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሰርቨር፣ ማኬታ የእጅ በእጅ ሽያጭ አባሪ ደረሰኝ መሆኑ፣

<u>አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒ</u>ብሎር እና ስዊች ግዥ ሲፈጸም አስመጪ ድርጅቱ ገንዘቡን ለመቀበሉ ያወራረደበት **<u>ቨርሲቲ</u>**

- **ብር 333,287.13** ደጋፊ ክፍያ ማስረጃ ሳይኖረው በባንክ ደረሰኝ /Advice/ ብቻ ተከፍሎና በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፣

ጅግጂጋ ዩኒቨርሲቲ

- በድምሩ ብር 41,141,299.89 ለመሠረተ ልማትና የፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ ፕላንት ግብዓት ግዥ ክፍያ ግንባታዎቹ ለመከናወናቸው የክፍያ ማረጋገጫ /Payment Certificate/ ሳይቀርብ፣ ድርጅቶቹ ገንዘቡን ለመቀበላቸው የክፍያ ማስረጃ ደረሠኝ ሳያቀርቡ እና ሌሎች የግንባታውን ደረጃ የሚገልጹ ደጋፊ ማስረጃዎች ሳይቀርቡ ከትምህርት ሚኒስቴር በተጻፈ ደብዳቤ መሠረት ብቻ ተከፍሎና በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፣

- ዩኒቨርሲቲው በብር 576,807.00 ከሳስኮ ኢንዱስትሪያል ድርጅት የትምህርት መሳሪያ ገዝቶ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ለክፍያው የቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ /Credit Sales Invoice/ መሆኑ፣

- **ብር 939,975.79** ለአማል ኮንስትራክሽን ድርጅት የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ክፍያው በውሉ መሠረት የተፈጸመ ለመሆኑ ለማጣራት የግንባታው ውል ያልቀረበ ሲሆን የክፍያ ማስረጃ ደረሰኝ /ኢንቮይስ/ ሳይቀርብ ክፍያው መፈጸሙ ታውቋል፡፡

በአጠቃላይ ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ በድምር ብር 42,658,082.68 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ

- ብር 29,783,000.00 ለመሰረተ ልማትና የፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ ፕላንት ግብዓት ግዥ በሚል ለGIZ-IS ክፍያ ለፈጸመበት ሂሳብ የወጪ ማስረጃ (ደጋፊ ማስረጃዎች) ሳይቀርብ በወጪ የተያዘ መሆኑ ታውቋል፡፡

ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ

- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ለግንባታ ብር 7,725,723.58 ክፍያ የፈጸመበት የክፍያ ሰርተፊኬት ማስረጃ ፎቶ ኮፒ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

አርባምንጭ ዩኒቨርስቲ

- አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ለግንባታ ወጪ ያደረገው ሂሳብ ትክክለኛነት ሲጣራ፣ በአማካሪ መሀንዲስ የጸደቀ ማስረጃ እና ለዋጋ ማስተካከያው መነሻ

የሆኑ ማስረጃዎች ሳይቀርቡ ብር 1,309,978.23 የዋጋ ማስተካከያ (Price Adjustment) ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም ያልተሟላ ማስረጃዎች እንዲሟሉ ለወደፊቱ የተሟላና ትክክለኛ የወጪ ማስረጃ የቀረበ መሆኑ ሳይረጋገጥ ሂሳቡ በወጪ እንዳይመዘገብ ክትትል እንዲደርግ አሳስበናል፡፡

3.7 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዥዎች

- ለድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ለተለያዩ ቋሚ ዕቃዎች መግዣ የተላለፈውን ገንዘብ በቀረበው ሰነድ መሰረት በወጪ የተመዘገበው ብር 3,555,855.25 ሲሆን የጨረታ ሰነድ ባለመቅረቡ ዩኒቨርሲቲው የገዛቸው **Duplicating machine, Drawing compass, Desk top dell computer, lap top toshiba** በግልጽ ጨረታ የተፈጸሙ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም:: በመሆኑም ማንኛውም የጨረታ ሰነድ በአግባቡ እንዲቀመጥና ለስራ በሚፈለግበት ግዜ በወቅቱ መቅረብ እንዳለበትና የትምህርት ሚኒስቴር ኃላፊዎችም ሰነዶች በአግባቡ እንዲያዙ ክትትል ማድረግ እንዳለባቸው ገልፀናል፡፡
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በባለሙያ አስተያየትና በናሙና መረጣ በሚል ከፍተኛ ዋጋ ከአቀረቡ ድርጅቶች ግዥ በመፈጸሙ ብር 2,482,320.18 ተጨማሪ ክፍያ የፈጸመ ሲሆን፣ በብር 3,530,994.50 ደግሞ አምስት ተወዳዳሪዎች በናሙና ጥራት ውድቅ ሆነው ከአንድ ድርጅት ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- የዕቃና አገልግሎት ግዥ በደንቡ መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ጨረታ ሳይወጣ፣

- የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ		ብር	1,731,650.00
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ			8,068,748.39
- የመቀሌ ዩኒቨርሲቲ			20,341,230.59
	በድምሩ	በብር	30,141,628.98

ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- አክሱም ዩኒቨርስቲ ብር 1,925,866.00፣ ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ ብር 167,701.94፣ ወልድያ ዩኒቨርስቲ ብር 2,852,604.45 የሚያወጡ ዕቃዎች፣ ወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 6745462.35፣ ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ 3 ጀኔረተሮች ብር 2,971,793.57፣ የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የህክምናና የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 395,975.00 የሚያወጡ የመማሪያ መጻህፍት ጨረታ

ሳይወጣና የዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ ሳይሰበሰብ በለቀማ የተገዙ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ጅማ ዩኒቨርሲቲ፣</u>

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ቁሳቁስ ማምረቻ እና ጥገና ኢንተርፕራይዝ ለሰርቪስ አገልግሎት የሚውሉ አውቶቢሶችን በብር 3,640,000.00 ግልጽ ጨረታ አውጥቶ ግዥውን መፈጸም ሲኖርበት በውስን ጨረታ ግዥን መፈጸሙ፣
- ዩኒቨርሲቲው ኪቶ ፉርዲሳ ምድረ ግቢ ለሚያስገነባው (ሎት1) የውሃ አቅርቦት ሪዘርቫየር፣ የፓምፕ ቤት ፣ አክስዬሽን ፖንድ ፣ የፍሳሽ መስመርና የአጥር ግንባታ ሥራ ባወጣው ጨረታ መሠረት አራት ተቋራጭ የጨረታ ሰነዱን የገዙ ቢሆንም አንድ ተቋራጭ (ዮቴክ ኮንስትራክሽን ፒ.ኤል.ሲ) ብቻ የጨረታ ሰነዱን ሞልቶ በማስረከቡ ዮቴክ ኮንስትራክሽን ያለምንም ተጨማሪ ጨረታ **በብር 212,871,623.63** እንዲያሸንፍ የተደረገ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ጨረታ አውጥቶ **በብር 17,600,000.00** ሚሊዮን በሚሆን ዋጋ ሊፍት ገጠማ ግዥ ሲያከናውን አማካሪ ድርጅቱ ኮንስትራክሽንና ዲዛይን አ/ማ ጨረታ ያወጣ ሲሆን ሁለት ተጫራቾች ብቻ ለውድድር መቅረባቸውና ሁለቱም የተሟላ ሠነድ ባለማቅረባቸው የቴክኒክ ግምገማውን አለማለፋቸውን የተገለጸ ሲሆን ተጨማሪ ጨረታ ለማውጣት በቂ ጊዜ እንደሌለና ሁለቱም ድርጅቶች የጎደለውን ሰነድ አሟልተው ውድድሩ እንዲቀጥል የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የወሰነ ቢሆንም ኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማህበር ከተወዳደሩት ድርጅቶች ውስጥ ለኤለጋንት ዲዛይንና ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ በፃፈው ደብዳቤ ቁጥር 610/00/200/2003 ቀን 26/5/2003 ዓ.ም የተጓደሉ መረጃዎች በማሟላት የጨረታ ግምገማው እንዲቀጥል በተወሰነው መሠረት ድርጅቱ እንዲያሟላ ከተጠቀሱት ጉዳዮች ውስጥ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በፋይናንሽያል ጨረታ ሰነድ ውስጥ የታሸገ በመሆኑ ሰነዱ በሚከፈትበት ወቅት ጨረታ ማስከበሪያው ባይኖር የሚሰጠውን ውሳኔ የሚቀበል መሆኑን በደብዳቤ እዲያረጋግጥ የተደረገ መሆኑ በዚሁ ምክንያት ኤለጋንት ዲዛይንና ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በፋይናንሽያል ጨረታ ሰነድ ውስጥ አልተገኘም በሚል ያለአግባብ ከውድድር ውጭ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን ቢያንስ ፍትሀዊ ውድድር እንዲኖር ሁለቱም ተወዳዳሪዎች ወደ ፋይናንሽያል ውድድር መግባት ሲኖርባቸው ኢኳቶሪያል ቢዝነስ ግሩፕ ኃ.የተ.የግ.ማህበር እንዲያሸንፍ የተደረገ መሆኑ፣

- በብር 6,109,950.00 ከጅማ ዩኒቨርሲቲ ቁሳቁስ ማምረቻ እና ጥገና ኢንተርፕራይዝ ወንበር፣ጠረጴዛ፣የተማሪዎች ቁም ሳጥን/ሎከር/ እና የመሳሰሉት ግዥ ሲፈጸም ያለውድድር ቀጥታ የተሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

በአጠቃላይ በጅማ ዩኒቨርሲቲ በድምር ብር 240,221,573.63 የግዥ አዋጅ ፣ ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዥዎች ተገኝተዋል፡፡

<u>ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ</u>

- ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ቋሚ ዕቃዎች ግዥ ሲፈጽም ለመግዛት በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተዘረዘሩት የዕቃ ፍላጎት በላይ (እንዲገዛ ከተጠየቀው የዕቃ ብዛት በላይ) ድምሩ **ብር 3,316,820.00** በሆነ ሂሳብ ግዥ ፈጽሞ መገኘቱ፣

- ዩኒቨርሲቲው ግልጽ ጨረታ አውጥቶ በብር 1,000,416.50 ከሀቢብ ዳቦና ካፌ እና የተለያዩ ለምግብ አገልግሎት የሚውሉ የምግብ እህሎች በብር 2,047,230.00 ከአይሻ ሱፐር ማርኬት በድምሩ **ብር 3,047,646.50** ውል ገብቶ ግዥ ሲፈጽም ድርጅቶቹ ለ2004 ዓ.ም የታደሰ የንግድ ፈቃድ ላቀረቡ መሆኑ፣

በድምሩ **ብር 438,320.78** በሆነ ሂሳብ የእንስሳት ተዋፅኦ የምግብ ግዥ ሲፈጸም ዩኒቨርሲቲው ጨረታ ለማውጣቱ ጨረታ የወጣበት ሰነድ፣የዋጋ ማወዳደሪያ እና ከአሸናፊው ድርጅት ጋር የገባው ውል ለኦዲት ያልቀረበ በመሆኑ በጨረታ ለመገዛቱ ማጣራት አልተቻለም፣

- ዩኒቨርሲቲው ገመድ አልባ የኢንተርኔት መስመር ዝርጋታ ዕቃዎች ግዥ **ብር 1,952,463.10** በሆነ ሂሳብ ግዥ ሲፈፅም በግዥ መመሪያው መሠረት ግልጽ ጨረታ ወጥቶ ግዥው መከናወን ሲገባው ከኦርቢስ የንግድና ቴክኒክ ማዕከል አክስዮን ማህበር ቀጥታ ግዥ የተፈፀመ መሆኑ ታውቋል፡፡

በአጠቃላይ በሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በድምር ብር 8,755,250.38 የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዥዎች ተገኝተዋል፡፡

<u>ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ</u>

- በጠቅላላ ድምር ብር 303,026.15 ከጨረታ ሰነዱ ላይ ከተዘረዘሩት የዕቃ ፍላጎት ውጭ የተለያዩ ዕቃዎች የተገዙ መሆኑ ታውቋል፡፡

- በድምሩ ብር 328,007.38 ከብሄራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ (አ.ማ) ያለአግባብ የኢንሹራንስ ዋስትና የገዛ መሆኑ ታውቋል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 1,489,994.80 በሆነ ሂሳብ የቋሚ ዕቃ ግዥ ሲፈፅም ግዥው ከብር 100,000.00 በላይ በመሆኑ በግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ በመጠቀም ግዥ መፈፀም ሲኖርበት ብር 1,098,994.80 በሆነ ሂሳብ ከጁፒተር የንግድ ስራ የኮምፒውተር ግዥ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ ግዥ የተፈፀመ መሆኑ እና በብር 391,000.00 ከኤም.ኤፍ.አይ ትሬዲንግና ኦፊስ ሶሉሽንስ ፎቶ ኮፒ ማሽን ግዥ ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ግዥውን የፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

- ድምሩ ብር 496,404.91 የኤሌክትሪክ ዕቃዎች በውስን ጨረታ ግዥ ሲፈፅም እና በድምሩ ብር 407,606.67 በአጠቃላይ ድምር ብር 904,011.58 በሆነ ሂሳብ የግንባታ ግዥ ለመፈፀም የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ ቢያንስ ለሁለት ጊዜ ያልወጣ መሆኑ፣ በውስን ጨረታ የተጋበዙት አቅራቢዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከውድድር በመሰረዛቸው ግዥው ከሁለት አቅራቢ የተፈፀመ ግዥ እንጂ ውስን ጨረታ ነው ብሎ መቀበል አያስችልም፡፡

- በአጠቃላይ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በድምር ብር 3,025,039.91 የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ የተፈጸሙ ግዥዎች ተገኝተዋል፡፡

<u>አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ</u>

- ለሆስፒታል አገልግሎት የሚውል አንሶላና ብርድ ልብስ ከራሄል ሀብተእ በርሄ አስመጪ ግዥ ሲፈጸም አቅራቢው በጨረታ ያሸነፉት አንሶላ ኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ 1ኛ ደረጃ 160x250 አንድ ጥንድ በብር 254.00 ብዛት 727 ሲሆን ገቢ ያደረጉት ግን 1ኛ ደረጃ 156 x230 መሆኑ ፣ ብርድ ልብስ ባለ በግ 160x250 ደብረ ብርሃን አንድ ጥንድ በብር 220.00 ብዛት 50 ማቅረብ ሲኖርባቸው ገቢ ያደረጉት ግን 156 x230 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

3.8 <u>ከውጭ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎች</u>

የትምህርት ሚኒስቴር በብር 171,006,760.27 ለዩኒቨርስቲዎች ከውጭ ሃገር ለገቡ ንብረቶች የቀረጥ ክፍያ ለጉምሩክ የከፈለና በወጪ የመዘገበ ሲሆን፣

- ንብረቱ ለየትኛው ዩኒቨርስቲ/መ/ቤት እንደተላከ እና ዕቃውም ለተቀባዩ ደርሶ ከሆነ በዝርዝሩ መሰረት ተጠቃሚዎቹ ዕቃዎቹን ለመረከቡ ማስረጃ ወይም ሞ/19 ተቆርጦ ተልኮ ከሆነ ያልተጠቀሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

የቀረጥ ክፍያ ሲፈፀም የዕቃዎች ዝርዝር ሊታወቅና ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመደረጉ የሞ/19 ቁጥር ሊጠቃቀስ ወይም ዕቃው ለመድረሱ ማስረጃ ሊያያዝ እንደሚገባ አሣስበናል፡፡

3.9 <u>ማስረጃ ያልተያያዘለት/ያልቀረበለት ወጪ</u>

- የሀገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 11,600,583.94 በሰነድ (በተሰብሳቢነት) ወጪውን በመያዝ ወደ ክልል ለስራ ማስኬጃ በሚል የሚልክ ሲሆን ክልሉ የደረሰው እና የተጠቀመበት መሆኑን በደብዳቤ ከማሳወቅ በስተቀር ወጪው በትክክል ስራ ላይ ለመዋሉ ደጋፊ ማስረጃ ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ የገንዘቡ ባለቤትና ሂሣቡንም ኦዲት ማስደረግ ያለበት የሀገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ በመሆኑ፣ ወጪ ላደረጋቸው ሂሳቦች ወጪው በትክክል ስራ ላይ መዋሉን በማጣራት የተሟላ (ማስረጃ) ደጋፊ ሰነድ ሊያቀርብ እንደሚገባ አሣስበናል፡፡ በተጨማሪም ብር 280,153.80 የሆነ በትምህርት ሚኒስቴር ዓመታዊ የሂሳብ ወጪ ሪፖርት ውስጥ የተካተተ ቢሆንም የወጪ ማስረጃዎቹ ለኦዲት ስራ ባለ መቅረባቸው የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም። ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ድምራቸው **ብር 29,790,947.40** የሆነ የወጪ ሂሳብ ሰነዶች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማ ለመዋሉ ለማረጋገጥ አልተቻለም። የክፍያ ማስረጃዎችን ማቅረብ ካልተቻለ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ሂሣቡ መስተካከል እንዳለበት ገልፀናል።

3.10 <u>በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ቅድሚያ ክፍያ</u>

የትምህርት ሚኒስቴር ለአሥሩ አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎች አገልግሎት የሚውሉ ልዩ ልዩ ፈርኒቸሮችና ተዛማጅ ዕቃዎች ለመግዛት ከትምህርት መሣርያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ጋር በገባው ውል መሠርት ቅድሚያ ክፍያ 30% ብር 27,841,980.00 እና የተለያዩ መሣርያዎች ከውጭ ሃገር ለመግዛት ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተከፈተበት ብር 20,146,515.21 በጠቅላላው ብር 47,988,495.21 የከፈለ ሲሆን በሂሣብ መደብ 4253 (ለዕቃ አቅራቢዎች

ቅድሚያ ክፍያ) መመዝገብ ሲገባው በቀጥታ በ6314 እና በ6313 የወጪ ሂሣብ መደብ በወጪ መዝግቧል፡፡ ተሰብሣቢ ሂሣብ በብር 47,988,495.21 ያነሰ ሲሆን፣ ወጪው ደግሞ በዚሁ የገንዘብ መጠን ከፍ ብሎ ይታያል፡፡ ቅድሚያ ክፍያ የተፈፀመላቸውን ሂሣቦችም ለመከታተል አስቸጋሪ ስለሚሆንና ከተገባለት ውለታ በላይ ክፍያ እንዳይፈፀም (በተለይ ለፈርኒቸር ግዥ) የቁጥጥር ሥርዓት ሊበጅለት እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሣስበናል፡፡ በተጨማሪም የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 841,555.05 የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በወጪ መዝግቦ ተገኝቷል።

3.11 <u>ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለ አግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች</u> <u>ለ'Material on site' የተከፈለ</u>

ጅማ ዩኒቨርሲቲ **ብር 53,431,622.62** ፣ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ **ብር 3,770,825.03** እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ **ብር 2,781,090.69** ሥራ ላይ ለመዋሉ ላልተረጋገጠ የግንባታ ግብአት ዕቃ ወይም " Material on site" ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል። በተመሣሣይ መልኩ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 34,771,018.34 እና ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,196,285.3 በድምሩ ብር 37,967,303.72 በግንባታ ቦታ ያለ ንብረት(Material on site) ተብሎ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል።

<u>ጅማ ዩኒቨርሲቲ</u>

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ የመኖሪያ ቤት በዩኒቨርሲቲው ላላገኙ የአስተዳደር ሰራተኞች በሚል ከብር 500.00 እስከ 250.00 በድምሩ ብር 38,950.00 የመኖሪያ ቤት አበል፣በተለያዩ ኃላፊነት ላይ ተመድበው ለሚሰሩ የአስተዳደር ሠራተኞች የኃላፊነት አበል በድምሩ ብር 169,200.00 ከደንብና መመሪያ ውጭ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣ ዩኒቨርሲቲው ለፋይናንስ የስራ ሂደት፣ ለውስጥ ኦዲት እና ሌሎች የስራ ክፍሎች ማትጊያ/Top Up/ በሚል በድምሩ ብር 309,450.00 ከደመወዝ በተጨማሪ የተከፈለ መሆኑ፣ ከዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ጀምሮ በተለያዩ ኃላፊነት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሠራተኞች በድምሩ ብር 100,500.00 ለኃላፊነት አበል ከመደበኛው በጀት ከሚከፈለው በተጨማሪ ከውስጥ ገቢ ተከፍሎ የተገኘ ሲሆን **በድምሩ ብር 618,100.00**፣በተጨማሪም ዩኒቨርሲቲው ብር 225,281.77 የኮሚቴ አባላት የጨረታ ዶክመንት ያዘጋጁበት በሚል እና ብር 34,879.16 የሪፈራል ሆስፒታል ሠራተኞች የቁሳቁስ ግዥ በርካታ

ውስብስብ ስራዎች በእረፍት ጊዜያቸውና የበአላት ቀንን ጨምሮ ለሰሩበት በሚል በድምሩ ብር 260,160.93 በአጠቃላይ ድምር ብር 878,260.93 አለአግባብ ከደንብና መመሪያ ውጭ ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- በድምሩ ብር 3,115,565.08 የሆነ ሂሳብ ለነዳጅ እና ቅባት ክፍያ እና ዩኒቨርሲቲው ኪቶ ፉርዲሳ ለሚያስገነባው የቢሮ ህንፃ ግንባታ ለራማ ኮንስትራክሽን ኃላ.የተ.የግ.ማ ብር 7,887933.61 በድምሩ ብር 11,003,498.69 በጀት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እስኪለቀቅ በሚል ከውስጥ ገቢ በፎቶ ኮፒ ማስረጃ ክፍያ ተፈጽሞ በወጪ ተመዝግቦ እና ሪፖርት የተደረገ ሲሆን ሂሳቡ ከመደበኛ አካውንት ወደ ውስጥ ገቢ አካውንት ሲተላለፍ በመደበኛ ሂሳብ በድጋሚ በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት ተደርጎ በመገኘቱ ሁለት ጊዜ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ኮምዩኒቲ ት/ቤት በዩኒቨርሲቲው ማስፋፊያ ምክንያት እንዲፈርስ እና ሌላ ቦታ በዩኒቨርሲቲው በጀት እንዲሰራ የተደረገ ቢሆንም ትምህርት ቤቱ ሲሰራ የወጣውን ወጪ ለማካካስ በሚል በካሳ መልክ ከዩኒቨርሲቲው ካፒታል በጀት ብር 8,812,578.98 አለአግባብ ወደ ትምህርት ቤቱ የባንክ ሂሳብ እንዲዛወር የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ከመደበኛ በጀት የራሱ የገቢ ምንጭ ላለውና በራሱ ገቢ ሊንቀሳቀስ ለሚገባው ለተከታታይና ርቀት ትምህርት ፕሮግራም በድምሩ **ብር 3,485,983.75** ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- በአጠቃላይ በጅማ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 77,611,944.97 ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለ አግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች ተገኝተዋል፡፡

<u>ሚዛን -ቴፒ ዩኒቨርሲቲ</u>

- ብር 990,662.26 ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንቶች እና አንዳንድ የአስተዳደር ሰራተኞች ያለአግባብ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣ ብር 343,380.00 የተለያዩ ሰራተኞች በኮሚቴነት ላገለገሉበት በሚል ክፍያ እና ብር 1,049,600.00 የካሪኩለም ሞጁላራይዜሽን የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ሲለበስ /Syllabus/ ላዘጋጁበት በሚል አለአግባብ ለመደበኛ ሥራ ከደመወዝ

ክፍያ ውጪ ተጨማሪ ክፍያ የፈፀመ ሲሆን በድምሩ ብር 2,383,642.26 ዩኒቨርሲቲው ያለአግባብ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፣

- በዋና ውሉ ላይ ሳይኖር ሥራ ተቋራጮች እንዲከፈላቸው ለጠየቁት ለውሀ ቦቴ መኪና ፣ ለጀኔሬተር /Water Truck & Generator/ ኪራይ እና ለለተጠቀሙበት ኤሌክትሪክ ፍጆታ ብር 1,886,334.14 አለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

በአጠቃላይ በሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 8,040,801.43 ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለ አግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች ተገኝተዋል፡፡

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

- በድምሩ ብር 28,700.00 ከመመሪያ ውጭ ለዩኒቨርሲቲው የበላይ ኃላፊዎች የመኖሪያ ቤት አበል የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

- የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በተሻረ መመሪያ ለአስተዳደር ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 485,801.92 እና ለምግብ ቤት ሠራተኞች Hardship Allowance በሚል የደመወዛቸውን 20% ብር 181,033.74 በድምሩ **ብር 666,835.66** አለአግባብ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በአጠቃላይ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 3,447,926.35 ደንብና መመሪያን ሳይከተሉ ያለ አግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች ተገኝተዋል፡፡

መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ

- ዩኒቨርሲቲው በ2003 ዓ.ም መጨረሻ ላይ በሰጠው የክረምት ተከታታይ ትምህርት ለተሳተፉ የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራሮች ፣ የአካዳሚክ ኃላፊዎችና አንዳንድ የአስተዳደር ሰራተኞች የሀምሌ እና የነሀሴ የክረምት ትምህርት አስተዳደራዊ ክፍያ በሚል ያለአግባብ ብር 553,040.00 የትርፍ ሰዓት ክፍያ መከፈሉ ታውቋል፡፡

- ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ የመኖሪያ ቤት ለተሰጣቸው ለዩኒቨርስቲው መምህራን በተጨማሪ ብር 551,700.00 የቤት አበል በጥሬ ገንዘብ አላግባብ የተከፈለ መሆኑ፣

- ወሎ ዩኒቨርስቲ ለቤቶች ልማት ኤጀንሲ ብር 12,632,872.43 የተከፈለ ቢሆንም በገዢና በሻጭ መካከል አስቀድሞ የተፈጸመ ውል ለመኖሩ የውል ስምምነት ዶክመንት እንዲሁም ሻጭ ለገዥ ቤቱን ለማስረከባቸው የርክክብ ቬርባል ለኦዲት ሊቀርብ አለመቻሉ፣

- ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ብር 10,496.99 አላግባብ ለውሎ አበል የተከፈለ መሆኑ፣

- ሰመራ ዩኒቨርስቲ ብር 33,967.70 አላግባብ ለውሎ አበል የተከፈለ መሆኑ ታውቋል፡፡

3.12 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ወጪ ሂሳብ

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 18,870,460.03 ዩኒቨርሲቲው ለአካዳሚክ ምርመር፣ ለላብራቶሪ ዕቃዎችና የህክምና እቃዎች እና ለመኪና፣ ላውንደሪ እና Retinal Camera ላስገባበት ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቀረጥ እንደከፈለ ቢገለጽም ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ወይም ደረሰኙን ሊተካ የሚችል ማረጋገጫ ደብዳቤ ባለመቅረቡ ንብረቱ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ለብር 1,325,755.75 የምግብ አቅርቦት ክፍያ በውሉ መሠረት ገቢ ሆነው አገልግሎት ላይ ለመዋላቸው የሚያረጋግጥ በዩኒቨርሲቲው አሠራር መሠረት የዕለት የምግብ መረከቢያ ቅጽ ካለመዘጋጀቱም በተጨማሪ ምግቡ ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት መሆኑ የታወቀ ሲሆን የዳቦ አቅርቦት ግዥ ክፍያ የሚፈጸመው በቅድሚያ እንደሆነና በተሰብሳቢ ሳይያዝ በቀጥታ በወጪ መመዝገቡ ታውቋል፡፡

3.13 ለሥራ ተቋራጮች ያለአግባብ ብር 7,628,903.54 ቅድሚያ ክፍያ መፈጸሙ

የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ለሥራ ተቋራጮች ቅድሚያ ክፍያ ያደረገው በደንቡ መሠረት መፈጸሙን ሲጣራ፣ የግንባታ ሥራዎች በትምህርት ሚኒስቴር በሚተዳደርበት ጊዜ 30% ቅድሚያ ክፍያ የተሰጠ መሆኑ እየታወቀ በድጋሚ ብር 7,628,903.54 ለሥራ ተቋራጮች ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።

3.14 የወጪውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ

ወሎ ዩኒቨርስቲ

- በ2004 በጀት ዓመት G.I.Z.በተባለው ድርጅት የሚከናወኑ የኮንስትራክሽንና መሠረተ ልማት ግንባታዎች ለኦዲት ሥራ ተፈላጊ የሆኑ ዶክመንቶች ሰነዶችና ልዩ ልዩ መረጃዎች ለኦዲት ሊቀረቡ ባለመቻሉ ካፒታል በጀት ብር 30,164,101.65 ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን እንዲሁም የግንባታው ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ተጠናቅቆ የሚፈለገውን አገልግሎት መስጠቱን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- ብር 11,124,750.54 የያዙ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ቫውቸሮችና ደጋፊ የክፍያ ሰነዶች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ መሆኑ፤

ሠመራ ዩኒቨርስቲ፡-

- ለኦዲት ሥራ ተፈላጊ የሆኑ ዶክመንቶች ሰነዶችና ልዩ ልዩ መረጃዎች ለኦዲት ሊቀረቡ ባለመቻሉ በ2004 በጀት ዓመት ለኮንስትራክሽንና ለመሠረተ ልማት ግንባታ ማስፈጸሚያ የተመደበው ብር 14,000,000.00 ካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን እንዲሁም የግንባታው ሥራ በተያዘለት የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ተጠናቅቆ የሚፈለገውን አገልግሎት መስጠቱን ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- የአስተዳደርና የመምህራን ቢሮዎች፣ወርክሾፕና ላይብረሪ ግንባታ፣ከፕሮጀክቱ ጠቅላላ ዋጋ ብር 28,332,773.92 ላይ ብር 20,143,721.71 ለተቋራጩ የተከፈለ ሲሆን በውል የተመለከተው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና የማስረከቢያ ቀን ማርች 29/2010 ቢሆንም

ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ 1657 ቀናት ወይም ከ 4 ዓመት በላይ የዘገየ ከመሆኑ በተጨማሪ የፕሮጀክቱ ሥራ ሙሉ በሙሉ መቋረጡንና አብይ ኃይሉ የተባሉት የፕሮጀከቱ ሥራ ተቋራጭ የግንባታውን ሥራ በማቋረጥ ጥለው መሄዳቸው እንዲሁም ውል ተቀባይ አብይ ኃይሉ የህንጻ ተቋራጭ በብድር የወሰዱት የሲሚንቶ ዋጋ ብር 642,044.88 ተመላሽ አለመደረጉ የተረጋገጠ ቢሆንም የህንጻ ተቋራጬ በገቡት ውል መሠረት ባለመፈጸማቸው በተቋሙ ላይ ለደረሰው ጉዳትና ኪሳራ G.I.Z.በተባለው ድርጅት እና M.H.ተብሎ በሚጠራው የፕሮጀክቱ ተቆጣጣሪና አማካሪ መሃንዲስ ወይም በተቋሙ ማኔጅመንት ምንም ዓይነት እርምጃ አለመወሰዱ ተረጋግጧል፡፡

4. ተሰብሳቢ ሂሳቦች

4.1 በወቅቱ ያልተሰበሰበ

ተሰብሳቢ ሂሳቦች ወቅታቸውን ጠብቀው የሚሰበሰቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ17 መ/ቤቶች ብር 644,459,753.54 በወቅቱ ያልተወራረደ ሂሳብ ተገኝተል/ዝርዝር በአባሪ-11 ተመልክቷል/

በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ከ10 ዓመት በላይ የቆየው ሰነድ ባፋጣኝ እልባት ሊያገኝና ሌሎችም ተሰብሳቢ ሂሳቦች ተወራርደው ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት ገልጸናል፡፡

4.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ የአሰራር ችግሮች

- በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 5,273.20 በተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር ላይ፣ ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 1,517,936.10 እና ወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 4,063,581.50 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ABNORMAL CREDIT BALANCE) በክሬዲት ላይ ተመልክቷል፡፡ያልተለመደ የሂሣብ ሚዛን ሊያሳዩ የቻሉበትን ምክንያት በማጣራት ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ ሊያዘጋጅ እንደሚገባ በሪፖርታችን ገልጸናል፡፡
- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛ አካውንት ውስጥ ገቢ ተደርጎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ መሆን የነበረበት የግንባታ ተቋራጮች የሲሚንቶ ብድር ተመላሽ ሂሳብ **ብር 8,790,970.02** ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈሰስ ሳይደረግ አለአግባብ በውስጥ ገቢ አካውንት ውስጥ ገቢ ሆኖ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ከኮንስትራክሽን ድርጅቶቹ የሚፈለግ የሲሚንቶ ብድር ብር 2,245,974.10 ተቀንሶ ክፍያ እንዲፈፀም የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት የገለፀ ቢሆንም የፋይናንስ ክፍሉ ግን ሳይቀንስ ክፍያውን የፈጸመ መሆኑ ፣
- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,310,087.73 በተሰብሳቢ ሂሳብ 4211 ለግዥ ሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ እና ብር 3,489,841.88 በሂሳብ መደብ 4251 ለሥራ ተቋራጮች ቅድመ ክፍያ በድምሩ ብር 5,799,929.61 ተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ ቢያዝም የሂሳብ ሠነዱ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑና ከመቼ ጀምሮ የሚፈልግ ሂሳብ እንደሆነ የሚገልጽ ማስረጃ እና ተቀጽላ ሌጀር ያልተቋቋመ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 21,399,805.70 የተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን ሂሳቡን በወሰደው በእያንዳንዱ ግለሰብ ወይም ድርጅት ስም የተከፈተ ሌጀር / subsidiary ledger / የሌለ መሆኑ፣
- ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4201 ብር 1,707,492.41 ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን በእያንዳንዱ ገንዘቡን በወሰደው ሰው/ድርጅት ስም የተከፈተ ተቀጥያ ሌጀር (subsidiary ledger) ባለመኖሩ ያልተወራረደው ሂሳብ ከማን እንደሚፈለግ የማይታወቅ መሆኑ ታውቋል፡፡
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,380,069.18 ለሌሎች ቅድሚያ ክፍያ እና ብር 789,111.40 ለግዥ ሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ በድምሩ ብር 3,169,180.58 ማስረጃዎቻቸው ለኦዲት አለመቅረቡ ታውቋል፡፡

5. ተከፋይ ሂሳብ

- በትምህርት ሚኒስቴር በዴቢት ብር 378,511.65 እና በክሬዲት ብር 64,327,615.57 በሀገር አቀፍ የተምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 2,670,005.52 በድምሩ /ክሬዲት ሲቀነስ ዴቢት/ ብር 66,619,109.44 የተመለከተ ሲሆን፣ ብር 378,511.65 ዴቢት በአመቱ መጨረሻ መመልከቱ ከሂሣብ መርህ አንፃር ትክክል አይደለም፡፡
- ጅማ ዩኒቨርሲቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በአጠቃላይ ብር 25,010,347.22 ተከፋይ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን ምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደቆየ እና ለማን እንደሚከፈል ለማረጋገጥ ሰነዶቹ ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን ብር 110,531.08 በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5035 ባልተለመደ ዴቢት ሚዛን /Abnormal Balance/ ሪፖርት ተደርጎ የተገኘ ሲሆን ሰነዱም ሆነ ስለሁኔታው የቀረበ አጥጋቢ

ምክንያት የሌለ መሆኑ ታውቋል። በተጨማሪም ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 846,728.84፣ ወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 59,741.11፣ ሠመራ ዩኒቨርስቲ ብር 118,124.17፣ ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ ብር 1,121,585.97 እና ሃዋሳ ዩኒቨረስቲ ወንዶ ገነት ኮሌጅ ብር 296,703.55 በዴቢት ተመልክቷል፡፡

- የጎንደር ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 14,143,774.42 የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ እልባት ያላገኙ መሆኑ ታውቋል።
- ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በአጠቃላይ ብር 2,842,529.98 ተከፋይ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን ተቀጽላ ሌጀር ባለመቋቋሙ ለነማን እንደሚከፈልና ለምን ያህል ጊዜ ሳይከፈል እንደቆየ ለማረጋገጥ አልተቻለም።
- አክሱም ዩኒቨርስቲ ብር 909,795.97፣ዲላ ዩኒቨርስቲ ብር 858,611.09፣ ወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 2,029,806.58፣ ሠመራ ዩኒቨርስቲ ብር 313,437.49 ተከፋይ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

  እንደዚህ አይነት ትክክለኛ ያልሆነ ሂሣብ ሲያጋጥም መንስኤው ተጣርቶ ማስተካከያ ማድረግ ተገቢነቱንና ተከፋይ ሂሣቦቹም ተጣርተው ማስተካከያ እንዲደርግባቸው አሣስበናል፡፡

5.1 የመያዣ ሂሳብ

በአምቦ ዩኒቨርስቲ የተከፋይ ሂሳቦች በተገቢው የሂሳብ መደብ እየተመዘገቡ ሪፖርት የሚደረጉ ለመሆናቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ ብር 154,448.67 የኮንትራት መያዣ ሂሳብ በበጀት አመቱ መጨረሻ በሪፖርት እንዳይታይ በሚል የሂሳብ ማስተካከያ (ሪቨርሲንግ) የተሰራ መሆኑ ተረጋግጧል። ዩኒቨርስቲው የፌዴራል መንግስት መስሪያቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያን ሊተገብርና ለሂሳቡም ተገቢው ማስተካከያ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል።

5.2 በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረጉ ሂሣቦች

የአምቦ ዩኒቨርስቲ

- ብር 153,640.78 የደመወዝ ተቀናናሽ ሂሳብ፤
- ብር 20,193.45 ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የተቀነሰ ሂሳብ፤

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

- ከሰራተኞች የተቀነሰ የስራ ግብር ብር 6,360.25
- በሌሎች የመያዣ ሂሳቦች ብር 568,090.16

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

- ከተከፋይ ላይ የሚቀነስ ታክስ ብር 43,268.17

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በወቅቱ ሳይከፈል ተገኝቷል። በተከፋይ ሂሳብ የተያዙት ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ፈሰስ ሊደረግና ማስረጃ ቀርቦለት ሊወራረድ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት ገልጸናል፡፡

6. በጀት

6.1 የበጀት ዝውውርን በተመለከተ

የበጀት ዝውውርን በተመለከተ በፌደራል መንግስት የፕሮግራም በጀት ዝውውር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 13/2004 ተራ ቁጥር 6.3 መሰረት ከአንድ የወጪ መደብ ወደ ሌላ የወጪ መደብ ዝውውር ከተፈጸመ በኋላ ቀደም ሲል በዝውውር ወደ ተቀነሰበት ወጪ መደብ መልሶ ማዛወር እንዲሁም ከተጨመረለት ወጪ መደብ ወደ ሌላ ማዛወር የማይቻል ሲሆን በተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች፣

በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የተጨመረ ብር 1,633,000.00 የተቀነሰ ብር 589,200.00

በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተጨመረ 2,558,884.00 የተቀነሰ ብር 2,286,524

በትምህርት ሚኒስቴር በተመሣሣይ የሂሣብ መደብ የተጨመረ በጀት ብር 514,709.59 እና የተቀነሠ በጀት ብር 15,000,000.00 ተመልክቷል፡፡

6.2 ከበጀት በላይ የወጣና ስራ ላይ ያልዋለ በጀት

ለየመ/ቤቶቹ የተመደበው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ሂሣብ ጋር ሲነፃፀር፤ በ17 መ/ቤቶች ብር 192,593,650.27 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የተደረገና በ29 መ/ቤቶች ብር 2,141,679,692.56 ሥራ ላይ ያልዋለ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-32 ተመልክቷል/

ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም የበጀት ሕግን ከመጣስ ባሻገር መንግሥት ያለውን ውስን ሃብት ለብክነት እንደሚያጋለጥና የታወጀን በጀት አለመጠቀሙ መ/ቤቱ ሊደርስበት ካቀደው ግብ እንዳይደርስ ከማድረጉም ባሻገር ሀገሪቱ ያላትን ውስን ሃብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዳይውል ስለሚያደርግ ዕቅድን ከክንውን ማጣጣም እንደሚገባና ለወደፊቱ የበጀት ዝግጅቱ በጥናትና በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን አሳስበናል፡፡

7. <u>የንብረት አያያዝና አስተዳደር</u>

7.1 የቋሚና አላቂ እቃ አያያዝና አጠባበቅ በንብረት አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ግኝቶች ተመልክተዋል፡፡

- ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ 10 መ/ቤቶች
- ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ 9 መ/ቤቶች
- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ 3 መ/ቤቶች
- ቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ 5 መ/ቤቶች
- አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶችን በመንግስት መመሪያ መሰረት ሳያስወግዱ የተገኘባቸው 7 መ/ቤቶች

እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-33 ተመልክቷል፡፡/

7.2 <u>የንብረት አያያዝ ድክመቶች</u>

በትምህርት ሚኒስቴር በኮሪዶር ላይ የተቀመጡ በርካታ የሽንት ቤት ዕቃዎችና የእጅ መታጠቢያ ሲንኮች ፣ ጠረጴዛና ወንበሮች ፣ በአንድ ዕቃ ግ/ቤት የተለያዩ በካርቶን ታሽገውና ተበታትነው የተቀመጡ የትምህርት መጻሕፍት ፣የማባዣ ወረቀትና በርካታ ቶነሮች ለመኖራቸው በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በICT መጋዘን ውስጥ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች አያያዝ ሲታይ፡-

- ዕቃ ግ/ቤት ሰራተኛ የነበሩት ግለሰብ ወደሌላ መ/ቤት ተመድበው ከሄዱበት ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ እስከአሁን ድረስ አምስቱ እስቶሮች የታሸጉ እና ሙሉ በሙሉ ርክክብ ያልተከናወነ መሆኑን፣
- በታሸገው እስቶር ውስጥ የሚወገዱና የሚያገለግሉ ዕቃዎች ሳይለዩ በአንድ ላይ በመቀመጣቸው ንብረቶች ለብልሽት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

በሃገር አቀፍ ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ የተለያዩ መወገድ የሚገባቸው አሮጌ ወንበሮች፣ጠረጴዛዎች፣ኮምፒውተሮች፣ፕሪንተሮች፣ ሽልፎች፣ ቁምሳጥኖች፣ቨንትሌተሮች፣ የመኪና ጎማዎችና መለዋወጫ እቃዎች፣ ስካነሮችና የተለያዩ የጽህፈት መሳርያዎች ሳይወገዱ ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

<u>ጅማ ዩኒቨርሲቲ</u>

- ግዥ ከመፈፀሙ በፊት በቋሚም ሆነ በአላቂ ዕቃዎች ግምጃ ቤት ውስጥ ንብረት ለመኖሩና ላለመኖሩ የግምጃ ቤት ሰራተኛው የሚያረጋግጥበት አሰራር የሌለ መሆኑ፣
- ጥቅም ላይ ውለው የተመለሱ ዕቃዎች ግምጃ ቤት ውስጥ በርካታ በሽያጭ፣በስጦታ ወይም መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል። ለምሳሌ፡- የመኪና ጎማ 7.5*16 ብዛት 801፣ጎማ 11*20 ብዛት 32፣ ዴል ኮምፒውተር ብዛት 139፣የቁም ፍሪጆች ብዛት 35 እና ሌሎች በርካታ ንብረቶች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ቤት መሰል ትልቅ ፍሪጅ ለበርካታ ዘመን ያለስራ የተቀመጠ መሆኑና የፍሪጅ ዕቃዎቹ በአቀማመጥ ምክንያት ለብልሽት በሚዳርግ ሁኔታ ላይ የሚገኙ መሆኑና አገልግሎት ሳይሰጡ በንብረት ክፍሉ ውስጥ የሚገኙ የመስክ ድንኳኖች ብዛት 18፣ አልጋ ብዛት 21፣ water pamp ከተገዛ ጊዜ ጀምሮ የማይሰራ የሚገኙ መሆኑ፣
- በ Building and Spare part ግምጃ ቤት ውስጥ ያለውን ንብረት በተመለከተ በንብረት ክፍል ውስጥ ባለው ቢን ካርድ ላይ የሚታየው እና በስቶክ ላይ የሚታየውን የንብረት ከወጪ ቀሪ እኩል ለመሆኑ ኦዲት ሲከናወን የተለያየ ከወጪ ቀሪ እንደሚያሳይ ለማየት ተችሏል። (ለምሳሌ፡- ፐላግ አዳብተር በንብረት ክፍል የሚገኝ ብዛት 1,728.00 በቢን ካርድ ላይ 1,426 እና ስቶክ ላይ 1,360.00)

<u>ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ</u>

- በንብረት መጠበቂያ መጋዘን የሚገኙት እቃዎች በዓይነት፣በባህሪይና በሚሰጡት አገልግሎት ተለይተው በሥርዓት ያልተቀመጡ በመሆኑ ከፍተኛ ዋጋና ብዛት ያላቸው እቃዎች ለብልሽትና ለጉዳት የተዳረጉ መሆኑ ፣
- ብዛት ያላቸው ያገለገሉ ዕቃዎች በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ በተለያዩ ስፍራዎች ተበታትነው የሚገኙ መሆኑ፣
- በቀን 19/12/04 ዓ.ም በጣለው ከፍተኛ ዝናብ ምክንያት በሾንጋ ወንዝ አቅራቢያ የሚገኘው የዩኒቨርሲቲው ምግብ ቤት በጎርፍ በመጥለቅለቁ ብር 422,251.08 የሚሆን የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ ከጥቅም ውጭ መሆኑ <u>ለምሳሌ</u>፡- አተር ክክ ብዛት 1800 ኪ.ግ፣ሩዝ ብዛት 3250

ኪ.ግ፣የጤፍ ዱቄት ብዛት ኪ.ግ 1200 እና የመሳሰሉት፣(ይህም ዩኒቨርሲቲውን መሃል ለመሃል ወንዝ አቋርጦ ከማለፉ አንጻር የምግብ ቤቱና የምግብ ዕቃዎች ስቶር አሰራር ግንዛቤ ያልተወሰደበትና የዩኒቨርሲቲው ግንባታ ከማከናወኑ በፊት የስጋት ጥናት / Risk Assesment / ያለማከናወኑን ያሳያል፣)

- በርካታ ወንበሮች ቁጥራቸውን ለማወቅ የማይቻል አገልግሎት መስጠት የሚችሉና የማይችሉ ተደባልቀው በተማሪዎች ምግብ ቤት አካባቢ በሚገኝ ንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣
- 2 የእህል ሚዛን፣19 ባለ 100 ሊትር የውሀ ፕላስቲክ በርሜል፣13 ባለ 20 ሊትር የውሀ ፕላስቲክ በርሜል፣8 ሎከሮች እና በርካታ እንጀራ መጋገሪያ ምጣዶች አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- በተማሪዎች መመገቢያ አካባቢ በሚገኘው የምግብ ግምጃ ቤት ውስጥ 10 ፓኬት ብዛት 10*20 = 200.00 ቹራሊያ ፓስታ፣1 ኩንታል አተር ክክ፣ ሶስት ባለ 100 ኩንታል ምስር ክክ፣ አንድ ኩንታል ጎመን ዘር፣ አንድ ኩንታል መኮረኒ እና 4 ኩንታል ሩዝ ለምግብ አገልግሎት መዋል የማይችሉ የምግብ እህሎች የሚገኙ መሆኑ፤
- በተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ ውስጥ በርካታ ትልልቅ ማሽኖች የሚገኙ ቢሆንም አይነታቸውን፣ንብረቶቹ የዩኒቨርሲቲው ለመሆኑ ማረጋገጫ፣በማን ቁጥጥር ስር እንደሆኑ የሚገልፅ ማስረጃ ሊቀርብ ያልተቻለ መሆኑና አንድ የዳቦ ማቡኪያ ትልቅ mixer 100 OMG ያለጥንቃቄ በመቀመጡ ለብልሽት የተጋለጠ መሆኑ፣
- በሚዛን እና በቴፒ ካምፓስ በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በርካታ ንብረቶች ለቁጥጥር አመቺ ባልሆነ ሁኔታ ተደባልቀውና ተበታትነው የተገኙ መሆኑ፣
- በርካታ የሠራተኛ ነጭ ጋወን በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኝ ቢሆንም መሬት ላይ በመቀመጡ ለብልሽት የተጋለጠ መሆኑ፣
- በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ Bentonite powder, Nitric Acid, Acetone ch3coch3, DL-CAMPHOR ብዛት ያላቸው የተለያዩ ኬሚካሎች ከአመት በላይ ከአላቂ ዕቃ ጋር ተደባልቀው የሚገኙ መሆኑና ኬሚካሎቹ በባለሙያ ታይተው በፍሪጅ መቀመጥ የሚገባቸው ኬሚካሎች ተለይተው መቀመጥ ሲገባቸው ያልተቀመጡ መሆናቸው፣ኬሚካሎቹ ለጤና አስጊ በመሆናቸው

ሽታ ያመጡ መሆኑና የሚመለከተው ዲፓርትመንት ወጪ አድርጎ የማይጠቀማቸው መሆኑ፣

- በሚዛን ካምፓስ የቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አሰር ከምፒውተር ብዛት 98፣ኤች ፒ ሌዘር ጄት ፕርንተር ብዛት 6 ኦኪ ፕሪንተር ብዛት 19፣ዴል ኮምፒውተር ብዛት 7 እና የመሳሰሉት የተበላሹ ንብረቶች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት ሲችሉ በግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣
- በቴፒ-ካምፓስ ቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በጣም በርካታ የሆኑ የተለያዩ በዝናብ ምክንያት የተበላሹ የባዮሎጂ እና የኬሚስትሪ ዕቃዎች መኖራቸውን ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣
- በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የመጡ 7 የማተሚያ ማሽኖች ከ2 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት በሚዛን ካምፓስ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተቀምጠው የተገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

- የመድሃኒት ገቢና ወጪ የሚመዘገብበት ካርድ ምዝገባው ባለመጠናቀቁ ወቅታዊ ከወጪ ቀሪ የማያሳይ መሆኑ፣
- በንብረት ክፍል ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ እና ውጭ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች የሚገኙ ሲሆን የሚሸጡ፣የሚተላላፍ ወይም የሚወገዱ ተለይተው እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፣
- በተመለሡ ዕቃዎች ስቶር ውስጥ ያሉ የተለያዩ ዕቃዋች አቀማመጣቸዉ ሲታይ የተበላሹትንና ያልተበላሹትን ለይቶ ለማወቅ በሚያስቸግር ሁኔታ እንደተቀመጡና አያያዛቸውም ጥንቃቄ በጎደለው መሆኑ ታውቋል፡፡

መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ

- በቋሚና አላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ሲሰሩ የነበሩት ንብረት በኃላፊነት የሚጠብቁ ሰራተኞች በአዲስ ሰራተኛ ሲተኩ በቆጠራ ርክክብ የተፈጸመ ሲሆን በርክክቡ ወቅት የነበሩት ንብረቶች ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲት አልተረጋገጠም፡፡
- ተመላሽ የተደረጉ ዕቃዎች ወደ ንብረት መጋዘን በሚገቡበት ጊዜ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው አንዳንድ ዕቃዎች መኖራቸውና ስላሉበት ሁኔታ የሚገልጽ ዝርዝር መግለጫ የሌላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

- በመለዋወጫ ንብረት መጋዘን አካባቢ የተለያዩ ብረታ ብረቶች እና የወላለቁ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች… ወዘተ ተከማችተው መገኘታቸውና ለንብረቶቹ ተገቢው የቁጥጥር ስርአት ያልተዘረጋ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ለአላቂ ዕቃዎች ቢን ካርድ አለተቋቋመም፡፡
- በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በብልሽት ምክንያት ተመላሽ የተደረጉ ኮምፒዩተሮች መከማቸታቸውን፣ ለጽዳት አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች ከአላቂ ዕቃዎች ጋር መከማቸታቸው፣ ከ2 ዓመት በላይ የሆናቸው የተለያዩ የፕሪንተር ቀለሞች ያለአገልግሎት መገኘታቸው፣ አሮጌ የመኪና ዕቃ መለዋወጫዎች፣ ብረታ ብረቶች መከማቸታቸው እና የግንባታ ቋሚ ዕቃዎች የተለየ መዝገብ አለመቋቋሙ ታውቋል፡፡
- የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ መጽሐፍ ኮፒ አድርጎ የሚጠርዝ ማሽን አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣ ከ2 ዓመት በላይ የሆናቸው ከትምህርት ሚኒስቴር የመጡ በእንጨት የታሸጉ የወጥ ቤት ዕቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ዩኒቨርሲቲው ያለተረከባቸውና አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆኑ፣ የጤፍ ወፍጮ ተገዝቶ አገልግሎት ላይ ያልዋለ መሆኑ እና ለምግብ ዝግጅት የምግብ ጥሬ ዕቃ የሚወጣው በግምት መሆኑ ታውቋል፡፡
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የመድሃኒቶች ምዝገባ ባለመደረጉ ቆጠራውን ከመዝገብ ጋር ለማስታረቅ አለመቻሉ፣ ጊዜአቸው ያለፈባቸው መድሃኒቶች በመድሃኒት ንብረት ክፍል መገኘታቸውና በሌሎች የንብረት ክፍሎች ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ ዕቃዎች መኖራቸው ታውቋል፡፡

<u>ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ፡-</u>

- ከኮድ ኢትዮጵያና ከሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች በዕርዳታ የተገኙ መጻህፍቶች ዓይነትና ብዛት በዝርዝር የሚገልጽ ማስረጃ ካለመኖሩ በተጨማሪ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው መሆኑ፤
- በምግብ ዕቃ ግምጃ ቤት ገቢና ወጪ የሚደረጉ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፤

<u>ዲላ ዩኒቨርቲ፤</u>

- በአገልግሎት ላይ ያልዋሉ ብዛት ያላቸው ቋሚ ንብረቶች/አልጋዎች፤የውኃ ማጠራቀሚያ ታንከሮች /Roto/ በዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ በጸሐይና በዝናብ ለብልሽት የተዳረጉ መሆኑ፤

- ዓይነታቸውና ብዛታቸው ተለይቶ የማይታወቅ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው በርካታ መድኃኒቶችና የህክምና መገልገያ መሣሪያዎች በመጋዘን ውስጥ የተከማቹ መሆኑን፤

ሠመራ ዩኒቨርስቲ

- ተቋሙ የንብረት ማከማቻ መጋዘን የሌለው በመሆኑ ንብረቶች በመማሪያና በላብራቶሪ ክፍሎች የሚገኙ መሆኑ፤
- በግዥ የሚገኙት የምግብ ግባቶችና ሌሎች አላቂና ቋሚ ዕቃዎች መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ /Stock Card/ የሌለ መሆኑ፤

7.3 የነዳጅና የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም ላይ የታዩ ችግሮች

- የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-12464 በቀን 30/10/04 ብቻ 326 ሊትር ነዳጅ የቀዳ መሆኑ፣
- ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የነዳጅ መቆጣጠሪያ ጌጃቸው የሚሠሩ የዩኒቨርሲቲው መኪናዎች ወጥነት ባለው አሰራር የተጓዙበት ርቀት /ኪሎ ሜትር/ እየተሰላ እና እየተቀናነሰ በአግባቡ ነዳጅ መስጠት እንዲያስችል አንድ መኪና በሊትር ስንት ኪሎ ሜትር መሄድ እንሚችል የሚያሳይ ማስረጃ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

7.4 የተሽከርካሪ መኪና አያያዝና አጠቃቀም

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ሊብሬ/የባለቤትነት መታወቂያ/ያልቀረበላቸው በ3 መ/ቤቶች 23 ተሽከርካሪዎች፤

በብልሽት ምክንያት የቆሙ በ1 መ/ቤት 6 ተሽከርካሪዎች፤

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -34 ተመልክቷል/

ስለሆነም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመነጋገር ለተሽከርካሪዎቹ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እንዲዘጋጅላቸውና የዎሙት ስራ ላይ እንዲውሉ አሳስበናል፡፡

8. ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ

ትምህርት ሚኒስቴር በተወሰኑ የኦዲት አስተያየቶች ላይ፣

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

- የጅማ ዩኒቨርሲቲ በ2003 በጀት ዓመት ለዕቃና አገልግሎት ግዢ የወጣው ሂሳብ በመንግሥት የግዢ መመሪያ መሰረት ለመፈጸሙ ኦዲት ተደርጎ ሕጋዊ ሰውነት ኖሮት ራሱን ችሎ ያልተቋቋመና ከተቋሙ የገቢ ማስገኛ ምንጮች አንዱ ከሆነው "የጅማ ዩኒቨርስቲ ኪቶ ፉርዲሣ ግብርና ልማት ኢንተርኘራይዝ" ጋር ተቀባይነት የሌለው ውል በመፈጸም **ብር 3,989,994.98** ለማገዶ እንጨት ግዥ ተብሎ ከዩኒቨርስቲው ሂሳብ አላግባብ ወጪ በማድረግ በኢንተርፕራይዙ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ መሆኑ ተጠቅሶ ገንዘቡ ወደ መደበኛ አካውንት ተመላሽ ተደርጎ ለገንዘብና ኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ እንዲደረግ ያሳሰብን ቢሆንም የእርምት እርምጃ አልተወሰደም፡፡
- ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ለህንፃዎች ግንባታ የተፈቀደው በጀት ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከዩኒቨርሲቲው የገቢ ማስገኛ ምንጮች አንዱ የሆነው የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ በመንገድ ግንባታ ሥራ ምክንያት በመፍረሱ ለካሳ ክፍያ ተብሎ ብር 4,517,544.47 ከተቋሙ ሂሳብ ወጪ በማድረግ በመዝናኛ ክበቡ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ገቢ በማድረግ አላግባብ መከፈሉን አስመለክተን በኦዲታችን የእርምት እርምጃ እንዲወሠድበት ያሳሰብን ቢሆንም ምንም ዐይነት እርምጃ ሳይወሰድበት ተገኝቷል፡፡
- ጅማ ዩኒቨርሲቲ በገቢ ማመንጫነት ላደራጃቸው ዘጠኝ ድርጅቶች የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ እንዲሰራላቸው በ2003 በጀት ዓመት ያሳሰብን ቢሆንም ማስታረቂያው መሠራት አልተጀመረም፡፡

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

- በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ በብር 123,280.00 ከተገዙት 400/Flash Disk 4 GB/ ውስጥ ብር 121,122.00 ዋጋ ያላቸው በቁጥር 393 ፍላሾች የተበላሹና አገልግሎት ላይ ሊውሉ የማይችሉ ሲሆን የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ሳሰብን ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

በመሆኑም በሚሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ መውሰድ የመ/ቤቱን የፋይናንስና የንብረት አስተዳደሩን ከማሻሻሉም በላይ የተጠያቂነት መርህ የበለጠ እየተጠናከረ እንዲሄድ እንደሚያደርግ ገልፀናል፡፡

9. ልዩ ልዩ

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

- ዩኒቨርሲቲው ከመቋቋሙ በፊት ሀጂ ናስር ደረቀ ቡና መቀሸሪያ የሚሰራበትን ቦታ ለዩኒቨርሲቲው አስረክቦ ሲለቅ ድርጅቱ ሲጠቀምበት በነበረው ቦታ ላይ የቡና ገለባ በመኖሩ ገለባው በዝናብ ምክንያት እየታጠበ ወደ ሾንጋ ወንዝ የሚገባ በመሆኑ ወንዙን የሚበክልበት ሁኔታ እና መጥፎ ጠረን የፈጠረ መሆኑ፣

- በሚዛን ካምፓስ ከተማሪዎች ካፍቴሪያ የሚወጣ ተረፈ ምግብ፣የሽንኩርት ልጣጭ፣የድንች ልጣጭ፣አመድ፣ አጥንት እና የመሳሰሉት በመመገቢያ አዳራሽ አቅራቢያ እና በሾንጋ ወንዝ አካባቢ በአግባቡ ባልተሰራ የቆሻሻ ማስወገጃ እየተደፋ በመሆኑ በአካባቢው ላይ መጥፎ ጠረን እና ወደ ወንዙ የሚገባበት ሁነታ በመኖሩ ወንዙ የሚበክልበት ሁኔታና ለጤና አስጊ ደረጃ ላይ ቢደርስም የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ልብሳቸውንና ገላቸውን እንደሚታጠቡበት ለማወቅ የተቻለ መሆኑ፣

- በቴፒ ካምፓስ ጊዜአዊ ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውል በቆርቆሮ የተሰራ መጸዳጃ ቤት እና ገላ መታጠቢያ አብሮ የተሰራ ሲሆን መጸዳጃው ተማሪዎች ማደሪያ ክፍል/ዶርም/ አካባቢ የሚገኝ በመሆኑ እና መጸዳጃውና ገላ መታጠቢያ አብሮ በመሰራቱ መጸዳጃ ቤቱ ቶሎቶሎ በመሙላቱ አካባቢው ላይ መጥፎ ጠረን መፍጠሩና ገላን ለመታጠብ እንደማይቻል በመስክ ጉብኝት ወቅት መታየቱ፣

- ዩኒቨርሲቲው ባጠናው BPR ጥናት መሠረት ሠራተኛ እንደ አዲስ ሲደለደል የሰው ኃብት ልማት አሰተዳደር እና የበጀት፣ ፋይናንስ፣ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ኃላፊ ያልተመደበላቸው ሲሆን በቦታው የነበሩ የቀድሞ ኃላፊዎች ያለውክልና እየሰሩ ሲሆን በተለይ የበጀት፣ ፋይናንስ፣ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ባልተመደቡበትና የዩኒቨርሲቲው ውክልና በሌለበት ሁኔታ በቦታው እየሰሩ እና እስከ ብር 50,000.00 ወጪ የሚያጸድቁ መሆኑ ታውቋል፡፡

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2004 በጀት ዓመት

በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንጻር

ተ.ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት ያቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	አምቦ ዩኒቨርስቲ	30/01/05	147,940,111.00	291,000,590.00	438,940,701.00
2	ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ	30/01/05	80,916,852.00	75,988,030.00	156,904,882.00
3	አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ	30/01/05	46,697,922.00		46,697,922.00
4	መገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	30/01/05	24,870,450.00	218,980,166.73	243,850,616.73
5	ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር	30/01/05	23,209,760.00	390,495,920.00	413,705,680.00
6	ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር	30/02/05	21,986,294.00	20,507,460.00	42,493,754.00
7	ከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ	30/12/04	6,314,250.00		6,314,250.00
8	ትምህርት ሚኒስቴር	05/04/05	331,667,993.33	2,895,043,487.71	3,226,711,481.04
9	የከፍተኛ ትምህርት ስትራተጂ ማዕከል	30/12/04	6,007,880.00		6,007,880.00
10	ዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ	28/01/05	20,849,527.25	13,836,948.35	34,686,475.60
11	ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ	30/02/05	102,812,506.00	105,884,880.80	208,697,386.80
12	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	09/04/05	246,861,381.00	471,626,500.00	718,487,881.00
13	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	18/03/05	325,539,000.00	567,850,000.00	893,389,000.00
14	ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ	11/01/05	352,745,700.00	558,651,000.00	911,396,700.00
15	ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	29/0105	262,423,185.00	616,230,385.00	878,653,570.00
16	ወሎ ዩኒቨርስቲ	10/03/05	104,411,892.67	95,261,458.73	199,673,351.00
17	ወልዲያ ዩኒቨርስቲ	22/12/04	26,998,763.00		26,998,763.00
18	ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ	12/01/05	26,423,041.00		26,423,041.00
19	ሠመራ ዩኒቨርስቲ	27/03/05	92,650,879.40	72,851,670.00	165,502,549.40
20	ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ	17/03/05	333,838,314.90	496.155,999.9	829,994,314.8
21	ዲላ ዩኒቨርስቲ	26/12/04	166,472,693.00	101281967.00	267,754,660.00

ተ. ቁ	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት ያቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
22	ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	07/01/05	20,208,860.00		20,208,860.00
23	አክሱም ዩኒቨርስቲ	04/01/05	150,873,925.00		150,873,925.00
24	ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	28/01/05	80,164,000.00	108,376,130.00	188,540,130.00
25	አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	28/02/05	274,674,200.00	110,000,000.00	384,674,200.00
26	ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ	22/12/04	21,000,000.00	0.00	21,000,000.00
27	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	09/02/05	80,842,380.00	103,454,710.00	184,297,090.00
28	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	14/03/05	405,219,500.00	701,720,000.00	1,106,939,500.00
29	መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	15/12/05	73,005,700.00	103,283,040.00	176,288,740.00

በልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖር

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የልማትና ማኅበራዊ ኦዲት ዳይሬክቶሬት በ28 የመንግስት መሥሪያ ቤቶቹ የ2004 በጀት ዓመት ሂሣብን ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ መያዙ ይታወቃል።

በዕቅድ ከተያዙት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢኒስቲትዩት ሂሳቡን ዘግቶ ማቅረብ ያልቻለ በመሆኑ የኦዲቱ ሥራ ተቋርጧል። የሃያ ሰባቱ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሥራ ግን ተጠናቆ ለየመሥሪያ ቤቶቹ የተዘጋጀው የሥራ አመራር ሪፖርት የተላከ ሲሆን፣ መሥሪያ ቤቶች በተሰጠው የማሻሻያ ሀሣብ መሠረት የወሰዱትን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው ከግብርና እና ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በስተቀር ሁሉም ምላሽ ሰጥተዋል። የኦዲት አስተያየቱን የያዘ የኦዲት ሪፖርትም ለሁሉም መሥሪያ ቤቶች ተልኳል።

1. የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ የዕቅድ ክንውንን በተመለከተ

1.1 ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ ከያዛቸው ሃያ ስምንት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ሃያ ሰባት መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሥራ አጠናቋል። የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ኢኒስቲትዩት ግን ሂሳቡን ዘግቶ ማቅረብ የማይችል መሆኑን በደብዳቤ የገለጸ በመሆኑ የኦዲቱ ሥራ ሊቋረጥ ችሏል። በመሆኑም ዳይሬክቶሬቱ የዕቅዱን 100% የሸፈነ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

በጀትን በተመለከተ መረጃው አባሪ አንድ ላይ ተያይዟል።

1.2 የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ ለሁሉም መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ ለሁለት መሥሪያ ቤቶች የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት፤ ለስምንት መሥሪያ ቤቶች የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት

አስተያየት፣ ለአስራ ሰባት መሥሪያ ቤቶች ደግሞ ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ዝርዝሩ ከአባሪ-2 እስከ አባሪ-6 ተመልክቷል።

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች

በዳይሬክቶሬቱ በ2004 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረገ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሒሳብ

1.1 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

1.1.1 ግኝት

- በገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት ላይ የታዩ ድክመቶች ፤ዋና ዋናዎቹ ፡
  - በየወሩ እና በጀት አመቱ መጨረሻ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራና የማመዛዘን ሥራ ያልተከናወነ መሆኑ ፤
  - የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤
  - ኮሌጁ ለጥቃቅን ወጪዎች ብር 30,000.00 ብቻ በካዝና መያዝ ሲገባው በአንድ ጊዜ ከብር **200,000.00** በላይ ከባንክ ወጪ በማድረግ ወደ ካዝና የሚያስገባ መሆኑ፤
  - ለጥቃቅን ወጪዎች በካዝና ከሚገኘው ገንዘብ በአንድ ጊዜ ከብር **2,000.00** በላይ የሚከፈል መሆኑ ፤
  - ተንጠልጣይ ሰነዶች ሳይወራረዱና ለሒሳብ ክፍል ሳይተላለፉ ከአንድ ዓመት በላይ በገንዘብ ያዥ እጅ የሚቆዩ መሆኑ ፤
- በሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በ2004 በጀት አመት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ያልተከናወነ ሲሆን ፣ ከ2003

በጀት አመት ወደ 2004 በጀት አመት የዞረው የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ ደግሞ ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ መሆኑ፤

- በሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የመደበኛና የእርዳታ ሂሳብ በአንድ የባንክ የሂሳብ ቁጥር የሚንቀሳቀስ መሆኑ፤
- በመንገድ ፈንድ ጽህፈት ቤት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ያልተከናወነና ከመዝገብ (ከሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመዛዘን ያልተደረገ መሆኑ፤
- በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ከሚያዚያ ወር 2004 ዓ.ም ጀምሮ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ያልተደረገና በመዝገብ (በሌጀር) ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ፤

ታውቋል።

1.1.2 የማሻሻያ ሀሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ በጥሬ ገንዘብ አስተዳደሩ መመሪያ ላይ በተቀመጠው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢ የሆነ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

2 ተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ

2.1.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁንና ኦዲት የተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በደንቡና በመመሪያው መሰረት የፈጸሙ መሆኑ ሲጣራ፤በ15 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 235,322,553.47 በወቅቱ

ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ የተገኘ መሆኑ ታውቋል።/ዝርዝሩ በአባሪ-11 ተመልክቷል/

2.1.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ መሰብሰብ የማይችሉት ደግሞ በመመሪያው መሰረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ ይደረግ ዘንድ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

2.2 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ ልዩ የአሰራር ክፍተቶች</u>

<u>በክሬዲት አቅጣጫ የሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመኖሩ</u>

በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 435,339.00 የተሰብሳቢ ሂሳብ ክሬዲት አቅጣጫ የሚታይ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ መሆኑ፤

- <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ምዝገባ ላይ የኮድ ስሕተት ስለመገኘቱ</u>

<u>በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር</u>

- ለሥራ ማስኬጃና ለሠራተኞች ውሎ አበል በቅድሚያ የተከፈለው ሂሳብ ብር 863,969.80 በሂሳብ መደብ 4211 መመዝገብ ሲገባው በ4203 የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፣
- ከሠራተኞች የሚፈለግ የረጅም ጊዜ ብድር ብር 87,678.62 በሂሳብ መደብ 4203 መመዝገብ ሲገባው የግዥ ቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በሚመዘገብበት የሂሳብ ኮድ በ4211 የሂሳብ መደብ የተመዘገበ መሆኑ፣

ታውቋል። በ2003 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት ላይም ሁኔታው እንዲስተካከል አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ሳይስተካከል ተገኝቷል፡፡

2.2.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በክሬዲት አቅጣጫ የተመዘገበው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እንዲሁም ተሰብሳቢ ሂሳቦች የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በተገቢው የሒሳብ መደብ (ኮድ) እንዲመዘገቡ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3 የገቢ ሂሳብ

3.1 ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ

3.1.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቶች ከኪራይ ወይም ከተለያዩ የሽያጭ አገልግሎት የሚፈልጓቸውን ገቢዎች በውሉ መሰረት የሚሰበሰቡ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፡

- በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ብር 2,439,125.79 በመሥሪያ ቤቱ ሥር ከሚገኙ የማምረቻ ህንጻዎች ኪራይ እና ከማምረቻ መሳሪያዎች ሽያጭ ያልተሰበሰበ መሆኑ ፣

- የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን በአዲስ አበባ ስታድየም ዙሪያ የሚገኙ ቤቶች አስተዳደር ቦርድ ባደረገው ጥናትና በወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር በተወሰነው የቤት ኪራይ የዋጋ ተመን መነሻ ዋጋ መሰረት ያልሰበሰበው ገቢ ብር 31,562 .70 የተገኘ መሆኑ፣

- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የግል ጤና አገልግሎቱ ከሚያገኘዉ ገቢ ዉስጥ በመመሪያው መሰረት የሆስፒታሉን ድርሻ 15% ገቢ ያላደረገ መሆኑ፤ ታውቋል።

3.1.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በውዝፍ የሚገኘው የሽያጭ ተሰብሳቢ እንዲሰበሰብ እንዲሁም የሚሰበሰበው ገቢ በተመኑ መሰረት እንዲሰበሰብ መሥሪያ ቤቶቹ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

3.2 በገቢ ግብር ፣ ቀረጥና ታክስ ህግ መሰረት ያልተሰበሰበ ገቢ

3.2.1 ግኝት

- ለቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ባለሙያዎች ከመደበኛ በጀትና ከግል የጤና አገልግሎቱ ከሀምሌ 2003 እስከ ሰኔ 2004 ዓ.ም ድረስ ከተፈጸመው የቤት አበል ክፍያ ብር **1,039,200.00** ላይ የሥራ ግብር ብር **361,800.00** ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

- የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለአፋር ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ከፈጸመው ክፍያ ብር 53,339,727.00 ላይ 2% የቅድሚያ ግብር ታክስ ብር **1,066,483.48** ያልሰበሰበ መሆኑ፣
- የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን ለሰራተኞች ከፈጸመው የቤት አበልና የኃላፊነት አበል ላይ ብር **25,241.70** የሥራ ግብር ተቀናሽ ያላደረገ መሆኑ ፤

3.2.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በገቢ አዋጁ፣ በገቢ ግብር ደንቡና በተላለፈው መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰበው የገቢ ግብርና የቅድሚያ ግብር እንዲሰበሰብ ለወደፊቱም ግብሩ በአግባቡ እየተሰበሰበ ለግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ገቢ እንዲሆን ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

3.3 <u>በገቢ ሒሳብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ</u>

3.31 <u>ግኝት</u>

በፋይናንስ መመሪያው መሰረት የሚሰበሰቡት ገቢዎች በተገቢው የሂሳብ ኮድ ተመዝግበው በሒሳብ ሪፖርት ውስጥ የሚካተቱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡

- የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ከተለያዩ አርእስቶች የሰበሰበውን ገቢ ብር **519,631.63** በሙሉ ያልመዘገበና ለግብርና ቴክኒክ ሞያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ሪፖርት ባለማድረጉ ገቢው በሂሳብ ሪፖርት ላይ ያልተካተተ መሆኑ፤
- የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በ2004 በጀት አመት ብር 82,454.75 ከተለያዩ የገቢ ርዕሶች የሰበሰበውን ገቢ በሙሉ ያልመዘገበ፣ ወደ ባንክ ገቢ ያላደረገ እና ለግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ሪፖርት ባለማድረጉ ገቢው በሂሳብ ሪፖርት ላይ ያልተካተተ መሆኑ፤
- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከቦርድና ለተለያዮ ኮሌጆች የጤና ተማሪዎች የተግባር ልምምድ ሥልጠና

ለሰጠበት ብር 61,560.00 ገቢ የሰበሰበ ሲሆን፣ ገቢው በሂሳብ ሪፖርት ላይ ያልተካተተ መሆኑ፤ ታውቋል።

3.3.2 የማሻሻያ ሀሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ ከውስጥ ገቢ የሚሰበስቡትን ገቢ በመመሪያው መሰረት በመመዝገብ በሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ማካተት ያለባቸው ለመሆኑ አሳስበናል።

3.4 ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያልተደረገ ገቢ

3.4.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቶች የሰበስቡትን ገቢ በሙሉ ወይም ከሚሰበስቡት ገቢ ላይ እንዲጠቀሙ በተፈቀደላቸው መጠን ልክ ተጠቅመው ተራፊውን ገንዘብ ፈሰስ የሚያደርጉ ለመሆኑ ሲጣራ፡

- የአርዳይታ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ብር 8,374,107.36 እንዲሁም የገዋኔ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ብር 9,422,488.83 በድምሩ ብር 17,796,596.19 ከወጪ ከውስጥ ገቢ ከሰበሰቡትና ከግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ከሚላክላቸው ውስጥ ተጠቅመው ከወጪ ቀሪውን ሂሳብ ፈሰስ ያላደረጉ መሆኑ፤
- በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች ሽያጭ የተሰበሰበው ገቢ ብር 1,137,789.85 ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፤

ታውቋል ።

3.4.2 የማሻሻያ ሀሳብ

መሥሪያ ገንዘቡን ፈሰስ እንዲያደርጉ ለወደፊቱም ፈሰስ መደረግ ያለበት ሂሳብ በወቅቱ ፈሰስ ይደረግ ዘንድ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

3.5 ማስረጃ ባለመሟላቱ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያለመቻሉ

3.5.1 ግኝት

መሥሪያ ቤቶች የሰበሰቡት ገቢ በተሟላ መረጃ የተደገፈ ለመሆኑ ሲጣራ የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ከሚያስተዳድራቸው ብሔራዊ ፓርኮች ተሰብስቦ ባንክ ገቢ ለተደረገው ገንዘብ ገቢው ከተሰበሰበበት ደረሰኝ ጋር ተያይዞ ስለማይቀርብ በተሰበሰበው ልክ ገቢ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

3.5.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ባንክ ገቢ ከተደረገበት የባንክ አድቫይስ ጋር ተያይዘው እንዲቀርቡ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ያለበት ለመሆኑ አሳስበናል፡፡

3.6 ባልጸደቀ ተመን ገቢ የሚሰበሰብ መሆኑ

3.6.1 ግኝት

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑ ሲጣራ ፡

- የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች ሽያጭ ገቢ የሚሰበስብ ሲሆን፣ ለሚሰበሰበው ገቢ ግን በሚመለከተው አካል የጸደቀ ተመን የሌለው መሆኑ ፣
- የማሪታይም ጉዳዮች ባለስልጣን ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያስከፍለውን ልዩ ልዩ ታሪፍ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሕግ (በደንብ) ሳያጸድቅ ለባህረኛ መታወቂያ ደብተር መስጠትና ማደስ፤ የመርከብ መኮንኖች የብቃት ማረጋገጫ ዕውቅና የምስክር ወረቀት፤ የወችኪፒንግ የምስክር ወረቀት፤ የጤንነት ምርመራ ማረጋገጫ ውጤት ዕውቅና የምስክር ወረቀት፤ እና የመልቲ ሞዳልትራንስፖርት አከናዋኞች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፤ የንግድ ስራ ፈቃድና የሰነድ መመርመሪያ ክፍያ የምስክር ወረቀት ለሰጠበት ገቢ የሰበሰበ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

3.6.2 የማሻሻያ ሀሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ ለሚሰበስቡት ገቢ የገቢ ተመን ሊኖራቸው ስለሚገባ ታሪፎች በሚመለከታቸው አካላት እንዲጸድቁ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

3.7 በተገቢው የገቢ ሂሳብ መደብ (ኮድ) መሰብሰብ ሲገባው በአደራ ሒሳብ የተሰበሰበ የገቢ ሒሳብ

3.7.1 ግኝት

የገቢ ሂሳቦች የሚሰበሰቡትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በ2004 በጀት ዓመት ብር 21,819,664.39 የሰበሰበ ቢሆንም ገቢው በተገቢው የገቢ የሂሳብ መደብ መሰብሰብ ሲገባው በአደራ ሂሳብ መደብ (5054) እንዲሰበሰብ የተደረገ መሆኑ ታውቋል።

3.7.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ገቢዎች የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ መሰረት በትክክለኛው የገቢ ሂሳብ መደብ (ኮድ) እንዲመዘገቡ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

3.8 በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የታዩ የአሰራር ድክመቶች

3.8.1 ግኝት

የመሥሪያ ቤቶች የገቢ አሰባሰብና አመዘጋገብ ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- **የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ**
  - ኮሌጁ ከተለያዩ አርእስቶች የሰበሰበውን ገቢ ብር **519,631.63** ያልመዘገበና ለግብርና ቴክኒክ ሞያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ሪፖርት ያላደረገ መሆኑ ፤

- ኮሌጁ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ለሰበስበው ገቢ በመረጃ የተደገፈ የገቢ ተመን የሌለው መሆኑ ፤
- ኮሌጁ ከውስጥ ገቢ ከሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ ለኮሌጁ ካፌ ብር 100,000.00 በብድር የሰጠ መሆኑ፤
- ለኦዲት ከቀረበው የገንዘብ መቀበያ ሰነድ ቁጥር 05101- 05150 ውስጥ የገንዘብ መቀበያ ሰነድ ቁጥር 05104 ለኦዲት ሥራው ያልቀረበ መሆኑ፤
- ከቁጥር 06501-06550 እና 05701-05750 የሆኑ ሁለት የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ፓዶች ከዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ የተደረጉ ቢሆንም በኦዲት ወቅት ያልቀረቡ መሆኑ፤

☛ **<u>የሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ</u>**

- ኮሌጁ በ2003 በጀት ዓመት ብር 20,005.16 ከተለያዩ የገቢ ርዕሶች የሰበሰበውን ገቢ ያልመዘገበ ፣ ወደ ባንክ ገቢ ያላደረገ እና ለግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ሪፖርት ያላደረገ መሆኑ፤
- ኮሌጁ በ2004 በጀት አመት ከሰራተኞች የሰበሰበውን የስራ ግብር ገቢ ብር ብር 4,120.40 በሂሳብ መዝገብ ያልመዘገበ ከመሆኑም በተጨማሪ ከሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ ብር 3,009.15 ለግብር ሰብሳቢው አካል ገቢ ያላደረገ መሆኑ፤
- የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የከፍተኛ ትምህረት የወጪ መጋራት ክፍያን ያልሰበሰበ መሆኑ ፤

☛ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል የመያዣና የተመላሽ ሂሳብ በመዝገብ (በሌጀር) የማይመዘገብ፤ ከወጪ ቀሪው የማይታወቅ እንዲሁም በፋይናንስ መመሪያው መሰረት በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ እንዲታይ ያልተደረገ መሆኑ ፤

☛ ለቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ለልዩ ፋርማሲ የዕለት ገንዘብ መቀበያ የሚያገለግል ደረሰኝ በገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፍቃድ ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ ታትሞ በሥራ ላይ ውሎ የተገኘ መሆኑ፤

- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የግል ጤና አገልግሎቱ ከሚያገኘዉ ገቢ ዉስጥ በመመሪያው መሰረት የሆስፒታሉን ድርሻ 15% ገቢ ያላደረገ መሆኑ ፤

- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ የመያዣ (የአደራ) ሂሳብ ገቢና የተመላሽ ሂሳብ በመዝገብ (በሌጀር) የማይመዘገብ ፤ ከወጪ ቀሪው የማይታወቅ እንዲሁም በፋይናንስ መመሪያው መሰረት በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ እንዲታይ የማይደረግ መሆኑ፤

3.8.2 የማሻሻያ ሀሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ በመመሪያው መሰረት የገቢ አሰባሰብ ሥርዓቱን ማስተካከል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4 የወጪ ሂሳብ

4.1 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ

4.1.1 ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት መንግሥት ያወጣቸውን የፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ተከትለው ተገቢው የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡

- የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሞያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለሚያስገነባው የሰራተኞች መኖሪያ ቤት ለኮንትራክተሩ የከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 1,252,655.37 እና ኮሌጁና ኮንትራክተሩ በከፈቱት የጋራ የሂሳብ ቁጥር (Joint Account) የገባው የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 1,724,669.63 በድምሩ ብር 2,977,325.00 ሥራው ለመሰራቱ የክፍያ የምስክር ወረቀት እስኪቀርብ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤

- የግብርና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከሙሉ ገብሩ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ኮንስትራክሽን ድርጅት ጋር የሱፐርቪዥን ሥራ ውል በብር 1,569,980.00 የገባ ሲሆን፣ በውሉ መሰረት 30% የቅድሚያ

ክፍያ ብር 470,994.00 ፈጽሟል። ሆኖም ሥራው ለመሰራቱ የክፍያ የምስክር ወረቀት እስኪቀርብ ድረስ የቅድሚያ ክፍያው በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤

- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከመደበኛ በጀት በብር 225,028.54 የፈጸመው የነዳጅ ግዢ ለግሎባል ናሽናል ፕሮጀክት አገልግሎት እንዲውል የተደረገ ቢሆንም ገንዘቡ ተመላሽ ያልተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ገንዘቡ እስኪተካ ድረስ ሂሳቡ በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በወጪ ተይዞ የተገኘ መሆኑ፤

- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ፡

  - ለመድኃኒትና የህክምና ዕቃ ግዥ ብር 3,750,000.00 በሰኔ ወር 2004 መጨረሻ ለመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የፈጸመው የቅድሚያ ክፍያ ፤

  - ለኤም አር አይ ሴንተር ግንባታ ሥራን ለመላኩ ወ/ሰንበት የህንጻ ሥራ ተቋራጭ የተፈጸመው ብር 323,791.67 የቅድሚያ ክፍያ ፤

በድምሩ ብር 4,073,791.67 በመመሪያው መሰረት ሥራው ለመሰራቱ የክፍያ የምስክር ወረቀት እስኪቀርብ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤

- የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ለውሀ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ብር 250,000,000.06 እና ለኦሮሚያ ውሀ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ብር 47,809,267.40 በድምሩ ብር 297,809,267.46 ለቅድሚያ ክፍያ የተፈጸመው ሂሳብ ሥራው ለመሰራቱ የክፍያ የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤

- የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በሳይት ላይ ያሉ እቃዎች ዋጋ ብር 5,115,640.00 ለኮንትራክተሩ ሲተካ በተሰብሳቢ ሒሳብ መመዝገብ ሲገባው ሥራው ለመሰራቱ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ከመሆኑም በተጨማሪ የግዥ መመሪያው በሳይት ላይ ያሉ

ዕቃዎች በገንዘብ እንዲተካ የማይፈቀድ ቢሆንም ውሉ የግዥ መመሪያውን መሰረት አድርጎ ያልተፈጸመ መሆኑ፤

- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በብር 60,000.00 ለግል የጤና አገልግሎቱ ከመደበኛ በጀት የፈጸመው የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ ገንዘቡ ተመላሽ ያለመደረጉ እና ሂሳቡ በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ ፣
- የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከተለያዩ ተቋራጮች የክፍያ የምስክር ወረቀት በቀረበበት ወቅት የመያዣ ሂሳቡ በተከፋይ ሒሳብ (5061) በክሬዲት ሳይመዘገብ ቆይቶ የመያዣው ሂሳብ ተመላሽ ሲደረግ ብር 1,339,670.16 በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤
- የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሥር የሚገኘው የተቀናጀ የመሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 7,085,018.80 እንዲሁም ለኢትዮጵያ ካርታ ስራ ኤጀንሲ ብር 2,317,915.25 በድምሩ ብር 9,402,934.05 ለቅድሚያ ክፍያ የፈጸመው ሂሳብ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፤
- የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ለ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ግንባታ የከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 15,049,315.03 ፤
- ማዕድን ሚኒስቴር ለዳታ ሥራ አመራር (ማኔጅሜንት) ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት የከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ብር 28,630,317.74 ፤
- የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ከውሃና ኢነርጅ ሚኒስቴር የሚተካ ለኢትዮጵያ አየር መንገድ ለሁለት ሰልጣኞች የከፈለው ብር 49,568.00፤

በድምሩ ለብር 363,864,181.49 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል።

4.1.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ለተለያዩ ተቋራጮች የቅድሚያ ክፍያ ሲፈጸም የክፍያ የምስክር ወረቀት ቀርቦ ሂሳቡ በወጪ እስኪመዘገብ ድረስ በመንግሥት የሒሳብ አያያዝ ሥርዓቱ መሰረት በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ እንዲሁም ለውሎ አበል፣ ለነዳጅና ለመሳሰሉት መግዣ ወጪ የሆነው ሂሳብ ከመወራረዱ በፊት ተገቢው ማስረጃ የቀረበላቸው ለመሆኑ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.2 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ ግኝት

በወጪ ለተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ መመሪያው መሰረት ተገቢው የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በበጀት አመቱ መወልወያና መጥረጊያ በብር 98,000.00 እና ለህሙማን አገልግሎት የሚዉል የምግብ ሸቀጥ በብር 3,200.00 በድምሩ የብር 101,200.00 ሲፈጽም በሻጩ የቀረቡት ደረሰኞች በማተሚያ ቤት ያልታተሙ ፣ ተከታታይ ቁጥር የሌላቸውና ህጋዊ የሻጮቹ ድርጅቶች ማህተም ያልታተመባቸው መሆኑ፤

- በዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን የውሎ አበል መቆጣጠሪያና የስራ ክንውኖች መመዝገቢያ ቅጽ ሳይሞላ እንዲሁም ስራው ለመሰራቱ በቅርብ ኃላፊ ሳይረጋገጥ ብር 2,520.00 ለውሎ አበል የተከፈለ መሆኑ፤

  በድምሩ 103,720.00 ተገቢው የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ ታውቋል። እንዲሁም ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ፤

- የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለስልጣን ለውሎአበል ለነዳጅ መግዣ ወጪ ላደረገው ብር 3,223.36 የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ ፤

- የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ለውሎ አበልና መስተንግዶ ወጪ ለሆነው ብር 67,800.00 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

4.2.1 የማሻሻያ ሀሳብ

- የዕቃ ወይም የአገልግሎት ግዥዎች ተፈጽመው የሚቀርቡት ማስረጃዎች በድርጅቶቹ ሥም የታተሙ ህጋዊ ደረሰኝ ለመሆናቸው፤

- በመስክ ሥራ ላይ የቆዩ ሰራተኞች የወጪ ሂሳብ ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ሰራተኞቹ በሥራው ላይ ቆይተው ሥራቸውን አጠናቀው የተመለሱ ለመሆኑ ስራውን ባዘዘው የስራ ክፍል ሊረጋገጥና የቆዩባቸው ቀናትም በዝርዝር በውሎ አበል ቅጾቹ ተሞልቶ በሚመለከታቸው ኃላፊዎች መረጋገጥ እንዳለበት፤ አሳስበናል፡፡

4.3 ደንብና መመሪያ ሳይከተል ያለአግባብ የተፈጸመ ክፍያ

4.3.1 ግኝት

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ደንብና መመሪያን ተከትለው የተፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በ5 መ/ቤቶች በድምሩ 869,414.24 ደንብና መመሪያ ሳይከተል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል።/ዝርዝሩ በአባሪ-23 ተመልክቷል/

4.3.2 የማሻሻያ ሀሳብ

መሥሪያ ቤቶቹ መንግሥት ያወጣቸውን የክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ተከትለው ክፍያ መፈጸም ያለባቸው ለመሆኑ አሳስበናል፡፡

4.4 የግዢ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸመ ግዢ

4.4.1 ግኝት

የግዥ መመሪያውን ሳይከተል በውስን ጨረታ የተፈጸመ ግዥ

ሰኔ 2002 በወጣው የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 23 መሰረት የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ተግባራዊ የሚሆነው ግልጽ ጨረታ ሁለት ግዜ ወጥቶ እቃው በሚፈለገው ጥራትና መጠን ካልተገኘ ቢያንስ አምስት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ መጋበዝ አለባቸው ። ይሁን እንጂ፡

- የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሞያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ፤
    - ከዘቢብ ጎማና ባትሪ ንግድ በብር 179,149.76 በውስን ጨረታ የጎማ ግዥ ሲፈጸም፤ ግዥው በውስን ጨረታ ከመከናወኑ በፊት ግልጽ ጨረታ ያላወጣ ከመሆኑም በላይ በውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ቢያንስ አምስት አቅራቢዎች መጋበዝ ያለባቸው ቢሆንም በአገሪቱ ውስጥ በርካታ የተለያዩ ጎማ አቅራቢዎች ቢኖሩም

አዲስ ጎማንና ብሪጂስቶን ጎማን በማነጻጸርና በሪጂስቶን ጎማ ጠንካራ ነው በሚል የብሪጂስቶን ጎማ አቅራቢ የሆነውን ዘቢብ ጎማና ባትሪ ንግድን ብቻ በመጋበዝ ግዥውን የፈጸመ መሆኑ፤

- ለጽህፈት መሳሪያ ግዥ በመጀመሪያ ግልጽ ጨረታ ወጥቶ ሳተርን ስቴሽነሪ እና ኮምፒውተር አክሰሰሪ አሸናፊ የነበረ ቢሆንም አቅራቢው በሰጠው የአንድ ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ መሥሪያ ቤቱ የጨረታ ዶክመንት ግምገማውን ባለመጨረሱ እና ጊዜው በማለፉ ምክንያት አቅራቢው አቃው በመጋዘን የለም በማለቱ በግልጽ ጨረታ አሸናፊ ከነበረው ሳተርን ስቴሽነሪ እና ኮምፒውተር አክሰሰሪ በውስን ጨረታ በብር 127,840.00 ግዥው ሊፈጸም ችሏል። ሆኖም ድጋሚ ጨረታ መውጣት ሲገባው በግልጽ ጠረታ አሸናፊው የሆነውን ድርጅት በመጋበዝ መጀመሪያ በግልጽ ጨረታ ስጥቶ በነበረው የነጠላ ዋጋ ላይ በመጨመር ተወዳድሮ አሸናፊ መሆኑ፤
- ዱቄትና ጤፉ ከማለቁ በፊት ጨረታ ወጥቶ መገዛት ሲገባው ዱቄቱና ጤፉ ከለቀ በኋላ ግዜ ባለመኖሩ ምክንያት በሚል በብር 463,032.00 ከተባበሩት ዱቄት ፋብሪካ እና ከሸዋ አለም የእህል ንግድ የዱቄት እና የጤፍ ግዥ በውስን ጨረታ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፤

በጠቅላላው በብር 770,021.76 የተፈጸመው ግዥ መመሪያውን ያልተከተለ መሆኑ ታወቋል።

<u>ያለ ጨረታ የተፈጸመ ግዥ</u>

ኦዲት በተደረጉት መሥሪያ ቤቶች የተፈጸሙት ግዥዎች የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ከብር 100,000.00 በላይ የሚፈጽሙ የዕቃ ግዥዎች እንዲሁም ከብር 75,000.00 በላይ የሚፈጸሙ የአገልግሎት ግዥዎች በግልፅ ጨረታ መከናወን እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ የአርዳይታ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ፡

- ጨረታ ሳያወጣ በዋጋ ማወዳደሪያ በብር 167,960.00 የጤፍ ግዥ የፈጸመ መሆኑ ፤

- ኮሌጁ በብር 533,449.88 በጨረታ ሊገዙ የሚገባቸው እቃዎች በተለያዩ ጊዜያት ተከፋፍለው ከተለያዩ ድርጅቶች እንዲፈጸሙ የተደረገ መሆኑ፤

- የግብርና ሚኒስቴር

ለበለስ ኮንሰልቲንግ የግንባታ የማማከር አገልግሎት ለሰጠበት ብር **129,575.69** እንዲሁም የካቴክስ ኢነጂነሪንግ የእርሻ መሬት ለማስተካከል አገልግሎት ለሰጠበት ብር **478,687.50** በድምሩ ብር **608,263.19** ክፍያ ፈጽሚል። ሆኖም ፡

- ለአገልግሎት ግዥው በግዥ መመሪያው መሰረት ጨረታ ያልወጣ መሆኑ፤
- ዱብቲ ለሚገኘው የእርሻ ምርምር ማዕከል የእርሻ መሬት ለማስተካከል ለመኪናና ለማሽነሪ ኪራይ ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም፤ በፌዴራል መንግሥት የግዥ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 2.1 መሰረት ከብር 75,000.00 ሺ.ህ በላይ የሆኑ ግዥዎች ሲፈጸሙ በቂ ቁጥር ያላቸው ተወዳዳሪዎች እንዲሳተፉ አገራዊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ቢያንስ አንድ ግዜ መውጣት ያለበት ቢሆንም ከላይ ለተመለከተው ግዥ ማስታወቂያው በአካባቢው ብቻ እንዲለጠፍ የተደረገ መሆኑ፣
- ሥራው ተሰርቶ ስለመጠናቀቁ ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ያልቀረበ መሆኑ፤

- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፡

ለተሽከረካሪዎች ጥገና አገልግሎት የሚዉል የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ እቃዎችን ግዥ በብር 149,534.29 ከሞኤንኮ ሲፈጽም ግዥዉ በደንቡ መሰረት ጨረታ ያልወጣ መሆኑ ፣

- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከሚስሮይ አለም አቀፍ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በብር 184,233.84 ፤ ከሙተማ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በብር 287,700.00 ፤ እንዲሁም ከፋርማ አክሲዮን ማኅበር በብር 1,206,414.40 በድምሩ

በብር 1,678,348.24 የመድሀኒቶች ፣ የሪኤጀንት እና የህክምና ዕቃዎች ግዥ የፈጸመ ሲሆን ፣ ለግዥው በደንቡ መሰረት ጨረታ እንዲወጣ ያልተደረገ መሆኑ፤

- የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በግዥ መመሪያው መሰረት ቢያንስ በውስን ጨረታ ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ ግዥ መፈጸም ሲገባው በብር 99,322.13 የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ በቀጥታ ከራስ ሆቴሎች ድርጅት የፈጸመ ከመሆኑም በተጨማሪ ከድርጅቱ ጋር ውል ያልገባ መሆኑ ፣

በጠቅላላው ለብር 3,236,877.73 ግዥ ጨረታ ሳይወጣ መፈጸሙ ታውቋል።

<u>የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ</u>

- የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሞያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ፡
  - የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበስብ ከሞኤንኮ በብር 49,802.04 የመለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ የፈጸመ መሆኑ፤
  - ብር 38,355.06 ለተፈጸመው የመኪና ጥገና እንዲሁም በብር 30,076.15 ለተገዛው የጄንሬተር መለዋወጫ በድምሩ ለብር 68,431.21 በቅድሚያ የዋጋ ማወዳደሪያ ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
  - ኮሌጁ ለሚያስገነባው የተለያዩ አይነት የግንባታ ሥራዎች ለሱፐርቪዥን ሥራው ብር 14,000.00 ለኮንትራክት አስተዳደር ሥራው በወር ብር 8,100.00 በጠቅላላው በብር 22,100.00 ከኮንስትራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማህበር ጋር ያለምንም ውድድር ውል የተፈራረመ መሆኑ፤
- በምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት ከጄነራል ኤሌክትሮኒክስ ሰርቪስ ከተባለ ድርጅት በቀረበ የዋጋ ማወዳደሪያ ብቻ በተመሳሳይ ቀን በተለያዩ የወጪ ቫውቸሮች ተከፋፍለው በብር 2,932.50 የኮምፒውተር ጥገና እቃዎች ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የኪቼኔት ግንባታ በብር 72,627.38 እና የምንጣፍና የሴራሚክ ግዢ በብር 44,045.00 በድምሩ የብር 116,672.38 ግዥ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የፈጸመ መሆኑ፤

- **የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል፡**
  - የአይቤከስ ኔትዎርክ ዝርጋታ ሥራ የአገልግሎት ግዥ በብር 4,000.00 ሲፈጽም የዋጋ ማወዳደሪያ ያልሰበሰበ ከመሆኑ በተጨማሪ ሥራው የተከናወነው በሙያው ለመሰማራቱ ምንም መረጃ በሌለው ሲፈን የጽህፈት መሳሪያ ድርጅት መሆኑ፤
  - ለመገናኛ ሬዲዩ ግዥ በብር 20,000.00 ከጃኖራ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እንዲሁም ለመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ግዥ በብር 28,963.93 ከሞኤንኮ በድምሩ በብር 48,963.93 ግዥዎች ሲፈጽም በደንቡ መሰረት የዋጋ ማወዳደሪያ ያልሰበሰበ መሆኑ፤
- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ ለስብሰባ አዳራሽ አገልግሎት የሚውል ኮንፍረንስ ሪከርዲንግ ሲስተም በብር 83,030.00 ከኤቢሲ ትሬዲንግ ግዥ የፈጸመ መሆኑ፤
- የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ በቂ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በብር 278,673.03 የዕቃና የአገልግሎት ግዢዎችን የፈጸመ መሆኑ፣

በጠቅላላው በብር 674,605.09 ለተፈጸሙት ግዥዎች ጨረታ ያልወጣ መሆኑ ታወቋል።

4.4.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ግዥዎች በግዥ መመሪያው መሰረት ለመፈጸማቸው ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ያለበት ለመሆኑ አሳስበናል፡፡

4.5 የንብረት ገቢ ደረሰኝና ዲክላራሲዮን ያልቀረበለት የወጪ ሂሳብ

4.5.1 ግኝት

በፋይናንስ መመሪያው መሰረት በግዥና በዕርዳታ የሚገቡ ዕቃዎች የቀረጥ ሂሳብ ለሒሳብ አሰራር እንዲያመች ጥሬ ገንዘብ ነክ ያልሆነ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑን ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎችም ገቢ ለመሆናቸው በናሙና ኦዲት ሲደረግ ፡

- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከገቢዎችና ግምሩክ ባልሥልጣን በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ አከናውኗል ። ሆኖም ፡

  - ለብር 1,500,985.84 ዲክላራሲዮኑ እና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተያያዘና ሊቀርብ ያልቻለ በመሆኑ፣

  - ለብር **408,302,049.00** ደግሞ ከወጪ ሂሳቡ ጋር የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያያዝ ባለመደረጉና ሊቀርብ ባለመቻሉ፣

አቃዎቹ ገቢ መደረጋቸውን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

- የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከገቢዎችና ግምሩክ ባልሥልጣን በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት የብር 49,832,267.00 የቀረጥ ክፍያ ሂሳብ ምዝገባ ያከናወነ ቢሆንም አቃዎቹ ገቢ ለመደረጋቸው ከወጪ ሂሳቡ ጋር ዲክላራሲዮኑ እና የንብረት ገቢ ደረሰኙ እንዲያያዝ ባለመደረጉ እና እንዲቀርቡም ተጠይቆ ባለመቅረባቸው አቃዎቹ ገቢ ደረጋቸውን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

- በኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ብር 3,926,368.00 ቀረጥ የተከፈለባቸው የህክምና እቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፣

- በሕብረትሥራ ኤጀንሲ በብር 5,284.09 የተገዛው የመኪና የውስጥ ልብስ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣ ታውቋል ።

4.5.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ለጉምሩክ ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎች ሂሳብ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት እቃዎቹ ገቢ ለመደረጋቸው ዲክላራሲዮኑ እና የንብረት ገቢ ደረሰኞቹ እንዲያያዙ መደረግ እንዳለበት እንዲሁም ሌሎች ግዥዎች ተፈጽመው ሂሳቡ እንዲወራረድ ከመደረጉ በፊት በቅድሚያ የተገዙት ንብረቶች ገቢ ለመደረጋቸው መረጋገጥ እንዳለበት አሳስበናል ።

4.6 ያለ በጀት ዓመቱ የተመዘገበ ሂሳብ

4.6.1 ግኝት

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት በ2004 በጀት ዓመት በተፈቀደው የበጀት ድልድል መሠረት መሆኑን እና የበጀት ዓመቱ ሂሣብ በበጀት ዓመቱ የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤በ3 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 7,584,789.91 ከበጀት ዓመት በውጪ ተመዝግበው ተገኝተዋል።/ዝርዝሩ በአባሪ- 27 ተመልክቷል/

ስለሆነም ከበጀት ዓመቱ በፊት ወጪ የተደረጉ ሒሳቦችን ምዝገባ ከበጀት ዓመቱ ምዝገባ ለመለየት እንዲቻል መሥሪያ ቤቶቹ በሂሳብ መግለጫው ላይ ማብራሪያ (Note) እንዲሰጥ (እንዲገለጽ) ያላደረጉ መሆኑ ታውቋል።

4.6.2 የማሻሻያ ሀሳብ

የበጀት ዓመቱ ወጪ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ እና በወጪ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከበጀት ዓመቱ በፊት ወጪ የተደረጉ ሒሳቦችን ምዝገባ ከበጀት ዓመቱ ምዝገባ ለመለየት ይቻል ዘንድ በሂሳብ መግለጫው ላይ ማብራሪያ (Note) መሰጠት (መገለጽ) እንዳለበት አሳስበናል።

4.7 በወጪ ያልተመዘገበ ሒሳብ

4.7.1 ግኝት

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ለህንፃ ተቋራጭ የሚሰጥ ቅድሚያ ክፍያና የመያዣ ሂሳቦች የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

- የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ለተለያዩ የግድብ ግንባታ ሥራዎች የክፍያ ምስክር ወረቀት ቀርቦ ክፍያ ሲፈጸም ለቀነሰው የመያዣ ሂሳብ ብር 10,181,596.98 እና የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ ብር 41,214,693.54 በድምሩ 51,396,290.52 የሂሳብ ምዝገባው ያላከናወነ መሆኑ፤

- የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከተለያዩ ተቋራጮች የክፍያ የምስክር ወረቀት በቀረበበት ወቅት የቀነሰውን የመያዣ ሂሳብ ብር 41,419,848.07 በተከፋይ ሒሳብ ያልመዘገበ መሆኑ፤

- በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ሞያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለሚገነባው የመሰረተ ልማት ግንባታ የክፍያ የምስክር ወረቀት ቀርቦ ለተቀነሰው ብር 452,499.93 የመያዣ ሂሳብ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ተገቢውን ምዝገባ ያላከናወነ መሆኑ፤

- የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ከየተቋራጮቹ ክፍያ ላይ የቀነሰው የቅድሚያ ክፍያ ብር 2,123,500.12፣ የቅድሚያ ግብር ብር 4,116,177.47 እና የመያዣ ሂሳብ ብር 431,792.52 በድምሩ ብር 6,671,470.11 ሳይመዘገብ የተገኘ መሆኑ፤

- የማዕድን ሚኒስቴር ለዳታ ሥራ አመራር (ማኔጅሜንት) ህንጻ ግንባታ ፕሮጀክት የከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ብር 13,856,958.72 ሳይመዘገብ የተገኘ መሆኑ፤

በጠቅላላው ብር 113,797,067.35 ያልተመዘገበ በመሆኑ የወጪ ሂሳቡም በዚሁ መጠን ዝቅ ሊል ችሏል።

4.7.2 የማሻሻያ ሀሳብ

የገ/ኢ/ል/ሚር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ላልተመዘገቡት ሂሳቦች አስፈላጊዉ ማስተካከያ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ምዝገባዎቹ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓቱን ተከትለው ለመመዝገባቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ እናሳስበናል::

4.8 ማስተካከያ ያልተሰራላቸው ያልተከፈሉ የደመወዝ ሒሳቦች

4.8.1 ግኝት

በግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ በተለያዩ ምክንያቶች ላልተከፈሉ የቋሚና የኮንትራት ሰራተኞች ደመወዝ ብር 730,147.01 ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ፤

4.8.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ላልተከፈለው የደሞዝ ሂሳብ በሂሳብ አያያዝ መመሪያው መሰረት ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ፤ ለወደፊቱም ያልተከፈለ የደሞዝ ሂሳብ ሲያጋጥም ወዲያውኑ ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

4.9 በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ

4.9.1 ግኝት

የገቢና የወጪ ሂሳቦች የሚያዙትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት በተገቢው የሒሳብ መደብ የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡ በ8 መ/ቤቶች ብር 13,420,450.80 በተገቢው የወጪ የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ መሆኑ ታውቋል።/ዝርዝሩ በአባሪ-28 ተመልክቷል/

4.9.2 የማሻሻያ ሀሳብ

ወጪዎች ከመመዝገባቸው በፊት በጀት መያዙንና በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ለመመዝገባቸው መረጋገጥ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.10 ከግንባታ ወጪ ሂሳብ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመቀነሱ ማረጋገጥ ያልተቻለ ስለመሆኑ

4.10.1 ግኝት

የካቲት 8/2002 ዓ/ም በቁጥር ታክ/ቀ/5/102 በገገርው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሰረት ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት የተሰጣቸው የመንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ከመጋቢት 1 ቀን 2002 ዓ/ም ጀምሮ ከብር 5,000.00 በላይ ከሚፈጽሙት ግዥ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያውን በመቀነስ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ ማድረግ እንዳለባቸው ያዛል። ይሁን እንጂ፡የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት የ15 ከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት የግንባታ ወጪ ሂሳብ የሚመዘገበው በውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ሲሆን፣ የመንግሥትን ድርሻ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፍለው እና የሚመዘገበው በውሃና ኢነርጅ ሚኒስቴር በመሆኑ እና ምዝገባዎች ባለመጠቃቀሳቸው የተጨማሪ እሴት ታክስ

በህጉ መሰረት ተቆርጦ ለሚመለከተው አካል ገቢ ስለመደረጉ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

4.10.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ከክፍያው ላይ የተጨማሪ እሴት መቀነሱን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ማስረጃው ቀርቦ ከሂሳቡ ጋር ሊያያዝ ይገባል።

4.11 <u>ከውል በላይ የተፈጸመ ክፍያ</u>

4.11.1 <u>ግኝት</u>

የግንባታ ክፍያዎች በውሉ መሰረት የሚፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሞያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ ለሚያስገነባው የተለያዩ አይነት የግንባታ ሥራዎች ለሱፐርቪዥን ሥራው በወር ብር 8,100.00 ለስምንት ወር ብር 64,800.00 መከፈል ሲገባው ብር 140,616.00 በመከፈሉ ምክንያት ከኮንትራክት ውሉ የገንዘብ መጠን በላይ ብር 75,816.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ ታውቋል።

4.11.2 <u>የማሻሻያ ሂሳብ</u>

ከውል ውጪ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ ለወደፊቱ ክፍያዎች ሲፈጸሙ በውሉ መሰረት ለመሆኑ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.12 <u>የግዥ እቅድ ያልተዘጋጀ ሰለመሆኑ</u>

4.12.1 <u>ግኝት</u>

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዓመታዊ እቅድ እያዘጋጁ ለግዥ ኤጀንሲ ማቅረብ ያለባቸው በሆንም የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣንና የመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የግዥ እቅድ ያላዘጋጁና ለኤጀንሲውም ያላኩ መሆኑ ታውቋል።

4.12.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በግዥ መመሪያው መሰረት የግዥ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለግዥ ኤጀንሲ መላክ እንዳለበት አሳስበናል።

5 <u>የተከፋይ ሂሳብ</u>

5.1 <u>ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ</u>

5.1.1 <u>ግኝት</u>

የሂሣብ መግለጫዎች የተዘጋጁት በመንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሠረት መሆኑን እና በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑን እና በደንቡ መሰረት ለሚመለከተው አካል የተከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣በ7 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 43,135,173.52 ተከፋይ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል።የግብርና ሚኒስቴር ፣ በደንቡ መሰረት ያልተከፈለ ብር 825,975.01 የሚገኝ መሆኑ፤ ስለሁኔታው በ2003 በጀት ዓመት የኦዲት ሪፖርት ላይም አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤/ዝርዝሩ በአባሪ-31 ተመልክቷል/

5.1.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የተከፋይ ሒሳቦቹ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ አሳስበናል ።

5.2 <u>አለአግባብ በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበ</u>

5.2.1 <u>ግኝት</u>

የተከፋይ ሒሳቦች ምዝገባ ሁኔታ ሲጣራ በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 2,365,746.50 አለአግባብ በተከፋይ ሂሳብ ተመዘግቦ ተገኝቷል፡፡

5.2.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በተከፋይ ሒሳብ ምዝገባው ሁኔታ ላይ አስፈላጊው ማጣራት ተደርጎ ሂሳቡ እንዲስተካከል አሳስበናል።

5.3 በዴቢት አቅጣጫ የሚታይ ተከፋይ ሒሳብ

5.3.1 ግኝት

የተከፋይ ሂሣብ አጠቃላይ ሌጀር በተቀጽላ ሌጀሮች ላይ ከተመዘገቡት ጋር ተመሳሳይ ለመሆናቸው ሲጣራ በተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ ብር 344,856.43 በዴቢት አቅጣጫ የሚታይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

5.3.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በተከፋይ ሒሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ የተመለከተው ምዝገባ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል።

6 የሒሳብ ሪፖርትን በተመለከተ

6.1 በሒሳብ ሪፖርት ላይ ያልተጠቃለለ ሂሳብ

6.1.1 ግኝት

በግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያና በሥሩ ያሉት ኮሌጆች ከውስጥ ገቢ የሰበሰቡት ገቢና ከገቢው ላይ የተጠቀሙት ሂሳብ በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት በሂሳብ ሌጆሮች ላይ በፋይናንስ ምንጫቸው መሰረት የሚመዘገቡና በዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሚካተቱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በአላጌ፣ አጋርፋና አርጳይታ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጆች የተሰበሰበው የውስጥ ገቢ እንዲሁም ከገቢው ሂሳብ ላይ ወጪ የተደረገው ሒሳብ ብር 45,685,008.00 ከፕሮጀክት ማስተባበሪያው ሂሳብ ጋር ተጠቃሎ ለግብርና ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል። የፕሮጀክት ማስተባበሪያው በኮሌጆቹ የተሰበሰበውን ገቢ፣ ከገቢው ላይ ወጪ የተደረገውን ሒሳብ፣ እንዲሁም ተሰብሳቢና ተከፋይ ሒሳቦችን አጠቃሎ ለግብርና ሚኒስቴር ሪፖርት አለማድረጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም። ለዝርዝሩ አባሪ ሁለት ተያይዟል፡፡

6.1.2 የማሻሻያ ሐሳብ

የኮሌጆች የውስጥ ገቢና ከውስጥ ገቢ ላይ የተጠቀሙት የወጪ ሒሳብ ከማስተባበሪያው የሂሳብ ሪፖርት ጋር ተጠቃሎ ለግብርና ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

7 የዕቃና ንብረት አስተዳደር

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የንብረት አስተዳደር ሥርዓት የፌዴራል መንግሥት ባወጣው አዋጅና የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

7.1 ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት

7.1.1 ግኝት

የንብረት ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፣

- ለቋሚ ንብረት አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ያልተቋቋመባቸው (ምዝገባ ያላከናወኑ) 13 መሥሪያ ቤቶች
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያላደረጉ 3 መሥሪያ ቤቶች
- ቆጠራ ከመዝገብ ያላገነዘቡ 1 መ/ቤት
- ለቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው 7 መ/ቤቶች

መኖራቸው ተውቋል/ዝርዝራቸው በአባሪ-32 ተመልክቷል/

በመሆኑም መሥሪያ ቤቶቹ በንብረት አስተዳደር መመሪያው መሰረት ዓመታዊ ቆጠራ በማድረግ የቆጠራው ውጤት ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር መመዛዘን እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ።

7.2 ሌሎች የንብረት አያያዝ ድክመቶች

- **በግብርና ሚኒስቴር**

  - በእቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ እቃዎች አገልግሎት ከማይሰጡ እቃዎች ጋር ተቀላቅለው የተከማቹ ከመሆኑም በላይ የማያገለግሉ ንብረቶች ቦታ በመያዛቸው አዲስ የገቡ ንብረቶችን ለብልሽት በሚያጋልጥ መልኩ መሬት ላይ የተከማቹ መሆኑ፤

  - የንብረት መጋዘኖች እጅግ ቆሽሸውና እና እቃዎችም በአቧራ ተሸፍነው የሚታዩ መሆኑ፤

- የንብረት መጋዘኖች የእሳት አደጋ መከላከያ የሌላቸው መሆኑ፤
- የአገልግሎት ግዜ ያለፈባቸው የላብራቶሪ ኬሚካሎች፤ በርካታ ሲሚንቶዎች ፤ሰብሎች፤ እጅግ ብዛት ባላቸው ኮንቴነሮች የታሸገ የመሬት ማዳበሪያ እና ሌሎች ቋሚና አላቂ እቃዎች እርምጃ ሳይወሰድባቸው ለረጅም ጊዜ በመጋዘን ውስጥ እና ከመጋዘን ውጭ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- በግብርና ሚኒስቴር አገልግሎት ሰጥተው ተመላሽ ለተደረጉ ቋሚ ንብረቶች የእቃ ገቢ ማድረጊያ ሰነድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤
- በግምጃ ቤት ገቢ የተደረጉ እና በተለይም በ1996 ዓ.ም የተለያየዩ መሥሪያ ቤቶች ሲዋሃዱ ተመላሽ የተደረጉ ንብረቶች በአይነትና አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡት ሳይለዩ ለቁጥጥር በሚያስቸግር ሁኔታ ለረጅም ዓመታት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ ፤

አገልግሎት በማይሰጡ ንብረቶች ላይ በ2003 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት አሰፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ ታውቋል።

- <u>**በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ**</u>
    - ኮሌጁ ስታክ ካርድ ጥቅም ላይ ባለማዋሉ ምክንያት እያንዳንዱ ስታክ የእህል መጠን እና እንቅስቃሴ የማይታወቅ መሆኑ፤
    - በማከማቻ መጋዘኑ የሚገኙ እቃዎች በአይነታቸው ተለይተው የመለያ ኮድ ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
    - ጥቅም ላይ ቢውሉ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የተለያዩ እቃዎች (ዳቦ መጋገሪያ ፣ የዘር መዝሪያ ማሽን ፣ የጸረ አረም መርጫ ማሽን፣ ኮምፐርሰር ፣ የማስተማሪያ የእርሻ መሳሪያዎች እና የመሳሰሉት) ያለአገልግሎት ለረጅም ጊዜ የተቀመጡ በመሆኑ ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፤
    - በበጀት አመቱ መጨረሻ በተከናወነው የንብረት ቆጠራ በማነስ የታዩ የተለያዩ እቃዎች ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያልተደረጉና አስፈላጊው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

- በመጋዘኖች ውስጥ የተበላሹና የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው እቃዎች ከደህናው ዕቃ ተለይተው ያልተቀመጡና በወቅቱም ያልተወገዱ መሆኑ፤
- በቋሚና አላቂ እቃ መጋዘኖች ውስጥ እቃዎች እጅግ በተዘበራረቀና በተዝረከረከ መልኩ የተከማቹ መሆኑ፤
- የእቃ ማከማቻ መጋዘኖቹ የእሳት አደጋ መከላከያ የሌላቸው መሆኑ፤
- በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጁ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ ተመላሽ ለሚደረጉ እቃዎች በተለይ የመለዋወጫ እቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤
- በቋሚና አላቂ እቃ ማከማቻ መጋዘኖች እቃዎች በአግባቡና በሥርዓቱ ካለመደርደራቸው ወይም ከመዝረክረካቸው የተነሳ በቂ መተላለፊያ መንገድ የሌላቸው በመሆኑ ምክንያት መጋዘኖቹ ንጽህናቸውን የጠበቁ አለመሆናቸው ፤
- በአሳሳ የሚገኘው የእቃ ማከማቻ መጋዘን እቃ ከመጋዘን የሚወጣው በሚመለከተው አካል በጸደቀ የእቃ መጠየቂያ አለመሆኑ፤
- አሳሳ በሚገኘው የእህል ማከማቻ መጋዘን እህሉን የያዙ ማዳበሪያዎች በመቀደዳቸው እህሉ በመጋዘኑ ሜዳ ላይ በብዛት ፈሶ የሚታይና ሰው የሚረማመድባቸው መሆኑ፤
- የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው (771 ሊትር ቱ4ዲ የጸረ ቅጠል ሰፋፊ ኬሚካልና 2 ሊትር ሰልፈሪክ አሲድ) በአንድ ክፍል ውስጥ ለረጅም ጊዜ ታሽገውና በመጋዘኖች ውስጥ ከደህናው እቃ ጋር ተቀላቅለው የሚገኙ መሆኑ፤

በንብረት አስተዳደሩ ላይ በታዩት በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች ላይ ቀደም ሲል በ2003 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድባቸው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል።

➢ **<u>በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>**

- በኮሌጁ አልፎ አልፎ እስቶክ ካርድና ቢን ካርድ የተዘጋጀላቸው ቢሆንም ብዛት ላላቸው በመጋዘን ለሚገኙ ቋሚና አላቂ እቃዎች ስቶክ ካርድና ቢን ካርድ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ ፣
- የንብረት መጋዘን ኃላፊዋ እቃዎችን የምትረከበው እቃውን ለመረከብ የሚያስችል ከሚመለከተው ሥራ ክፍል በተሰጠ ትእዛዝና ስፔስፊኬሽን መሰረት ያለመሆኑ ፣
- በመጋዘኖች ውስጥ የተበላሹና የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው እቃዎችና ኬሚካሎች (ጸረ አረም፤ ጸረ ተባይና የአፈር ኬሚካል) ከደህናው እቃ ተለይተው ያልተከማቹና እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑ፣
- በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ እያንዳንዱ እቃ ወደ መጋዘን ሲገባና ሲወጣ በመጠንና በዋጋ ተለይቶ ስቶክ ካርድ ላይ መሆኑ
- በቋሚና አላቂ እቃ እንዲሁም በተመላሽ እቃ ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ አቃዎች እጅግ በተዘበራረቀና በተዝረከረከ ሁኔታ በመከማቸታቸውና በአግባቡና በሥርዓቱ ባለመደርደራቸው ምክንያት፡
- በቂ መተላለፊያ መንገድ የሌላቸው መሆኑ ፣
- አንዳንድ እቃዎች ያለአግባብ ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣
- መጋዘኖቹ ንጽህናቸውንያልተጠበቀና ከጸዱም ረጅም ጊዜ የሆናቸው መሆኑ፣
- የእቃ ማከማቻ መጋዘኖቹ የእሳት አደጋ መከላከያ የሌላቸው መሆኑ ፣
- ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ እቃዎች እርምጃ እንዲወስድባቸው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፣
- የኮሌጁ የዳቦ መጋገሪያ በሰው ኃይል እጥረት በሚል ምክንያት ለረጅም ጊዜ አገልግሎት መስጠት በማቆሙ የተነሳ ለብልሽት እየተዳረገ መሆኑ፣

➢ **<u>በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጁ</u>**

- በማከማቻ መጋዘኑ የሚገኙ እቃዎች በአይነታቸው ተለይተው የመለያ ኮድ ያልተሰጣቸው መሆኑ፤

- በ2004 በጀት አመት የንብረት ቆጠራ የተከናወነ ቢሆንም እስቶክ ካርድ ባለመቋቋሙ ምክንያት የቆጠራውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ ፣
- እቃ የመረከብና መጪ የማድረግ እንዲሁም የመመዝገብ ሥራ በአንድ ሰው የሚከናወን መሆኑ፤
- በመጋዘኖች ውስጥ የተበላሹና የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው እቃዎችና ኬሚካሎች (ማላታይን፤ቦሪክ ሲድ ፓውደር፤ፋርማሊን እና ካርብሪል መድሃኒት) ከደህናው እቃ ተለይተው ያልተከማቹና እንዲወገዱ ያልተደረጉ መሆኑ፤
- ከአንድ አመት በፊት ወደ ኮሌጁ የገቡት የጠብታ መስኖ እቃዎች ያለምንም አገልግሎት በኮሌጁ ቅጥር ግቢ ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጁ አገልግሎት ከሰጡ በኋላ ተመላሽ ለተደረጉ እቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀላቸው መሆኑ፤
- በአላቂና በቋሚ እቃ ማከማቻ መጋዘኖች ውስጥ አቃዎች እጅግ በተዘበራረቀና በተዝረከረከ መልኩ ከመከማቸታቸውም በላይ አንዳንድ እቃዎች ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፤
- የእቃ ማከማቻ መጋዘኑ የእሳት አደጋ መከላከያ የሌለው መሆኑ፤
- በኮሌጁ የሚገኙ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ እቃዎች እርምጃ እንዲወስድባቸው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፤

➢ <u>በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ</u>

- የኮሌጅ የመድኃኒት ክፍል ተረኞች በሚቀያየሩበት ወቅት የመድኃኒት ርክክብ ሳይደረግ ተረኛው ባለሙያ ወደ ሥራ የሚሰማራ መሆኑ፣
- የግል ህክምና አገልግሎት ክፍሉ ከመደበኛ በጀት የሚጠቀመው የአላቂ ህክምና መገልገያ ዕቃዎች በወቅቱ ተመላሽ ባለመደረጋቸው ምክንያት በመደበኛው ሥራው ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽህኖ እያሳደረ መሆኑ፣

- የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸዉ መድሃኒቶች እና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የህክምና እቃዎች ላይ የማስወገድ እርምጃ ሳይወሰድ በንብረት ክፍል ተከማችተዉ የሚገኙ መሆኑ፤•
- ከጥር ወር 2004 ዓ.ም በፊት ያሉት በተለያዩ ምክንያት ተበላሽተዉ በኮሌጁ ጥገና ክፍል ጥገና ተደርጎላቸው የተቀየሩ አሮጌ ንብረቶች ወደ መጋዘን ያልተመለሱ መሆኑ፤
- በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በበጀት ዓመቱ የተገዙት መድኃኒቶች ወደ መድኃኒት ማደያ (መሸጫ) ክፍል ከገቡ በኋላ በመዝገብ ያልተመዘገቡና ከወጪ ቀሪ ሚዛኑን ለማወቅ የማያስችል መሆኑ፣
- በተለያዩ አሮጌ ንብረቶች ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወሰድባቸው በንብረት ክፍል ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን፤ በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ደግሞ መወገድ የሚገባቸው የተለያዩ የተንቃቀሉ የቢሮ ዕቃዎች፣ ጣውላዎችና የመሳሰሉት ንብረቶች ያልተወገዱ ከመሆኑም በተጨማሪ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶች አገልግሎት መስጠት ከሚችሉ አላቂ ንብረቶች ጋር ተደባልቀው የሚገኙ መሆኑ፤

- <u>በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ</u>
  - በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ሰቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ የተቋቋመ ቢሆንም በከፊል እስከ የካቲት 2004 ድረስ ከተመዘገበ በኋላ የተቋረጠ መሆኑ፣
  - በሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ዕቃዎች ተመላሽ ሲደረጉ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረጉና በመዝገብም ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- <u>በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ</u>
  - በዋና የመስክ ዕቃ ግምጃ ቤት የሚያገለግሉ እና የማያገለግሉ ዕቃዎች ባንድ ላይ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- <u>መካኒሳ በሚገኘው የዕቃ መጋዘን</u>
  - ግምጃ ቤቱ በአለቁ የኬሚካል ጠርሙሶች እና በመሳሰሉት እስከ ውጭ ድረስ ተሞልቶ የሚገኝ ሲሆን ባስቸኳይ ካልተወገደ በአካባቢውና በጤና ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል መሆኑ፤

- በግምጃ ቤቱ የሚገኙ ፈሳሽ ኬሚካሎች ብዙ ጊዜ ከመቆየታቸው የተነሳ እየተነኑ እንደሚገኙ እና አንዳንድ የኬሚካል ጠርሙሶችም ደግሞ በመሰበራቸው ምክንያት ኬሚካሉ እየፈሰሰ አካባቢው ለብክለት እየተጋለጠ መሆኑ፤
- አገልግሎት የማይሰጡና ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የድሪሊንግ ቁጥር አንድ ግምጃ ቤት በቆርቆሮ የተሰራና አጥሩም አስተማማኝ ባለመሆኑ ለደኅንነት እና ለጥበቃ ምቹ አይደለም። ነገር ግን በግምጃ ቤቱ ውስጥ በጣም ውድ የሆኑ የድሪሊንግና የመሳሰሉት መለዋወጫ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

➢ **ከውጪ ተገዝተው ገቢ ያልተደረጉ ዕቃዎች**

- በዩኤስ ዶላር 1,620.76 የተገዛው ቢት ብሬከር 17 1/2 እንዲሁም 10,000.00 ዶላር ከሚያወጣው ስታንዳርድ አክሰሰሪስ ፎር ድሪሊንግ ውስጥ ሁለት አዳብተር ቢት ብሬከር ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤
- በዩኤስ ዶላር 812,800.04 የተገዛው የውሃ መቆፈሪያ ሪግ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤
- በዩኤስዶላር 3,235.00 የተገዛው የድሪሊንግና ሌሎች ተጓዳኝ መሣሪያዎች መለዋወጫ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ከተገዙት የመለዋወጫ ዕቃዎች ውስጥ በዩኤስ ዶላር 4,600.00 የተገዙት የመለዋወጫ ዕቃዎች ያልመጡ መሆኑ፤

7.1.2 የማሻሻያ ሀሳብ

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል ተገቢው ጥረት መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

7.3 በነዳጅና የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ

- እያንዳንዱ ተሽከርካሪ ከተገዛበት ጊዜ ጀምሮ የነዳጅ እና ቅባት ፍጆታ

እንዲሁም የመለዋወጫ እና የጥገና ወጪን በግልጽ የሚያሳይ የግል ማህደር የሌላቸው መሆኑ ፣

- ተሽከርካሪዎች በሚጓዙበት ርቀት (ኪሜ) ተሰልቶ ነዳጅ የማይሞላ መሆኑ፣

<u>በግዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

- ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ መኪና የነዳጅ እና ቅባት ፍጆታ እንዲሁም የመለዋወጫ እና የጥገና ወጪ በግልጽ የሚያሳይ የግል ማህደር ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- ተሽከርካሪ መኪናዎቹ በሰአት ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚሄዱ በተቀመጠው የምርመራ ስታንዳርድ መሰረት በሚጓዙበት ርቀት (ኪ.ሜ) ልክ ተሰልቶ ነዳጅ የማይሞላ መሆኑ፤

<u>በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>

ለተሽከርካሪዎች በብዛት ነዳጅ ተገዝቶ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦ ገቢ ከተደረገ በኂላ የተጠቃሚዎች የነዳጅ ጥያቄ ሳይኖር ወዲያው ወጪ የሚደረግ ከመሆኑም በላይ ወጪ ከተደረገ በኂላ በየጊዜው ለተጠቃሚዎች ያለምንም ህጋዊ ማስረጃ የሚታደል መሆኑ፤

☛ **<u>የገቢ ደረሰኝና ሌሎች የህትመቶች አያያዝ</u>**

በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጁ የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች በተከታታይ ቁጥራቸው ቅደም ተከተል መሰረት ከንብረት ክፍል ወጪ የማይደረጉ መሆኑ ፣

7.4 <u>የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም</u>

7.2.1 <u>ግኝት</u>

በየመሥሪያ ቤቶቹ ውስጥ ያለው የተሽከርካሪዎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትና መረጃ አያያዝ በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ሊብሬ ያልቀረበላቸው ተሽከርካሪዎች፤ — በ4 መ/ቤቶች 11
- በብልሽት ምክንያት የቆሙ ተሽከርካሪዎች፤ — በ5 መ/ቤቶች 32

- በተለያዩ ድርጅቶች ሥም ሊቢሬ ያላቸው
  ወደ መ/ቤቱ ስም ያልተቀየረላቸው በ2 መ/ቤቶች 12 ተሽከርካሪዎች
  መኖራቸው ታውቋል:: /ዝርዝሩም በአባሪ -34 ተመልክቷል/

8 የበጀት አጠቃቀም

መሥሪያ ቤቶች የተቀፈደላቸውን በጀት በዓመታዊ እቅዳቸው መሰረት ሥራ ላይ የሚያውሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

8.1 ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ

8.1.1 ግኝት

የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ከውስጥ ገቢ እንዲጠቀም ከተፈቀደለት ገቢ ውስጥ ብር 1,630,094.08 ከበጀት በላይ የተጠቀመ መሆኑ ታውቋል።

8.2 ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነ ሂሳብ

8.2.1 ግኝት

ለየሂሳብ መደቦቹ (ኮዶቹ) ከተደለደለው በላይ ወጪ የሆነው ሂሳብ በ5 መ/ቤቶች ብር 1,395,369.47 በመ/ቤቶቹ አንፃር በአባሪ-32 ተመልክቷል።

8.3 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

8.3.1 ግኝት

ለየመሥሪያ ቤቶቹ የተፈቀደው የመደበኛና የካፒታል ወጪ በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 174,543,827.58 ፤ ከካፒታል በጀት ደግሞ ብር 136,161,586.52 በድምሩ ብር 310,705,414.10 በ24 መ/ቤቶች ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ተገኝቷል /ዝርዝሩ አባሪ-31 ተመልክቷል/

8.3.2 የማሻሻያ ሀሳብ

በበጀት እቅድ ዝግጅት ወቅት እንዲሁም በበጀት አጠቃቀምና አፈጻጸም የበጀት ሕጎን ተከትሎ መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል።

9 ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ

ባለፉት ዓመታት የኦዲት ግኝቶች ላይ ተገቢው እርምጃ የተወሰደ መሆኑ ሲጣራ፣

9.1 ግኝት

- በአላጌ፣ አጋርፋና አርዳይታ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጆች የተሰበሰበው ገቢና እንዲሁም ከገቢው ሂሳብ ላይ ወጪ የተደረገው ሒሳብ እንዲሁም ተሰብሳቢና ተከፋይ ሒሳቦች በድምሩ ብር 31,779,357.45 በዴቢትና በክሬዲት ከፕሮጀክት ማስተባበሪያው ሂሳብ ጋር ተጠቃሎ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ተገልጾ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ በተለያዩ ምክንያቶች ለሰራተኞች ላልከፈለው የደመወዝ ጠቅላላ ወጪ ብር 136,153.81 እና ለተቀናናሽ ሒሳቦች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- <u>የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል፡</u>
  - ለዴንታል ዩኒት ስትሪም ስቴራላዘር ግዥ ለቅድሚያ ክፍያ የፈጸመው ብር 1,141,675.20 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ መመዝገቡ ተገልጾ ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግ አስተያየት በተሰጠው መሰረት ያልተፈጸመ መሆኑ፤
  - ጠምበሎ ትሬዲንግ ከተባለ ድርጅት የዱቄት ሳሙናና የእጅ ሳሙና ግዥ ሲፈጸም በብልጫ የተከፈለው ብር 6,736.02 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
  - የፋርማሲ ግምጃ ቤት ሰራተኞች በየስድስት ወሩ ሲቀያየሩ በኃላፊነት የተረከቧቸውን መድኃኒቶችና መገልገያ ዕቃዎች ተቆጥሮ የሚረካከቡ ቢሆንም ርክክቡ ኦዲት ያልተደረገ መሆኑ፤
  - በመደበኛ ፋርማሲ ዕቃ ግምጃ ቤት የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድኃኒቶች የአገልግሎት ጊዜያቸው ካላለፈባቸው መድኃኒቶች ጋር ተቀላቅለው የሚገኙ መሆኑ፤

- በህክምና መሣሪያዎች ግምጃ ቤት ለአገልግሎት የሚውሉና የማይውሉ የህክምና መሣሪያዎች በአንድነት ተቀላቅለው የሚገኙ መሆኑ ፤

- በሆስፒታሉ ቅጽር ጊቢ ውስጥ ያለ አገልግሎት ቆመው የተገኙ 4-06448፣ 4-4625 እና 4-02835 አሁንም እርምጃ ሳይወሰድባቸው የሚገኙ መሆኑ፤

- የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ለኦዲት ያልቀረቡ መሆኑ በተገለጸው መሰረት የውስጥ የኦዲት ክፍሉ 94 የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች መጥፋታቸዉን ሪፖርት ቢያደርግም በሆስፒታሉ የተወሰደ እርምጃ የሌለ መሆኑ፤

- ከአገልግሎት ውጪ ሆነው በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ አሮጌ ኮምፒውተሮች ጠረጴዛና ወንበሮች የፎቶ ኮፒ ማሽኖች ፕሪንተሮች ዩ.ፒ.ኤስ (UPS) ጎማዎች ፋይል ካቢኔቶች እና ተመሳሳይ ዕቃዎች ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ፤

<u>በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር</u>

- ለተቋራጮች የተከፈለውና በተሰብሳቢ ሒሳብ መያዝ ሲገባው በወጪ ለተመዘገበው የቅድሚያ ክፍያ ሒሳብ ብር **155,841,115.97** ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ ፣

- ከከሰም ግድብና መስኖ ፕሮጀክት ብር **1,874,863.33** ከውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ብር **20,738,321.72** በድምሩ ብር **22,613,185.05** የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ ፣

- ከአፋር ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ያልተሰበሰበ ብር **348,633.70** የቅድሚያ ግብር ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ ፣

- የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር **45,226,370.13** እንዲሁም የመያዣ ሂሳብ ብር **49,014,371.83** በድምሩ **94,240,741.96** ሳይቀነስ ለተቋራጩ ለውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ የተከፈለ መሆኑ፣

- **<u>የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ</u>**
  - በአሮጌ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኙት አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ የሳይንቲፊክ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች እንዲወገዱ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ ኦዲት ወቅትም ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ ፣
  - ጊዜ ያለፈባቸው በርካታ የላቦራቶሪ ኬሚካሎች መካኒሳ በሚገኘው መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ ተገልጾ እንዲወገዱ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ ኦዲት ወቅትም ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ፣
  - የሰሌዳ ቁጥር 4-13342 የሆኑ ተሽከርካሪ መኪና የቻንሲ ቁጥር ከሊቢሬው ጋር የማይመሳሰል መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፣ በዚህ ኦዲት ወቅት ሁኔታውን ለማጣራት ተፈልጎ ሊቢሬው ባለመቅረቡ ማጣራት ያልተቻለ መሆኑ፣
- **<u>የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን</u>**
  - ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ስታዲየም ዙሪያ ከሚከራዩ የንግድ ቤቶች ለኪራይ ገቢ ተመን የዋጋ ማስተካከያ ሳይደረግለት የቆየ መሆኑና በ2004 በጀት ዓመትም የኪራይ ተመን ጥናት የተደረገ ቢሆንም የተመን ለውጥ ያልተደረገ መሆኑ ፣
  - ከክልል ለመጡ ሠልጣኞች በመስክ ሥራ ላይ ላልቆዩበት 3 ቀናት የውሎ አበል ብር 2,520.00 የተከፈለ ሲሆን፣ በተሰጠው አሰተያየት መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣
  - የኢትዮጵያ ክብደት ማንሳት የሰውነት መገንባት ፌዴሬሽን ለአማተር ሰራተኞች ያላግባብ ብር **17,987.00** ለውሎ አበል የከፈለ መሆኑ ተገልጾ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን በተሰጠው አስተያየት መሰረት ብር **9,460.50** ከሚፈለግባቸው ግለሰቦች ከደሞዛቸው ተቆራጭ እየተደረገ ብር **3,109.99** የተሰበሰበ ሲሆን፣ ብር **8,526.50** በሚፈለግባቸው ግለሰቦች ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ፣
  - የፌዴሬሽኑ ንብረት የሆኑትና የጠፉት ሁለት የብረት ዲስኮች

ተመላሽ ያልተደረጉ (ያልተተኩ) መሆኑ፣

- የቀድሞው የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ሲንጋፖር በሄዱበት ወቅት ከተከፈላቸው የአሜሪካን ዶላር 4,125.00 ውስጥ 3,525.00 ዶላር ማስረጃ ያልቀረበለት ከመሆኑም በተጨማሪ ተመላሽ የተደረገው ዶላር 600.00 ዘግይቶ በመሆኑ መክፈል የነበረባቸውን 50% ጭማሪ ሳይከፍሉ መቅረታቸውን እና ማስረጃ እንዲያቀርቡ ወይም ገንዘቡን ተመላሽ እንዲያደርጉ በተሰጠው አሰተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ፣
- በዕርዳታ ለገቡ የስፖርት ትጥቆች፣ ቱታዎች ፣ጫማዎች፣ ለውስጥ ማሊያና ሱሪዎች ለመቆጣጠሪያ የሚሆን ስቶክ ካርድ፣ እና ቢን ካርድ ያልተቋቋመላቸው እና በመጋዘን ያለው ንብረት ምን ያህል እንደሆነ ቆጠራ ያልተደረገላቸው በመሆኑ በትክክል ማወቅ የማይቻል መሆኑ፣

9.1 የማሻሻያ ሀሳብ

መሥሪያ ቤቶች በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት ተገቢ እርምጃ ሊወስዱ እንደሚገባ አሳስበናል ፡፡

አባሪ 1

ኦዲት የተደረገ የበጀት ሽፋን

ተ ራ ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ሥም	የመ/ቤቶቹ የስጋት ደረጃ	የሂሳብ ሪፓርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
				መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	የግብርና ሚኒስቴር	ከፍተኛ 1	18/04/05	208,523,582.33	2,396,392,000.00	2,604,916,182.33
2	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	ከፍተኛ 1	15/03/05	153,805,590.00	122,841,153.00	276,646,590.00
3	የውና ኢነርጂ ሚኒስቴር	ከፍተኛ 1	29/02/05	52,052,160.98	3,092,093,084.40	3,144,145,245.38
4	የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	ከፍተኛ 2	20/04/05	50,445,470.94	184,247,700.00	234,693,170.94
5	የኢትዮጵያ መድኃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	ከፍተኛ 2	07/03/05	23,125,754.39	14,348,000.00	37,473,754.39
6	የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	ከፍተኛ 2	2/4/2005	31,173,660.00	24,950,000.00	56,123,660.00
7	የማዕድን ሚኒስቴር	መካከለኛ	12/03/05	18,537,143.41	83,426,786.20	101,963,929.61
8	የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት	መካከለኛ	21/02/05	2,325,150.00	87,022,970.00	89,348,120.00
9	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዩት	መካከለኛ	26/02/05	11,248,540.00	10,000,000.00	21,248,540.00
10	የትራንስፖርትና ሚኒስቴር	መካከለኛ	16/01/05	15,683,969.90		15,683,969.90
11	የብሄራዊ ነዳጅ መጠባበቂያ ዴፖዎች አስተዳደር	መካከለኛ	12/03/05	11,516,590.00	15,026,850	26,543,440.00
12	የኢትዮጵያ ጤናና ሥነ ምግብ ኢኒስቲትዩት	መካከለኛ	05/03/05	21,260,830	13,721,966.00	34,982,796.00
13	ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	መካከለኛ	23/02/05	18,887,500.00	2,147,000	21,034,500.00
14	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	መካከለኛ	11/03/05	22,637,500.00	5,483,700	28,121,200.00
15	የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ	መካከለኛ	19/02/05	8,758,560.00	3,151,500.00	11,910,060.00

16	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	መካከለኛ	25/12/05	33,102,692.00	27,533,800.00	60,636,492.00
17	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን	መካከለኛ	13/02/05	20,006,235.00		20,006,235.00
18	የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር	መካከለኛ	10/01/05	15,029,000.00		15,029,000.00
19	የኢፌዲሪ ስፖርት ኮሚሽን	መካከለኛ	04/12/04	59,571,656.61	150,889,900.00	210,461,556.61
20	ማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን	ዝቅተኛ	04/01/05	7,257,971.82		7,257,971.82
21	የብሔራዊ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ አስተዳደር	ዝቅተኛ	15/01/05	1,092,600.00		1,092,600.00
22	የህብረት ሥራ ኤጀንሲ	ዝቅተኛ	19/03/05	13,651,270.00		13,651,270.00
23	የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን	ዝቅተኛ	10/11/04	8,756,730.00		8,756,730.00
24	የመንገዶች ፈንድ ጽሕፈት ቤት	ዝቅተኛ	18/12/04	4,283,200.00		4,283,200.00
25	የሰራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር	ዝቅተኛ	05/03/05	14,529,200.00		14,529,200.00
26	የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ	ዝቅተኛ	15/01/05	3,726,000.00		3,726,000.00
27	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	ዝቅተኛ	02/12/04	11,361,313.00		11,361,313.00
	ድምር			842,349,870.38	6,233,276,409.60	7,075,626,726.98

አባሪ 2

ያልተጠቃለለውን ሒሳብ የሚያሳይ ዝርዝር

I. አላጌ ኮሌጅ				
የሒሳቡ ዓይነት	ዴቢት		ክሬዲት	
	ብር	ሳ	ብር	ሳ
የገቢ ሒሳብ			3,874,438	97
የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ	382,596	32		
የባንክ ሒሳብ	760,512	50		
የዝውውር ሒሳብ			856,569	35
የተሰብሳቢ ሒሳብ	1,791,531	74		
የተከፋይ ሒሳብ			62,419	00
የወጪ ሒሳብ	5,488,246	48		
ሐብት(EQUITY)			3,629,459	72
ድምር	**8,422,887**	**04**	**8,422,887**	**04**
II አጋርፋ ኮሌጅ				
የገቢ ሒሳብ			8,242,842	71
የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ	12,789	28		
የባንክ ሒሳብ	3,081,544	26		
የዝውውር ሒሳብ	54,678	17		
የተሰብሳቢ ሒሳብ	304,693	41		
የተከፋይ ሒሳብ			342,939	62
የወጪ ሒሳብ	5,334,475	25		
ሐብት (EQUITY)			202,398	04
ድምር	**8,788,180**	**37**	**8,788,180**	**37**

III አርዳይታ ኮሌጅ				
	ዴቢት		ክሬዲት	
የሒሳቡ ዓይነት	ብር	ሳ	ብር	ሳ
የገቢ ሒሳብ			20,221,174	54
የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ	8,543	98		
የባንክ ሒሳብ	8,120,921	35		
የዝውውር ሒሳብ	4,005,475	00		
የተሰብሳቢ ሒሳብ	2,003,902	33		
የተከፋይ ሒሳብ			309,081	31
የወጪ ሒሳብ	14,335,097	67		
ሐብት (EQUITY)			7,943,684	48
ድምር	28,473,940	33	28,473,940	33
ጠቅላላ ድምር	45,685,008	00	45,685,008	00

የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2004 በጀት ዓመት የኦዲት ዕቅድ ክንውንና ዋና ዋና

የኦዲት ግኝቶች ሪፖርት

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ

የጥሬ ገንዘብ የባንክ ሂሣብ አያያዝ ድክመቶች

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር

- የሣጥን ጉድለት ብር 155,651.62
- በበጀት ዓመቱ በባንክ የተገኘ ገንዘብ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ ማድረግ ሲገባ ከመመሪያ ውጭ በባንክ ያለ ገንዘብ ተብሎ ሪፖርት የተደረገ ብር 18,328,018.41

- **በሰኔ 30/2003 በቆጠራ ከተገኘው በታች ሪፖርት የተደረገ**

- በንግድ ሚኒሰቴር ብር 10,563.77
- በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 14,548.60

ከላይ ለተገለጹት 3 መ/ቤቶች በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በባንክ ያለ ገንዘብ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ /Block/ መደረገ ሲገባው ከመመሪያ ውጭ ገንዘቡ ብሎክ ሳይደረግ ሪፖርት መደረጉ አግባብ አለመሆኑን፣ ለወደፊቱም አሰራሩ እንዲስተካከል፣ ለረጅም ጊዜ የታየው ጉድለት እንዲተካ እርምጃ እንዲወሰድ በንግድ ሚኒስቴር በብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት በሰኔ 30,2004 በቆጠራ ከተገኘው በታች ሪፖርት የተደረገው ሁኔታው ተጣርቶ ምዝገባው እንዲስተካከል በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ፈሰስ ስለአልተደረገው ሂሣብ የገንዘብና ኢኮኖሚ ል/ሚ/ር ሂሣቡ ፈሰስ እንዲደረግ ለባንኮቹ ትዕዛዝ እንዲሰጥ ደብዳቤ መጻፉን ሆኖም ከመስሪያቤቱ አቅም ፈሰስ አለመሆኑን፣ ሂሳቡም የማዕከላዊ ዕዝ መሆኑንና በጥሬ ገንዘብ ጉድለቱ ላይ ክትትል እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቆጠራ ከተገኘው በታች ሪፖርት ስለተደረገው ሁለቱ መ/ቤቶች እያጠሩ መሆኑን በሰጡት መልስና በኦዲቱ ወቅት ገልጸዋል፡፡

2. ተሰብሳቢ ሂሣቦች

2.1 ውዝፍ የሠነድ /ተሰብሳቢ/ ሂሣብ

ስለመንግስት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፤ የስራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዥ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ13 መ/ቤቶች ብር 307,294,534.54 የሰነድ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡/የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ -11 ተመልክቷል/

በመሆኑም ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡ የሀገር መከላከያ ሚ/ር ለሥራ አመራር ሪፖርት በሰጠው መልስ ብር 18,500,490.05 በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ማለት በመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ብር 11,593,098.46 እና በሌሎች 8 ክፍሎች በድምሩ ብር 6,907,391.59 የወደመ፣ የጠፋና የተሰረቀ መሆኑን እና በፋይናንስ ሕግ መሠረት ከመዝገብ ለማስረዣ ኮሚቴ መቋቋሙን፣ ለዝቋላ ስቲል ማምረቻ ፋብሪካ በበጀት ዓመቱ በብድር የተሰጠው ብር 45,000,000.00 እና ከ3 ዓመት በፊት ለብራና ማተሚያ ቤት በብድር የተሰጠው ብር 3,000,000.00 በ2005 በጀት ዓመት በሙሉ እንደሚሰበሰብ፣ በአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ በተሰብሳቢ የሚገኘው ውስጥ ብር 4,213,093.82 በተመለከተ የአስተደደር መምሪያው ምን ያህል እንደሰበሰበ ቀሪው ምን ያህል እንደሆነ ከወጪ ቀሪው እንዲሁም እስካሁን እርምጃ ያልተወሰደባቸው ካሉ በማጣራት እንዲሰበሰብ እርምጃ እንደሚወሰድ ሌሎቹ በተለያየ ምክንያት ሊሰበሰቡ ያልቻሉትን በማጣራት ለውሣኔ እንደሚያቀርብ፣ ከተቋራጮች ስለሚፈለገው ብር 10,627,372.19 ከመከላከያ መሠረተ ልማትና ግንባታ ዘርፍ በተሰጠው ምላሽ መሠረት የመከላከያ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬቱ ክትትል እንደሚያደርግ፣የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በላከው መልስ እስከ 2005 በጀት ዓመት አጋማሽ ብር 4,377,170.82 እንዲወራረድ መደረጉን የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና ሌሎቹ የተሰጠውን አስተያየት የተቀበሉት መሆኑንና የተጠቀሰውን ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን እርምጃ እንደሚወሰዱ በላኩት መልስ ገልጸዋል፡፡ የንግድ ሚኒስቴር በላከው ምላሽ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲቋቋም በጀት እስኪፈቀድለት ከመ/ቤቱ በተለያየ ጊዜ

መከፈሉንና በክፍፍሉ ወቅት ኢንዱስትሪ ሚ/ር ያልመለሰለት ገንዘብ ስለአለ አልከፍልም ማለቱን ጠቅሶ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጋር በጉዳዩ ላይ እንደሚወያይ የፌደራል ፖሊስ ንብረቱ ገቢ ሆኖ ክፍያ ባለመፈጸሙ መሆኑን በላኩት መልስ ገልጸዋል፡፡ ሌሎቹም መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ሂሣቡን ለመሰብሰብ ጥረት እንደሚያደረጉ በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

2.2 በተሰብሳቢ ሂሣብ የታዩ የአሠራር ችግሮች

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሂሣብ መደብ 4201 በተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት የተደረገው ሂሣብ በተቀጽላ ሌጀሮች ድምር ከታየው በብር 1798758.33 በልጦ መገኘቱንና ይህ ባለፉት ኦዲቶችም ልዩነት መታየቱን በመግለጽ ሁኔታው እንዲጣራ አሳስበናል፡፡ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሰጠው መልስ የጽ/ቤቱ ፈቃድ ያላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች ቀጥሮ እንዲጣራ በማድረግ ላይ መሆኑን ገልጿል፡

2.3 የኘራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ

ኤጀንሲው በ2004 በጀት አመት መጨረሻ ከ52 የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሽያጭ ያልተሰበሰበ ቀሪ ሂሳብ ብር 1,490,646,401.65 ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር በቀረበው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት አለማቅረቡን በመግለጽ ኤጀንሲው የፋይናንስ መመሪው በሚያዘው መሰረት በየወሩ ለሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ከሚያቀርበው ሂሳብ ሪፖርት ጋር ያልተሰበሰቡ ቀሪ ሂሣቦችን ማቅረብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡ኤጀንሲው የበጀት ሂሳብ የሚመዘግብበት IBEX ኘሮግራም የተሸጡ ድርጅቶችን ወለድ በየቀኑ ለማስላት የማያስችል በመሆኑ በሪፖርቱ ውስጥ ያልተካተተ መሆኑንና ለወደፊቱ ግን ከሪፖርቱ ጋር አያይዘው እንደሚያቀርብ በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅትና በሰጠው ምላሽ ገልጸዋል፡፡

3. ተከፋይ ሂሣቦች

3.1 በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰኔ 30/2003 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ብር 163,504,599.94 የሠራዊቱ አባላት ደመወዝ ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ሂሣብ የተያዘና ሂሣቡም በወጪ የተመዘገበ መሆኑን በመጥቀስ አሠራሩ ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በመሆኑ እንደማንኛውም የፌደራል መንግሥት መ/ቤት ያልተከፈለ ደመወዝ

በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት ደመወዝ ካልተከፈላቸው አባላት ጥያቄ ሲቀርብ ከገ/ኢ/ል/ማ/ር እየተጠየቀ እንዲከፈል አሳስበናል፡፡ እንዲሁም ከዚህ ሂሣብ ውስጥ ከላይ በ2.1. እንደተጠቀሰው በሥሩ ለሚገኙት ሁለት ድርጅቶች ብር 48,000,000.00 ብድር መስጠቱ አግባብ አለመሆኑን ገልጸናል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በሰጠው መልስ ገንዘቡ በመከላከያ ሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ የባንክ ሂሣብ እንደሚገኝ ገንዘቡን ሙሉ በሙሉ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመለስ እንደማይቻል ሆኖም ገንዘቡ እንዳይከማች ደረጃ በደረጃ ወደ ገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ የሚደረግበት አሠራር መቀየሱንና በዕቅድ መያዙን በላከው መልስ ገልጿል፡፡

3.2 በሀገር መከላከያ ሚ/ር በሂሣብ መደበ 5054 ብር 10,319,949.16 ለረጅም ዓመታት በተከፋይ የተያዘ መሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ አሳብበናል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በላከው መልስ በተለያዩ ዓመታት ከመከላከያ ክፍሎች ወደ መከላከያ ፋይናንስ በጀታዊ ሂሣብ ገቢ ሆኖ ወደ ገ/ኢ/ል/ሚ/ር እንደሆነ የምዝገባ ሥርአቱ የተከፋይ ሂሳብን ከመዝገብየሚያጠፋ አለመሆኑን በመጥቀስ ስለሁኔታው የገ/ኢ/ል/ሚ በደብዳቤ መጠየቁን ገለጿል፡፡

3.3 <u>ያልተከፈለ ውዝፍ ሂሳብ</u>

• የፍትህ ሚኒስቴር	ብር	189,234.72
• ንግድ ሚኒስቴር	ብር	150,136.95
• የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን	ብር	5,629.45

በወቅቱ ሳይከፈል ወይም ተመላሽ ሣይደረግ ተገኝቷል፡፡

3.4 <u>በተከፋይ ሂሳብ ላይ ልዩ ልዩ የአሰራር ችግሮች</u>

<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት</u>

በጀት ዓመቱ መጨረሻ የቀረበው የሂሳብ ሪፖርት ፍ/ቤቱ በዓመቱ ውስጥ ያንቀሳቀሰውን ሂሳብ በሙሉ ያካተተ ለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ ፣ ፍ/ቤቱ በገቢ ብር 694.77, በጥሬ ገንዘብ ብር 50,000.00, በባንክ ያለ ገንዘብ ብር 9,120,882.19, ዝውውር ብር 694.77, ተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 85,203.91, ተከፋይ ሂሣብ ብር 9,255,413.01 በድምሩ ብር 9,256,780.87 በሰኔ 30 ቀን 2004ዓ.ም በ D-account የተመለከተው ሂሳብ ሰኔ 30,2004 ለኦዲት በቀረበው ሪፖርቶች ላይ ያልተካተተና ለገ/ኢ/ል/ሚ/ርም ሪፖርት ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡ የተከፋይ ሂሣቦቹ በሪፖርቱ ውስጥ አለመካተት በተጣራ ሃብት (Equity) ላይም ተጽዕኖ ስለአላቸው በሪፖርቱ ውስጥ ያልተካተተው የተከፋይ ሂሣቦች

ትክክለኛነታቸው ተጣርቶ ፍ/ቤቱ የሚያዘጋጃቸው የሂሳብ ሪፖርቶች የአጠቃላይ የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊያሳዩ የሚችሉ መሆኑን በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሣብ መደብ 5054 ብር 3,196,043.11 ከ2002 ዓ.ም. ጀምሮ ለሚመለከተው ክፍል ሳይከፈል የተገኘ ሲሆን ፣ ከዚሁ ሂሳብ ውስጥ ብር 1,200,816.28 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ፈሰስ የተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ለወደፊቱ የተከፋይ ሂሣቦች ክፍያው እንዲፈጸም አስፈላጊው ክትትል መደረግ እንዳለበት ባሳሰብነው መሰረት ሂሳቡን ከመዝገብ ለመሰረዝ አጣሪ ቡድን ተቋቁሞ የማጣራት ስራው ተሰርቶ ቡድኑ የደረሰበትን ውጤት ሪፖርት ያቀረበ መሆኑን፣ በቅርቡ ለበላይ አካል በማቅረብና የሂሳብ ማስተካከያዎች በመስራት ከመዝገብ እንዲስረዙ የሚደረግ ስራ እንደሚከናወን ኤጀንሲው በሰጠው ምላሽ ገልፀዋል፡፡

4. <u>የገቢ ሂሳብ</u>

4.1 <u>በገቢ ግብርና ታክስ አዋጅ፤ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ</u>

የፌደራል ፖሊስ

- ወንጀል መከላከል ዘርፍ ከብረታ ብረትና ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የጋፋት አርማመንት ኢንዱስትሪ ጋር በብር 2,086,071.49 የተለያዩ የጦር መሳሪያዎች ጥገና ሲያከናውን ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 306,652.20 እንዲሁም የብር 1,982,699.40 AKM ጥይት ግዢ ሲከናወን ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 297,404.91 በድምሩ ብር 604,056.11 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል ።

4.2 <u>ገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የታዩ የአሰራር ድክመቶች</u>

ሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ

- በውስጥ ኦዲት በቀረበው የኦዲት ሪፖርት መሠረት የመዝናኛ ክበቡ ለስራ አገልግሎት የሚጠቀምበት የቁሳቁስ፤ የመብራት እና የውሃ አገልግሎት ኪራይ በመደበኛ በጀት የሚከፈለውን ሂሳብ ድጎማ ከኪራዩ ጠቅላላ ገቢ 20% ለማዕከሉ ገቢ ሆኖ ፈሰስ እንዲደረግ በማናጅመንት ኮሚቴ በተወሰነው መሰረት ገቢ መሆን ሲገባው ብር 4,800.00 ገቢ ሣይሆን ተገኝቷል፡፡

ንግድ ሚኒስቴር

- በበጀት ዓመቱ ብር 3,574,366.00 በሂሣብ መደብ 1417 ከንግድና ሙያ ምዝገባ እና ፈቃድ የተሰበሰበው በአደን ፈቃድ የገቢ ርዕስ ተመዝግቦና ሪፖርት ተደርጐ ተገኝቷል፡፡
- ከተለያዩ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በመሂ/1 ቁጥር 525744-525750 የሆነው ብር 9,876,613.35 ከሀምሌ 2003 እንዲሁም በግንቦትና በሰኔ/2004 በመሂ/1 ቁጥር 526050 እና 526109 ብር 3,364,398.66 በድምሩ ብር 13,241,013.01 መሂ/1 የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት ገቢ ባንክ ገቢ ለመደረጉ የባንክ አድቫይስ ማስረጃ ሳይያያዝ ተገኝቷል፡፡

4.3 <u>የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የወጪ መጋራት ገንዘብ የማይሰበሰቡ መ/ቤቶች</u>

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም እና የፌደራል ፖሊስ

- ከመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ተመርቀው ስራ ከተቀጠሩ ሰራተኞች ከደመውዛቸው የወጪ መጋራት ክፍያ መቁረጥ ጀምረው ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ለማድረግ ሲዘጋጁ የመፍትሔ አቅጣጫ በመፈለግ ፖሊስ ኮሚሽን መ/ቤት የወጪ መጋራት ክፍያ በአገልግሎት እንዲያዝለት ለሚመለከተው አካል እየጠየቀ በመሆኑ መልስ እስከሚገኝ ለጊዜው ክፍያ እንደቆመ ገልጸዋል ፡፡

በከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት አዋጅ እና የእዳውን አሰባበሰብ በተመለከተ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በወጣው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ክፍያ አሰባሰብ የአፈፃፀም መመሪያ መሰረት ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ተሰብስቦ ለገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ገቢ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.4 <u>ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያልተደረገ ገቢ</u>

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን	ብር	5,629.45
ንግድ ሚኒስቴር፡		
➢ የተጨማሪ እሴት ታክስና እና የተከፋይ ሂሣብ)	ብር	88,811.85
➢ -የህክምናመዋጮ	››	4,667.30
-ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት/ያልተቀነሰ ተ.እ.ታ.		5,756.97
ድምር		104,965.57

4.5 ያለ ሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ የተገኘ የገቢ ሂሳብ

ንግድ ሚኒስቴር

- በገቢ ደረሰኝ ቁጥር ከ519001-519050 እና ከ519051-519100 ከተሰበሰበው ገቢ ብር 7300.00 በሂሣብ መደብ 1429 መመዝገብ ሲገባው በሂሳብ መደብ በ1417 ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

4.6 የገቢ ደረሰኝ አያያዝ

የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ድርጅቶችናማህበራት ኤጀንሲ

የኤጀንሲው የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኝ አጠቃቀም ኦዲት ሲደረግ ከቁጥር 976101 እስከ 976150 1 ጥራዝ፣ ከ976651 እስከ 976750 2ጥራዝ ፣ ከ889051-889100 1 ጥራዝ፣ እንዲሁም ከ11 የተለያዩ ጥራዝ ደረሰኞች በመሀል የተዘለለ 309 ገጽ ሳይሰራበት ተገኝቷል፡፡

የገንዘብ ገቢ ደረሰኝ ከንብረት ክፍል ወጪ ተደርጎ ሲሰጥ ተከታታይነቱን የጠበቀ የገቢ ጥራዝ መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም በገቢ ደረሰኝ አጣቀቀም ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

5. የወጪ ሂሣብ

5.1 ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት መንግሥት ያወጣቸውን የፋይናንስ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን ተከትለው ተገቢው የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡በ6 መ/ቤቶች ብር 6819507.67 ማስረጃ ሳይቅ‑ብ በጪ የተመዘገበ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪጠ-21 ተመልክቷል/

የኢተዮጵያ ብሔሪዊ ምርጫ ቦርድ ለሶስት የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሰጠው ድጋፍ ብር 1,968,330.27 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበለት፣ ብር 28,700.00 ለምርጫ ሥራ አበል ሲከፈል ያለውክልና የተከፈለ መሆኑን፣የብር 139,998.23 የወጪ ማስረጃው ለኦዲት ተጠይቆ የልቀረበ መገኘቱን፣ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ማስረጃ ሳይቀርብ በሰነድ መያዝ የሚገባውን በወጪ መዝግቦ መገኘቱን፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት በቻይና ዩኒቨርስቲዎች ለሚያስተምራቸው ወጪ ላደረው ሂሳብ የገንዘብ ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱን አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ ማስረጃዎቹ እንዲሟሉ ለወደፊቱም ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሣቦች በወጪ እንዳይመዘገቡ አሳስበናል፡፡

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ፓርቲዎቹ ደረሰኞቹን እንዲልኩለት ደብዳቤ መጻፉን፣ ኢንፎርሜሽን መረብ ደረሰኙን ማግኘት እንደሚችሉ ተጻጽፈው መልስ ማግኘታቸውንና እንደመጣ እንደሚያያዙ የፌዴራል ጉዳዮች ሚ/ር ገንዘቡ በሰኔ መጨረሻ በሰነድ ወጪ መሆኑንና በ2004 በጀት ዓመት ሥራ ላይ ይውላል ወይም ለሙስሊሙ ህብረተሰብ በአክራሪነትና ጽንፈኝነት ዙሪያ ስልጠና ይሰጣል ተብሎ መታቀዱን ሆኖም ከተቋሙ አቅም በላይ በሆነ ጉዳይ ሐምሌና በነሐሴ መስጠቱንና በሰኔ ወጪ ከተደረገው ሠነድ ጋር መያያዙን በላኩት መልስ ገልጸዋል ሆኖም አሠራሩ አግባብ አለመሆኑን አስተያየት ሰጥተናል፡፡

5.2 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት/በፎቶ ኮፒ የተወራረደ/	ብር 208,365.01

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት የውጭ መረጃ ዋና መምሪያ በውጭ ሃገር ለሚገኙ ሠራተኞቹ በውጭ ጉደይ ሚ/ር በኩል ወጪ ያደረገውን ሂሣብ በፎቶ ኮፒ ማስረጃ መዝግቦ ሂሣቡ በዋናው ማስረጃ ሊወራረድ እንደሚችል በመግለጽ ኦሪጅናሉ እንዲቀርብ አሳስበናል፡፡

5.3 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸመ ግዥ

- የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር /ጤና ዳይሬክቶሬትና አየር ኃይል/ ብር 1,485,027.23
- ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት/ለቢሮ የውጭ አገር ግዥ " 36,198,641.27
- ፌዴራል ፖሊስ " 93,162.01

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ከብር 100 ሺ በላይ ግዥ ቢፈጽም በጨረታ ወይም በሌሎቹ የግዥ ዘዴዎች ተጠቅሞ መፈጸም ሲገባው በፕሮፎርማ ግዥ መፈጸሙና ከአንድ አቅራቢ፣ወይም በውስን የጨረታ የግዥ ዘዴ የተቀመጡትን መስፈርቶች ሳይሚሉ ግዥ መፈጸሙ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ በህጉ መሠረት ግዥዎች እንዲፈጸሙ በተለይ በዕዞች ሥር ለማገኙ ክፍለ ጦሮች ዕዙ በጥቅል /በአንድ ላይ ግዥ እንዲፈጽም እንዲደረግ አሳስበናል፡፡ በምዕራብ ዕዝ ጨረታ የማይወጣው ክፍለ ጦሮቹ የሚገኙት በረሃማ አካባቢ በመሆኑ ተወዳዳሪዎች የማይቀርቡ መሆኑን፣የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ለቢሮ የሕንጻ ኪራይ ብር 15,042,000.00 እና ለውጭ አገር ግዥዎች ብር 21,156,641.27 በግልጽ

ጨረታ ወይም ከአንድ አቅራቢ ወይም ውሱን የግዥ ዘዴ ሳይጠቀም በመፈጸሙ አሠራሩ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡ ኤጀንሲው በሰጠው መልስ የሴኩሪቲ ተቋም በመሆኑ ለሥራ የሚጠቀምበትን ቢሮ የግልጽ ጨረታ አውጥቶ መከራየት እንደማይችል፤ እንዲሁም የታጠቃቸው ሲስተሞች አለም አቀፍ ስታንዳርድ የላቸው መሆኑንና ከማንኛውም ቦታ በማንኛውም የግዥ ዘዴ የማይገኙ መሆኑን በፋይናንስ አዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 21 መሠረት የተለየ የግዥ መመሪያ እንደፈቀደለተ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ማቀረቡን ገልጿል፡፡

5.4 የንብረት ገቢ ደረሰኝ /መ/19/ ያልቀረበ

- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን	13,000.00
- የሀገር መከላከያ ሚ/ር	15,583.94
- ጠቅላይ ፍ/ቤት	10,323.55

ሶስቱ መ/ቤቶች የዕቃ ግዥ ፈጽመው ሂሣቡ ሲወራረድ ሞ/19 በማሰረጃነት ሳይቀርብ በመወራረዱ ግዥው ለመ/ቤቶቹ አገልግሎት የዋለ መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉን በመግለጽ ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ አሳስበናል፡፡የሀገር መከላከያ ሚ/ር በላከው መልስ ሂሣቡ ሲወራረድ ሞ/19 አለመቅረቡ ስህተት መሆኔን ጠቅሶ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲቆረጥ እንደማያደርግ ገልጿል፡፡

5.5 የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የሚሊተሪ ደሞዝ	3,169,110,595.13
- በሃገር መከላከየ ሚ/ር ለመረጅ ግዢ	51,985,911.39
- ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	187,857,058.50
- በፌደራል ፖሊስ ለመረጅ ግዢ	1,148,825.25

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልገሎትና በሥሩ የሚገኙ ዋና መመሪያዎች ለደመወዝ ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ፔሮሉ በኮድ በመቅረቡ ኮዱን የሚገልጽ ማስረጃ ለመሰጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፤ ሌሎቹ የወጪ ሂሣቦች ለምሳሌ የመኪና ጥገና የነዳጅ ለማጣራት የመኪኖች ታርጋ የስልክ ቁጥሮችና የመሳሰሉት ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረባቸው ሂሣቡን ኦዲት በማድረግ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ መ/ቤቱ ከሚስጥራዊነት አንጻር ማቅረብ እንደማይቻል በኦዲት ወቅት ገልጿል፡፡ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የደመወዝ ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ በበጀት ዓመቱ የተቀጠሩ በዝውውር የመጡ በጡረታ የተገለሉ እና በተለያየ ምክንያት የተሰናበቱ የሠራዊት

አባላት ስም ዝርዝር እና የተወሰኑ ዓመታተ በማገልገላቸው ማበረታቻ የተሰጣቸው አባላት ስም ዝርዝር ለኦዲት ተጠይቆ መ/ቤቱ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሠራዊት ደመወዝ ወጪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለና ይህም ወጪ ለሚ/ር መ/ቤቱ ከተመደበው በጀት በመቶኛ 50% በመሆኑ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰን ማስረጃዎቹ ለኦዲት የሚቀርቡበት ሁኔታ እንዲመቻች አሳስበናል፡፡ እንዲሁም በሃገር መከላከያ ሚ/ር ብር 51,985,911.39፤በፌደራል ፖሊስ ብር 1,148,825.25 በ6251 የወጪ መደብ የተመዘገበው ማስረጃ ሳይቀርብ መሆኑ ታውቋል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በላከው መልስና ቀደም ብሎም በኦዲቱ ወቅት በደብዳቤ ለመ/ቤታችን እንደገለጸው ከወታደራዊ ሚስጥራዊነት አንጻር በሀገር ደህንነት ላይ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ መረጃዎችንና ዶክመንቶችን ለኦዲት ለማቅረብ እንደሚያስቸግር ተገልጿል፡፡ፌደራል ፖሊስም በሂሣብ መደብ 6251 የወጣውን ከሚስጥራዊነት አንጻር ለማንና ለምን እንደተከፈለ መግለጽ እንደማይቻል ገልጿል፡፡

5.6 ከቀረበው የወጪ ማስረጃ በላይ የተመዘገበ የተወራረደ ሂሣብ

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 29,170.20 በዋጋ ማቅረቢያ ከተገለጸው ዋጋ በላይ እና ከቀረበው የክፍያ ማስረጃ በላይ ከፍሎ መገኘቱን በመግለጽ ገንዘቡ ከሚመለከተው ሠራተኛ እንዲሰበሰብ ለወደፊቱም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡ ብር 12,717.20 ከሚመለከታቸው የተሰበሰበ መሆኑን ሌላውን ወደፊት እንደሚያስተካ ገለጿል፡፡

5.7 በሀገር መከላከያ ሚ/ር በሎጁስቲክስ ዋና መምሪያ በ2003 በጀት ዓመት ለተደረገ የተሽከርካሪዎችና የመሳሪያዎች ጥገና ወጪ ብር 27,017,259.48 ከበጀት ዓመቱ ወጪ ክፍያ ተፈጽሞ በመገኘቱ እንዲህ አይነት ክፍያ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ተጨማሪ በጀት በመጠየቅና አስፈቅዶ ወጪ ማድረግ ሲገባ በበጀት የልተያዘን የአገልግሎት ግዥ ክፍያ መፈጸሙ አግባብ አለመሆኑን አሳስበናል፡፡ መ/ቤቶ በላከው መልስ የገ/ኢ/ል/ሚ/ረ ጠይቀው በቃል በላከው መልስ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ጠይቀው በቃል በላከው መልስ የገ/ኢ/ል/ሚ/ረ ጠይቀው በቃል ከዘመኑ በጀት እንዲከፍሉ እንደተነገራቸው ገልጿል፡፡

5.8 በሀገር መከላከያ ሚ/ር የምዕራብ ዕዝ ግንባታ በመሃንዲስ ግምት /bill of quantity/ መሠረት ብር 32,158,416.64 በመገንባት ላይ የሚገኝና እስከ ሰኔ 30, 2004 ብር15,545,738.30 ወጪ የሆነው ለግንባታው የተፈቀደ በጀት

የሌለው መሆኑ፣በሚ/ር መ/ቤቱ ግንባታው እንዲካሄድ የተፈቀደ አለመሆኑን፣የተሠራውንና ቀሪ ሥራዎችን የሚያሳይ በባለሙያ የተደገፈ ዝርዝር ማስረጃ የክፍያ ሰርተፍኬት አይነት አለመቅረቡንና የግባታው ወጪ አግባብ አለመሆኑን ገልጸናል፡፡ መ/ቤቱም በሁሉም ዕዞች የግንባታ ሥራዎችን የሚከታተል የግንባታ ዲፓርትመንት መኖሩን የዕዙ ግንባታ ከትልቅነቱ አንጻር ተቆጣጣሪ መሃንዲስ ተመድቦ የክፍያ ሰርተፍኬት እየተዘጋጀ ክፍያ ያልተፈጸመ ከሆነ አማካሪ እንደሚመደብና ተገቢው ቁጥጥር እየተደረገ ክፍያ እንደሚፈጸም ገልጿል፡፡

5.9 <u>የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የክፍያ መመሪያ መሠረት ያልተፈጸሙ</u>

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 120,995,163.73 በተለያዩ ክፍሎች ለተለያዩ ግዥዎች ከመመሪያ ውጪ መፈጸሙን፣የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው የክፍያ መመሪያ ቁጥር 4 ከብር 50,000.00 በላይ መ/ቤቶች የሚፈጽሙት ክፍያ በቀጥታ አቅራቢው ወይም ተጠቃሚው የባንክ ሂሣብ እንዲገባ የሚያዘውን መተላለፉን በመግለጽ በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡ መ/ቤቱ በላከው መልስ፣በደብዳቤ የሚተላለፉ ክፍያ የማይቀበሉ የልማት ድርጅቶች መኖራቸውን መብራት ሃይል፣ቴሌ፣ስኳር ኮርፖሬሽን፣በምሳሌ ገልጿል፤ደረሰኝ ለማግኘት ችግር መኖሩን አንዳንድ ድርጅቶች በመንግሥት የንግድ ባንክ የባንክ ሂሣብ የሌላቸው መሆኑንና ከመንግሥት የንግድ ባንክ ወደ ግል ባንኮች በተጠቀሰው ዘዴ ክፍያ መፈጸም እንደማይችል በመግለጽ ለወደፊቱ በመመሪያው መሠረት ክፍያ እንደሚፈጸም ገልጿል፡፡

6. <u>ዕቃና የንብረት አስተዳደር</u>

6.1 <u>አላቂና ቋሚ ዕቃዎች መዝገብ ያልተቋቋመባቸው፤</u>

- ለቋሚ ንብረት አላቂ ዕቀዎች መዝገብ ያልተቋቋመባቸው (ምዝገባ ያላከናወኑ) 2 መሥሪያ ቤቶች
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያላደረጉ 4 መሥሪያ ቤቶች
- ቆጠራ ከመዝገብ ያላገነዘቡ 3 መ/ቤቶች
- ለቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው 4 መ/ቤቶች

መኖራቸው ተውቋል/ዝርዝራቸው በአባሪ-32 ተመልክቷል/

በመሆኑም መሥሪያ ቤቶቹ በንብረት አስተዳደር መመሪያው መሰረት ዓመታዊ ቆጠራ በማድረግ የቆጠራው ውጤት ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር መመዛዘን እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል ።

6.2 ሌሎች የንብረት አያያዝና ድክመቶች የታየባቸው

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

- በሞዴል 19 ገቢ ደረሰኝ እና በሞዴል 22 ንብረት ወጪ ደረሰኝ በንብረት መዝጋቢዋ መዘጋጀት ሲገባ በንብረት ጠባቂዋ ተሰርቶ ተገኝቷል፡፡
- የንብረት መጋዘን በተጨናነቀ የዕቃ አቀማመጥ ተቀምጦ ተገኝቷል፡፡

ሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ

- በቋሚ ዕቃዎች መጋዘን ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡና የማይሰጡ ዕቃዎች ለብልሽት በሚጋለጡበት ሁኔታ በአንድ ላይ ተቀምጠው ተገኝቷል ፡፡
- የሚወገዱ ዕቃዎች ዝርዝር በከፍተኛ የንብረት ባለሙያ የቀረበና ኮሚቴም የተቋቋመ ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል ፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን

- ንብረት ቆጠራ ተደርጎ ከወጪ ቀሪ ሪፖርት ማስረጃ አልቀረበም፤
- ለየክፍሎቹ ለሥራ ለአገልግሎት ወጪ የተደረጉ ቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር (ፒን) የተሰጠበት ማስረጃ ሳይኖረው ተገኝቷል ፡፡

የፍትህ ሚኒስቴር

- በሞ/19 እና በሞ/22 ገቢና ወጪ የሚሆኑት ዕቃዎች በአብዛኛው ወደ ስቶክ ካርድ ያልተላለፉ እና በትክክል ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- አላቂና ቋሚ ዕቃዎች ተለይተው ቢቀመጡም አሮጌ ዕቃዎች ተደባልቀው ተቀምጠው መገኘታቸው፡፡ለምሳሌ፡ (የመኪና ጎማና የኮምፒዩተር ማባዣ የመሳሰሉት) አሮጌውም አዲሱም በአንድ ላይ ተቀምጦ ተገኝቷል፤
- የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚ/ር ለሁለት ሲከፈልና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ከፊሎቹ ወደ ኢንዱስትሪ ሚ/ር ሲመደቡ በስማቸው ያለውን ቋሚ ዕቃ በህጋዊ መንገድ ክፍፍል ሳይፈጸም ተገኝቷል፤፤

<u>የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን</u>

- ለአገልግሎት ውጪ ለተደረጉ ቋሚ ንብረቶች መከታተያ ፋይል ያልተዘጋጀና ለዕቃዎቹ መለያ ቁጥር ሙሉ በሙሉ ያልተሰጠ መሆኑ ፣
- በቁጥር 133 ያገለግሉ ልዩ ልዩ አይነት ዕቃዎች እርምጃ ሳይወሰደባቸው በለገሀር ጉምሩክ ግቢ እንደሚገኙ ፣
- ታውቋል፤፤

- የቋሚና አላቂ ንብረት ገቢ እና ወጪ መዝገብ እንዲሁም ቢን ካርድ ሊቋቋም እንደሚገባ ፤ የንብረት ቆጠራ ከመዝገብ ወይም ከስቶክ ካርድ ከወጪ ቀሪ ተገናዝቦ በልዩነቱ ላይ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት፤ የንብረት መዝጋቢ፤ የዕቃ ግምጃ ቤት ጠባቂና የንብረት ክፍል ኃላፊ ሠራተኞች የተለያዩ ሊሆኑ እንደሚገባ፤ እንዲሁም በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ ከአገልግሎት ውጭ በሆኑት ዕቃዎች ላይ በመመሪያው መሠረት እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው በአጠቃላይ የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የፌዴ.ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር</u>

- በከፍተኛ ፍርድ ቤት አካባቢ በሚገኘው በአስተዳደሩ የድሮ ዳቦ ቤት መጋዘን ውስጥ ብዛት ያላቸው ኮምፒዩተሮች፤ ፕሪንተሮች፤ የሂሳብ መደመሪያ ማሽኖች፤ የስልክ ቀፎዎች፤ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፤ የበርና የመስኮት መዝጊያዎች እና የመሳሰሉት ለረጅም ዓመታት ከጥቅም ውጪ ሆነው ተከማችተው ተገኝተዋል።

<u>ነዳጅና የነዳጅ አጠቃቀም ላይ የታዩ ችግሮች</u>

የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም

- የተሽከርካሪዎች ነዳጅ አጠቃቀም በተመለከተ የሰሌዳ ቁጥር 4-12187 ሱዙኪ ቪታራ ተሽከርካሪ የኪሎሜትር ንባብ የማይሰራ በመሆኑ የተሽከርካሪውን የነዳጅ ፍጆታ መጠን ለመቆጣጠር የሚቻልበት አሰራር አለመኖሩ ፤

- በሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያሉት ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ለተቋሙ አገልግሎት መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ተሽከርካሪዎቹ ለሥራ በሚሰማሩበት ወቅት የተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያ እና መዘዋወሪያ ቅፅ የማይዘጋጅ መሆኑ ታውቋል፡፡

የተሽከርካሪው የኪሎ ሜትር የንባብ መሣሪያ የማይሰራ በመሆኑ የፈጀው /የተጠቀሙትን/ የነዳጅ መጠን እና ኪሎ ሜትር ማረጋገጥ የሚቻልበት አሰራር አለመኖሩ፤ የተቋም የነዳጅ አጠቃቀምን ትክለኛነት ማረጋገጥ እንዲቻል የመንግሥት ተሽከርካሪ አገልግሎት መጠየቂያ ቅጅ መጠቀምና የነዳጅ ፍጆታ መቆጣጠር የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

6.3 <u>የተሽከርካሪ መኪናዎች አያያዝና አጠባበቅ</u>

በየመሥሪያ ቤቶቹ ውስጥ ያለው የተሽከርካሪዎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትና መረጃ አያያዝ በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ሊብሬ ያልቀረበላቸው በ2 መ/ቤቶች 257 ተሽከርካሪዎች
- በብልሽት ምክንያት የቆሙ በ5 መ/ቤቶች 145 ተሽከርካሪ ዎች

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -34ተመልክቷል/

<u>የኢት.ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት</u>

በጽ/ቤቱ ውስጥ ካሉት ተሽከርካሪ መኪናዎች ውስጥ 3 ተሽከርካሪዎች ከ1 ዓመት እስከ 2 ዓመት በብልሽት የቆሙ መሆናቸው ፣2 ተሽከርካዎች የሠሌዳ ቁጥር 4-10696 እና የሠሌዳ ቁጥር UN-0078 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ እና ይኸው የሠሌዳ ቁጥር 4-10696 በንብረት መዝገብ ላይ ያልተመዘገበ መሆኑን በ2003 ኦዲት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት ቢሰጥም እስከ አሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡

በመሆኑም መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች እንዲወጣላቸው፣ በጊዜያዊነት ሊብሬ ያላቸውም ቋሚ ደብተር ሊወጣላቸው እንደሚገባ፣ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑት ተጠግነው ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉት እንዲጠገኑ፣ ሊጠገኑ የማይችሉትን ደግሞ በመንግስት መመሪያ መሠረት የሚወገድበት ሁኔታ መመቻች ያለበት መሆኑን በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7. <u>በጀት</u>

በ2003 በጀት ዓመት የተመደበው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲገናዘብ ከ10% በላይ ያለውን ብቻ በመውሰድ ያልተሠራበት በጀት በ19 መ/ቤቶች ብር 141,724,380.49 እና

ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ በ3 መ/ቤቶች ብር 553,5285.01 ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ-32 ተመልክቷል/

በመሆኑም የበጀት ዝግጅት በበቂ ጥናት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን፣ የበጀት እጥረት ሲያጋጥም የበጀት ዝውውር በመጠየቅ እንዲፈጸም በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የ2004 በጀት ዓመት ሒሳብ ኦዲት ሪፖርት

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ

ጥሬ ገንዘብ ሂሣብ

1.1 ግኝት

በመንግስት መመሪያ መሠረት በበጀት አመቱ መጨረሻ በሚሲዩኖች የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ሰለመደረጉ ማስረጃዎች ያልቀረበላቸው 11 ፎቶ ኮፒ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ማሰረጃ የቀረበላቸው 3 ፡በሚመለከታቸው ወይም ቆጠራውን ባደረጉት ያልተፈረመ 8 በቆጠራው ሠነድ ላይ የተለያዩ የገንዘብ አይነቶች በመገለጻቸው አንዱን ለመቀበል ያልተቻለ 1 ሚሲዬኖች መገኘቱን በመግለጽ በመንግሥት መመሪያ መሰረት በበጀት አመቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

የቆጠራ ማስረጃ ያላቀረቡት 11 ሚሲዬኖች በበጀት አመቱ መጨረሻ የሚቆጠር የጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ የሌላቸው መሆኑን፣ ሆኖም ለወደፊቱ በበጀት አመቱ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ባይኖራቸውም ይህንኑ የሚገልጽ መተማመኛ ሚሲዬኖች እንዲልኩ እነደሚያደርግ፡ፎቶ ኮፒ የቆጠራ ማስረጃውን በተመለከተ ዋናው እንደደረሰው እንደሚያቀረብ፡ተፈርሞ ያልተላከውን የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ መተማመኛ ለሚሲዬኖቹ መላኩንና ተፈርሞ እንደደረሰው የሚያቀርብ መሆኑን መ/ቤቱ በላከው መልስ ገልጿል፡፡

የባንክ ሂሳብ

1.2 ግኝት

በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሣብ ሪፖርት በውጭ ምንዛሪ በባንክ ያለ ገንዘብ (በ4102) ብር 391.765.908.01 ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሰኔ 30/2004 የባንክ ስቴትመንቶች እንዲቀርቡ ተጠይቆ

- የ23 ሚሲዮኖች 32 የበጀት ሂሳብ እና 15 የቪዛ የባንክ ሂሳቦች በድምሩ የ47 የባንክ ሂሳቦች የሰኔ 30/2004 የባንክ ሂሳብ ከወጪ ቀሪን የሚያሳዩ የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያዎች (Bank Statements) ለኦዲት አልቀረቡም፡፡

- በ7 ሚሲዮኖች 1 የበጀት ሂሳብ እና 6 የቪዛ ሂሳብ በድምሩ 7 የባንክ ሂሳቦች የሰኔ 30/2004 የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ (Bank Reconciliations) ሲዘጋጅ ትክክለኛውን የሰኔ 30/2004 በባንክ ያለ ገንዘብ ከወጪ ቀሪን መሰረት አድርጎ ባለመዘጋጀቱ በድምሩ ብር 2,086,399.85 ከባንክ ሂሳብ ማስታወቂያው በማነስ፣ብር 151,770.54 ደግሞ በመብለጥ ተገኝቷል፡፡

- የ13 ሚሲዮኖች 17 የበጀት ሂሳብ እና 3 የቪዛ ሂሳብ በድምሩ 20 የባንክ ሂሳቦች የሰኔ 30/2004 የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያዎች (Bank Reconciliations) ለኦዲት አልቀረበም፡፡

- በ19 ሚሲየኖች 29 የበጀት ሂሳብ እና 18 የቪዛ ሂሳብ በድምሩ የ47 የባንክ ሂሳቦች የሰኔ 30/2004 የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያዎች (Bank Reconciliations) በሚመለከታቸው የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ያልተፈረሙ(ያልተረጋገጡ)ተገኝቷል፡፡

በ7 ሚሲዮኖች 8 የበጀት ሂሳብ እና 9 የቪዛ ሂሳብ በድምሩ የ17 የባንክ ሂሳብ ቁጥሮች የሰኔ 30/2004 የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ (Bank Reconciliations) ፎቶ ኮፒ ፣ ሆኖ መገኘቱን በመግለጽ የሂሣብ ሪፖርቶች ሲዘጋጁ በቅድሚያ የተሟላ ማስረጃ ያላቸው መሆኑ በየደረጃው ሊረጋገጥ እንደሚገባ፣በቀረቡት የባንክ እስቴትሜንቶች ላይ የተመለከተው የገንዘብ መጠን ብር 257'671'836.59 ብቻ ሲሆን በሪፖርት የተገለጸው የገንዘብ መጠን በብር134'093'261.91 ከፍ ብሎ ተገኝቷል፡፡ ይህም ገንዘብ መኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም ያለማስረጃ ሪፖርት የተደረገ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በባንክ ሂሣቦች ላይ ከላይ የተገለጹት ግድፈቶች በሪፖርቱ የተመለከተውን በባንክ ያለ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ገንዘቡም ስለመኖሩ የማያረጋግጡ በመሆኑ መ/ቤቱ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት እንዲጣሩና ለወደፊቱም በዚህ ረገድ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

መስሪያቤቱም በሰጠው መልስ በባንክ መግለጫና በባንክ ማስታረቂያ ዝግጅት ዙሪያ በተወሰኑ ሚሲዬኖች ለአብነት የባንክ ቁጥር አሟልቶ

አለመጻፍ፣የተቀየሩትን የባንክ ሂሳብ ቁጥሮች በወቅቱ ተከታትሎ አለመስተካከል፣የባንክ ማስታረቂያ ሲዘጋጅ ከወጪ ቀሪ የሚወሰድበትን ቀን በትክክል ለይቶ አለመዘጋጀት ላይ የአሰራር ክፍተቶች መኖራቸውን መገንዘቡን፣ሚሲዮኖቹ በሚገኙበት አገር የሚገኙ ባንኮች የውስጥ አሰራር ከቴክኖሎጂ ለውጥ እና ከደህንነት ጋር በተያየዘ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ለውጥ የሚያደርጉ መሆኑን፣ የ46 ሚሲዮኖች የበጀት ሂሳብ የባንክ መግለጫዎች እና የባንክ ማስታረቂያዎች መቅረባቸውን ጠቅሶ በእንዚህ የአሰራር ክፍተቶች ላይ ትኩረት በመስጠትና የክትትል ስርአት በመዘርጋት ችግሩ እንዲቀረፍ የሚያደርግ መሆኑን መ/ቤቱ ገልጿል፡፡

በመውጫ ስብሰባ ወቅት ለኦዲት አልቀረቡም የተባሉት የባንክ ሂሳብ ማስታወቀያዎችን በተመለከተ የሁሉም የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያዎች በእጃቸው እንደሚገኝ በመግለጻቸው ከውይይቱ በኋላ እንዲታዩ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ በዚሁ መሰረት ከመውጫ ሰብሰባ በኋላ በተደረገው ኦዲት ለኦዲት ያልቀረቡት የ49 የባንክ ሒሣቦች የባንክ እስቴትሜንቶች ያለመኖራቸው ታውቋል፡፡ ለዚህም የተሰጡት ምክንያቶች ሚሲዮኖቹ ከሰኔ 30/2004 በፊት ባለ ቀን ሂሳብ በመዝጋታቸው ወይም የሰኔ 30/2004 የባንክ ማስረጃ(እስቴትሜነት) አለመቅረቡን ጠቅሰው ፤ለወደፊቱ የእርምት እርምጃ እነደሚወሰድ፤በባነክ ማስታወቂያ እና መሰታረቂያ ላይ የተገለጸውን በተመለከተ በመውጫ ውይይት ወቅት በተሰጠው አቅጣጫ እርምጃ እንደሚወስዱ፤ የሰኔ 30/2004 ለቆዲት የቀረበው የባንክ ከወጪ ቀሪ በባንክ እስቴትሜንቶች መሰረት ብር 257,671,836.59 መሆኑን እና ይህ ሂሳብ የባንክ ማስታረቂያዎች ላይ ያሉ ማስተካከያዎች(deposit intransit, outstanding checks,recording errors) እንዲሁም አልቀረቡም የተባሉት የባንክ እሰቴትሜንቶች እና የባንክ ማስታረቂያዎችን ያላካተተ በመሆኑ በሪፖርት የተመለከተውን ብር 391,765,098.50 የባንክ ሒሳብ ከወጪ ቀሪ እንደማያመለክት እና በመውጫ ውይይቱ ወቅት በተሰጠው ሀሳብ መሰረት በውስጥ ኦዲት እዲጣራ እንደሚደረግ የፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክተር እና የሚሲዩኖች ፋይናንስ አሰተዳደር ዋና ክፍል ሀላፊ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 ግኝት

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2004 በሂሳብ ሪፖርት የተመለከተውን የተሰብሳቢ ሂሳቦች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለኦዲት በቀረበው የተሰብሳቢ ሂሣቦች ዝርዝር መሠረት፣

- የሂሳብ መደባቸው ያልተገለፀ/የማይታወቅ ብር 2,326,798.36
- ማስረጃ የሌለው /የክፍያ ቅጽና ምዝገባ ማዘዣዎች/ " 64,879,336.68
- ከማን እንደሚሰበሰብ ያልተገለፀ/የማይታወቅ " 60,098,423.70
- በኔጌቲቭ /ክሬዲት/ የተመዘገበ ሂሳብ " 7,379,716.96

መገኘቱን ጠቅሰን የተሰብሳቢ ሂሣቦች ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ተመሳሳይ ችግር የተስተዋለባቸው መሆኑን፤ እንዲስተካከሉ በተደጋጋሚ የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት መሆኑን ይሁን እንጂ ችግሮቹ ሊቀረፉ አለመቻላቸውን በመግለጽ መ/ቤቱ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ችግሩ እንዲወገድ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ እና ባልተሟላ ማስረጃ ሪፖርት እንዳይዘጋጅ ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

መስሪያቤቱም በላከው መልስ ለረጅም ጊዜ ሲንከባለል የቆየውን የተሰብሳቢ ሂሣብ ክምችት መልክ ለማስያዝና መፍትሄ እንዲያገኝ የመ/ቤቱ የበላይ አመራር ትኩረት በመስጠት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ፣ የኮንትራት ሠራተኞች ቀጥሮ ሂሣቡን የማጣራትና ዝርዝር በማዘጋጀት የተጓደሉትን መረጃዎች ማለትም ቀን፣ የሂሣብ መደብ የማጣቀሻ ቁጥር እና ሌሎች ማስረጃዎችን የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሶ በኦዲት ግኝቱ ቀን የሌላቸው ተብሎ ከተገለጸው ውስጥ ብር 18,219,620.05 ቀኑ እንዲሟላ መደረጉን፣ የማጣቀሻ ቁጥር የሌላቸው ተብሎ ከተጠቀሰው ሂሣብ ብር 42,522,328.04 እና ከማን እንደሚሰበሰብ ካልተገለጸው ብር 5,210,531.90 ማስረጃዎቹ እንዲሟሉ መደረጉን መ/ቤቱ ገልጿል፡፡

3. የተከፋይ ሂሳብ

3.1 ግኝት

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2004 የሂሳብ ሪፖርት የተመለከውን የተከፋይ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለኦዲት በቀረበው የተከፋይ ሂሣቦች ዝርዝር መሠረት፣

- የሂሳብ መደባቸው ያልተገለፀ/የማይታወቅ ብር 8,240,700.09
- ሂሳቡ የተመዘገበበት ቀን ያልተገለፀ/የማይታወቅ " 10,562,176.07
- ሂሳቡ የተመዘገበበት ሰነድ ያልተገለፀ/የማይታወቅ " 69,628,309.76
- ለማን እንደሚከፈል ያልተገለፀ/የማይታወቅ " 91,367,682.10
- በነገቲቭ /ዴቢት/ የተመዘገበ ሂሳብ " 8,568,445.89

መገኘቱን በመግለጽ የተከፋይ ሂሣቦች ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ተመሳሳይ ችግሮች የተስተዋለባቸው መኖሩን፣ እንዲስተካከሉ በተደጋጋሚ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ መሆኑን፤

ይሁን እንጂ ችግሮቹ አለመቀረፋቸውን በመጥቀስ መ/ቤቱ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ችግሮቹ እንዲወገዱ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ ባልተሟላ ማስረጃ ሪፖርት እንዳይዘጋጅ ቁጥጥር እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

ለረጅም ጊዜ ሲንከባለል የቆየውን የተከፋይ ሂሣብ ክምችት መልክ ለማስያዝና መፍትሄ እንዲያገኝ የመ/ቤቱ የበላይ አመራር ትኩረት በመስጠት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ፣ የኮንትራት ሠራተኞች ቀጥሮ ሂሣቡን የማጣራትና ዝርዝር በማዘጋጀት የተጓደሉትን መረጃዎች ማለትም ቀን፣የሂሣብ መደብ የማጣቀሻ ቁጥር እና ሌሎች ማስረጃዎችን የማሰባሰብና የማደራጀት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቅሶ በኦዲት ግኝቱ ቀን የሌላቸው ተብሎ ከተገለጸው ውስጥ ብር 10,610,976.24 ቀኑ እንዲሟላ መደረጉን፣የማጣቀሻ ቁጥር የሌላቸው ተብሎ ከተጠቀሰው ሂሣብ ብር 8,677,762.53 እና ለማን እንደሚከፈል ካልተገለጸው ብር 11,125,830.47 ማስረጃዎቹ እንዲሟሉ መደረጉን መ/ቤቱ ገልጿል፡፡

4. የሂሳብ ሪፖርቶች

4.1 ግኝት

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2004 ተጠቃሎ የቀረቡት የሂሳብ ሪፖርቶች የሚ/ር መ/ቤቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ የሚያሳዩ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በ24 ሚሲዮኖች 26 የቪዛ ሂሳብ ሪፖርቶች እንዲሁም በ27 ሚሲዮኖች 31 የበጀት ሂሳብ ሪፖርቶች ለኦዲት የቀረቡት የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች የሂሳብ ሪፖርቶች እርሳስና በእስኪሪብቶ የተሰረዙና የተደለዙ መሆኑ፤

- በ28 ሚሲዮኖች 28 የቪዛ ሂሳብ ሪፖርቶች እንዲሁም በ34 ሚሲዮኖች 46 የበጀት ሂሳብ ሪፖርቶች ፎቶ ኮፒ መሆኑ፣

- በ16 ሚሲዮኖች 16 የቪዛ ሂሳብ ሪፖርቶች እንዲሁም በ10 ሚሲየኖች 14 የበጀት ሂሳብ ሪፖርቶች ሳይፈረሙ የቀረቡ መሆኑ፤

- በ5 ሚሲዮኖች 5 የቪዛ ሂሳብ ሪፖርቶች እንዲሁም በ8 ሚሲየኖች 8 የበጀት ሂሳብ ሪፖርቶች በአንድ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን /በተመሳሳይ የባንክ ሂሳብ ቁጥር/ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሂሳብ ሪፖርቶች ለኦዲት የቀረቡ መሆኑ፣

- በ4 ሚሲዮኖች 4 የቪዛ ሂሳብ ሪፖርቶች እንዲሁም በ7 ሚሲየኖች 7 የበጀት ሂሳብ ሪፖርቶች ያልቀረቡ መሆኑ፤

- በ9 ሚሲዮኖች 9 የቪዛ ሂሳብ ሪፖርቶች እንዲሁም በ10 ሚሲየኖች10 የበጀት ሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የተገለፀው የባንክ ሂሳብ ቁጥር በዋናው መ/ቤት ለኦዲቱ ከቀረቡት የሚሲዮኖች የባንክ ሂሳብ ቁጥሮች ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ መሆኑን

በመግለጽ የተሰረዙትና የተደለዙት ሂሣቦች ወደ ማጠቃለያው ሪፓርት ከመካተታቸው በፊት ከሚመለከታቸው ሚሲዮኖች ጋር በእርማቱ ላይ መግባባት ላይ ሊደርስ ሲገባ ይህ ሳይደረግና ሳይፈርሙ በቀረቡት ሪፖርቶች የተመለከቱት ሂሣቦች ሳይረጋገጡ ማጠቃለያ ውስጥ ማስገባቱ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ዋናው ማስረጃ በፋይላቸው ውስጥ እያለ ይዘበራረቃል በሚል ዋናውን ሪፖርት ለኦዲት አላቀረብንም በማለት የተሰጠውን መልስ ለመቀበል

ያስቸግራል፡፡ምክንያቱም በኦዲቱ ወቅት ለተጠየቁት ጉዳዮች ለግዥ፣ ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጀነራል እና የፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክተር ባቀረበነው ጥያቄና መልስ ከላይ የተገለጸው መልስ ከተሰጠን በኋላ በሁለቱ ኃላፊዎች ፊርማ የተዘጋጁ ሪፖርቶች ቀርበዋል፡፡ዋናው ሪፖርት ካለ ለምን ሌላ ሪፖርት ማቅረብ አስፈለገ? በሁለቱ ኃላፊዎች ፊርማ የቀረቡት የሚሲዮኖች ሪፖርቶች ኃላፊዎቹ ከተሰጣቸው የሥራ ድርሻ ውጪ በመሆኑና ሚሲዮኖቹ የራሳቸውን የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለባቸው በሥራ መዘርዝራቸው የተገለጸ በመሆኑ ሪፖርቱን አልተቀበልነውም፡፡ በሌላ በኩል ሁለት ሪፖርት ለአንድ የባንክ ሂሣብ በአንዳንድ ሚሲዮኖች ቀርበዋል ለተባለው የተሰጠው ዋና እና ቅጅ ነው ለተባለው በሁለቱ ሪፖርቶች ላይ የተለየየ አሃዝ እየታየ ዋና እና ቅጅ ነው እንጂ ሁለት ሪፖርት አይደለም ማለት አያስችልም፡፡ ስለዚህ የሂሣብ ሪፖርቶቹ ሲዘጋጁ በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ እና በሚመለከተው ኃላፊ ተፈርመው የተላኩ ኦርጅናል ማስረጃዎች መሆናቸው ሊረጋገጥና ለኦዲትም ዋናው ቅጂ ሊቀርብ ይገባል፡፡ እንዲሁም በአንድ ሚሲዮን ሁለትና ከዚያ በላይ ሪፖርት እንዳይቀርብ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡ የቀረበው የሚሲዮኖች የሰኔ 30,2004 ሪፖርቶች በእርሳስ የተሰረዘና የተደለዙ መሆኑ በተገለጸው መሠረት የተደረጉትን ማስተካከያዎች በማካተት እንዲሁም የማጠቃለያውን ዝርዝር በማያያዝ የተስተካከለውን ሪፖርት በፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት፣ በዲኘሎማቲክ ሚሲዮኖች ክፍል ኃላፊዎች እና በግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጄነራል ፊርማ ማቅረቡን፣34 ሚሲዮኖች የቀረቡት ሪፖርቶች ፎቶ ኮፒ ናቸው ለተባለው ማስረጃዎቹን ለሂሣብ ማጠቃለል ስራ እንዲያመችና ፎቶ ኮፒ በማድረግ ዋና ሪፖርቶቹን በእያንዳንዱ ሚሲዮን ሰነድ ውስጥ በመመለስ የሂሣበ ማጠቃለል ስራው የተከናወነ መሆኑን፣በ8 ሚሲዮኖች የቀረበው ሪፖርት ሁለት ሪፖርቶች ቀርበዋል ለተባለው የተለያዩ ሁለት ሪፖርቶች ሳይሆኑ ኦርጅናልና ፎቶ ኮፒ ሪፖርቶች መሆናቸውን፣ጠቅሶ ለወደፊቱ የሚሲዮኑን የተጠቃለለ ሪፖርት የሚያቀርብ መሆኑን መ/ቤቱ በላከው መልስ ገልጿል፡፡

5. የቁጥጥር ስርዓት

5.1 ግኝት

በቀረበው የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሳቦች ዝርዝር ውስጥ የተገለጹት ቀናት በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር እና በአውሮፓውያን የቀን አቆጣጣር በተዘበራረቀ መልኩ የተመዘገበ እንዲሁም የቀን፣ወርና ዓ.ም ቅደም ተከተል መለየት ያልተቻለ ሆኖ መገኘቱን በመግለጽ ሚ/ር መ/ቤቱ የፌዴራል መንግሥትን የቀን አቆጣጠር ስለሚጠቀም ሚሲዮኖችም የሂሣብ እንቅስቃሴአቸውን በተመለከተ የሚጠቀሙት ቀን እና አመተ ምህረት ይህንኑ መሠረት ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

መስሪያቤቱ በላከው መልስ የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሣብ ዝርዝር በሚዘጋጅበት ወቅት በአሁኑ ጊዜ ተሻሽሎ የተቀረጸው የፋይናንሻል ሶፍትዌር ቀኑን በኢትዮጲያ አቆጣጠር ሚሲዮኖች እንዲመዘገቡ አስገዳጅ በማድረግ መቀረጹንና ችግሩን ለማቃለል የተዘጋጀ መሆኑን፣በቀጣይ እልባት እንደሚያገኝ ገልጿል፡፡

6. የ2003 በጀት አመት የክትትል ኦዲት

6.1 ግኝት

የሚ/ር መ/ቤቱ የ2003 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ መወሰዱ ሲጣራ፣

- በብራስልስ የኢትዮጲያ ኤምባሲ ምንም ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀረብ ብር 120,291.42 በወጪ በመመዝገቡ ማስረጃ እንዲቀረብ ወይም ከሚመለከታቸው ሠራተኛ፣ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡

- በብራስልስ የኢትዮጲያ ኤምባሲ ብር 2599.27 ከቀረበው ማስረጃ በላይ ክፍያ በመፈጸሙ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ሳይተካ ተገኝቷል፡፡

- በተለያዩ የተሰብሳቢ የሂሣበ መደቦች ብር 23,767,620.87 ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ ሁኔታው ተጣርቶ ከማን እንደማፈለግ ጊዜውና ሌሎች አስፈላጊ ማስረጃዎች ተሟልተው እንዲያዙ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አልተገኘም፡፡

- የውጭ መልዕክተኞች በሂሣብ መደብ 4203፣4210 እና በ4274 በድምሩ ብር 8,968,986.06 ያልተለመደ የሂሣብ ሚዛን ክሬዲት የሚያሳይ መሆኑን በመግለጽ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡
- በተለያዩ የተከፋይ ሂሣበ መደቦች ማስረጃ የሌላቸው ብር 19,336,114.33 መገኘታቸውን በመግለጽ ሂሣቡ ተጣርቶ መረጃዎቹ ሊሟሉ እንደሚገባ አስተያየት ቢሰጥም በዚህም ዓመት በተመሳሳይ ሁኔታ የተገኘና እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡
- የሚሲዮኖች የተከፋይ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ባልተለመደ የሂሣበ መደብ ዴቢት ሚዛን ብር 112,770.06 መገኘቱን በመግለጽ ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ቢገለጽም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡

ማስረጃ ሳይቀረብላቸው በወጪ የተመዘገቡት በሳጥን ጉድለትና በተሰብሳቢ ሂሣብ ቢመዘገቡም በአንዳንዶቹ ላይ ምንም እርምጃ ሳይወሰድ(ለምሳሌ ብራስልስ) በመገኘቱ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ፤የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሣቦችን በተመለከተ ባለፉት 2 ዓመታት መ/ቤቱ ሠራተኞች በኮንትራት ቀጥሮ እየተጣራ መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም ጊዜ በመውሰዱ ችግሮቹን ለመፍታት አለመቻሉንና በዚህ በጀት ዓመተም ተመሳሳይ ሁኔታዎች መከሰታቸውን በመግለጽ ለሂሣቦቹ ትኩረት ተሰጥቶአቸው ለማጣራቱ ሥራ የጊዜ ገደብ ተወስኖ ሂሣቡ ሊጣራና ውሳኔ ሊያገኝ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

መ/ቤቱ በብራስለስ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ስለተመዘገበው እና ከማስረጃ በላይ ስለተከፈለው ሂሣብ ሠራተኛው መረጃውን እንዲየቀርቡ የተነገራቸው መሆኑንና መረጃ ማቅረብ ካልቻሉ በቀጣይ ከሠራተኛው ተመላሽ እንደሚያደርግ፣በተሰብሳቢና በተከፋይ ሂሣበ መደቦች ማስረጃ የሌላቸው፣እንዲሁምያልተለመደ የሂሣብ ሚዛን ያላቸውን በተመለከተ የኮንትራት ሠራተኞች ተቀጥረው እየተሠራ መሆኑን፣የተወሰኑ ሂሣቦች እንዲወራረዱ መደረጉን፣ቀሪዎቹን በቀጣይ የማጣራቱ ሥራ የሚፋጠንበትን፣ሁኔታ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሠረት ለመፈጸም ጥረት እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

7. የውስጥ ቁጥጥር ስርአትን በተመለከተ

7.1 የውስጥ ቁጥጥር ስርአት ድክመቶች

ማንኛውም ክፍያ ወጪ ከመደረጉ በፊት በሚመለከታቸው ኃላፊዎች የተረጋገጠ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን

- የማጥን የወጪ ማስመስከሪያ እና የባንክ የወጪ ማስመስከሪያ voucher) ቁጥር 035396፣ 035475፤ 035501፤ 035574፣ 075090፣ 075057፣ 075128፣ ክፍያ ሲዘጋጅ በጀት ለመፈቀዱ ሥምና ፊርማ ፤ ሂሣቡን ያረጋገጠው ሰው ሥምና ፊርማ ያልተፈረመ እና ስለትክክለኛነቱ ያልተረጋገጡ የወጪ ሂሳቦች ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 075094 ለጽ/መሣሪያ ግዢ ብር 4,120.00 ለጂ.ጄ.ኤ ትሬዲንግ ወጪ ሆኖ ሲከፈል ወጪውን ያዘዘው ባለሥልጣን፤ በጀት ስለመፈቀዱ እና ያረጋገጠው ሰው ሥምና ፊርማ ሳይፈረም መገኘቱ፣
- በ2003 ኦዲት ሪፖርት ላይ ገንዘብ ወጪ ከመሆኑ በፊት በሚመለከተው ኃላፊ መፈቀዱንና መፈረሙን ሲጣራ፣ በወጪ ቫውቸር ቁጥር 087816 ብር 15,420.42 ወጪውን ያዘዘውና ተቀባዩ በአንድ ሰው ሆኖ መገኘቱ፤
- የኮሚሽኑ የውስጥ ኦዲት የ2004 በጀት ዓመት ዓመታዊ የሥራ እቅድና በበጀት ዓመቱ የተከናወነውን የሦስተኛ እና አራተኛ ሩብ ዓመት የኦዲት ውጤት ሪፖርት እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

የፌደራል ፖሊስ

- በሰኔ 18 እና 20 ቀን 2004 ዓ.ም ኮሚሽኑ ከ4 ድርጅቶች ግዢ ለመፈጸም ብር 19,722,510.00 በቅድሚያ የከፈለ ሲሆን በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ይህን ያህል ከፍተኛ ግዢ መፈጸሙ ግዢው በእቅድ ላይ የተመሠረተ ሆኖ አልተገኘም፡፡

የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም

- በተቋሙ የሂሳብ አመዘጋገብ በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሣብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 6 መሠረት ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለሚከናወነው የሂሳብ እንቅስቃሴ የጥምር የሂሳብ አያያዝ ስርዓት /Double Entry/

መሰረት የሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ያልተቋቋመ እና በየሂሳብ መደቦቹ ሌጀር ተከፍቶ የማይወራረድ መሆኑ ታውቋል፡፡

- የጽ/ቤቱ የውስጥ ኦዲት ክፍል በተፈቀደው መዋቅር መሰረት ሠራተኛ ያልተመደበለት መሆኑ ታውቋል፡፡
- የሥነ ምግባር ደንብ ተዘጋጅቶ ለሠራተኛው ያልታደለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ፍትህ አካላት ሥልጠና ማዕከል

- በስልጠና ማዕከሉ የፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር ኦዲት አገልግሎት ባለሙያ በማዕከሉ ያልተቀጠረና የኦዲት ቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ ተገኝቷል፡፡
- የስልጠና ማዕከሉ ድርጅታዊ መዋቅር ለኦዲት ያልቀረበ በመሆኑ በመዋቅሩ መሰረት የተዘረጋውን የቁጥጥር ስርዓት በኦዲቱ መገምገም አለመቻሉ፤
- በተለያየ ጊዜ በሚሰጣቸው ስልጠናዎች ለሚሳተፉ ሰልጣኞች ስልጠናውን ለመከታተላቸው የሚያረጋግጥ የሰዓት መቆጣጠሪያ ፎርማ /attendance sheet/ በተሟላ ሁኔታ የማይፈረም እና ከወጪ ሰነዶች ጋር የማይያያዝ መሆኑ ተገኝቷል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የአፈጻጸም የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

8. የ2003 በጀት ዓመት የክትትል ኦዲት

8.1 የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር

8.1.1 ግኝት

በኢትዮጵያ አየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ለስፖርት ፌስቲቫል ተሳታፊዎች ለተደረገ መስተንግዶ ወጪ ከሆነው ብር111,500.00 መቀነስ የሚገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 16,725.00 ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ በመገኘቱ ገንዘቡ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ የኦዲት አስተያየት ቢሰጥም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን በመግለጽ ፤ጠቅላይ መምሪያው አገልግሎቱን ላገኘበት የከፈለው

ክፍያ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ሳይደረግ በመሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ገንዘቡ ለኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

8.1.2 **ግኝት**

በጤና ዋና ዳይሬክቶሬት ለጦር ሃይሎች ሪፌራል ሆስፒታል ለመድሃኒት መግዣ ወጪ የተደረገ ብር 20,000 ገንዘቡ ለአቅራቢው ለመከፈሉ የቀረበ የክፍያ ደረሰኝ አለመኖሩንና መድሃኒቶቹ ተገዝተው ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ባለመቅረቡ ማስረጃው እንዲቀርብ ወይም ከሚመለከተው ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ የለም፡፡ እንዲሁም ለሆስፒታሉ ተማሪዎች ለጥናት ማከናወኛ ብር 12,000 ከተከፈለው ብር 2,000 ለአቶ ምትኩ አስረስ በቅድሚያ የተከፈለ ሲሆን ደጋፊ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት ሂሣቡ ተወራርዶ በመገኘቱ በማስረጃነት የቀረበው ግለሰቡ ደብረዘይት መሄዱን የሚገልጽ የትራንስፖርት ቲኬትና የውሎ አበል ፎርም ተሞልቶ ቢሆንም በቲኬቱ ላይ ግለሰቡ መቼ ደብረዘይት እንደሄደና እንደተመለሰ ያልተገለጸ በመሆኑ ማስረጃውን ለመቀበል አለመቻሉን በመግለጽ ሂሳቡ የተወራረደው ተገቢው የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በመሆኑ ዋና ዳይሬክቶሬቱ ወጪውን በማስረጃ በማስደገፍ ክፍያ እንዲፈጽም ሚ/ር /ቤቱ ክትትል እንዲያደርግ እናሳስባለን፡፡
በጤና ዋና ዳይሬክቶሬት ለመድሃኒት መግዣ ወጪ የተደረገው ሂሣብ ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብለት የተወራረደው ሂሣብ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብለት ወይም ገንዘቡ ከግለሰቡ ደመወዝ ላይ ተቀንሶ ገቢ እንዲደረግ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

8.1.3 **ግኝት**

የመሠረተ ልማት ግንባታ ዘርፍ የኖሪንኮ ላሊበላ ኢንጅነሪንግ ኮንስትራክሽን ድርጅት በባለድርሻ አካላቱ ውይይት ሲፈርስ ቀደም ብሎ ለዚሁ ድርጅት የተሰጠው የጃንሜዳ ስታፍ ኮሌጅ የግንባታ ሥራ ውሉ የተቋረጠ ቢሆንም ለድርጅቱ የተሰጠው ቅድሚያ ክፍያ ብር 3,113,746.82 ለዘርፉ ተመላሽ አለመደረጉን ፤ እንዲሁም የጎፋ

ኮንዶሚኒየም ቁጥር 1. ግንባታ ሥራው የተጠናቀቀ ቢሆንም ለሥራ ተቋራጩ ለቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ብር 4,543,625.67 ሳይሰበሰብ መገኘቱን፤ በተጨማሪም ለአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ለሀንጋር ማሰሪያ ለኖሪንኮ ላሊበላ የተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ ብር 2,970,000.00 ግንባታው ባለመከናወኑ በተሰብሳቢ ተይዞ በመገኘቱ ገንዘቡ ከድርጅቱ ተመላሽ እንዲደረግ የኦዲት አስተያየት ቢሰጥም ምንም እርምጃ ሳይወሰድ መገኘቱን በመግለጽ ቅድሚያ ክፍያዎቹ ላይ ክትትል ተደርጎ ለመንግስት ገቢ እንዲደረጉ በድጋሚ አሳስበናል፡፤በአየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ በተሰብሳቢ የተያዘው ሂሣብ ተመላሽ እንዲደረግ ወይንም ያልተሰበሰበበትን ምክንያ እንዲያሳውቅ በተገለፀው መሠረት ምላሽ በመጠበቅ ላይ መሆናቸውንና ከክፍሉ በሚሰጠው መልስ መሠረት ክትትል በማድረግ ገንዘቡን ለማስመለስ ወይንም ሰነዶችን በማሰባሰብ ሂሣቡ የሚወራረዱበትን ሁኔታ የሚያመቻች መሆኑን መ/ቤቱ ገልጸዋል፡፡

8.1.4 <u>ግኝት</u>

በመከላከያ አስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት በሣጥን ጉድለት የተያዘው ብር 43,500.50 ከሚመለከተው አካል እንዲተካ በተደጋጋሚ የኦዲት አስተያየት ቢሰጥም ሚ/ር መ/ቤቱ እርምጃ አለመውሰዱ ታውቋል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በ2003 ግኝቶች ላይ እርምጃ የሚወሰድበትን መርሃ ግብር ለመ/ቤታችን እንዲያሳውቅ ተጠይቆ በ16/8/2004 በላከው መርሃ ግብር ጉድለቱን ከሚመለከተው አካል ተከታትሎ ከመጋቢት 2004 እስከ ነሐሴ 2004 እንደሚያስተካ ቢገልጽም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን በመግለጽ ጉድለቱ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች እንዲተካ እና ለወደፊትም ጥሬ ገንዘብ በአግባቡ እንዲጠበቅ መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትል እንዲያደርግ በድጋሚ አሳስበናል፡፡መ/ቤቱ ጉድለቱን ለማስተካት ወይንም ከመዝገብ ለማሰረዝ ኮሚቴ አቋቁሞ በመስራት ላይ መሆኑን በላከው መልስ ገልጸዋል፡፡

8.1.5 ግኝት

በመከላከያ በአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት በሂሳብ መደብ 4211 ብር 4,813,048.67 ለረጅም አመታት ለውጭ ጉዞ እና ለልዩ ልዩ ወጪዎች ተከፍሎ ባለመወራረዱ ክትትል ተደርጐ እንዲሰበሰብ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩን በመግለጽ በተሰብሳቢ የተያዘው ሂሳብ ከሚመለከታቸው ክፍሎች እና ግለሰቦች ተመላሽ እንዲደረግ እና ለወደፊቱም ሚ/ር መ/ቤቱ ተገቢውን ክትትል እንዲያደርግ አሳስበናል፤፤

በተሰብሳቢ የተያዘው ሂሣብ በመጋቢት 4/2004 በቁ መ15/ሐ4/935/2004 በተጻፈ ደብዳቤ ለክፍሉ ጠይቀን ክፍሉ ክትትል በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን ገንዘቡን ካላወራረዱት አባላት ላይ ስብሰቦ ገቢ ለማድረግ አስፈላጊውን ክትትል እንደሚያደርግ መ/ቤቱ ገልጸዋል፡፡

8.1.6 ግኝት

በሂሳብ መደብ 4210 በተሰብሳቢ ከተያዘው ለብራና ማተሚያ ድርጅት በብድር የተሰጠው ብር 3,000,000.00 ተመላሽ እንዲደረግ የኦዲት አስተያየት ቢሰጥም እርምጃ አለመሰዱ ታውቋል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በላከው መርሃ ግብር በ2004 በጀት ዓመት እንደሚያስመልስ ቢገልጽም እስከ ታህሳስ 30, 2005 ድረስ ሳይተካ ተገኝቷል፡፡የተሰጠውን ብድር ለማስመለስ የሚደረገው ክትትል ደካማ መሆንን ለመንግሥት ገንዘብ ብክነት በር ይከፍታል የሚል ሥጋት እንደሚፈጥር በመግለጽ ገንዘቡ በአጭር ጊዜ ተመላሽ እንዲደረግ እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡ለብራና ማተሚያ ድርጅት በብድር የተሰጠው ብር 3000,000.00 በ2005 በጀት አመት ተመላሽ እንደሚያስደርግ መ/ቤቱ ገልጸዋል፡፡

8.2 የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት

ከጽ/ቤቱ ኦዲት መምሪያ በሰኔ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በድልድልና ክምችት ክፍል በተደረገ ኦዲት በክምችት ክፍል ብር 881,842.17 በድልድል ክፍል ብር 692,288.71 የሚገመቱ ቁሣቁሶች በድምሩ የብር 1,574,134.88 ንብረት በጉድለት የተገኘ መሆኑን በ2002

ኦዲቱ ወቅት ለማወቅ መቻሉን በመግለጽ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በመ/ቤታችን አስተያየት ተሰጥቶአል፡፡ ይሁን እንጂ እስከ አሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡ በሁለት የኦዲት በጀት አመት የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እስከ አሁን ውሳኔ አለመገኘቱ ታውቋል። ስለዚህ ጽ/ቤቱ ጉዳዩ ውሳኔ እንዲያገኝ ተገቢውን ክትትል እንዲያደርግ በድጋሚ ባሳሰብነው መሰረት ጽህፈት ቤቱ ለፌዴራል ሥነምግባር እና ፀረ-ሙሰና ኮሚሽን አፋጣኝ ውሳኔ እንዲሰጥበት ክትትል እየተደረገ ቢሆንም በኮሚሽኑ በኩል የሚታይ አጥጋቢ እንቅስቃሴ እንደሌለና በክምችትና ድልድል ክፍል የነበሩ ኃላፊ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶ ከምድብ ቦታቸው እንዲነሱ መደረጉን በኦዲት መውጫ ውይይት ወቅት እና በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

8.3 የፌዴ.ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር

በልዩ ልዩ የአደራ ተከፋይ ሂሳቦች ብር 3,379,252.40 በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2003 ተዘጋጅቶ በቀረበው የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት ሣይካተት መገኘቱ በ2003 የአስተዳደሩ ኦዲት ሪፖርት የተገለፀ ቢሆንም ከዚሁ ሂሳብ ውስጥ በ2004 በጀት ዓመት ብር 643,514.42 ብቻ በሂሳብ መደብ 5054 የተመዘገበ ሲሆን ቀሪው ብር 2,735,737.98 በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30/2004 ተዘጋጅቶ በቀረበው የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል። በሪፖርት ያልተካተተው የተከፋይ ሂሳብ በአጠቃላይ የሂሳብ እንቅስቃሴው ውስጥ እንዲካተት መመሪያ የተሰጠ መሆኑና አፈጻጸሙም በስራ አመራሩ ክትትል እየተደረገበት እንደሚገኝ ለሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

ከአቅም ግንባታ ሚኒስቴር የሚተካ በሚል በ2002 በጀት ዓመት ከአደራ ሂሳብ በብድር ብር 700,360.43 ወጪ መደረጉንና ሂሳቡ እስኪተካ በሰኔ 30/2003 ሪፖርት ላይ በተሰብሳቢ ሂሳብ ያልተያዘ መሆኑን በ2003 ኦዲት ሪፖርት ወቅት ለማወቅ መቻሉን በመግለፅ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በመ/ቤታችን አስተያየት ተሰጥቷል። ይሁን እንጂ እስከ አሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል።የአቅም ግንባታ ሚ/ር የተካውን የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚ/ርን ጉዳዩን በመግለጽ በደብዳቤ እንዲጠየቅ ለሚመለከተው ዘርፍ መመሪያ የተሰጠ መሆኑን ለሪፖርቱ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

8.4 የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶችቆጣጣሪ ኤጀንሲ

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 4203 ብር 4,680.41 እና በሂሳብ መደብ 4253 ብር 5,322.68 በድምሩ ብር 10,003.09 ከአምስት ዓመት በላይ ሳይወራረድ መገኘቱ በ2003 ኦዲት ሪፖርት ወቅት ለማወቅ መቻሉን በመግለፅ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በመ/ቤታችን አስተያየት ተሰጥቷል። ይሁን እንጂ እስከ አሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል።በአሁኑ ሰዓት አጣሪ ቡድኑ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶት በመንቀሳቀስ ሥራውን በማጠናቀቁ በአብዛኛው ውሳኔ በመስጠት ተገቢውን የሂሳብ ማስተካከያ በመስራት ከመዝገብ ለመሰረዝ እንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኙ በሰጡት ምላሽ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተከፋይ ሂሣብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 5002 ብር 445,906.05 በሂሳብ መደብ 5028 ብር 1,413.11 በሂሳብ መደብ 5035 ብር 120,154.70 እና በሂሳብ መደብ 5054 ብር 1,986,226.83 በድምሩ ብር 2,553,700.69 ከአንድ ዓመት እስከ ሰባት ዓመት ሳይወራረድ መገኘቱ በ2003 ኦዲት ሪፖርት ወቅት ለማወቅ መቻሉን በመግለፅ አስፈላጊዉ እርምጃ እንዲወሰድ በመ/ቤታችን አስተያየት ተሰጥቷል። ይሁን እንጂ እስከ አሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታዉቋል።በአሁኑ ሰዓት አጣሪ ቡድኑ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶት በመንቀሳቀስ ሥራውን በማጠናቀቁ በአብዛኛው ውሳኔ በመስጠት ተገቢውን የሂሳብ ማስተካከያ በመስራት ከመዝገብ ለመሰረዝ እንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኙ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

8.5 የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

የተጣራ ሀብት በሰኔ 30, 2004 በሂሳብ ሚዛን ሙከራ ብር 32,500.74 ዴቢት ሚዛን ሊያሳይ የቻለበት ምክንያት ሊታወቅ አልቻለም:: በዴቢት ባላንስ የተያዘዉ የተጣራ ሀብት ሂሳብ ተጣርቶ ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ በ2003 ኦዲት ወቅትም አስተያት የተሰጠበት ቢሆንም ተግባራዊ አልተደረገም። ለማስተካከል ጥረት እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

8.6 <u>በፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን</u>

በፌ/ፖሊስ ወንጀል መከላከል ዘርፍ በሰኔ 30/2003 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ብር 34,030.90 በ2001 በጀት ዓመት ዘርፉ ለድሬድዋ ፖሊስ ሁርሶ ማሰልጠኛ ከራሱ በጀት ወጪ አድርጐ ከፍሎ ከአሁን ቀደም የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶበት ከ 3 ዓመት በላይ የቆየና እርምጃ ያልተወሰደበትና ለዘርፉ ያልተመለሰ፣ በ2002 በበጀት ዓመት ዘርፉ ለአፋር ፖሊስ በሁርሶ ማሰልጠኛ ለአፋር ምልምል ፖሊሶች ብር 78,905.31 ከራሱ በጀት ወጪ ያደረገው ከአሁን ቀደም የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶበት ከ2 ዓመት በላይ የቆየና ያልተሰበሰበ ተገኝቷል፡፡

8.7 <u>የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን</u>

በሰኔ 30/2004 ዓ.ም በተዘጋጀው የሂሣብ ማመዛዘኛ ሪፖርት በ4104 (ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተገደበ) ሂሣብ መደብ እና በሂሣብ መደብ 5501 (የመንግስት የፍትህ አካላት) ብር 1,331,963.72 የተመለከተ ሲሆን ባለፉት በጀት ዓመታትም በሂሣብ ማመዛዘኛው ላይ የነበረ በመሆኑ እርምጃ ሣይወሰድ መገኘቱ፣

በ2003 ኦዲት ሪፖርት ላይ በሰኔ 30/2003 የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገው ብር 20,201.10 ሪፖርት መደረግ ሲገባው ለገ/ኢ/ል/ ሚኒስቴር ሪፖርት የተደረገው የዕለቱ የሌጀር ከወጪ ቀሪ ብር 41,224.47 በመሆኑ በልዩነት የታየው ብር 21,023.37 በ2004 ዓመት አዲትም ተስተካክሎ በ4202 (የሣጥን ጉድለት) የተያዘ ቢሆንም ገንዘቡ አሁንም ሣይተካ መገኘቱ፤

8.8 <u>የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ማዕከል</u>

በአንዳንድ ሣጥን የወጪ ማስመስከሪያ እና የባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ክፍያ ሲዘጋጅ በጀት ስለመፈቀዱ ሥምና ፊርማ እና ሂሣቡን ያረጋገጠው ሰው ሥምና ፊርማ ሳይፈረም ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፤

8.9 <u>ንግድ ሚ/ር</u>

በኢንዱስትሪ መንደር ለረዥም ጊዜ ያለአገልግሎት የቆመ ተሽከርካሪ (ማርቸዲስ) በቀድሞው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር ስር እንደነበር ነገር ግን አሁን የተሽከርካሪዎች ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ የተሽከርካሪው

ንብረትነት የማን እንደሆነ አለመታወቁ በባለፈው ኦዲት ሪፖርት የተገለጸ ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል ፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባዘጋጀው በሣጥን የወጪ ማስመስከሪያ (cash payment voucher) እና በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ (Bank payment voucher) ላይ በጀቱ ስለመፈቀዱ እና ሂሳቡን ያረጋገጠው ሰው ያልተፈረመ እና ስለትክክለኛው ያልተረጋገጠ አብዛኛው የወጪ ሂሳቦች ላይ በባለፈው ኦዲት ሪፖርት ቢጠቀስም አሁንም በ2004 መገኘቱ፤ (ለመጥቀስ ያክል CPV 062243፤BPV 032240፤JV 30975፤055011)

8.10 የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

ተቋሙ ከ2002 በጀት ዓመት ጀምሮ በተደጋጋሚ በተሰጠ የኦዲት አስተያየት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር 4-12187 ሾፌር አቶ ምኒልክ አለማየሁ ጥፋት ባደረሰው አደጋ ከተቋሙ ስራ ማስኬጃ ብር 32816.88 በ2001 በጀት ዓመት ለካሳ ተከፍሎ መገኘቱን ተገልፆ ተቋሙ ጥፋት የፈፀመውን አሽከርካሪ በዕዳ መጠየቅ እንደሚገባው እና ወጪው እንዲተካ ክትትል እና የማስተካከያ እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡

8.11 የፍትህ ሚኒስቴር

በ1980 ዓ.ም ለጨረታ ውል ማስከበሪያ ብር 67,082.72 ከአቅራቢዎች በሞ/85 ተይዞ ድርጅቶቹ ማስረጃ አቅርበው ባለመውሰዳቸው እርምጃ ሳይወሰድ በተከፋይ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ አሳስበናል፤፤

8.12 የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት

በ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ውጤትና አስተያየት መሠረት በኢንስቲትዩቱ የተወሰደ እርምጃ ሲጣራ፣ብር 1,275,750.00 ለአሠልጣኝ፣ ለቱተር እና ለወታደራዊ አሰልጣኞች ከውል ውጭ በብልጫ የተከፈለው ያልተተካ ተገኝቷል፡፡

ኢኒስቲትዩቱ የፖሊስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በ20/6/2004 በቁጥር 117/ፖዩኮ2/1/68 ለኢነስቲትዩቱ ሲጽፍ የበጀት ዕቅድን የያዘ እንጂ ውል የሌለው መሆኑን እንደገለጸለት መልስ ሰጥቷል፤፤

በኦዲቱ ወቅት ፖሊስ ኮሌጅ በመገኘት ስለሁኔታው ባደረግነው ማጣራት የውል ስምምነት አለመኖሩንና ሆኖም የፖሊስ ኃይልን ለማጠናከር ታስቦ ሥልጠናው እንዲካሄድ በበላይነት የሚመራው የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር መሆኑ ለስልጠናው የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ወጪዎችም በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር በኩል መዘጋጀቱን የሥልጠና ወጪ ፕሮጀክትን በፌዴራል ፖሊስ በኩል የደረሰውን 12 ገጽ ፎቶ ኮፒ ኮሌጁ ለኦዲት ቡድኑ አቅርቧል፡፡ በመሆኑም ከቀረበው ዝርዝር ውስጥ ከዚህ በፊት በቀረበው የኦዲት ሪፖርት ሂሣቡን ኦዲት አድርገን በመስፈርትነት ተጠቀምንበት አስተያየት ከሰጠንበት ማስረጃ በስተቀር ሌላ ውል እንደሌለ ታውቆ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ ባለመሆኑ፣ ትኩረት ተሰጥቶት ከውሉ ውጭ የተከፈለው ሂሣብ ኮሌጁ ተመላሽ እንዲያደርግ በድጋሚ አሳስበናል፡፡

የ2004/2005 በጀት ዓመት ሂሳብ
ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ዝርዝር

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ በጀት/ሥራ ላይ የዋለ		መግለጫ
			መደበኛ	ካፒታል	
1	የፌደራል ፖሊስ	3/4/2005	776,495,230.00	104,009,900.00	
2	ንግድ ሚኒስቴር	3/3/2005	20,124,100.00		
3	ፍትህ ሚኒስቴር	3/3/2005	50,569,613.00	48,163,810.00	
4	የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት		20,804,800.00	17,730,100.00	
5	የሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት	3/3/2005	30,849,900.00		
6	የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	3/4/2005	14,203,500.00		
7	ሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ	3/3/2005	11,703,400.00		
8	የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን	3/3/2005	9,664,940.00		
9	የኢትዮጵያ አክሬዴቴሽን ጽ/ቤት	3/4/2005	4,993,400.00		
10	የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት	01/04/05	20,351,107.00	_	20,351,107.00
11	የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት	11/03/05	32,383,276.53	64,009,400.00	96,392,676.53
12	የፌደራል ሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን	19/02/05	34,997,950.40	-	34,997,950.40
13	የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	06/02/05	198,086,011.50	192,421,300.00	390,507311.50
13	የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	06/02/05	198,086,011.50	192,421,300.00	390,507311.50
14	የቆዳኢንዱስትሪልማት ኢንስቲትዩት	05/02/05	20,412,099.00	37,358,213.00	57,770,312.00
15	የጨርቃጨርቅኢንዱስትሪልማትኢንስቲትዩት	21/12/04	44,855,260.00	70,998,140.00	115,853,400.00
16	የኢት.ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ	17/03/05	8,470,093.64	_	8,470,093.64
17	የኢት.ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	26/02/04	18,355,564.24	_	18,355,564.24
18	የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ	26/03/05	15,202,804.74	_	15,202,804.74

ተ. ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ በጀት/ሥራ ላይ የዋለ		መግለጫ
			መደበኛ	ካፒታል	
19	ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት(የተጠቃለለ)	26/3/.2005	271,384,672.00	-	271,384,672.00
	መረጃና ደህንነት አገልግሎት(ዋናው መ/ቤት)	26/3/2005	49,395,884.00		49,395,884.00
	የውጭ መረጃ ዋና መምሪያ	21/1/2005	18,956,583.00	-	18,956,583.00
	የውስጥ ደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ	5/2/2005	38,858,070.00	-	38,858,070.00
20	ፌደራል ጉዳዮች ሚ/ር	30/2/2005	47,334,086.00	2,391,000.00	49,725,086.00
21	ፍትህና ሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት	15/1/2005	6,640,538.29	-	6,640,538.29
22	ፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ	3/1/2005	16,795,359.98	-	16,795,359.98
23	የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ	25/1/2005	14,922,964.77	-	14,922,964.77
24	ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	22/2/2005	189,208,367.09		189,208,367.09
25	ብረታ ብረት ልማት ኢንስቲትዩት	6/3/2005	11,553,644.3		11,553,644.3
26	የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ማህራት ኤጀንሲ	25/1/05	9,985,553.6		9,985,553.6
27	የኢትየጵያ አእምሯዊ ጽ/ቤት	7/12/04	6,033,182.42		6,033,182.42
28	የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች ሥልጠና ማዕከል	3/3/2005	10,494,000.00		10,494,000.00
29	የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	26/03/2005	6,500,000,000.00		6,500,000,000.00
30	ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር		603,228,960.00		603,228,960.00

1.2 <u>የተሰጠው የኦዲት አሰተያየት</u>፡ ከአባሪ-2 እስከ አባሪ-6 ተመልክቷል

በበጀት አመቱ ኦዲት ለማድረግ የታቀደው የኦዲት ሥራ በሙሉ ተከናውኗል፡፡

--------------------//-----------------